# መጽሐፈ ፈውስ

መዝገበ ጥበብ ወፈለገ ጠቢብ
ዘስርወ እፀዋት

ለኢትዮጵያውያን ሊቃውንቶችና ለእፀዋት ቀማሚዎች
እንዲሁም ለሚመረምሩና ጥናት ለሚያደርጉ ብቻ
የተዘጋጀ።

ከመሪራስ አማን በላይ
ተጻፈ

በሁለት ሺህ ዘጠኝ ፳፻፱ (2009) ዓ.ም
ሥድስተኛ ዕትም ፮

አሳታሚና አከፋፋይ
መልአከ መዊዕ ቀሲስ ፀጋዬ ሽፋራው
0918 252540 /0909 270603

Scanned by CamScanner

# መጽሐፈ
# ፈውስ

## መዝገበ ጥበብ ወፈለገ ጠቢብ
## ዘሰርወ እፀዋት

ለኢትዮጵያውያን ሊቃውንቶችና ለእፀዋት ቀማሚዎች
እንዲሁም ለሚመረምሩና ጥናት ለሚያደርጉ ብቻ የተዘጋጀ።

ከመሪራስ አማን በላይ
ተጻፈ

በሁለት ሺህ ፳፻ (2000) ዓ.ም.

Scanned by CamScanner

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።
ካለደራሲው ቤተሰብ ፈቃድ ደግሞ ማሳተም ወይም ኮፒ ማድረግ በሕግ የተከለከለ ነው።
Copyright ©

ዋጋው 100 ብር በኢትዮጵያ
ከኢትዮጵያ ውጭ $85 /ዶላር/

# ማውጫ

ገጽ

1. ፈውስ፡ ሁልቆ ፈደላት ——— 1
2. ሐሳበ ፈደላት ወትርጓሜ ——— 13
3. ሐሳበ ፈደላት ወባህርያት ——— 14
4. መፍትሔ ሐብት ——— 24
5. ጸሎተ በእንተ መፍትሔ ሥራይ ——— 31
6. አስም ——— 33
7. ዉጓራ ——— 38
8. የስኳር ህመም ——— 42
9. ሣልና ጉንፋን ——— 44
10. ጉንፋን ——— 47
11. የሆድ ደዌ ለድርቀት መፈውስ ——— 48
12. የእጅና የአካል መንቀጥቀጥ ፈውስ — 53
13. የግብረ ወሲብ ድክመት ፈውስ——— 56
14. ክፍል ፩ መንስኤ እስኪት ——— 61
15. ክፍል ፪ መጽንኤ እስኪት ——— 63
16. ክፍል ፫ መፍትሔ እስኪት ——— 65
17. ክፍል ፬ ዘኢያወርድ /ገትር/ ——— 67
18. ክፍል ፭ ——— 68

19. ክፍል ፮ ———————————— 69

20. ክፍል ፯ ———————————— 72

21. የልብ ህመምና ድካም ፈውስ ——— 75

22. የራስ ሕመም ዓይነቶችና ፈውስ— 78

23. ለማንኛውም ነገር አስፈላጊውን መርጦ ለሚጸልይ 93

24. መፍትሔ ሐብት ——————— 104

25. ሁሉን ቻይ የሆነው የፍጥረት ባለቤትና ጌታ
እግዚአብሔር የሚመሰገንበት ቅዱስ ስሙ – 114

26. ለሰላምና ለምህረት ለመልካም ዜና የተዘጋጁና
የሚላኩ የእግዚአብሔር ቅዱሳን መላእክቱ ስም —117

27. ለጥፋትና ለመቅሰፍት ለፍርድ የተዘጋጁ የፍዳ
መላእክት ነገዶች ——————————— 119

28. የነቀርሣ መንስኤውና ፈውሱ ——— 121

29. ለማንኛውም ለጡት ህመም ፈውስ - 122

30. ለተደበቀ ወይም ውስጥ ውስጡን ለሚያመውና በውጭ
ለአበጠ ነቀርሣ ወይም ለቆሰለ ምኺር ፈወስ ——124

31. የኪንታሮት ፈውስ ——————— 132

32. ለለምጥ ሥጋ ደዌ ፈውስ ————— 141

33. ለቁስል ለሥጋ ደዌና ለነቀርሣና
ለኪንታሮት የሚሆኑ እጽዋቶች ፈውስ – 143

34. ሰውነትን ለሚያንቀጠቅጥና ለሚጥል



Scanned by CamScanner

ለሚያዝል ለሌጌዎን መድኃኒት ፈውስ —151

35. ስለ አራዊትና ስለ እንስሳ ሥጋ መድኃኒትነት 154

36. የአትክልትና የእህል አገልግሎት ፈውስ 169

37. መክስት - እፀአንግሥ ———— 183

38. በግእዝና በአማርኛ ከሀ እስከ ፈ

የእፀዋት ስም ዝርዝር እና ዝ.ር —— 185



Scanned by CamScanner

# መቅድም

“ይቤ እግዚአብሔር ለአዳም አቡነ ለእመ ትበልኦ
እንትኮ በለሰ ሞተ ትመውቱ”

እግዚአብሔር ለአዳም አባታችን የበለስን ቅጠል ወይም ፍሬውን ብትበሉ ሞትን ትሞታላችሁ አትንኩት አትብሉትም ብሎ የአዘዘውን ትእዛዝ ላለማስፈጸምና ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ለማውጣትና ለመግደል አዳም ሕያው ነፍስ ያለውም ቢሆን በሥጋውና በነፍሱ ላይ ለመሰልጠን ሲል፡

“ለእመ ትበልኦ ፍሬሁ ለበለስ ትከውኑ አማልክተ ከመለሊሁ ቅጽበተ ወፍጡነ”

በእባብ ላይ የአደረ ሰይጣን ለሄዋን እንዲህ አለ፡- ሞትንስ አትሞቱም ከበለስ ፍሬ ሁላችሁ አንድ ግዜ ብትበሉ እግዚአብሔር የሚያውቀውን ስለምታውቁ እንደ እርሱም አምላክ እንደምትሆኑ ክፉንና ደጉን ሞትንና ሕይወትን እንደምትመርጡ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ የበለስን ፍሬ በበላችሁስ ጊዜ በቅጽበት እንደ እርሱ አምላኮች ትሆናላችሁ አላት፡



Scanned by CamScanner

ሄዋንም የበለሱ ዛፍ ፍሬውን ለመብላት የአማረ ለዓይንም የአስጐመጀ ለጥበብም መልካም እንደሆነ እንደ እግዚአብሔር አምላክ እንደሚያደርግ አመነች፡

ወዲያውኑ አምላኮች ለመሆን የዛፉን ፍሬ ቆረጠችና ሴት ለባልዋ ባልም ለሚስቱ ምግብን እንደሚያጐርስ ወይም ምግብንና መጠጥን ቀምሰው እንደሚሰጡ ሁሉ እንዲሁ ቀምሳ ለአዳም አበላችው።

አዳምም የፈጣሪውን ትእዛዝ ረስቶ በላና ሕያው ነፍስ ያለው ሰው ሁና የተፈጠረው ሰው ሞትን የሚሞት ሆነ፡

ይህ ትእዛዝ በመጀመሪያው ሰው በአዳም ላይ ሞትንም ቢያስለጥንበት በሥጋ ባይሻር በአካለ ነፍስ ለአሉና የማይበሰብሰውን መንፈሳዊ አካል በትንሳኤ ቀን በሚለብሱት ቅዱሳን ዘንድ ሕይወት በሚሰጠው በዳግማዊ አዳም በክርስቶስ ተሽሮአል።

ምክንያቱም አዳም እፀበለስን በልቶ ሞትን እንዳመጣ ሁሉ እንዲሁ ሞትን ለመሻር ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብን ፍቃድና ትእዛዝ ለመፈጸም ሰውንም ሕያው ለማድረግ በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞቶአል።



Scanned by CamScanner

በእርሱ ሞት ዓለም ዳነ፡ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ቤዛ ሆኖ እንደሞተና በሶስተኛው ቀንም እንደተነሣ በአርባ ቀኑም ወደ ሰማይ እንዳረገ ዳግመኛም እንደሚመጣ ለአመነና እፀ መስቀሉን ለተሸከመ ሁሉ መድኃኒት ሆኖአል።

በእፀበለስ ምክንያት ለሞተው ለአዳም ዘር ሁሉ ክርስቶስ በእንጨት ላይ ተሰቅሎ አድኖናል፡ ሕያውም አድርጐናል። ለዚህ ነው "እፀ ይቀትል እፅ የሐዩ" እጽ ይገድላል፡ እጽ ያድናል ተብሎ የተነገረው።

አሁንም መጽሐፈ ፈውስ ብዬ የሰየምኩት የህቡእ ስም ጸሎትና የእፀዋት መዝገብ ጥበብ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ጠቢባን ሊቃውንት ከመጽሐፈ ኖህና ከሌሎችም አባቶች መጽሐፍት እግዚአብሔር በመልአኩ አማካኝነት የገለጸላቸውን የጥበቡን ምስጢር ሁሉ ለእኛ ለልጆቻቸው ለኢትዮጵያውያን መዝግበው አስቀምጠውልናልና ስለዚህ እኔም መሪራስ አማን በላይ እውቀቱን ለማዳበር ጥበብን ለሚመረምራትና ተግቶም ለሚፈልጋት ወይም እፀዋትን በመትከልና በመመራመር በጥናትም ስለ አዋቂ ወይም የሀገር ባህል መድኃኒት ቀማሚ ዶክተር ለምርምር ይረዳው ዘንድ ጽፌ አሳትሜው አለሁ እንጂ ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚያመዝን



Scanned by CamScanner

ማንኛውም ግለ ሰብእ ከመጽሐፈ ፈውስ ላይ ተጽፎ አግኝቼአለሁ ብሎ አንድን እፅ ቀጥቅጦ በራሱም ይሁን በሌላ ወገን ሕይወት ላይ መፈተን አዳም አትብላ ተብሎ በልቶ እንደሞተው እንዲሁ የእግዚአብሔር ሕንፃ የሆነን ሰውን እንደማፍረስ ነው። ይህም እፀዋትን በመቀመምና ጥናት ከአደረጉት ከሀገር ባህል መድኃኒት አዋቂ ዶክተር በቀር ወይም ህጋዊ የሆነ የሥራ ፈቃድ ኑሮት መንግሥት እንዲሰራና በቀና አገልግሎት ሕዝብን እንዲረዳና እንዲያክም ከፈቀደለት ከዶክተር በቀር ማንኛውም ግለሰብእ በራሱ ላይ ወይም በሌላ ወገን ላይ እንዳይፈትን በእግዚአብሔር ስም አደራ እላለሁ።

እሄንም ስል እራሴን ከስህተት ነጻ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን ቅድም እንዳልኩት ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝን ስለማውቅ ነው። ሆኖም አንዳንዶቻችሁ እንደዚህ ከሆነ ለምን ተጻፈና ታተመ? ትሉኝ ይሆናል፡ አዎን እናንተ እንደምትሉት እኔም አምናለሁ፡ ነገር ግን ከአባቶቻችን የወረስነውን የጥበብ መዝገብ ሁሉ ለትውልድ እኛም ማስተላለፍ ግዴታችን ሁኖ ስለአገኘሁት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ሁላችሁ እንደምታውቁት ሁሉ እንኳን በኢትዮጵያ አገራችን የሚኖሩ ወገኖታችንና



Scanned by CamScanner

ዘመዶቻችን ቀርቶ በሌሎች ጐረቤት አገሮች የሚኖሩ ወገኖች ሁሉ የሚበልጡት በተለያዩ በሥጋ ደዌዎች የሚሰቃዩ ሕሙማን ሁሉ ብዙ ሚሊዮን ናቸው፡ ስለዚህ ህሙማን በመድኃኒት የሚፈውሱና የሚረዱ መድኃኒት ቀማሚ ዶክተሮች የአሉን ቁጥራቸው የአነሰ እንጂ ብዙዎች አይደሉምና እነሱን የመሰለ ለማግኘት ሁሉም ድርሻውን በበኩሉ እንዲወጣ ለማድረግና ጥናት እንዲደረግበት ስል በእግዚአብሔር አነሳሽነትና አስፈጻሚነት ፍቃዱ ሆኖልኝ ይህን "መጽሐፈ ፈውስ" የአልኩትን መጽሐፌን ጽፌ አሳትሜላችሁ አለሁ።

ይህ የጥበብንና የእውቀትን መጽሐፍ ሁሉ የሚመረምሩና የሚያጠኑ አባቶቻችን ኢትዮጵያውያን ሰብአሰገል ጠበብት እንኳ እግዚአብሔርን ከማመናቸውና ከመውደዳቸው የተነሣ የተሰፋው ዘር የሆነው ክርስቶስ ከድንግል ማርያም በቤተልሔም በተወለደ ጊዜ ከዓለም በፊት ደርሰው ኢትዮጵያኖች ይሰግዱለታል የተባለውን ትንቢት ለመፈጸም ሰግደውለታል። ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች የተባለውን ትንቢት እንዲሁ ለመፈፀም ስጦታን አቅርበዋል።

የእግዚአብሔርን ስም ከመላእክትና ከእረኞች ጋር በአንድነት ቆመው አመስግነዋል።



Scanned by CamScanner

እኛም እንደነሱ እንዲሁ የምናደርገውን ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገን ክብርም እየሰጠን በእግዚአብሔር ስም ማድረግና መፈጸም አለብን።

ለዚህ ነው ኢትዮጵያውያን ሊቃውንትና መምህራን ጠበብት "የቅዱሳን መድኃኒታቸው ከእግዚአብሔር ነው፡ ሕዝቡም ከኃጢአታቸው ያድናቸዋል" የሚለውን ትንቢት መመሪያ በማድረግ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ ለማግኘት ሲሉ እነዚህ የዘረዘርኳቸውን መንፈሳዊ ጸሎቶችን፡ ይጸልዩባቸውና አሳባቸውን ምኞታቸውንም ይፈጽሙባቸው ነበር።

እነዚህን የመሰሉ ሁሉ መንፈሳዊ ጸሎቶች የምስጢር ወይም የግል ጸሎት ስለሆኑ ህቡእ ስም ይባላሉ። ህቡእ ስም ማለት የተደበቀ የእግዚአብሔር ስም ወይም አስማተ እግዚአብሔር ይባላል። የእግዚአብሔር ስሞች ሚስጢራዊ ከመሆናቸው የተነሣ ድብቅ የሆነውን ክፉ መንፈስ ወይም በክፉ መንፈስ ደዌ የተለከፈውን የተያዘውን ሕሙም ወይም እድሉ የተጣመመበትን ሐብቱ የተሠወረበትን እሄን በመሰለ ሁሉ በደረሰበት ሰው ላይ ይጸልዩበትና ይረዱበታል። ከዚህም አልፎ መጭውን ነገር በራእይ ያዩበት ነበር፡



Scanned by CamScanner

እግዚአብሔርን በንጽህና ሁነው ሱባኤ ገብተው በክብር ስሙን እያመሰገኑ ይጠቀሙባቸው ነበር።

እንዲሁ እኔም መንፈሳዊ ጸሎትንቱን ታስተውሉትና ትመረምሩት ዘንድ ለመንፈሳውያንና ለመንፈሳዊያት ወንድሞቼና እህቶቼ ከብዙ በጥቂቱ አዘጋጅቼአለሁ።

እኛም እግዚአብሔር የሚወደውን መልካም ተግባር ለመፈጸም ከክፉ ነገርና ሥራ ለመራቅ ያብቃን።

እግዚአብሔር ከታጋሽነቱና ከምህረቱ ብዛት የተነሣ ይማረን በረድኤቱና በጸጋው አይለየን፡ ፈጽሞ ይጠብቀን፡ የእግዚአብሔር አብ ቸርነት የእየሱስ ክርስቶስ ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ አንቃቂነት አይለየን። የኢትዮጵያን አንድነት ይባርክልን፡ ሕዝቦችዋንም በህብረት ያቁምልን፡ ለዘለዓለም አሜን።

ከደራሲው ከመሪራስ አማን በላይ



ፈውስ

# ፈውስ

## ጉልቆ ፈደላት

ከጉሮሮና ከትናጋ ተነስተው በአንደበት ጉልተው የሚራሰጩ አሥሩ አናባቢና ተናባቢ ድምጾች፣ በሱባ-ልሣነ ሰብእና በአማርኛ በላቲንም

ኈ-A-a - አልፋ አሌፍ አንተ ካሀኑ ለዓለም አሐዩ አብ

i i - እ-l.i - እግዚእነ እየሱስ ክርስቶስ እንለሕያው እግዚአብሔር

l – ኧ- a – ኧኽያ ኧዶናይ ኧዴር ኧማኑኤል አድማኤል

ፀ- ኤ - a – ኤልአሄ ኤልሻዳይ ኤልማስ ኤዌን

e - ኢ - e - ኢያኤል ኢያሱ ኢዩኤል ኢዮኤል

u - ኡ - u - ኡዱኤል ኡዱማኤል

w - ኡ - ኡይ- ue - ኡይሳኤል ኡደራኤል

m - ኤ - ኡየ - ua - ኡየኤል ኡየዊል ኡዌኤል

ወ - ኢ - ኡዋ - owa - ኡዋኤል

o ኦ - ኦ - o – ወኦ ኦሜጋ



Scanned by CamScanner



ባ ብ በ ቤ ቢ ቡ ቡይ ቡየ ቧ በ

በርስባሔል ብርሱድናኤል ቤጣ ቤቃ ቢቃ ቡርሃናኤል

ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላሀ ላሄ ሉሄ አልአሄ ኤልሻዳይ አዶናይ በላ ለነፍየ አነ ውእቱ ረዳኢኪ አንተ ባህረ ጥበብ ወምህረት፡



ፓ ፐ ፐ ፔ ፒ ፐ ፑይ ፑየ ፗ ፖ

ፓኤል

ፓና ፀዳለ ብርሃን ሙሐዘ ፈለግ ዘምስጢር ፓኤል ፫ ፓፓሮስ ሜሉስ ሰይፈ እሳት ወመፍርሀ ወጼጋ እሳት ዘመንፈስ ቅዱስ ረሰየኒ እንብብ ቃለ መለኮትከ በውስተ ልብየ ሳእለአፉየ፡

ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላሀ ላሄ ሉሄ ኤልአሄ ኤልሻዳይ አዶኒ



ጸ ጸ ጸ ጼ ጺ ጹ ጹይ ጹየ ጿ ጸ

ጸላሜዎን

ጸጦስ ጸጦሳውይ ኢያውእዮ ነበልባለ እሳተ ጸገወነ ጸራቅሊጦስሃ መንፈሰ ጽድቅ ዘበአማን

## ፊውስ

ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላሀ ላሄ ሉሄ
ኤልአሄ ኤልሻዳይ አዶኒ



ማ ም መ ሜ ሚ ሙ ሙይ ሙየ ሟ ሞ

መክስታኤል

ማሩኤል ማራታ ማሩታኤል ማእምረ ልብ ህቡዕ
መንክር ስብሐቲከ ዘትገብር መንክረ

ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላሀ ላሄ
ሉሄ ኤልአሄ ኤልሻዳይ አዶናይ



ራ ር ረ ሬ ሪ ሩ ሩይ ሩየ ሯ ሮ

ራሀማንርግብ ረብርስባሔል ሪኮን ሩፋኤል ሩይኤል ሯሀማርሂምኤል
ርጎሩሀ ወየዋሀ ረዳኢ ወመሠውር
ርተዕ ፈታሒ በጽድቅ ወበርትዕ
ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላሀ ላሄ ሉሄ
ኤልአሄ ኤልሻዳይ አዶናይ



ላ ል ለ ሌ ሊ ሉ ሉይ ሉየ ሏ ሎ
ላሀ፡ ሉያ ሉሄ



Scanned by CamScanner

ሎቱ ስብሐት ወ እስከ ለዓለም ላህየ ፀዳሉ ወገጹ

ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላህ ላሄ ሎሄ ኤልአሄ ኤልሻዳይ



ዳ ድ ደ ዴ ዲ ዱ ዱይ ዱየ ዷ ዶ

ቶዱ ወይም ነዴ /በኦሮምኛ/



ዳ ድ ደ ዴ ዲ ዱ ዱይ ዱየ ዷ ዶ

ዳር

አላዶር

ዳኪሮስ ዳግማዊ አዳም ቤዛኩሉ ዓለም ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላህ ላሄ ሎሄ ኤልአሄ ኤልሻዳይ አዶናይ



ጣ ፕ ጠ ጤ ጢ ጡ ጡይ ጡየ ጧ ጦ

ጣጣኤል ፕውርኤል ጠኤል ጤገሮስ ጡጣኤል ጤቃ

ጣዕመ ቃሉ መንክር ወእፁብ ጠቢብ ወለባዊ እምህሲና መዋቲ ሥውር ወተወለጠ አርአያሁ በመለኮቱ ጣእሙ ወታእምሩ ከመኄር እግዚአብሔር



Scanned by CamScanner

# ፈውስ

ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላሀ ላሄ ሉሄ ኤልአሄ ኤልሻዳይ አዶናይ፡

ተ ቲ ቲ ቴ ቴ ቴ ቴ ቴ ቴ ቶ
ታ ት ተ ቴ ቲ ቱ ቱይ ቱየ ቷ ቶ
ትናኤል

ቶስሀ መንፈስከ ላእለ ህዝብከ ታኦስ ታኦሣዊ ታቦራዊ በመለኮቱ ቤዛ ኩሉ ዓለም ወቤዛ ኩሉ ዘነፍስ ተንሥእ እግዚእ ርድአነ ወአድህነነ በእንተ ስምከ ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላሀ ላሄ ሉሄ ኤልአሄ ኤልሻዳይ አዶናይ ጳራቅሊጦስ መንፈሰ ጽድቅ ቶስዕ ጥበበ በውስተ ልብየ በፈሪሆተ ስምከ

S S S S S S S S S §
ሱሣ ሥ ሠ ሤ ሢ ሡ ሡይ ሡየ ሧ ሦሶ
ሥሉስ ሰብእ ሴቃ

ሣህሉ ወምሕረቱ ዘይወርድ ከመጠል እምርዕሰ ሳኔር ወኤርሞን ሣራሪሃ ለምድር ወዘእምቅድመ ዓለም ንጉሥ ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላሀ ላሄ ሉሄ ኤልአሄ ኤልሻዳይ አዶናይ ሰንተው ዘንተው ቀንተው ቀርነው ቀርነለው ባኤል ኢዮኤል አማኑኤል አርታኤል አርታታኤል፡



Scanned by CamScanner



ጸ-ባ ፅ ፀ ፄ ፂ ፁ ፁይ ፁየ ጿ ፆ-ጸ

ጸሩፋኤል ጼቃ

ጸዴ ጸድቅ ሕይወተ ብርሃን ጽርሕ ንፁህ ዘእምአርያም /ፀዳልወ/ መጸልወ /ብርሃን/ ፀሐይ ዘአልቦቱ ጽልመተ አንተ ውእቱ ፀሐየ ጽድቅ ዘታበርህ ውስተ አልባቢሆሙ ለቅዱሣን፤ መጸልው ኩሉ ፀሐይ አብርህ ብርሃነከ በውስተ ለብየ ወገጽየ በገፀ ላህይከ። ወአዕይንትየ ይብርሃ በዓይንቲከ። ወአእናፍየ ይጼነዋ ጼናመንፈስከ ወልሳንየ ይነብብ በቃለ ልሳንከ። ለአልሆስስ ውስተ አዝንየ ምስጢራተ መለኮትከ

ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላህ ላሄ ሉሄ ኦልኮሄ ኤልሻዳይ አዶናይ



Tዘaዛ ዝ ዘ ዜ ዚ ዙ ዙይ ዙየ ዟ ዞ



ዛ ዝ ዘ ዜ ዚ ዙ ዙይ ዙየ ዟ ዞ

ዘራዳኤል



Scanned by CamScanner

# ፈውስ

ዛይ አዶናይ እግዚአብሔር ዘሀኑ ለባሕር ወመርሶ ለአሕማር

ብሉየ መዋዕል ለእግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ባህ ባሄ ሎሄ ኤልአሄ ኤልሻዳይ አዶናይ



ጫ ጭ ጨ ጩ ጪ ጬ ጩይ ጩየ ጯ ጮ

ጫጫኤል ጨረቃ ጨርዋቅ ጨርቅያ ጩርቃ

ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ባህ ባሄ ሎሄ ኤልአሄ ኤልሻዳይ አዶናይ



ቻ ች ቸ ቼ ቺ ቹ ቹይ ቹየ ቿ ቾ

ብሉይ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ባህ ባሄ ሎሄ ኤልአሄ ኤልሻዳይ አዶናይ



ሻ ሽ ሸ ሼ ሺ ሹ ሹይ ሹየ ሹዋ ሾ

ሸራኽያ ሽለሹ ሸኤል ሼማልዳ ሺረሺ ሹራኤል

ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ባህ ባሄ ሎሄ ኤልአሄ ኤልሻዳይ አዶናይ



Scanned by CamScanner

ዋ ዊ ዉ ዊ ዌ ዊ ዊ ዊ ዊ ቆ

ኘ ኻ ኘ ኜ ኚ ኙ ኙይ ኙየ ኟ ኘ

ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላሄህ ላሄ ሉሄ
ኤልአሄ ኤልሻዳይ አዶናይ

ቀ ቂ ቂ/ ቂ ቄ ቂ ቂ ቂ ቂ ቆ

ጃ ጅ ጀ ጄ ጂ ጁ ጁይ ጁየ ጇ ጆ

ጃማን ጅሊል ጀምሊላ ጀም ጁማን ጁይኤል ጁየዋ ጇባር
ጀሚኤል

ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላሄህ ላሄ ሉሄ
ኤልአሄ ኤልሻዳይ አዶናይ

ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላሄህ ላሄ ሉሄ
ኤልአሄ ኤልሻዳይ አዶናይ

V V V/ V V V V V V V

ኃ ኀ ኀ ኄ ኂ ኁ ኁይ ኁየ ኇ ኆ

ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላሄህ ላሄ
ሉሄ ኤልአሄ ኤልሻዳይ አዶናይ

l l l/ l l l l l l l



Scanned by CamScanner

ጋ ግ ገ ጌ ጊ ጉ ጉይ ጉየ ጓ ጎ

ግዮን ጉድናኤል

ጋዳ ያበውኡ ቊርባነ

ገብረ ለነ ሕይወተ ዘለዓለም

ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላሄህ ላሄ ሎሄ

ኤልኦሄ ኤልሻዳይ አዶናይ

[illegible]

ቃ ቅ ቀ ቈ ቊ ቁ ቁይ ቁየ ቋ ቆ

ቅምሐሹን ቊርሰድናኤል ቆፍ

ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ቃል

ቃለ እግዚአብሔር በኃይል ቃለ እግዚአብሔር በዓቢይ

ስብሐት ቀንተው ቀርነው ቀርነለው

ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላሄህ ላሄ ሎሄ

ኤልኦሄ ኤልሻዳይ አዶናይ

[illegible]

ካ ክ ከ ኬ ኪ ኩ ኩይ ኩየ ኳ ኮ

ካፍ ኩዋይ ከለላይ ኬር ኩኩህ ዕኑእ ዘኢይጸንን

ኬድናኤል

ኮነ ለነ ሕይወተ ዘለዓለም አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሲመቱ ለመልከ ጼዴቅ ወአንተ ካህነ አርያም ክቡር ወስቡህ ስምከ በምድር ወበሰማያት

ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላሄህ ላሄ ሎሄ ኤልኦሄ ኤልሻዳይ አዶናይ ክስብኤል ክስትኤል ክስትናኤል፡

ሐ [illegible] [illegible] [illegible] [illegible] [illegible] [illegible] [illegible] [illegible] ሖ

ኻ ኸ ኸ ኼ ኺ ኹ ኹይ ኹየ ዃ ኾ

ኸቢር አልኸቢር

ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላሄህ ላሄ ሎሄ ኤልኦሄ ኤልሻዳይ አዶናይ

ሠ [illegible] [illegible] [illegible] [illegible] [illegible] [illegible] [illegible] [illegible] ሦ

ሗሐኀ ሀ ሀ ሄ ሂ ሁ ሁይ ሁየ ኋ ሆሐኆ

ሃሌ ሃዋ ሄዋን

ኆህታዊ ኃራታዊ ኃራታን ኃራቱን

በኍልቈ ኩሉ ልሣን ዘይሴባሕ በአፈሔር እግዚአብሔር ሕያው

ብሉየ መዋዕል እግዚአብሔር ሃሌ ሉያ ላሄህ ላሄ ሎሄ ኤልኦሄ ኤልሻዳይ አዶናይ



Scanned by CamScanner

# ሐሣበ ፊደላት፡ ወትርጓሜ

ፏ - ኣ - A  አልፋ አሌፍ አዊን አድማኤል

A – ኣ  ብሂል አቢይ አበ ብዙሃን አዳም ወአብርሃም

i - እ - i  እያስጲድ እያሆ እየሱስ

I - እ ብሂል እም(እናት) እግዚእ

l – ኧ - a ኧኸያ ኧማኑኤል

a - ኤ - a ኤልሻዳይ ኤአሄ ኤልማስ ኤዔ ኤልአሂ

- ኤ - ብሂል

e -ኢ- e ኢዩኤል ኢያኤል ኢዮኤድ ኢያሱ ኢትኤል

E - ኢ - ብሂል ኢምንት ወኢፍሉጥ ኢይትከሃል ለተነግሮ

U - ኡ-U ኡዱኤል ኡዱማኤል ኡድላልኤል

ᵕ - ኡ ብሂል

ω - ኡይ - ኡ‹ - ue ኡይሣኤል ኡይራኤል

ω – ኡ‹ - ብሂል

m - ኡይ- ኌ-ua ኡየኤል

m ኌ - ብሄል

ወ - ኡዋ-ኊ-owa ኡዋው ኡዋኤል

ග - ኊ - ብሂል

O - ኦ - o ኦወ ወዖ ኦሜጋ ኦሎዳኤል

o - ኦ ብሂል ኦ እግዚኦ ኦ ቡሩክ ኦ ድንግል



Scanned by CamScanner

# ሐሳበ ፊደላት ወባህርያት

⌒ - ዋ፡ ዋው

\- Wa – ወጣኒ ወፈጻሚ የጀመረውን ዋሚጨርስ በቃሉ የጸና ነው።

◡ - ዋ̄

wa

Y - ያ ፡ ዮድ

ya - ይሬኢ ኵሉ ነገረ ሕቡአት የተደበቀ ያያል የዋህ ቅን ነው።

P - ያ̄

la

X - ኛ

nga

\- ና፡ ኖን፡ ኑን

na - ንጹሐ ልብ ዘሀሉ፤ ንጹህ ልብ ያለው ነው አዋቂ።

\- ፋ ፡ ፌ

fa - ፈካሬ ምስጢራት፤ ምስጢራትን የሚተረጉም ነው።

V - ቫ

va



Scanned by CamScanner

ᑲ - ባ ፡ ቤት

ba - ባዕል ወጠቢብ እምብሔረ ባዕድ፤ ባለጸጋና ጥበበኛ ነው።

ᑭ - ፓ

- pa

ᐃ - ጰ

Pa - ጰዝዮን እንቊዮጵ ሠናይ፤ ይብልዋ ተዓጋሣ በኩሉ ነገር

ᐁ - ማ ፡ ሜም ፡ ሚሞ

ma - ማእምር ወመምሕር ውእቱ ይነብር በማእከለ አዝማዲሁ

ᓀ - ራ ፡ ሬስ

ra - ረጋሚ ወርቱዕ ልቡ ወግብሩ ሠናይ

ᓴ - ላ ፡ ላሜድ ላም

La - ለባዊ ወልዑል ውእቱ ፤ ትልቅና አስተዋይ ነው።

(ዻ) - ዻ ዻል ዹዋድ

tda

D - ዳ ፡ ዳሌጥ

da - ድልው በኩሉ ነገር ከመ ንጉሥ ዳዊት ወዳንኤል።

T - ጣ ፡ ጤት ፡ ጡዋ

ta - ጠቢብ ወጠዋይ ውእቱ



Scanned by CamScanner

ተ - ቃ : ቃው

ta - ትሁት ወተአጋሲ ውእቱ ፤ ትህተኛና ትእግሥተኛ ነው።

S – ሣሳ : ሣምኬት ሳን ሲን

sa - ስርግው ወስቡሕ ሰብእ በኩሉ ጊዜ

ፀ- ጸዓ : ጸዴ

sa - ጽዱል ወጸድቅ ብእሲ ፤ ጻድቅና ብሩህ ሰው ነው።

ጶ - ዣ̄ : ዘጥ

tha

ዘ - ዛ : ዛይ : ዙዋ

za - ዝክረ ገብሩ ክሉት ይዜክር ዘመዱ ወዘ ውጉ

ሃ - ጪ

cha

[illegible]- ሻ : ሺን

sha: ሽራክያ የአቅቦ ወያከብሮ በቅድመሰብእ

ዋ - ዣ

zha: ዣንሸዋ ቡሩክ ወክሉት ተአምረ ኤልሻዳይ

ቀ - ጀ : ጂም

ja ጀባር ወግሩም ነፍሱ ዓቢይ ውሉደ ይወልድ እንጣ

∀ - ጋ

ga: ገባሪ ወተአጋሚ በኩሉ ነገር ሥቃይ ወፍዳ



Scanned by CamScanner

፩ - ጋ ፡ ጋሜል ጋዴን

ga - ግሩም ብእሲ ዘአልቦቱ ጌጋይ ወግፍዕ

፪ - ቃ ፡ ቆፍ ቃፍ

k̄a ፡ ቀዊም ሠናይ ይከውን ማእምረ ወጠቢበ ወልቡ ፍሱሀ

፫ - ካ ፡ ካፍ

ka - ክቡር ብእሱ ይከውን ኀበካልዕ ሀገር ይረክብ ክብረ

፬ · ኻ ሔት

ha – ሐዋዝ ውእቱ ለጉልቆ ፊደላት ወምስጢራት ይትከሰቱ ሎቱ

፭ - ሃሐኀ ፡ ሄ

ha - ኃያል ውእቱ ወሃይማኖቱ ጽኑዕ ወሕዝብ ያፈቅርዎ



Scanned by CamScanner

ኧሌፍ ብሂል አብ ፈጣሬሁሉ ዓለም

አፍኤል

ቤት ብሂል ባዕል እግዚአብሔር

ብትራኤል

ጋሜል ብሂል ገባሬ ኃይል እግዚአብሔር

ገዳኤል

ዳሌጥ ብሂል ደምሳሴ ሥራይ እግዚአብሔር

ድብራኤል

ሄ ብሂል ሕልው እግዚአብሔር

ሃገራኤል

ዋው ብሂል ዋሕድ እግዚአብሔር

ወልታኤል

ዛይ ብሂል ዝኩር እግዚአብሔር

ዝማኤል

ሔት ብሂል ሕያው እግዚአብሔር

ሐይመታኤል

ጤት ብሂል ጥንቋቁ እግዚአብሔር

ጠፈራኤል

ዮድ ብሂል የማን እግዚአብሔር

የማንኤል ዮፍታሔኤል

ካፍ ብሂል ከሃሊ እግዚአብሔር



Scanned by CamScanner

ከናፍራኤል

ላሜድ ብሂል ልዑል እግዚአብሔር

ልሐኩናኤል

ሜም ብሂል መሐሪ እግዚአብሔር

መዝራታኤል መራሁታኤል

ኖን ብሄል ንጉሥ እግዚአብሔር

ነጉድጓድኤል

ሳምኬት ብሂል ስቡህ እግዚአብሔር

ሲአፍኤል ሲኢያፍኤል

ዔ ብሂል ዓቢይ እግዚአብሔር

ዓእይንታኤል

ፌ ብሂል ፈጣሪ እግዚአብሔር

ፍታሕኤል ፍክርናኤል

ጸዴ ብሂል ጻድቅ እግዚአብሔር

ጸዳታኤል

ቆፍ ብሂል ቅሩብ እግዚአብሔር

ቀስታምኤል

ሬስ ብሂል ረዳኢ እግዚአብሔር

ርማሃኤል

ሳን ብሂል ሰፋኒ እግዚአብሔር

ሰንበልታኤል

ታው ብሒል ትሁት እግዚአብሔር

ተሰፋኤል



Scanned by CamScanner

መቅድመ ነገራተ ፈደላት እለቦሙ ነጥብ እስመ እሙንቱ መሠረቱ ወጉንዱ ለኩሉ ነገር ወበሙ ይትሌዓል ግብር ዘነገር አእምር ከመ ቦሙ ምስጢር ለጉላቂሆሙ ፈደል ወከመ ቦሙ በቍኤት ሠናይት ለፈደላት፡

ዘይሁብ ዓለም ላእላይ ለዓለመ ታህታይ
ዓለመ መንበረ ፀባኦት ይሁብ ለዓለመ ኩርስ
ወዓለመ ኩርሲ ፈለገዙኃል ይሁብ ለዓለመ ፈለገሙሺተራ
ወዓለመ ፈለገሙሽተራ ይሁቦ ለዓለመ ፈለገሚረሀ
ወዓለመ ፈለገ ሚረሀ ይሁቦ ለዓለመ ፈለገሸምስ /ፀሐይ/
ወዓለመ ፈለገ ፀሐይ ይሁቦ ለዓለመ ፈለገዝሁራ
ወዓለመ ፈለገ ዝሁራ ይሁቦ ለዓለመ ፈለገ አጣርድ
ወዓለመ ፈለገ አጣርድ ይሁቦ ለዓለመ ፈለገ ቀመር ጀንበር
ወዓለመ ፈለገ ጀንበር ይሁቦ ለዓለመ እሳት ውእት
ወዓለመ ፈለገ እሳት ይሁቦ ለዓለመ ነፋስ
ወዓለመ ፈለገ ነፋስ ይሁቦ ለዓለመ ፈለገማይ
ወዓለመ ፈለገ ማይ ይሁቦ ለዓለመ ፈለገ መሬት
ወዓለመ ፈለገ መሬት ይሁቦ ለዓለመ ፈለገ አርያም
ወዓለመ ፈለገ አርያም ይሁቦ ለፈለገ ዓለመ ሕይወት
ወዓለመ ፈለገ ህይወት ውእቱ ትፍስሂት ወትፍስሂትስ ብርሃነ ሕይወት ለደቂቀ እግዚአብሔር



Scanned by CamScanner

# ፌውስ

ኍላቍያተ ፊደላት ይከውን ፳፱ ወስሞሙ ተናባቢያት ሠራዊተ ፊደል ሊቃሙ ወመርሆሙ እስማቲሁ ለእግዚአብሔር ወግብሮሙ አናባቢያን ወተናባቢያን ሳእለ ሠራዊቶሙ

ፕ - አ - ኤልኤፍ አሌፍ አልፋ አሐድ

ʌ - እ - እየሱስ እግዚ እያሁ

ı - ኧ - ኧዶኒ ኧኸያ ኧማኑኤል አንያኤል

ɑ - ኤ - ኤልአሄ ኤሉሄ ኤልማስ ኤልሻዳይ

e - ኢ - ኢያኤል ኢዩኤል ኢዮኤድ ኢያሱ ኢዝራኤል

υ - ኡ - ኡዱኤል ኡዱማኤል ኡድላላኤል

ω - ኦ - ኦይ - ኦይላኤል እደራኤል

¬ - ኋ - ኦየ - ኦየኤል

ɷ - ኦዋ- ኋ - ኦዋው ኦዋኤል

ዐ - አ - አየ ወአ አሜጋ አሉዳኤል

ո - ዋ

ʊ - ዋ

Y - ያ

የ - የ

X – ኛ

ቷ - ና

[illegible] - ፉ



Scanned by CamScanner

V - ቫ

9 - ባ

C - ፓ

6 - ጳ

♡ - ማ - አጆብ መድአያኤል ያሸሊሁስያ ያሸሙሸላ። ለምንገድ አጆብ ያሚካኤል ያሙዚሰፍ ያኑረሻሳ ለመከራ ጻልይ።

● - ራ

● - ላ

- ዻ - ደውዳኤል አጆብ፡ ከድንጋጼ ከሀመም ያወጣል።

a - ዳ

T - ጣ

ተ - ታ

S - ሣ

ʔ - ፃ

ዞ - ዛ

H - ዛ

ሃ - ጫ

ሉ - ቻ

〜 - ኻ - ሸሊሁስያ ቪሙቪላ - ይህን ጽሮ አስር ቢደግሙ አይደክምም

ቀ - ኘ

✚ - ጃ

ዶ - አንጣጣ -

V - ጛ

/ - ጋ

የ - ቃ

7 - ካ - ካሩ ኻጀጠብ አጂብ ይማህያኤል ለጸእር ድገም

ሐ - ኻ

Ψ - ሀ-ሃ-ሑ-ኀ

በጉሮሮ የሚነገሩ

ለ i l a e u w m ወ ๏

ኣ እ ኧ ኤ ኢ ኡ አ ኣ ኣ ኦ - ሁ·ሃ·ሓ·ኻ

በትናጋ የሚነገሩ

Y ρ V / የ 7 Y ሰ ጥ ዋ
ያ የ ጋ ጋ ቃ ካ ዺ ቻ ሻ ዠ

በምላስና በድድ የሚነገሩ

ᴗ D T + x ጿ o ● ᚋ ጆ
ዲ ዳ ጣ ታ ኛ ና ራ ላ ጀ ጣጣ

በከንፈር የሚነገሩ

∩ ω ● V ፀ ፆ ♥ Δ
ዋ ቐ ፋ ሸ ባ ፓ ማ ጸ



Scanned by CamScanner

# መፍትሔ ሐብት

በስመ እግዚአብሔር ምሕሳበ ንዋይ ወመፍትሔ ሐብት አውናኤል ፯ አቅናኤል ፯ ፡ ኢያኤል ፯፡ ድምናኤል ፯፡ አክምናኤል ፯፡ አልፋኤል ፯፡ ሹሹድናኤል ፯፡ ከማሁአግናኤል ፯፡ አርጋኤል ፯፡ አርግናኤል ፯፡ አርወዮጋርናኤል ፯፡ አግድራኤል ፯፡ በብርናኤል ፯፡ ብርስብሔል ፯፡ ብርሃናኤል ፯፡ ሚካኤል ወገብርኤል ሱራፌል ወኪሩቤል ሩፋኤል ወፋኑኤል ዑራኤል ወራጉኤል አፍኒንኤል ወሣቁኤል በኃይለ እሉ አስማተ መላእክቲከ አብርህ ሐብትየ ወጥሪትየ ስሐብ ወሰብስብ ወርቀ ወብሩረ ወንዋያተ ዓለም ሀበኒ ሐብተ ወብእለ ጸጋ ወሞገስ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሊተ ለገብርከ

የበትረሙሴ የቁልቋል የግመሮ ተቀጽላቸውን አፈር ሳታስነካ ከአለት ድንጋይ ላይ ደቁስህ በነጭ ቄብ ዶሮ ደም ለውስህ ፺፱ ጊዜ ደግመህ ያዝ

በእለተ እሁድ መልአኩ ረውቅያኤል ነው። ከንጋት እስከ ሦስት ሰአት መልካም ነው። ከ3 እስከ ሰባት 7 ሰዓት ክፉ ነው። ከሰባት እስከ 9 ጥሩ ነው። ከዘጠኝ ሰአት በኋላ ምንም አታድርግ።



Scanned by CamScanner

በእለተ ሠኑይ /ሰኞ/ መልአኩ ጅብሬኤል ነው። ከንጋት እስከ ቀትር መልካም ነው። ከቀትር በኋላ ውል አትዋዋል ምንገድም አትሂድበት።

በእለተ ሠሉስ /ማክሰኞ/ መልአኩ ስምስማኤል ነው። ከነግህ እስከ 3 ሰዓት ክፉ ነው። ከ3 እስከ ቀትር ጥሩ ነው። ከቀትር እስከ 9 ሰዓት አደገኛ ነው ከዘጠኝ ሰአት በኋላ ወደ ፈለከው ሂድ።

በእለተ ረቡዕ /ሮብ/ መልአኩ ሚካኤል ነው። ከነግህ እስከ 3 ጥሩ ከ3 እስከ ሰባት ክፉ ከሰባት እስከ 9 መልካም፡ ከዘጠኝ ሰአት በኋላ አትዋዋል አትሂድ።

በእለተ ሐሙስ መልአኩ ሱርፍያኤል ነው። ከነግህ እስከ ሰባት መልካም ነው። ከሰባት በኋላ ቦታ አትቀይር ምንገድ አትሂድ ክፉ ነው።

በእለተ ዓርብ መልአኩ አንያኤል ነው። ከነግህ እስከ ቀትር መልካም ነው፡ ከቀትር በኋላ አዲስ ነገር አትጀምር።

በእለተ ቀዳሚት መልአኩ ይዝራኤል ነው። ከነግህ እስከ 3 ሰዓት ክፉ ነው ከ3 እስከ ቀትር ጥሩ ነው፡ ከቀትር እስከ አሥር ወላዋይ ነው። ከአሥር በኋላ አርፈህ ተቀመጥ።



Scanned by CamScanner

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ጸሎት በእንተ ሕማም ዓይነጥላ ወአይነ ወርቅ በእንተ ጋራጂ ወገርጋሪ ሐብት በእንተ መዝባሪ ወተጻራሪ ሐብት ወዓይነ ነሐስ

ብሐል ጥብሐል ፲፰፡ የሐል ጥብሐል ፲፰፡ ያጥብሐል ፲፰፡ ያጥብሺ ፲፰፡ ዮድ ፲፰፡ ድድ ፲፰፡ ያጥብሔር ፲፰፡ ዮድድዮስ ፲፰፡ አርጼሜዎስ ፲፰፡ አጹርሜዎስ ፲፰፡ አርጼዎስ ፲፰፡ አናጺዎስ ፲፰፡ አርስጣስዮስ ፲፰፡ በኃይለ ዝንቱ አስማቲከ ፍታሕ ሥራየ ዓይነጥላ ወዓይነ ወርቅ ፍታሕ ሥራየ ጋራጂ ወገርጋሪ ሐብት እምላእለ ገብርከ፡

በርሁ ፯፡ ላጉ ፯፡ ዮድ ፯፡ መራሄል ፯፡ መራሁታኤል ፯፡ ዮፍታሔ ፯፡ ወክፍትኤል ፯፡ ፍንኤል ፯፡ ዘርባኤል ፯፡ ዮፍታኤል ፯፡ ኮይ ኮለላይ ፯፡ ኤል ፯፡ ሶይሶለላይ ፯፡ ሱኤል ፯፡ ሱሐል ፯፡ ኃል ፯፡ ራፎን ፯፡ ራኮን ፯፡ ያውድከን ፯፡ ወጢያከን ፯፡ ሰንተው ዘንተው ቀንተው፡ ቀርነው፡ ቀርነለው፡ ባኤል፡ ኢዮኤል፡ አማኑኤል፡ ኦ፡ ታኤል፡ አርታታኤል፡ ፍናኤል፡ ፍታሕናኤል፡ ብርስባሔል፡ ብርሃናኤል፡ ብርጋሕኤል፡ ፌ፡ ዮፍታሀኤል፡ ኤፍታኤል፡ ጣኤል፡ ባኤል፡ ዘረዳኤል፡ ሰተናኤል፡ ጥኤል፡ ክስትኤል፡ ክስትናኤል፡



Scanned by CamScanner

መክስትናኤል፡ ክፍትናኤል፡ በኃይለ እሉ አስማቲከ ፈትፈነወ ሊተ መንፈስ ቅዱስ ከመያብርህ ገጽየ ወኵለንታየ ወፍታሕ ማእሰረ ሐብትየ ወማህደረ ሥጋየ በቅድመ ሕዝብ ወአሕዛብ ፍታህ እደዊሆሙ ከመ የሐቡኒ ንዋየ ሊተ ለገብረከ፡

ወራፎን፡ ወራኮን፡ ወባፍትን፡ ፍልፍልናኤል፡ ምዝብርናኤል፡ አኽያ፡ ሸራኽያ፡ ኤልሻዳይ፡ አዶናይ፡ እግዚአብሔር፡ ጸባኦት፡ በዝንቱ፡ አስማቲከ፡ ወበዝንቱ፡ ቃለመንፈሣዊ፡ ጤኖ፡ ጤቃኖስ፡ ፍታሕ ሐብትየ ወአንጽሐኒ እምፍርሐትየ አሮይ ፍታሕ፡ ያወኢ ፍታሕ፡ ሰንተው ፍታሕ፡ ቀንተው ፍታሕ፡ ቀርነው ፍታሕ፡ ቀርነለው ፍታሕ፡ ጥበብ ዘከሰሊ፡ ዘአስኮሰሊ፡ ጥበብ፡ መስተሕብርት ዚአከ አብ ይመስል ነደሹር ወልድ ይመስል ቆሮስ መንፈስ ቅዱስ ይመስል ብርስባሔል ጸርደሴን በኃይለ ዝንቱ አስማቲከ አርህቆሙ ወስድዶሙ ለባርያ ወሌጊዎን ለዓይነት ወዓይነጥላ ለዓይነ ወርቅ ወለዓይነ ነሐስ ለጋራጂ ወለገርጋሬ ሐብት እምላእሌየ ወእምላእለኵሉ ኵለንታየ ፍታሕ ወክስት ነገረ ሐብትየ ወማህደረ ሥጋየ በመርሆ ጥበብከ መለኮታዊ አብርህ መልከአ ገጽየ ወኵለንታየ ከመ ብሩህ በቅድመ ሕዝብ

ወአሕዛብ ፍታሕ እደዊሆሙ ከመ የሐቡኒ ንዋየ ወሐብተ ሊተ

ዝኒሩ ፺፱ ወይም ፯ ጊዜ በየቀኑ መድገም የሴት ቀስት የፍየለ ፈጂ የሞይደር የቀጠጥና ሥራቸውን ከርቤ እጣን በአንድ ላይ ወቅጦ እየደገሙ መታጠን

2ኛ/ የቅንቦ የወይራ የዶቅማ የወርካ የወንዛ የእንባጮ ተቀጽላቸውን መሬት ሳያስነኩ በነጭ ዶሮ ደም አንግሶ ፺፱ ደግሞ በአዲስ ሸክላ ከበር መቅበር

3ኛ/ በገዴ ጭራ ሰባት ቀን እየደገሙ መታጠን፡ ልቡዋን ምላስዋን ጥፍሩዋን ከፈላዱት ስር ጋር ደቁስ በነጭ ቁብ ሴት ዶሮ ደም ለውሶ ሰፍቶ መያዝ

4ኛ/ በብርጉድ በሞይደር እየደገሙ ደጋግሞ መታጠን፡ የቀጠጥና አበባ የእንባጮ አበባ ከቅባት ጋር ቀላቅሎ ደግሞ መቀባት፡

## ጸሎተ በእንተ መፍትሔ ሐብት

ቡሩክ ሹር ስመአብ ስመ ወልድ ስመ መንፈስ ቅዱስ ሰውታን ቀንታን ቀስታን ይታን ዋይታን ረዋይታን ሮደታን ደሚሉ ዝዲ ዳታን ንታእ ረፈዓ ሀዓ ሰዓ ነዓ አርእየኒ ንዋየ አምጽእ ንዋየ አስተጋብእ ንዋየ ሰጣቁንዋይ በርዳኒ ንዋይ ቀሳጢንዋይ ዘተመነይኩ ንዋየ



Scanned by CamScanner

ኢይትርፍ መንዲገከ አውሪደከ ከመ እሳት አንዲደከ ልበሰብአዓለም አጥፊአከ ወአእዛኒሆሙ አድሚመከ ወአእይንቲሆሙ አጽሊመከ አምጽእ ንዋየ ወርቀ ወብሩረ ሊተ

ሻውዳ ሹዋዳ ሮሐውዳ ሮምዳ ሜልካሆ ሲልካሆ በስልጣነ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ዝር አላዝር ፯፡ ዝሮ ፯፡ ተከለስም ተከለረድአል ሰሐቦሙ ወኧቅረቦሙ ሰብአዓለም ለውሂበ ንዋይ አቅዝፎር አድቀዝፎር ስሐብ ወስብስብ ንጠቅ ወመንድግ ንዋያተ ወጥሪታተ ሊተ

እመላ እወላ እቀላ ኢአኡን መጁን ወጂም ጂም አብርር ወስብስብ አክንፍ አክነፍንፍ አምጽእ ኀቤየ ወስልብ ልቦናቲሆሙ ለሰብአዓለም ከመየኀቡኒ ንዋየ ወጥሪተ ሊተ

አግርርናኤል ቸቺኢኤል ወርደማኤል መርደመላ ጢእ አቅስዮን በኃይለ ዝንቱ አስማቲከ መንድግ መንዲገከ ንዋየ ኀበኒ ንዋየ ሊተ

ቸሪና ኩቁና ፍርቃ በኃየለ ዝንቱ አስማተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወበስሙ ለእግዚእነ እየሱስ ክርስቶስ መንድግ መንዲገከ ኀበኒ ንዋየ ሊተ

ሜጠለሸ ፯፡ አሸራሆይ አሸራዳይ በከመ አትለውከ ለናጌብ ከማሁ አትሉ ንዋየ ሊተ



Scanned by CamScanner

ላህ ወያላህ አትልል ፮፡ ልቦሙ ለኩሉሙ ሰብአዓለም ሊተ

አላሁማን አጀሚህ አሸር አሸማሁማን በዝንቱ አስማቲከ ፍታህ እደዊሆሙ ለሰብአ ዛቲ ዓለም የኀቡኒ ንዋየ ሊተ

በስሙ ሙራኤል ኤርዮን ሰዋል ሕልቅ መልቅ መሊሃ እምሩከ ግዘተቦሙ ሐሻልቀት ወአቅረብታ ወይመስንቅ ወያዮብእ ወሸሩን ኃይልክን ወረሀምት ስመዋት ሸቶሬ ሩሪህ በኃይለ እሉ አስማቲከ ፍታህ ማእሰረ እዳዊሆሙ ለሰብአ ዓለም ከ ሃየኀቡኒ ንዋየ ሊተ

ያላሁዎሙ ያሆማ ያዋህ ሩረሁህ ወዞመልያየ ምን ያውሉን ልቡይ ህጀር ላሙንሊስ የህ ኩን ሊየ አኸያ ሸራህያ አልሻዳይ ኤልሻዳይ ፀባኦት አዶናይ በኃይለ ዝንቱ አስማቲከ ሀበኒ ዘተመነይኩ ወዘሀሰስኩ ንዋየ ወፈጽም ፈቃደ ልብየ በኩሉ ጊዜ ወበኩሉ መዋእለ ህይወትየ ሊተ

ዝቢር ከሺኮኮ ጉመን ስር አዲስ መስታዊት ዘርግቶ ነጭ ዶሮ አርዶ ስሩን መቁረጥና የስረብዙ የቀረጥ የፍየለፈጂ ፍሬና ስር የቺፍርግ አበባ አንድ በቀል ፍየለ ፈጂ አሩጥ የዝግባ የደቅማ የዋርካ ተቀጽላ ግማሹን በሜሮን ለውሶ ፵፱ ጊዜ መድገምና መቀባት ግማሹን ከሰባት ቀለማት ጋር ቀላቅሎ መጻፍና በቤት ውስጥ ማስቀመጥ ወይም መያዝ።



Scanned by CamScanner

## ጸሎት በእንተ መፍትሔ ሥራይ ወበእንተ መሥገርተ መሠርያን

ፍልድ ፯፡ ፍልድምያስር? ፯፡ ኤጤሚስር ፯፡ ግልድምያስር ፯፡ ግብቶምር ፯፡ ግምቶምር ፯፡ ሬድማዎስ ፯፡ አዊል ፯፡ አዊን ፯፡ አው ፯፡ አውድውድ ፯፡ አሐዋዲን ፯፡ አውድ ፯፡ አውድለላካኤል ፯፡ ብርስባሔል ፯፡ ወበስመሮምና ያምጅጅ ያሞጅጅ ያሞጅብ ያሙዚ አልተጀባሩዲ አልተጀባሩ በኃይለ እሉ አስማቲከ እቀበኒ ወአድህንኒ እምነ መሠረያን ወቁራኛ ወእመስተሕምም ሊተ ለገብርከ

ሖሮፓሮስ አርከመሀዮድ አልዩድ ሴሮሴር ናሴር ቁቁናሽ አኩናኩኤል ምዝኤል ሎፍሐም መሐፍሎን ንምሎስ አብታረ ማረማረድ ሰሎሞን ኤልዳን ህቡዕ ስሙ ለእግዚአብሔር በእሉ አስማት ወበእሉ ቃላት እከልእከሙ ወአውግዝኩከሙ መሠርያን በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወበስመ እግዚእነ እየሱስ ክርስቶስ ከመ ኢትቅረቡ ኀበ ነፍስየ ወሥጋየ ወመንፈሰ አእምሮየ ወተሰደዱ እምቅድመ ገጽየ ለገብርከ



Scanned by CamScanner

አላሁማሁማ ፫፡ ወያትሩሐጅ ፫፡ በሐቅለወግኑን በሀቅለረጀረጂ በሐቅለ መግሙን እለበቆን ወበሸሹን ጠበሸሹን ነንሁን በሀዱን ሻሻበከረቢ ሉኋቀቢ አስማተ እግዚአብሔር አብ መደንግፅ ወልድ ነጐድጓድ መንፈስ ቅዱስ ነበልባለ እሳት ነዳዲ ፌፌቢ ሲፌቢ ፌፌ ቢፌሆን አመሐል ኩክሙ ወአውገዝኩክሙ ቡዳ ወቁመኛ ጋኔን ወቁራኛ ሙዋርተኛ ወአስማተኛ ተያዝ ወጠምዛዢ ወቁራኛ ሙዋርተኛ ወአስማተኛ ተያዝ ወጠምዛዢ

ገቢር

አቱች አባሮ ጭቁኝ ቅጠላቸው ነጭ ሽንኩርት ጥቁር አዝሙድ ጤና አዳም እፀልቡና እፀመናሂ ሁሉንም በአንድ ላይ ወቅጦ በምስር ቂጣ እየደገሙ መብላት ወይም እንደሻሂ እያፈሉ መጠጣት

2/ የእንባሮ የሎሚ የእንቆቆ የልምጭ ተቀጽላቸውን የእፀሣቤቅ የጠሌንጂ ቅጠላቸውን ሥራቸውን የግመሮ የግምሐረግ ሥራቸውን በአንድ ላይ ወቅጦ በአዲስ ሸክላ ዝፍዝፎ ሰባት ቀን ፯ ፯ ጊዜ እየደገሙ መታጠብ ማታ ሲተኛ በዝቃጩ ብረት አግሎ በበላዩ እያደረጉ ታጥኖ መተኛት ነው ማንኛውንምሥራይ ይፈታል።

## አስም

የአስም መንስኤውና ሁኔታው የሳንባ ደምስሮችንና የአየር ማስተላለፊያ ቱቦዎችን የሚዘጋ የሳንባ በሽታ ነው።

በአየር መበከልና በብናኝ የአየር መተላለፊያ ቱባዎች በታወኩና በተዘጉ ጊዜ የመተንፈሻ አገልግሎቶቹ ይቋረጣሉ። የውጭ አየር ወደ ሳንባ መግባቱን ባቆመ ጊዜ የደረት መወጠር የጉሮሮ ፉጭት ሳል ማቃሰት መጨነቅ መታፈን እነዚህን የመሰሉ ሁሉ በህመምተኛው ላይ ይታዩበታል።

በመጀመሪያ የአስም መንስኤው ከዘር የሚተላለፍ ከመሆኑም ሌላ የአካባቢው የአየር ብክለት፡ ጢስ፡ ሻጋታ፡ ኬሚካል የአለባቸው ምግቦች፡ ቀዝቃዛ መጠጦች፡ ያልተመረመሩ መድኃኒቶች፡ የምግብ እጥረት፡ የፀጉርማ እንስሳ ብናኝ ወይም የድመትና የውሻ ጠጉር ብናኝ፡ የራስ ጠጉርና የጥፍር ቁራጭ ወደሳንባ በሚወርደው የደም ስርና የአየር ቱቦ ማስተላለፊያ ላይ በመለጠፍ እጢዎችን ይፈጥሩና በቆሻሻ ልጋግ ይታፈናሉ። በዚህን ጊዜ ነው የልብ ድካም፡ ጭንቀት፡ ድካም፡ የደረት መወጠርና የመፈራገጥ ዓይነት በህመምተኛው ይታያል።



Scanned by CamScanner

ስለዚህ አሰቃቂ ህመም ከሆነው ከአስም በሽታ ነጻ ለመሆን ወይም እድሜውን ለማስረዘም ህመሙን ለመቀነስ ከዚህ በታች የምዘረዝራቸውን የእፀዋት ቅመም በንጽህና በአግባቡ መጠቀም ነው። ሲጠቀሙም ልምምድ ካደረጉ ከመድኃኒት ቀማሚዎችና አስተዋይ ከሆኑ ሰዎች መማከር አስፈላጊ ነው።

1. የዋጊኖስ ፍሬ ከሰባት ቀን በላይ አንድ ማንኪያ የሚሆን መውሰድ ነው። ጉሮሮን ያቆስላልና አለመፍራት ነው። ከውስጥ ያለውን ቆሻሻ ልጋግ ጠርጐ በትውኪያ ያስወጣዋል። በዚህን ጊዜ የእጃ ቅንጨ፣ የጥቁር ስንዴ ንፍሮ፣ የሽንብራ ቆሎ፣ ንፍሮ መመገብ ነው።

ከሚበሉት ጋር ነጭ ሽንኩርት ቀይ ሽንኩርት ቀላቅሎ መብላት ወይም ቀቅሎ መጠጣት ነው። እስከሚሻል ደጋግሞ መውሰድ ነው። እሄን መድኃኒት በሚጠቀሙበት ጊዜ እንዳይወስዱ የተከለከሉ ከባድ ምግብ ጥቅል ጐመንና የባቄላ ወጥ ምስር ዳቦ ጨው ስኳር ቅቤ የሰባ ሥጋ እነዚህን የመሰሉ ምግቦችና ቀዝቃዛና ሆምጣጣ መጠጦች ፈጽመው አይወሰዱም፣ ህመም

አስታጋሽ ተብለው የሚሰጡ ኪኒኖች አስፕሪን የመሰሉ ሁሉ አይወሰዱም መጠንቀቅ ነው።

2. አስም ገና ለጀመረው እፀተከዜ በአንት ዘፍዝፎ አንድ ማንኪያ መጠጣትና ትንሽ ቆየት ብሎ አንት በብዙው መጠጣት ያስታውከውና የውስጡን ቆሻሻ ይዞት ይወጣል። ይህ ለደከመ ሰው ሳይሆን ልቡ ጠንካራ ለሆነ ሰው ነው የሚሰጥ፡ ደረትና ጉሮሮ ይልጣል።

3. የገተም የሺነት ቅርፍት የአሚራ የግምሐረግ ሥር በብዙው ወቅጦ በጠጅ ጥሎ መጠጣት ወይም እንደሻይ እያፈሉ በባዶ ሆድ መጠጣት ነው።

4. የቡና የጫት ቅጠል አውዛ አውጥተህ ከጣዝማ ማር ጋር በባዶ ሆድ መጠጣት ነው። ከዚያ በኋላ አቀበትና ቁልቁለት መውጣት መውረድ ነው፡ እስከሚያስታውከው ድረስ፡

5. ሺፈራው የተባለውን እፀጠንታይ ስሩን በብዙው ወቅጦ ከሱፍ ውኃ ጋር ጧትና ማታ መጠጣት። ቅጠሉን እንደጐመን ከተልባ ዘይት ጋር መብላት ነው።

6. የደረት ውጥረት ለሚሰማው የጂባራ ፍሬ በቅቤ ወይም በተልባ ዘይት አንፍሮ በሻሽ አድርጐ



Scanned by CamScanner

ከደረቱ ላይ ማስቀመጥ ነው። የወይን ፍሬ ከበሉ በኋላ የሱፍ ውኃ ደጋግሞ መጠጣት ነው። ከዚያ በኋላ የዋጊኖስ ፍሬ በጣዝማ ማር መዋጥ ነው።

7. ከደረቱ ላይ እንደቁስል ለሚሰማው የአደስ፡ የአመድማዶ፡ የጤና አዳም፡ የደጋ እንስላል ቅጠላቸውን ወቅጦ እንደሻይ እያፈሉ መጠጣት ነው። በሰባተኛው ቀን የጉርጠብ፡ የሁለገብ ቅጠል፡ በማር ለውሶ መዋጥና በሶ መብላት ወይም የገብስ /ኡብቅ/ ገለፈት ከቅቤ ጋር መውሰድ ነው።

8. ለአስም፡ ለደረት፡ ለራስ ምታት፡ ሐሞት ለሚያስተፋው

የዶግ የወርቅ በሜዳ፡ የእንዘረዘይ፡ የምድር እንቧይ፡ ሥራቸውን ቀይ ሽንኩርት፡ ነጭ ሽንኩርት፡ ጤና አዳም እኩል በእኩል ሰብስበህ በብዙው የአሚራ ቅጠል የጂባራ ፍሬ ሁሉንም በአንድ ላይ ደቁሶ ሲተኛ ከወተት ጋር አፍልቶ ማጠጣት ነው። የበግ ወይም የፍየል ወተት ከሁሉ የተሻለ ነው።

9. ደረቱን ለሚያስጨንቀው የዶግ፡ የምሳና፡ የመቅመቆ፡ የእንዘረዘይ፡ የምድር እንቧይ፡



Scanned by CamScanner

ሥራቸውን ቀቅሉ እንደሻይ ደጋግሞ መጠጣት ነው።

10. መግል ከደረቱ ውስጥ ለሚወጣ ለሚያስተፋው የድንጋይ ሙጫ ድንጋይ መሰሉ ከመሬት ውስጥ የሚወጣና ሲደርቅ ድንጋይ የሚመስለውን የፍየል ጨው፣ የአሚራና የሎሚ ቅጠል በአንድ ላይ ወቅጦ በሱፍ ጭልቃ ማጠጣት ነው። ወይም ከቅቤና ከማር ጋር አፍልቶ መጠጣት ነው።

11. ለፈራና ለሣል ለአስም ፦ የአረግ ሬሣ፣ የእፀ መናሂ፣ የሴት ቀስት፣ የቁራ አረግ፣ የግሜ አረግ /ግም አረግ/ ሥራቸውን ቅጠላቸውን የደብዛ ስር ቅርፍት የግመሮ ስር በብዙው ወቅጦ በወተት እያፈሉ መጠጣት ነው።

12. የአሚራ ስር ቅጠል ነጭ እጣን እንጭብር በወተት እያፈሉ መጠጣት ነው።

13. በጥፍር ቁራጭ ወይም ከድመት ከውሻ ጠጉር ብናኝ ምክንያት በሳንባ ላይ ተለጥፎ ሚያስጨንቅ አስም በሽታ፣
የበረሃ እርያ ደሙን አጠራቅሞ ከስጉን እንቁላል ወይም ከጣዝማ ማር ጋር ወስዶ ወዝለል ወይም መሮጥ ነው።

14. የአሚራ ፍሬ፣ ፌጦ፣ የዋጊናስ ተቀጽላ ፍሬ፣ የሮማን ፍሬ፣ ከጨው ጋር ደጋግሞ ቧትና ማታ መብላት ነው።



Scanned by CamScanner

## ጨጓራ

የጨጓራ ህመም ከመጠበብና ከመጨነቅ የተነሣ በየትኛውም አንጀት ወይም በሆድ እቃ ውስጥ አሲድ ይፈጥርና አገልግሎት እንዳይሰጥ ጨጓራን ይልጠዋል። ከዚህ በኋላ ከምግብ በኋላ ሆድ ቁርጠት፣ መለብለብ፣ ደረትን መፋቅ ይጀምራል። በእንቅልፍ ጊዜም ያሰቃያል። ይህ በጨጓራ ላይ የተፈጠረ አሲድ ጨጓራን ከመላጡ ሌላ አንጀቱም እንዳያስተላልፍ በመከልከል የደም ፈሳሽ እንዲወጣ ይሰነጣጥቀዋል ይልጠዋል።

ለዚህ መድኃኒቱ በቅድሚያ ጭንቀትን፣ አሳብን የሚያመጡ ነገሮች ለመተው ለመራቅ የሚያዝናና ነገር ለማድረግ መሞከር ነው። ወይም ከመጠን በላይ አለማዘን አለመደሰት አለመበሳጨት ነው።

ሌላው ደግሞ ራስምታት የሚሆኑ ኪኒኖች አስፕሪን፣ አድቪል፣ ኑፕሪን፣ አብፕሩፍን (IBUPROFEN) የመሰሉትን ሁሉ አለመውሰድ ነው። ሆምጣጣ የሆነ ነገር ሻይ፣ ቡና፣ ደረቅ መጠጥ፣ ጥብስ ሥጋ፣ ጉመን፣ ቸኮሌት፣ ቅመም የበዛበት ምግብ፣ እርድ፣ ቀረፋ፣ ቁንዶ በርበሬ፣ ጨው፣ ጮማ ሥጋ፣ ቅቤ፣ ትኩስ ወተት፣ ፈጽሞ አለመውሰድ ነው።



Scanned by CamScanner

እነዚህ ሁሉ አሲዱ እንዲበረታ ያደርጉታል። ቀዝቃዛ ወይም በጣም ትኩስ የሆነ ምግብና መጠጥ አለመጠቀም ነው።

በጨጓራ ህመም የተጎዳ ሰው ጉመንና በጨጓራ ላይ ሂዶ የሚለጠፍ ለስላሣና ልጣጭ የሆነ ነገር አለመብላት ነው።

ህመሙን ለማስታገስ ለጊዜው ለብያለ ወተት መጉንጨት ወይም ንጹህ ማር ሣያጣጥሙ በዛ አድርጉ መዋጥ ነው። ሌላው ደግሞ ፓፓያ፣ አቡካዶ፣ ካሮት፣ ሙዝ፣ በማሽን ፈጭቶ የፍየል ወተት፣ የተልባ ውኃ መጠጣት ነው። በሶ፣ የገብስና የስንዴ የማሽላ እሸቶች፣ የገብስ ቆሎ ማዘውተር እስከ ገለባውም ቢበሉት የተሻለ ነው። ከሥጋ የበሬ ምላስ፣ ሰንበር፣ ጨጓራ፣ ብቻውን ያለ እንጀራ ያለዳቦ መብላት ነው።

ምግብ መመጠን እንጂ ቁንጣን እስከሚይዝ መብላት ህመሙን ያባብሰዋል። ነገር ግን የምግብ ሰአት አለማሳለፍ ነው። ከዚህ በታች የምዘረዝራቸውን ለመጠቀም መሞከር ነው።

1. ባምያ ወይም ዋይካ የለንቋጣ ልጥ መሉክያ ልት ላንቁስ ሁለገብ ጉርጠብ እነዚህን የተገኙትን



Scanned by CamScanner

ሰብስቦ በባዶ ሆድ አንድ አንድ ማንኪያ በማር መውሰድ ነው። ዟንዟብል አድርቆ ወቅጦ እንደዚሁ መዋጥና ውኃ አብዝቶ መጠጣት ነው።

2. የቆላ ጦስኝ የፓፓያ ቅጠል አሚራ የሾርባ ቅጠል ጤና አዳም በማር እንደሻይ አዘውትሮ መጠጣት ነው።

3. አልቴት ወይም ከርቤ፣ የእሬት ልብ ከነዚህ ሞቅ ባለ ውኃ በጥብጦ ሲተኙ ሲነሱ ደጋግሞ መጠጣት ነው።

4. የፓፓዬ ፍሬ፣ የድብርቅ ፍሬ፣ ነጭ ሽንኩርት በአንድ ላይ ወቅጦ በማር ለውሶ አንድ አንድ ማንኪያ ጧትና ማታ መዋጥ ነው። ወዲያውኑ የተልባ ውኃ ማለት ተልባ ቀቅሎ ውኃውን አጥሎ ሲበርድ መጠጣት ነው።

5. የሁለገብ፣ የእንጆሪ፣ የጐርጠብ ቅጠላቸውን ወቅጦ በማር በባዶ ሆድ መዋጥ ነው።

6. የግዜዋ የጐርጠብ የቡና የፓፓዬ ቅጠላቸውን እንደሻይ በማር እያፈሉ መጠጣት ነው። የገብስ የአጃ አጥሚት ትንሽ ቁንዶ በርበሬ ነስንሶ መጠጣት ነው።

7. በጣም ለታመመ ቀረፋ፣ ጂንጂብል፣ ቁንዶ በርበሬ፣ የአሚራ ፍሬ፣ የቀጠጥና ቅጠል ፍሬ፣ ነጭ ሽንኩርት፣ እነዚህ ወቅጦ ከአልኮል ጋር ዘፍዝፎ ግማሽ ማንኪያ መውሰድ ነው። ወይም በራሱ ሽንት ዘፍዝፎ አሳድሮ አጥሎ መጠጣት ነው። የጨጓራን አሲድ ያስታግሣል፡ ለጊዜው ግን በጣም ያመዋል ወይም ሽንቱን እያጠራቀመ በባዶ ሆዱ ቢጠጣው የጨጓራን አሲድ ያጠፋለታል። የተላጠው ጨጓራው እንደገና እንዲበቅል አዘውትሮ የገብስ ቆሎ ይብላ። እርሾ የበዛው እንጀራ አይብላ።

8. ጥሬ ተልባ በባዶ ሆድ ከአርባ ቀን በላይ አዘውትሮ በውኃ መዋጥ ነው። እንደዚሁ የሬት ልብ በብዙው አድርቆ ከአብሽ ጋር በጥብጦ መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

# የስኳር ህመም

የስኳር ህመም ተብሎ የሚጠራው ሁለት ዓይነትም ቢሆን መንስኤውና ህመሙ ስለደረሰበት ግለሰብ ጠባይ እጠቁማለሁ።

የመጀመሪያው መንስኤው የምግብ ጊዜን በማሳለፍና ያለመዱትን ምግብ በመመገብ የዓይን መፍዘዝ፣ የጥፍር መውለቅ፣ የነርቭ ጭንቀት፣ ግራ የመጋባት፣ የከንፈር መንቀጥቀጥ፣ መደንዘዝ፣ የልብ ትርታ፣ ማጥወልወል፣ ደርሶ መራብ፣ እነዚህን የመሰሉ ሁሉ በግለሰቡ ይታዩበታል።

ህመሙ ሲበረታ የአይን መታወር፣ የአካል መዛል፣ ማንቀላፋት፣ የሽንት ብዛት፣ የመሰሉ ሁሉ ይደርስበታል።

አስፈላጊ የሆኑ የእፅዋትን ቅመምና ምክርን እንዲጠቀሙበት ከዚህ በታች እዘረዝራለሁ።

1. በቅድሚያ ጨው፣ ስኳር፣ ቅቤ፣ ጮማ ሥጋ፣ አለመብላት ነው። ለመመገብ የሚያገለግሉ ሽንብራ፣ ገብስ፣ አተር፣ ማሽላ፣ ጥራጥሬዎችንና አሾቶችን መብላት። የፍየል፣ የአሣ ሥጋና መረቅ



Scanned by CamScanner

መጠጣት፣ ሚጥሚጣ፣ ቁንዶ በርበሬ፣ ጥቁር አዝሙድ የበዛው ወጥ መመገብ፣ የነጭ ሽንኩርት፣ የጥቁር አዝሙድ፣ የሰናፍጭ ዘይት መጠቀም፣ ውኃ ከሎሚ ውኃ ጋር አዘውትሮ መጠጣት ነው። ስፖርት ማይበዛ መጠቀም ነው።

2. የአሚራ፣ የፈላጹት ቅጠልና ስር እንደሻይ አዘውትሮ መጠጣት የዋጊኖስ የድግጣ ፍሬ በቀን አንድ አንድ መዋጥ ነው።

3. የወፍ ህመም ተብሎ ለሚጠራው የስሚዛና የድግጣ ቀንበጥ ደቁሶ እሩብ ማንኪያ በውኃ በጥብጦ መጠጣት ነው። ማርከሻው ተልባ ወይም ወተት መጠጣት ነው። የድግጣ ፍሬ በየቀኑ መውሰድ ነው።

4. ቼሪ (chery) አጋም የመሰለ ፍሬውን፣ ቅርፊቱን እንደሻይ እያፈሉ አዘውትሮ መጠጣት ነው።

5. ለስኳር ህመም፣ ለጭንቀት፣ ለድካም ለሌላም ህመም ጂይንሰን (Ginseng) ስሩ፣ ካሮት መስሉ ነጭ የጉመን ስር ይመስላልና አዘውትሮ ከሚበሉት ከሚጠጡት ጋር ጨምሮ መጠቀም ነው።

6. አርማጉሣ ወይም ጡት አስጥል አቆራራጭ ቅጠሉን ወቅጦ በሙዝ ውስጥ አድርጉ መዋጥ ነው። ደጋግሞ መጠቀም ነው።



Scanned by CamScanner

# ሣልና ጉንፋን

ሣልና ጉንፋን መንስኤያቸው የታመከ ነገር ሲከፈት የሚበነው ብናኝ ወይም በጣም የቀዘቀዘ ምግብና መጠጥ ወደሆድ በሚወርድበት ጊዜ ግጭት ከሙቀቱ ጋር ይጋጭና በተበከለ አየር ውስጥ ለሚትረመሰመሱ ቫይረሶች ይጋለጣል።

ሲጀምርም የንፍጥ ክምችትና አክታ የበዛው ሳል ወይም ደረቅ ሳል፣ ትኩሳት የራስ ምታት፣ መወራጨት የደረት መወጠር፣ ማላገግ፣ የጉሮሮ መቁሰል፣ የመሰሉት ሁሉ በግለሰቡ ላይ ይታያሉ።

ከዚያም ከደረት ሣል ወደ ሣንባ የአየር ከረጢት ይተላለፍና በየጊዜው ብቅ እልም እያለ ሥሩን ይሰዳል። ከዚያ ጊዜ እየጠበቀ በየምክንያቱ ይነሣል ይስላል። ሌላው ደግሞ ወባ /ንዳድ/ ተይዘው በታመሙ ሰዎች ላይ የሚጀምር ሣል አለ።

ለሁሉም ከዚህ በታች የምዘረዝራቸውን የእጽዋት ቅመም መጠቀምና ራስን ማከም የሚቻልበትን ምክር እለግሣለሁ።



Scanned by CamScanner

1. ዘቢብ በብዙው አሺቶ ከእንቁላል ጋር ሞቅ አድርጎ ጧት ማታ ሲተኙ ከምግብ በኋላ መጠጣት ነው።
2. ቀይ ሽንኩርትና ድንች ወቅጦ ቀቅሎ ውኃውን ደጋግሞ መጠጣት ነው።
3. እንጭብር ቀይስር በአንድ ላይ ወቅጦ እያፈሉ ጧት ማታ መጠጣት ነው።
4. ነጭ ሽንኩርት ወቅጦ በማር ለውሶ በባዶ ሆድ አንድ ማንኪያ መዋጥና ነጭ ሽንኩርት ከወተት ጋር እያፈሉ ጧትና ማታ መጠጣት ነው።
5. ጣዝማ ማር ቅቤ የተልባ ወይም የኑግ ዘይት በአንድ ላይ ለውሶ ለሰባት ቀን ማቆየትና በሰባተኛው ቀን ጠጥቶ አቀበት ቁልቁለት መሮጥ ነው። ጠርጉ እንዲያወጣው ማድረግ ነው።
6. የቀጋ የግመሮ ስር ወቅጦ ጢሱን መጠጣትና ነጭ ሽንኩርትና እጣን ከወተት ጋር አፍልቶ መጠጣት ነው።
7. ማርና ቅቤ፣ ጥቁር መጣፍጥ፣ ነጭ ሽንኩርት፣ እንጭብር ከወተት ጋር እያፈሉ መጠጣት ነው።
8. ሰናፍጭ፣ ኑግ፣ የድንጋይ ሙጫ፣ ጦስኝ፣ በማር ለውሶ በባዶ ሆድ መዋጥ ነው። ወይም የገበር

እንቧይ የውስጡን ፍሬ አጥቦና አድርቆ ከቅቤ ቡና ጋር መጠጣት ነው።

9. ሣል ሆነ መግል ለሆነበት ደረቅ ጂንጂብል የበርበሬ ፍሬ ወቅጦ በማር በባዶ ሆድ መዋጥ ነው። ወይም የክትክታ ቅጠል እንደሲጃራ መጠጣት ነው።
10. ከርቤ፣ እጣን፣ አቡሱዳ፣ አብሽ፣ የደረቀ ጂንጂብል፣ ሚጥሚጣ፣ ሁሉንም በአንድ ላይ ወቅጦ ከወተት ጋር እያፈሉ መጠጣት ነው።
11. በንዳድ ለተነሣ ሣል የቀጋና የቀይ ግመሮ ስር ከዳሞይ ሙጫ ጋር አፍልቶ መጠጣት ነው።
12. የአዞአረግ ቅጠል ወቅጦ ከበግ ሣንባ ውስጥ ከድልህ ቅቤ ጋር ከቶ ጠብሶ መብላት ነው።
13. የብርብራ ፍሬና ቅጠል በማር ለውሶ ከበሉ በኋላ ጤናዳምና እንስላል ከወተት ጋር አፍልቶ መጠጣት ነው።
14. ቀይ ሽንኩርት የሬት ፍሬ ደቁሶ በማር ከበሉ በኋላ የአመድማዶ ቅጠል ከእንቁላል ጋር በጥብጦ መጠጣት ነው።
15. ሣንባው ታሞ ሣል ለሆነበት የቆላ ጦስኝ ቅጠል ከሬት ልብ ጋር በባዶ ሆድ በማር መዋጥ ነው።



Scanned by CamScanner

16. የአሚራ የዱግ የድግጣ ሥራቸውን፣ የአዞ አረግ አበባ የእንስላል ፍሬ፣ የቆላ አባሉ ቅጠል፣ የእፀመናሂ ስር፣ ደረቅ ጅንጅብል ሁሉንም ወቅጦ እንደ ሲጃራ ጢሱን መጠጣት ነው።
17. የእንጭብር፣ የአሚራ፣ የቀበርቾ፣ የአለብላቢት፣ የእንጆሪ፣ የጦስኝ፣ የቁንዶ በርበሬ ቅጠላቸውን ሥራቸውን በአንድ ላይ ቀምሞ በጣዝማ ማር ለውሶ በባዶ ሆድ ግማሽ ማንኪያ መዋጥ ነው። በብርድ ለተነሣ ሣል ከአረቄ ጋር ዘፍዝፎ ሲተኙ አንድ መለኪያ መጠጣት ነው።
18. ለሣልና ለጉበት ፦ የጦስኝ ቅጠልና ስር ከሎሚ ቅጠል ጋር እየቀቀሉ ጧትና ማታ መጠጣት ነው።

## ጉንፋን

1. ለጉንፋን የዳማከሴ ወይም የባህር ዛፍ ቅጠል ቀቅሎ ታጥና መተኛት ነው።
2. ደረቅ ጅንጅብል ከአልኮል ጋር ዝፍዝፎ መጠጣት ነው። ወይም እንደሻይ በቀን ሶስት ጊዜ እያፈሉ መጠጣት ነው። ይህ ንፍጥና አክታ ለበዛው ጉንፋን ነው። ነገር ግን ሣል ወይም ደረቅ ሣል ከአለው ነጭ ሽንኩርት ወቅጦ ከውተት ጋር እያፈሉ ጧት ማታ ደጋግሞ መጠጣት ነው።
3. ቁንዶ በርበሬ የሾርባ ቅጠል እንደሻይ እያፈሉ መጠጣት ነው።
4. ለሣል የሎሚ ቅጠል የቡና ቅጠል የተገኘው ቀቅሎ ደጋግሞ መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

# የሆድ ደዌ ለድርቀት ፈውስ

የሆድ ደዌ ወይም ድርቀት መንስኤውና ህመሙ ከሆድ እቃ ማለት አንጀትና ጨጓራ ከመታወካቸው የተነሣ የተቀበሉትን ምግብ አለመፍጨትና አለመስተላለፍ የሆድን ችግር ያባብሱታል።

በዚህን ጊዜ የአንጀት ኪንታሮት እጢዎች የትርፍ አንጀት መቃወስ የጨጓራ አገልግሎት መድከም ወይም ምግቦችን አለመቀበል ወደ አዳሪ እንዲወጡ አለማድረግ የቆሻሻ ክምችት ይፈጥራል። በፊንጢጣ ላይ ተመሳሳይ ችግር በተፈጠረ ጊዜ የሆድ ህመምን ያባብሰዋል።

ለዚህ ውሉ የተሻለና የተሙዋላ ጤና እንዲኖር ለማድረግ ከዚህ በታች የምዘረዝራቸውን የእፅዋት ቅመምና ምክር መጠቀምና ራስን ለማከም መሞከር ካልተሻለ አዋቂዎችን ማማከር ነው።

1. በባዶ ሆድ ከመኝታ ሲነሱ ንጹህ ውኃ በጣም ያልቀዘቀዘ አዘውትሮ መጠጣት እንደዚሁ ንጹህ ያልተወቀጠ ተልባ በባዶ ሆድ አንድ እፍኝ

በውኃ መዋጥ። ከወር አንድ ቀን እፍኝ አብሽ ጥሬውን እንዲሁ መዋጥ ነው። የአንጀትን ሲስተም አገልግሎት እንዲያቀላጥፍ ከማድረጉም ሌላ በውስጥ ያሉትን የቆሻሻ ክምችትንና እጢዎችን ጠርጐ ያወጣል። አስከሚሻል ጥብስ ሥጋ ጮማ አልኮል ስኳር ጨው ስንዴ ሽንብራ ለተወሰነ ጊዜ ማቆም ነው።

2. የለንቋጣ ልጥ ወቅጦ ከሬት ልብ ጋር ለውሶ ጠዋትና ማታ መዋጥ ነው።
3. የእንስላል ፍሬ ቀቅሉ ከተልባ ጭልቃ ጋር መጠጣት ነው። የጥቁር አዝሙድ ዘይት በባዶ ሆድ አንድ ማንኪያ ያክል መጠጣት ነው።
4. ሆዱ ለደረቀበትና መጸዳጃ ሲሄድ ለሚያስቸግረው የይበደሙ፣ የቀጠጥና የምስርች፣ የዘርጭ እንቧይ የምሳና ሥራቸውን ቅጠላቸውን ወቅጦ ቀቅሉ የተቀቀለውን ውኃ በቀይ ጤፍ ቂጣ ጋር ጋርሮ በትንሹ መብላትና አጓት መጠጣት ነው። ነጭ ሽንኩርት ከተልባ ጋር ለሰባት ቀን ሳያቋርጡ መጠጣት ነው።
5. ስገራ ለከለከለው ሆዱ ለተነፋ አንድ አንድ የዋጊናስ ፍሬ እየዋጠ የላንቁስ የላንቁጣ



Scanned by CamScanner

ቅጠላቸውን ልጣቻውን ወቅጦ በማር በባዶ ሆድ መዋጥ ነው።

6. ሆዱ ለአበጠበት የግዜዋ ስር ከጥጥ ፍሬ ጭልቃ ጋር አፍልቶ በባዶ ሆድ ደጋግሞ መውሰድና በመጨረሻ ቀን ወርቅ በሜዳ በማር ለውሶ ይዋጥ ተጠራርጉ ይወጣለታል።

7. ሆዱ ለነፋውና ለሚላወስበት የምድር እንቧይ ስር የአዞ አረግ ቅጠል የምሳና ቀንበጥ የአዘምር ቅጠል የምሬዝ ተቀጽላ ሁሉንም ወቅጦ ግማሽ ማንኪያ ከቀይ ጤፍ ቂጣ ጋር መብላትና አንት መጠጣት ነው።

8. ሆዱን ለታመመና ለሚያቅለሸልሸው የዝንጅብልና የቀርሻሺበ ቅጠላቸውን ደቁሶ ስንዴ አሳርሮ በአንድ ላይ ለውሶ በማር መብላት ነው።

9. ሆዱን እያመመ ደም ለሚያስቀምጠው የሮማን ቅርፍት የተምር የቀረጥ ፍሬ ጦስኝ ሁሉንም ወቅጦ ከቅቤ ጋር ቀቅሉ አጥሎ መጠጣት ነው።

10. አብሽ ዝግጅብል ነጭ ሽንኩርት በአንድ ላይ ወቅጦ ከማርና ከቅቤ ጋር አንጥሮ በባዶ ሆድ መውሰድ ነው።



Scanned by CamScanner

11. አብሽ ስናፍጭ እንስላል በአንድ ላይ ቀቅሎ የሬት ልብና የሎሚ ውኃ ጨምሮ በማር መጠጣት ነው።

12. በሆዱ ውስጥ ስራይ ላለበት የምሳና የቆላ እንቧይ የዋጊኖስ ፍሬያቸውን የሮማን ቅርፍት የአሚራ የፌጦ ቅጠልና ፍሬ የአንግም የምስርች የቀጠጥና የቀንጠፋ ሥራቸውን ወቅጦ ከጤፍ ዱቄት ጋር ገንፎ አድርጉ መብላት ነው። ጠመን ውሎ በተልባ ወይም በሱፍ ጭልቃ እንጀራ ይብላ። በጧት ተነስቶ የወገርት ስር ቀቅሎ በማር መጠጣት ነው።

13. በሆዱ የበላው ስለሚቆይበት የእንጆሪ ቅጠል ከሚበላው ከሚጠጣው እየጨመሩ መውሰድ ነው። አቱች ጅንጅብል ነጭ ሽንኩርት በማር ለውሶ በባዶ ሆድ መዋጥ ነው።

14. በሆድ ውስጥ ስላለ ወስፋት ወይም ትል ለማስወጣት፡- ምጫምጮ ወገርት አዛምራ ምሳና ቀጋ ቀጤስን ጥንጁት ገራም ጡንጂት ቀንበጣቸውን አርና ኮሶ ዛፍ ስራቸውን ነጭ ሽንኩርት ጅንጅብል ሹሺ ወገርት ጦስኝ አቱች ሥራቸውን ቅጠላቸውን በአንድ ላይ ወቅጦ ከኑግ



Scanned by CamScanner

ጋር መብላትና አጓት መጠጣት። ማርከሻው የዶሮ ጉበት ነው።

15. ለወስፋትና ለኮሶ፦ የክትክታ የጠንበለል የአዛምር የምሳና ቀንበጣቸውን የኮሶ ዛፍ የእንቆቆ የምሳና ፍሬያቸውን ወገርት መቅመቆ ጅንጅብል ሁሉንም በአንድ ላይ አቡክቶ ለሰባት ቀን ማሸግና በሰባተኛው ቀን አድርቆ ወቅጦ በቀይ ጤፍ ቂጣ መብላትና አጓት መጠጣት ነው።

16. ሆዱን ለነፋው የምድር እንቧይ ስር በአጓት ውኃ ቀቅሎ መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

# የእጅና የአካል መንቀጥቀጥ ፈውስ

የእጅ መንቀጥቀጥ የአንጐል መዛባትና መጉደል በአካል ውስጥ የሚተላለፋትን የደም ጋኖችና አውታሮች ማገልገላቸውን ያቋርጣሉ። በየጊዜውም ጡንቻና የጡንቻ ስሮች መወጠርና መልፈስፈስ ይጀምራሉ። በዚህን ጊዜ አውራ ጣት እና ጠቋሚ ጣት መፍተግ፣ የአንደበት መንተባተብ መቆለፍ ይታያል።

አእምሮ የአካል ብልቶችን ማዘዝና ማንቀሳቀስ ያቅተዋል። ለዚህ አስቀድሞ የፍየል ግልገል ጉበትና ሳንባ በትኩሱ መብላት ጅንጅብል በየቀኑ መቆርጠም ወይም እንደሻይ እያፈሉ መጠጣት ነው። አቱች ቅጠል ጨምቆ በባዶ ሆድ መውሰድ፣ ከከብትና ከዶሮ ሥጋ መራቅ፣ ሎሚ በየጊዜው በእጅ ማሸትና ማሸተት ነው።

1. የነጭሽንኩርት የአቱች የአሚራ ቅጠላቸውን እጣን በአንድ ላይ ወቅጦ ከማር ጋር እየበጠበጡ መጠጣት ወይም ነጭ ሽንኩርት፣ አቱች፣ ጅንጅብል በጣዝማ ማር ለውሶ ከቅቤ ጋር አንጥሮ ከተልባ ጭልቃ ጋር መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

2. እጁ ለማይንቀሳቀስ፡- የጦስኝ ቅጠል ስር ወቅጦ እንደ ሻይ አፍልቶ ከጠጡ በኋላ የጦስኝ ቅጠልና የአቱች ቅጠል በቅቤና በተልባ ለውሶ የፈዘዘው እጁ ላይ ደፍድፎና ደምድሞ በክትክታ ቅጠል ሸፍና በሻሽ ማሰርያ ከሙቅ ውኃ ውስጥ እስከሚያልበው ማቆየት፡፡ ከዚያ የፈዘዘውን እጁን ወደ ቀፎ ውስጥ ከቶ ንብ ያስነድፈው፡ ደጋግሞ ካደረገ ይሻለዋል፡፡
3. እጁን ለሚቆረጥመው፡- የአለብላቢት፣ የምስርች፣ የሰመግ ሥራቸውን እፀመናሂ፣ ዲን ሁሉንም ወቅጦ በቅቤ ተቀብቶ እስከሚያልበው እሳት ያስሙቃው፡፡
4. እጁን ለሚያሳክከው አብሽና ሰናፍጭ ከማር ጋር እያፈላ ደጋግሞ ይጠጣ፡፡
5. እጅ እና እግሩ ለሚቆረጥመው ቀረጥ፣ ቀጠጥና ዘርጭ፣ እንቧይ፣ ኮርሽም ወቅጦ ቀቅሉ በማር እንደሻይ እያፈሉ መጠጣት ነው፡፡
6. ለእግር ህመም ከግራር ግንድ ላይ የበቀለን እንጉዳይ የመሰለውን ደቁሶ በበግ ሐሞት ለውሶ መቀባት ወይም ከሙቅ ውኃ ውስጥ አቆይቶ ይቀባው፡፡ እንደዚሁ የአረግ ሬሳ፣ የቁራ አረጊ



Scanned by CamScanner

የስሚዛ የአሰረት የግሜ ሐረግ ሥራቸውን ቅጠላቸውን በአንድ ላይ ወቅጦ ቀቅሉ እግሩን ከቶ ማሞቅ ነው። መጨረሻ በትኩሱ ከእግሩ ላይ ደፍድፎ በክትክታ ቅጠል ማጀልና በሻሽ አሽጉ ማሰር ነው።

7. ሰውነቱ ሁሉ ለፈዘዘ፦ የቀንጣፋ ተቀጽላና ሥሩን፣ የአሚራ ቅጠል ስር፣ የቆላ ጦስኝ፣ የአቱች ቅጠላቸውን፣ መቅመቆ፣ እንጆሪ፣ ወገርት ሥራቸውንና ቅጠላቸውን ወቅጦ ከሚዳቋ ሥጋ ጋር ቀቅሉ መረቁን መጠጣት ወይም ከቁስ ፍየል ሥጋ ጋር ቀቅሉ መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner




# የግብረ ወሲብ ድክመት ፈውስ

ከስነአካላዊና ከስነ ልቡናዊ ወይም ከስነህሊናዊ የተነሣ የግብረ ወሲብ ችግሮች ላሉት ወይም ችግሮችን ለመፍታት ከዚህ በታች በዝርዝር የአስቀመጥኳቸውን የስም ዝርዝር መረዳትና ማስተዋል አለባችሁ።

1. መንስኤ እስኪት — የሚያነሣሣ የሚያነቃቃ
2. መጽንኤ እስኪት — የሚያጠነክር
3. መፍትሔ እስኪት — የሚፈታ
4. ዘኢያወርድ ገትር — የማያስወርድ የማያስቸኩል
5. ጸላኤ ወሲብ /ዓይነጥላ/ — የግብረሥጋ ጥላቻ ወይም ፍራቻ
6. በሴት ላይ ለሚደርስ የግብረ ሥጋ ጥላቻና ፍራቻ
7. የውሃ ሽንት ለሚንጠበጠብበትና ለሚከለክለው

እነዚህ ናቸው። ከእነዚህ መካከል የትኛው እንደሆነ አስተውሎ ማወቅና መረዳት ነው። ከታወቀ የሚረዱትን የእፅዋት ቅመም መጠቀም አለበት።
ለማንኛውም የትኛው ችግር እንደሆነ ለማወቅ ከተፈለገ

ለ1/ ለምሳሌ አንድ ሰው ብቻውን ተኝቶ ሳለ በእንቅልፉ ብልቱ የሚነሣ ከሆነ በወሲብ ጊዜ የማይነሳ



Scanned by CamScanner

ከሆነ ወይም የሚሰንፍ ከሆነ ይህ አካላዊ ችግር ሳይሆን ልቦናዊ ወይም የግብረሥጋ /ጾላኤ ወሲብ/ ጥላቻ ነው።

ለ2/ በግብረወሲብ ጊዜ ስሜቱን ለመቆጣጠር ወይም ለማዘግየት የማይችል ከሆነ የሚያስፈልገው ዘኢያወርድ ተብላው ከሚጠሩት የእፅዋት ቅመም ሌላ ስለዚህ የማስረዳትና የመምከር ችሎታ ካላቸው ጠበብት መማከሩ የተሻለ ነው ወይም ራሱን በመቆጣጠር ወይም ከጓደኛው ሴት ጋር በሚያደርጉት ግብረ ወሲብ ከቀን ወደ ቀን ለማሻሻል መሞከር የተሻለ ነው። ሁኖም ይህ ችግር ልቦናዊ እንጂ አካላዊ ችግር አይደለም።

ለ3/ መፍትሔ እስኪት ለተባለው የእጽዋት ቅመም የሚያስፈልግ አንድዋን ሴት በጣም ከመውደዱ የተነሣ ወይም ስሜታቸው አንድ ዓይነት ይሆንና ሌላዋን ሴት ለመገናኘት ቀርቶ ለመንካት ያስፈራዋል። የውስጡ ስሜት ያፍራል ምክንያቱም ያቺ የወደዳት ሴት ጠረንዋ ወይም አንድ የሆነ ስሜታቸው አስርታልና ችግሩ አካላዊና ልቦናዊ አይደለም ህሊናዊ ችግር እንጂ።

ለ4/ መጽንኤ እስኪት ተብሎ ለሚጠራው የሚበጀው የእፅዋት ቅመም በግብረ ወሲብ ጊዜ ብልቱ ለሚሰንፍበትና ለሚደክምበት ነው።



Scanned by CamScanner

ይህም የወሲብ ድክመት የሚመነጨው ከባድና ደረቅ መጠጥ በሚያበዙ እንደዚሁ የአባለዘርና በውስጣቸው የሥጋ ደዌ በአላቸው፣ በደም ግፊት እና በስኳር በሽታ በተለከፉ ነው።

ምክንያቱም የደም ወሳጅ ወይም የደም መስንዎች ቱቦዎችን የሚዘጉ አሲድን የሚቀንሱና እጢዎችን የሚያበዙ የኬሚካል አዝርእቶችን የሚመገቡ ሁሉ በግብረ ወሲብ ጊዜ መድከምና መስነፍ ከጊዜ በኋላ ይመጣልና በተቻለ ከደረቅ አልኮልና ካልታወቁ መድኃኒቶች መጠበቁ ወይም መጠንቀቁ የተሻለ ነው። ነገር ግን ችግሩ በስተእርጅና ከመጣ ምንም ማድረግ አይቻልም። ይህ የስነ ልቦናና የስነ ህሊና ሣይሆን አካላዊ ነው።

ለ5/ መንስኤ እስኪት ተብሎ ለሚጠራው የሚያስፈልገው የእፅዋት ቅመም

የግብረ ወሲብ ፍላጉትና አሳብ ኑሮት ፈጽሞ ብልቱ የማይነሣ እንዲሁም ዘር የሌለው ሁና ከተገኘ ብዙ ለውጦች እስከሚያገኝ ድረስ ተስፋ ሣይቆርጥ የመንስኤ እስኪት የተባሉትን የእፅዋት ቅመም ለብዙ ጊዜ መውሰድ አለበት ምክንያቱም የወንድነቱ አካል ከአምሮው ጋር የሚያገናኙ የብልቱ የጂማት ስሮች ስብ

በተሞላው እጢና በእንስት ስሜት እንቁላሎች ስለተሞሉ አገልግሎታቸውን አቋርጠዋል።

በዚሁ ምክንያት ከፍራቻም ይሁን ከአስተሳሰብ የአካላዊ የወሲብ ክፍሉ ከስነልቦናዊ ከስነህሊናዊ ጋር ያለውን ግንኙነት ፈጽሞ አቋርጠዋል ስለዚህ የእጽዋት ቅመም ያስፈልጉታል።

ከእጽዋት ቅመሞች በፊት በቅድሚያ ከዚህ በታች የምዘረዝራቸውን ፈጽሞ እንዳይበላ እንዳይጠጣ ማድረግ ግዴታ ነው።

1. ከባድ መጠጥና የመጠጥ ሱስ ከመሆን መጠንቀቅ
2. ከማር በቀር ጣፋጭ ስኳር መቀነስ
3. ጮማና ጥብስ ሥጋዎችን አለማዘውተር
4. የግብረ ወሲብ ጥላቻና ንቀት ወይም ጭንቀት
5. ቁንጣን እስከሚይዝ አለመብላት ነው።

እንደዚሁ ከእፀዋት ቅመሞች በፊትም ይሁን በኋላ የሚበሉና የሚጠጡ ቀጥለው የተዘረዘሩት ይሆናሉ።

1. የአልደቀረ የማር ወይም የተምር ጠጅ ትኩስ ወተት የርግብ ጫጩትና የቁብ ዶሮ መረቅ የምስር የሽንብራ ንፍሮ ውኃ ደጋግሞ መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

2. የአትክልት ቅጠሎችና የፍራፍሬ አዲስ እህል አሸቶች በቆሎ፣ ሽንብራ፣ ማሽላ፣ ገብስ፣ ቦሎቄ፣ ስንዴ፣ ምስር፣ የመሰሉ መብላት ነው።
3. ነጭ ሽንኩርት ጅንጅብል መጣፍጥ የበዛው ወጥ መመገብ ነው።
4. ጾም ማዘውተር ወይም የተመጣጠነ ምግብ ሳያበዙ መብላት ነው።

እነዚህን የመሰሉትን ሁሉ መፈጸም ማድረግ ነው። ነገር ግን የሚበሉትንና የሚጠጡትን አለመቆጣጠርና ማግበስበስ ወይም የህሊናን ድካመትና ውፍረትን አለመቀነስ ከችግሩ ነጻ መሆን አይቻልም።

ከችግሩ ነፃ ለመሆን ለፈለገ በአካሉ ውስጥ የሚገኙትን ስቦችና በስብ የተሸፈኑትን እጢዎችን እንዲጸዱ ማድረግ ነው። እንዲሁ የደም ቱቦዎች እንዲሰሩ ከተፈለገ ጾም ማብዛት ጥራጥሬ መብላት ጧትና ማታ እስፖርት ማድረግ ከሁሉ የተሻለ እርምጃ ነው። በዚህ ውጤት ካልተገኘ ከዚህ ቀጥዬ ስማቸውን የምዘረዝራቸውን የእጽዋት ቅመም መጠቀም ነው። ሌላው ጥንቃቄ ከአሁን በፊት ጥናት ያልተወሰደበትን እፅ ማብዛት ከጥቅሙ ጉዳቱ ይበልጣልና መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

## ክፍል ፩ መንስኤ እስኪት የሚያነሣ የሚያነቃ

1. የታሜ፣ የዶግ፣ የስረብዙ፣ የሴት ቀስት፣ የቀረጥ፣ የደድሆ፣ የአለብላቢት፣ የሣማ ሥራቸውን፣ የጋንቢሉ ቅርፍት ሥር፣ የሙት አንሣ፣ የአደንድን፣ የበረሃ ስኳር፣ እንዳለ ሁሉንም በአንድ ላይ ወቅጦ በሽንብራ ዱቄት ለውሶ ለሰባት ቀን በወይራ ቅጠል ማሸግ። በሰባተኛው ቀን አውጥቶ አድርቆ አንዳንድ ማንኪያ በባዶ ሆድ በነጭ ማር ለውሶ ማዋጥ ሊተኛ ሲል ከዶሮ መረቅ ወይም ከብርዝ ጋር ማጠጣት ነው።
2. አለብላቢት፣ ሣማ፣ ጥጥ፣ ወንዴ ታሜ፣ ዶግ ጉርጉር፣ እሬት፣ የሴትቀስት፣ ሥረብዙ፣ መቅመቆ፣ ቅንጭብ፣ አሞጭ፣ ጋንቢሉ፣ ሙትአንሣ፣ የተገኙትን ሰብስቦ፡ ጥቁር ስንዴ፣ ሽንብራ፣ ምስር፣ አጃ፣ በእነዚህ ዱቄት አቡክቶ የወይራ የምስርች ቅጠል ጉዝጉዞና በቅጠሉ አሽጉ ለሰባት ቀን እንደብቅል መቅበር ነው። በሰባተኛው ቀን አውጥቶ እየመጠኑ ከቂጣ ወይም ከገንፎ ጋር ማብላት ነው። ውኃ ሳይጠጣ ውሉ ብርዝ ጠጅ ወይም የስንዴ ጠላ ወይም ትኩስ



Scanned by CamScanner

ወተት ይጠጣ፣ የፍየል ቀንድ ጉኛውን ይታጠን፣ ከሰሉን በቅቤ ለውሶ የብልቱን ስር ይሸበት።

3. የርግብ ጫጩት፣ የቄብ ዶሮ ስጋ፣ የጅንጀሮ፣ የጅብ፣ የተገኙትን ብልት ወቅጦ ከጥቁር መጣፍጥ ከነጭ ሽንኩርት ጋር በመረቅ ወይም በማር ብርዝ ደጋግሞ ማጣጠት ነው።

4. የላምና የወጠጤ ፍየል ቀንድ የጥቁር ዛፍ የገንቢሉ ቅርፍት ሁሉንም አክስሉ ደቁሶ የአለብላቢት የችፍርግ የሴትቀስት የጠጠብ ሥራቸውን በአንድ ላይ ወቅጦ በጥቁር ስንዴ ጠላ ወይም በዶሮ መረቅ ደጋግሞ ማጠጣት ነው።

5. የአለብላቢት፣ የችፍርግ፣ የዘረጭ እንቧይ ሥራቸውን በነጭ ማር ለውሰህ አብላ

6. የርግብ ሥጋ፣ ከርቤ፣ ጥቁር መጣፈጥ፣ የጣዝማ ማር፣ ሁሉንም ከወተት ጋር ቀቅሎ መረቁን መጠጣት ነው።

7. የምድር አለንጋ ስር ከሰባት ቦታ ላይ ነቅሎ ከሽንብራ ጋር ቀቅሎ ውኃውን በባዶ ሆድ መጠጣት ነው። ሥሩንም አዘውትሮ ማላመጥ ነው።

8. የነጭሎ ፍሬ በብርዝ በጥብጦ መጠጣት

9. የወርቅበሜዳና የእፀ አሐዩ ሥራቸውን ከአውራ ዶሮ መረቅ ጋር ጠጣ።
10. የዶግ፣ የአለብላቢት፣ የአውጥ፣ የሴት ቀስት፣ የወንዴ ቃጫ ሥራቸውን ከሽንብራ ወይም ከምስር ከስንዴ ንፍሮ ጋር ቀቅሎ መረቁን መጠጣት ነው።

## ክፍል ፬ መጽንኤ እስኪት የሚያጠነክር

1. የላም ቀንድና የፍየል ቀንድ አሳርሮ ከጋንቢሉ ቅርፍት ጋር ወቅጦ ከዶሮ ሥጋ ጋር ወጥ ሰርቶ መረቁን መጠጣት ወይም ከብርዝ ጋር ቢጠጡት ፍትወት ያበዛል።
2. የገበሎ ብልት ወቅጦ ከፈላ /ውኃ/ ወተት ጋር ነስነሶ መጠጣት ነው ያበረታል።
3. የአርጃኖ ስብ አቅልጦ ብልቱን ቀብቶ እሳት መሞቅ፤ የአርጃኖን ብልት በማር መዋጥ ነው።
4. የጅብ ሐሞት ብልትን መቀባት ብልቱንም ወቅጦ በስንዴ ጠላ መጠጣት ነው። እንዲሁ የጅንጀሮ ብልት የአውራ ዶሮ ቆለጥ ከምስር ንፍሮ ጋር ቀቅሎ መረቁን መጠጣት ነው።
5. የሣማ የጀጀባ ሥራቸውን ወቅጦ ከተምር ፍሬ ጋር ዘፍዝፎ ደጋግሞ እየጠጡ ከሴት ጋር ማደር



Scanned by CamScanner

6. የአደንድን፣ የበረሃ ስኳር ድንች የወንዶው ቃጫና ሴቴ ቀስት የጉርጉር የሣማ የዘርጭ እንቧይ ሥራቸውን ወቅጦ ከጥቁር ስንዴና ከምስር ዱቄት ጋር ቂጣ ጋግሮ በወተት እያማጉ መብላት ነው። ወይም ከምስርና ከስንዴ ጋር ቀቅሉ ውኃውን መጠጣት ንፍሮውን መብላት ነው።
7. የጋንቢሉ የስሩን ቅርፍት ጠጠባ ችፍርግ ሥራቸውን ጅንጅብል፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ጥቁር አዝሙድ ሁሉንም ወቅጦ ከርግብ ወይም ከዶሮ ሥጋ ጋር አብስሉ መረቁን መጠጣት ሥጋውን መብላት ነው።
8. የአንዳሁላ፣ የበቶ፣ የአምጭ ሥራቸውን ነጭ ሽንኩርት፣ ጅንጅብል፣ ጥቁር አዝሙድ፣ መጣፍጥ በአንድ ላይ ወቅጦ በአዲስ ሸክላ እሳት ከሚነድበት መቅበር፣ በሰባተኛው ቀን ከጥቁር ስንዴ ወይም ከጥቁር ሽንብራ ጋር ግማሽ ማንኪያ ቂጣ ጋግሮ ለሰባት ቀን መብላት። ሌላ ምግብ መቀነስ፣ አትክልትና ንፍሮ መብላት ነው። የአጃ ገንፎ መልካም ነው።



Scanned by CamScanner

9. የቀጠጥና ስር በብዙው ወቅጦ መቀቀልና አውዛውን በጠርሙስ አድርጉ ከነጭ ሽንኩርት ከወተት ጋር አፍልቶ መጠጣት ነው።

10. ከሴት ሲሄድ የሴት ቀስት የጠጠብ፣ የአርገፍጋፎ የጋንቢሎ፣ የጉሺርጥ የምድር አለንጋ የተገኙትን ሥራቸውን እንደመፋቂያ ማላመጥ ነው። ወይም ወቅጦ ከብርዝ ጋር ነስንሶ መጠጣት ወይም ከወተት ጋር ቀቅሎ መጠጣት ብዙ ለውጥ ያሳያል።

## ክፍል ፫ መፍትሔ እስኪት

1. የሴት ቀስት ስር፣ ዝንጅብል፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ቀረፋ፣ ጥቁርመጣፍጥ፣ ቁንደበርበሬ፣ ሚጥሚጣ፣ ሁሉንም በአንድ ላይ ዘፍዝፎ ከተምር ብርዝ ጋር መጠጣት፡ ግማሹን በዶሮ መረቅ /ሾርባ/ መጠጣት ነው።

2. የልምጭ፣ የእንባሮ፣ የምስርች፣ የዶሮ ኩስ፣ የቁራ አረግ፣ የምድር እንቧይ፣ ሥራቸውንና ቅጠላቸውን ወቅጦ በመራራ ቅል ዘፍዝፎ ሰውነቱን ማጠብ ዝቃጩን ማረሻ አግሞ በበላዩ እያደረጉ ጉኛውን ማሞቅ። የምድር እንቧይና የምድር አለንጋ ሥራቸውን በማር ማብላት ነው።



Scanned by CamScanner

3. የሴት ቀስት ሜርቆ/እፀጳጦስ/ ጂባራ፣ ዶግ፣ ዝንጅብል፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ጤና አዳም፣ ጥቁር መጣፍጥ ሥራቸውንና ቅጠላቸውን ፍሬአቸውን አጠራቅሞ የእንቧጮ የሎሚ የዋርካ የልምጭ ተቀጽላ ሁሉንም በአንድ ላይ ወቅጦ ከጥቁር ስንዴ ቂጣ ጋር ማብላት፣ ከተቀመመው ዘፍዝፎ መታጠብ ነው።
4. የጀጀባ የአንዳሁላ የሰንሰል የአለብላቢት የሁለገብ የሴት ቀስት የወንዴቃጫ፣ የስረብዙ፣ የሳማ፣ የምስርች፣ የቀረጥ፣ የዘርጭ እንቧይ፣ የቀጠጥና የዶግ የቅንጭብ ሥራቸውን ቅርፍታቸውን ፣ ለውዝ፣ ተምር ፣ ጅንጅብል ነጭ ሽንኩርት ከርቤ አልቴት ጥቁር መጣፈጥ ቁንዶ በርበሬ ሁሉን አጠራቅሞ በውኃ ዘፍዝፎ ሰባት ቀን ማሸግ በሰባተኛው ቀን አውጥቶ ማድረቅ ነው። እፍኝ ሙሉ ከሽንብራ ከጥቁር ስንዴ ከምስር ጋር ቀቅሎ ብዙ ቀን መብላት ነው። የንፍሮ ውሃውንም መጠጣት ነው።
5. የዶግ የሰሌን የአለብላቢት ሥራቸውን ወቅጦ ከማርና ከወተት ጋር እያፈሉ መጠጣት ነው።
6. የአንበሳ ሐሞት ቢቀቡት ያበረታል

7. የወፍ አንቁር ቅጠል ወቅጦ በዶሮ ስብ ለውሶ መቀባትና ሁልጊዜ እንዲሁ ቢያደርግ ይወፍራል ያሳድጋል።

8. የግራዋ ተቀጽላ አድርቆ ወቅጦ በነጭ ማር ብርዝ ነስንሰው ቢጠጡት አይነጥላውና የታሰረው ይፈታለታል።

## ክፍል ፬

## ዘኢያወርድ /ገትር/

## ፍትወትን የሚያቆይ

1. በግብረ ወሲብ ጊዜ ለሚቸኩልበትና ለሚሰንፍበት፡-

ሙት አንሣ፣ አደንድን፣ የጐሎ የጋንቢሎ ቅርፍት ሁሉንም በአንድ ላይ ወቅጦ በነጭ ማር ወይም በስንዴ ጉሽ ጠላ እየበጠበጡ መጠጣት ነው።

2. እንደ ስኳር ድንች የመሰለ ሰንበታ አብዝቶ መብላት ብዙ ሽንት ያሸናል፡ ኩላሊት ያጥባል፡ ከዚያ በኋላ እፀፍትወት ድቡልቡል ዱባ መስሎ የሚገኝ ሥሩን በግብረ ወሲብ ጊዜ ማላመጥ ነው። እንዲሁ ትንሽ ለሆነበትም ከዶሮ ከቆቅ ወይም ከወጠጤ ፍየል ሥጋ ጋር ቀቅሎ መረቁን ቢጠጡና ከሴት አዘውትረው ቢሄዱ ያሳድጋል።



Scanned by CamScanner

3. የበረሃውን የጠጠብ ስር የዲዲቴ ስርና ፍሬ በወሲብ ጊዜ ቢያላምጡት ያበረታል።
4. የአኽያ አሾህ ሥሩን ቢያላምጡት ያዘገያል ያጸናልም።
5. የድግጣ ስር እያላመጡ መገናኘት ያዘገያል፡ እንዲሁ የዳማከሴ ስር ማላመጥ ጥሩ ነው።
6. የሴት ምላስ /እሾሃም/ ስሩን ማላመጥ ዘኢያወርድ ይሆናል። ወይም ከወገርት ጋር አፍልቶ እንደሻይ ጠጥቶ ግብረወሲብ መፈጸም ብዙ ለውጥ ያሳያል።
7. የዳማከሴ ስር ከመተኛትህ በፊት አላምጥ ወይም ቀቅለህ ጠጣ።

## ክፍል ፩

ጻላኤ ወሲብ ዓይነጥላ (የግብረ ሥጋ ጥላቻና ፍራቻ ለአደረበት ሰው የሚሆኑ)

1. የድንቢጥ ወይም የጥንቸል ብልት ከሴት ቀስትና ከአለብላቢት ጋር ቀቅሎ መረቁን መጠጣት ነው ወይም ከስንዴ ጠላ ጋር ነስንሶ መጠጣት የተሻለ ለውጥ ይገኝበታል።
2. የጦጣ ወይም የጅንጀሮ ወይም የጅብ ብልት የጋንቢሉ ቅርፍት የአሩጥ ስር ሁሉንም በአንድ



Scanned by CamScanner

ላይ ወቅጦ በገብስ ወይም በስንዴ ጠላ መጠጣት ነው።

3. ሙትአንሣ የበርሃግሜ /ግምሐረግ/ የበርሃ ስኳር ድንች አለብላቢት ችፍርግ ቢገኝ ጠጠብ እነዚህን ወቅጦ ከብቅል ጋር አዋህዶ በስንዴ ዱቄትና በግራዋ ቅጠል ተቀጽላውም ቢገኝ ጠንስስ በትኩሱ መጠጣት መብላት ነው። እንዲሁም ከሽንብራና ከምስር ጋር አስፈጭቶ ቂጣ እያስደረጉ መብላት፡ ጸላኤ ወሲብን አይነጥላን ያባርራል።

4. የቀርሽሽቦ ስር በነጭ ማር ብርዝ ደጋግሞ መጠጣት ነው።

5. የፍየል ቀንድ /የአውራ ፍየል/ የላም ቀንድ አሳርሮ ከጋንቢሎ ቅርፍት ጋር ወቅጦ ከድንቢጥ ሥጋ ጋር ወጥ ሰርቶ መረቁን መጠጣት።

## ክፍል ፮

## በሴት ልጅ ላይ ስለሚደርሰው የግብረ ሥጋ ወሲብ ጥላቻና ፍራቻ

አንዲት ሴት ለአቅመ ሄዋን ሳትደርስ ወይም በእድሜ ተመጣጣኝ ካልሆነ ሰው ጋር ያለፍላጐትዋ



Scanned by CamScanner

ተገዳ እንድታገባ ከተደረገ ወይም አረመኔአዊ ተግባር የተፈጸመባት ከሆነ ለብዙ ጊዜ ሁሉም ወንድ ያው እየመሰላት በውስጥዋ ጥላቻውና ፍራቻው እየበዛ ስለሚሄድ ወደወንድ ስትሄድ ትደነግጣለች ትጨነቃለች። ይህም የስነ አካላዊ ሣይሆን የስነ ልቦናዊና የስነ ህሊና ችግር ነው። ለዚህ ምክርና ተመሣሣይዋ ከሆነ ጋር ማግባባት ያስፈልጋል። ከዚህ ሌላ ከዚህ በታች የምዘረዝራቸውን መጠቀም ነው።

1. የሴት ድንቢጥ ሥጋ ከፍየል ማህፀን ጋር ወቅጦ በማር ለሰባት ቀን መስጠት ነው።
2. የሴት ልብ የቀጠጥና የአሩጥ አበባ በነጭ ማር ለውሶ ማዋጥና የሞይደር ስር ከከርቤ ጋር መስጠት ነው ትታጠነው።
3. የሴት ልብ ስር እና የአሬት አበባ በማር ደጋግማ ትብላ።

ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ቅመሞች ሌላ ደግሞ የጸላኤ ወሲብ ጥላቻው ለፀናባቸው ሴቶች ማድረግ የሚገባቸውን ከመግለጼ በፊት የፀላኤ ወሲብ ችግር ወይም ቀውስ እንዴት እንደተፈጠረ ማብራራቱ የተሻለ ነው።

# ፈውስ

አንዲት ሴት የተመጣጠነ ምግብ ካለመመገብ የተነሣ በአፈ ማህፀናቸውና በማህፀናቸው ውስጥ እጢዎች ይፈጠሩና በግብረሥጋ ጊዜ በስሜታቸው ከሚደሰቱ ይልቅ መሸማቀቅን መጨነቅን ጥላቻን በውስጣቸው ይፈጠራል። ምክንያቱም የስሜቱ ፈሳሽ ተቋርጦ በምትኩ ሌላ ሌላ ፈሳሽ ተተክቷልና በዚሁ ምክንያት የውስጥ እጢዎችና እከኮች በርክተው ችግሩን አባብሰውታል። የተለየ ጠረንም ከቀን ወደቀን ያመጣሉ። ደግሞም የሽንት ቤት ወረቀትና ናይሎን ሙታንታ የፊት ቅባቶች ሽታ ያላቸው ሳሙናዎች መጠቀም እንኳን ችግሩ ላለባቸው ለጤነኞች አደገኛ ችግር ስለሚያመጣ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

1. ለዚሁ ችግር ማስወገጃ አልቴት፣ ከርቤ፣ ነጭ እጣን፣ ነጭ ሽንኩርት ሁሉን ወቅጦ በአጓት ዘፍዝፎ ወይም አፍልቶ በቀን ሶስት ግዜ ለብዙ ቀን መታጠብ ነው።
2. ዘቢብ፣ የዕድ ፍሬ፣ ከርቤ ሁሉን ደቁሶ በጣዝማ ማር ለውሶ መቀባት ነው። የሬት ልብ፣ አልቴት፣ በአንድ ላይ ለውሶ ደጋግሞ መብላት ነው።
3. የምድር አለንጋ የግሜሐረግ /ግምሐረግ/ እፀ መናሂ ከርቤ አልቴት፣ ወገርት፣ ሁሉንም ደቁሶ



Scanned by CamScanner

በመራራ ቅል በራስዋ ሽንት ዘፍዝፋ ትታጠብበት፡ ብዙ ጊዜ ታድርግ ችግሩ ፈጽሞ ይወገዳል።

4. ሴትም ትሁን ወንድ የአፍረተሥጋ ችግር ላለባቸው ወይም መቆጣጠር ለአቃታቸው

የልት፣ የጦስኝ፣ የእንስላል፣ የቅል፣ ቅጠላቸውን የሬት ልብ ሁሉንም ደቁሶ መጠጣት ነው። ወይም የለንቋጣ ልጥ፣ የሬት ልብ አድርቆ ከሬት ልብ ጋር ወቅጦ በዶሮ ላባ በአፍረተ ሥጋው ወደ ውስጥ ማስገባት ነው። ቅቤ ሥጋ ተልባ ስኳር ለብዙ ጊዜ አለመጠቀም ነው።

5. ራስ አበራ የተባለውን ወቅጣ በውኃ ዘፍዝፋ ደጋግማ ብልትዋን ትታጠብበት።

## ክፍል ፯

## የውኃ ሽንት ለሚንጠበጠብበትና ወይም ለከለከለው

1. ሽንቱን ለመሽናት ለከለከለው፡- እንስላልና ዘቢብ ቀቅሎ ውኃውን ማጠጣት፣ በተቀቀለው ላይ አፍረተሥጋውን አድርጐ እስከሚያልበው ማቆየት ወይም በትኩሱ ደፍድፎ በሻሽ አሽጐ ማሰር ነው።

2. የጦስኝ ቅጠል በዶሮ ላባ በእፍረተ ሥጋው ማስገባት ወይም ከወተት ከእንቁላል ጋር አፍልቶ ማጠጣት ነው።
3. ሽንቱ ለሚንጠበጠብበት ወይም የሚመግልበት ከርቤና የራሱን ሽንት ከወተት ጋር አፍልቶ ይጠጣ። ወይም እንስላል ችፍርግ ቀስታንቻ ከወተት ጋር እያፈላ ደጋግሞ ይጠጣ ወይም የገተም ቅርፍት ከገብስ ጠላ ጋር አድርጎ መጠጣት ነው።
4. የልት ቅጠል በኑግ ዘይት አብስሉ አፍረተሥጋውን ይሽበትና የምድር ኮሶ ቅጠልና ስር ኮረሪማ ከወተት ጋር አፍልቶ ይጠጣ ብዙ ለውጥ ያያል።
5. የሽንት ችግር ላለበት የሬት ውኃ የጥድ ፍሬ ጦስኝ በአንድላይ አፍልቶ መጠጣት ነው።
6. ሽንትማጥ፣ የችፍርግ፣ የጦስኝ፣ የእንስላል ሥራቸውን ቅጠላቸውን ቀቅሎ ውኃውን ማጠጣት የጥርኝ ቅባት በአፍረተ ሥጋው ማስገባት ነው።



Scanned by CamScanner

7. ደም ለሚያሸናው የጦስኝ ቅጠልና የሬት ልብ በማር ለውሶ ማብላት ነው። ወይም የእንስላል ቅጠል ከበሶ ጋር ይብላ።

8. ብልቱ ለአበጠበት የጨረቃ አር የሚባል ከኩሸሽላ ላይ የሚገኝ አክስሎ መቀባት ነው ወይም የጫት የሽነት ቅጠል በዶሮ ሃሞት ኳውሶ መቀባት ነው፡ ወይም የልት ቅጠል እንደጉመን አብስሎ መብላት በትኩሱ ከብልቱ ላይ ደፍድፎ ማሰር ነው።

9. ብልቱ ለአበጠበት የግራር ፍሬ ቀቅሎ ማጠጣት እንዲሁም በማር ለውሶ ደፍድፎ ማሰር ነው።



Scanned by CamScanner

# የልብ ህመምና ድካም

## ፈውስ

የልብ ድካም የልብ ትርታ መንደፍደፍ ወይም የልብ ህመም እየተባለ የሚጠራው የህመሙ ዓይነትና መንስኤው ብዙ ነው። ለማንኛውም ልብን ለመርዳትና በልብ አውታሮች ላይ አደጋ የሆነውን የልብ ደዌ ወይም ከምግብ የሚገኘውን ፈሳሽ ወይም ጭማቂ ፈሳሽ እንዳይተሳሰፍ የሚያደርገውን አተላና ዝቃጭ የስብ ክምችት እጢዎችን የሚያረግፍ የእጽዋት ቅመም በመጠኑ እጽፍላችሁ አለሁ።

የልብ ህመም የልብ ድካም መሆኑ የሚታወቀው ከባድ ነገር ከደረት ላይ የተጫነ ይመስልና ጭንቅ ጭንቅ ይላል፣ የትንፋሽ እጥረት፣ የሰውነት ዝለት፣ ማቅለሽለሽ፣ ማስታወክ፣ ራስን መሳት፣ ምግብ ለመብላት መታከት፣ የመናገር ድክመት ይታያል። ሌላም በደም ግፊትና ወይም የደም መጠኑ በመዛባት የተነሣ የትንፋሽ እጥረትና ፈጣን የልብ ድቅታ፣ ድንጋጤ፣ የራስ ምታት፣ በመደጋገም ይታያል። ለዚህ አስቀድሞ ቅቤ፣ ስብ፣ ስኳር፣ ጨው፣ ቅባት የበዛው ምግብ ፈጽሞ ማቆም አዲስ



Scanned by CamScanner

እሸት እህል ቀይና ነጭ ሽንኩርት ከምግብ ጋር በማብዛት ውኃ በየጊዜው መጠጣት አስፈላጊ ነው።

1. አቱች ቅጠል ከሱፍ ጭልቃ ጋር አዘውትሮ መጠጣት ወይም ነጭ ሽንኩርትና ሱፍ ቀቅሎ ጧት ማታ ውኃውን እያጠለሉ መጠጣት ነው።
2. ለልብ ትኩሳት፦ ከርቤ፣ ተረን ማርና ቅቤ አንድ ማንኪያ በአንድ ላይ ለውሶ አቅልጦ አንጥሮ መጠጣት ዘቢብና ሱፍ ውኃ በበላዩ መውሰድ ነው።
3. ልብን እያመመ ለሚያስተፋው የገበር እንቧይ የምድር እንቧይ፣ የአረግሬሣ ሥራቸውን ወቅጦ በአንት ዘፍዝፎ ማጠጣት ያስተፋል።
4. ልቡን ለሚያመው የግልገል በግ ሳንባ በውስጡ የአዞ አረግ ቅጠል ደቁሶ ጨምሮ ነፍቶ መጥበስና መብላት ነው። ከዚያ ነጭ ሽንኩርት ሚጥሚጣ ከሱፍ ውኃ ጋር መጠጣት ነው።
5. ለልብ ህመም የአቱችና የግዜዋ ቅጠል ከሰሊጥ ጋር ቀቅሎ በባዶ ሆድ ደጋግሞ መጠጣት ነው።
6. ለልብ ድንጋጤ የጐርጠብ ቅጠል ቀረፋ ገውዝ ለውዝ በአንድ ላይ ወቅጦ እንደሻይ እያፈሉ መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

7. ለማንኛውም የልብ ደዌ የአዞአረግ ቅጠል ነጭ ሽንኩርት ሚጥሚጣ በአንድ ላይ ወቅጦ በበግ ሣንባ ውስጥ ከቶ ነፍቶ ጠብሶ መብላትና ለሰባት ቀን የሱፍና የሰሊጥ ቅባኑግ መጠጣት ነው።

8. ለልብ ውጋት የቀጠጥ ስር ከኑግ ጋር ወቅጦ ጧት መብላት፣ እንዲሁ የበለስ ፍሬ በባዶ ሆድ መብላት ነው።

9. ለልብ ወይም ለኩላሊት ህመም የአመድማዶና የቀይ ሽንኩርት ቅጠል ከወተት ጋር እያፈሉ መጠጣት ነው። ወይም ቀይ ሽንኩርት ቀቅሉ ውኃውን አብዝቶ መጠጣት ነው።

10. የድንብላል ፍሬና የጥጥ ፍሬ ወቅጦ አጥሎ የሬት ልብ በብዙው አጠራቅሞ በአንድ ላይ ጧት ጧት አዘውትሮ ከነጭ ማር ጋር ማብላት ነው።

11. ለጉበት፣ ለሳንባ፣ ለልብ ደዌ ትኩስ የበግ ጉበት ከበሉ በኋላ የአዞ አረግ ቅጠል ነጭ ሽንኩርት ሚጥሚጣ ከሳንባ ውስጥ ከቶ ነፍቶ ከበሉ በኋላ ትርንጉ ደጋግሞ መብላት የትርንጉ ቅጠል ከበጉ ሥጋ መረቅ ጋር መጠጣት ከሁሉ የተሻለ የልብ መድኃኒት ነው።



Scanned by CamScanner

# የራስ ሕመም ዓይነቶችና ፈውስ

## የራስ ሕመም ተብለው የሚጠሩት

1ኛ/ ራስ ምታት፡- በየምክንያቱ የሚያም የራስምች/የራስምትሃት/

2ኛ/ ራስ ፍልጠት

3ኛ/ ራስ መርገዝ፡- ራስ መርዘን

4ኛ/ ራስ ውጋት

5ኛ/ ራስ ማዞር፡- ልብ ማቅለሽለሽ፣ ራስ አዙር

6ኛ/ ራስ መቁሰል

7ኛ/ ራስ መከፈል፡- ግማሽ ራሱን የሚያመው

8ኛ/ ራስ ስንቀን፡- የራስ ግንባር ፊትን የሚያም

9ኛ/ ራስቅል ናላው የተጎዳ የአንጎል ነቀርሣ

10ኛ/ ኤንፍሉዌንዛ - ፍሉ የአየር ጠባይ መቀየር ኢንፍሎዌንዛ

1ኛ/ በተስቦ በሽታ የሚመጡ ተስቦ የወባ ልክፍት የመሰሉ የደም ግፊትና የደም ማነስ ወይም መብዛት ወይም መቅጠንና መወፈርን ወይም የደም ስኳር ማነስ የጉበትና የሳንባ የጨጓራ መታወክና መረበሽ ወይም የደም መበጥበጥ የሚያመጣው የራስ ህመም ራስ ምታት ወይም የራስ ምች ተብሎ ይጠራል። /የራስ ምትሃት/

## የራስ ምታት መድኃኒት ወይም ህመሙን ለመቀነስ የሚረዱ የእፅ ቅመሞች ፈውሶች

1. ነጭ ሽንኩርትና ጅንጅብል በአንድ ላይ ወቅጦ በአፍንጫ መሳብ ወይም ፌጦ ሰናፍጭ፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ጅንጅብል፣ አልቴት፣ እንስላል፣ ጭቁኝ፣ የሎሚ ቅጠል፣ ሁሉንም በአንድ ላይ ለውሶ በአፍንጫ መሳብ ነው።
2. ጭቁኝ፣ ጤና አዳም፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ቀይ ግመሮ፣ ጂባራ፣ አጋም፣ ግሜአረግ /ግምአረግ/ ሥራቸውን ወቅጦ በሻሽ አስሮ በሎሚ ውኃ እየነከሩ በአፍንጫ ማድረግ ነው። ሌላውን ድፍድፍ ከቅቤ ጋር በራስ ላይ ደፍድፎ ለ3 ቀን በሻሽ ሸፍኖ ማሰር ነው።
3. ጂባራ፣ እፀዘዌ፣ እፀመናሂ ሥራቸውንና ፍሬያቸውን ፣ ጭቁኝ፣ ጦስኝ፣ ታርይገማ ሁሉንም በአንድ ላይ ደቁሶ ቢገኝ በፍየል ቅቤ ወይም በቅልጥሙ ለውሶ አቅልጦ በአፍንጫው ውስጥ ማድረግና በመሃል ራሱ ደፍድፎ ማሰር ነው።
4. የርግብ ኩስ፣ ሰናፍጭ፣ ፌጦ፣ ጤና አዳም፣ ጅንጅብል፣ የኮክ ፍሬ ውስጡን በአንድ ላይ ወቅጦ በሻሽ ውስጥ አድርጉ እያሞቁ ከሚያመው



Scanned by CamScanner

ላይ መተኮስ ነው። መጨረሻ በቅቤ ለውሶ አሙቆ በትኩሱ ከራሱ መሐል ማሰር ነው። ወይም በፍየል ቅቤ አንጥሮ በአፍንጫው መውሰድ

5. የእፀመአዛ ስርና የራስ ክምር ቅጠል በአንድ ላይ ወቅጦ በአፍንጫ መሳብ ነው።
6. የእፀመናሂና የሺነት የሥራቸውን ቅርፍት ወቅጦ ሲያመው በአፍንጫ መሳብ ነው።
7. የደብዛ ቅጠልና የዳማከሴ ቅጠል ወቅጦ በአፍንጫ መሳብ ነው።

2ኛ/ የሆድ ድርቀት ያለው ሰው ቀኑ የተላለፈ ወይም የቀየረ ጉድለት የአለው ምግብ በመብላት ወይም የአልኮል መጠጦች በማብዛት የአንጉል እጢዎችን መታወክ ከብርድና በፀሐይ ግመት የሚመጣው የራስ ህመም የራስ ፍልጠት ተብሎ ይጠራል። ይህ ህመም ብዙ ከዘር የሚተላለፍ ነው።

## የራስ ፍልጠት መድኃኒት ወይም ህመሙን ለማስታገስ የሚደረገው ፈውስ

1. ከሴ፣ ዳማከሴ፣ የአረግሬሣ፣ ግዜዋ፣ ምስርች፣ ልምጭ፣ ጠስኝ፣ ወይራ፣ እንባጮ፣ ጭቁኝ/የቡና ቅጠል/ ቅጠላቸውን የተገኙትን ሰብስቦ እንደሻይ እያፈሉ ከሎሚ ውኃ ጋር መጠጣት ነው። ወይም ከነጭ ሽንኩርትና ከለውዝ ጋር እያፈሉ መጠጣት ነው።
2. ሁለገብ፣ እንባጮ፣ ወምበርት ቅጠላቸውን የሴት ቀስት፣ ዋጊኖስ ፍሬያቸውን በአንድ ላይ ወቅጦ በፍየል ቅቤ ወይም ቅልጥ አንጥሮ በአፍንጫ ማድረግ በመሐል ራሱ መደፍደፍ ነው።
3. የሽነት፣ የእፀመናሂ፣ የወርቅ በሜዳ ሥራቸውን ወቅጦ በሰሊጥ ዘይት አንጥሮ በአፍንጫ ማድረግ ነው።
4. የጨጐጐት፣ የወሊት፣ የዶማከሴ፣ ቅጠላቸውን አድርቆ ወቅጦ ሲያመው በአፍንጫው ይሳብ።
5. የእፀዘዌ ስር፣ ጭቁኝ፣ አልቴት፣ ከሰሊጥ ዘይት ጋር በእሳት ከአብላሉ በኋላ ሲበርድ አጥሎ በአፍንጫው ማድረግ ነው።



Scanned by CamScanner

6. እፀጌልጌላ የፈረስ ዘንግ የመሰለች ትንሽ አረም ቅጠልዋን ወቅጦ በአፍንጫው መሳብ ነው። ማርና ቅቤ ዘቢብ እያፈላ ይጠጣ። የበግ ላት በራሱ ያድርግ።

3ኛ/ ከመጠን በላይ ከመብላትና ከመጠጣት ደረቅ መጠጥንም ከማብዛት ጨጓራን ከመላጥና ከማጉስቆል አልፎ የሆድ ድርቀት የጉበት መታወክ ይመጣል። በዚህን ጊዜ ደም የተቀላቀለው ትውኪያ ወደ መጸዳጃ ክፍልም ሲሄዱ የደም መፍሰስ የራስ መክበድ ማጥወልወል የአፍ ምሬት የመሰሉ ሁሉ ይገለጡበታል።

ምንም መንስኤው የመነሻው ስሩ ከሆድ እቃ ውስጥ ከጉበት ላይ ቢነሱም በራስ ቅል ውስጥ ስለሚነዘንዙና ስለሚያሰቃዩ የራስ መርዝ ወይም የራስ መርዘን ተብሎ ስሙ ይጠራል።

የራስ መርዘን ወይም የራስ መርዝ ለተባለው ራስ ህመም መድኃኒት ወይም ማስታገሻው ለጊዜው ማስታገስ በሰናፍጭ ውኃ ልብስን ነክሮ በደረትና በራስ ላይ ማስቀመጥ የሉሚ ውኃ በወፍራም ቡና መጠጣት ነው።

1. የእንስላል ፍሬና ቅጠል አልቴት አፍልቶ ደጋግሞ ከማር ጋር መጠጣት በባዶ ሆድ የተልባ ዘይት የጥቁር አዝሙድ ዘይት መጠጣት ነው።
2. የእሴቴ ሬት ልብ በብዙው አድርቆ በባዶ ሆድ ከተልባ ውኃ ጋር መጠጣት ወይም ከነጭ ሽንኩርት ጋር በማር ለውሶ ለብዙ ጊዜ መውሰድ ነው።
3. የዋጊኖስ ፍሬ ቢቻል ከሱፍ ጋር ዘይት አውጥቶ ግማሽ ማንካ በባዶ ሆድ ደጋግሞ መጠጣት ነው። ብጫ የተቀላቀለው የመሰለ አረንጓዴ መልክ ያስታውካል ደጋግሞ መውሰድ ስፖርት መስራት ነው።
4. የቀጠጥና የአደይ አበባቸውን በብዙው ለቅሞ በአፍንጫው መሳብ ወይም ከፍየል ቅቤ ጋር በአፍንጫው ማድረግ ነው።
5. ሊንደን ቅጠሉን አበባውን ቅርፍቱን እንደ ሻይ አፍልቶ መጠጣት ነው ሲያም።

## 4ኛ/ የራስ ውጋት መፈውስ

የራስ ውጋት ተብሎ የሚጠራው የራስ ህመም ከዘር ወደዘር የሚተላለፍ በአንጉል ውስጥ የሚፈጠሩ እጢዎች ሲሆኑ እነዚህ እጢዎች ከደም ጋን ጋር



Scanned by CamScanner

የሚያገናኙትን የማጅራት ስሮችን ስለሚወጥሩና ስለሚያዛቡ እንዲሁም ጠቅ ጠቅ የሚያደርግና የሚወጋ ህመም ስለሚሰማ የራስ ውጋት ተብሉ ይጠራል፡ ለማገኛውም ይህ ህመም ለያዘው ለጊዜው ተሸፋፍኖ መተኛት ያስፈልጋል። ልብስን በውኃ እየነከሩ በማጅራቱ ላይ ማስቀመጥ ነው።

1. ለራስ ውጋትና ለራስ ፍልጠት እፀመናሂና ሺነት ቅርፍታቸውን ጅንጅብል ወርቅ በሜዳ ጭቁኝ ወቅጦ በእፍንጫው መሳብ ነው። በቅቤ አንጥሮ ከመሃል ራስ ላይ ደፍድፎ ማስቀመጥና በሻሽ ሸፍኖ ማሰር ነው።
2. የቆለቆልዳ፣ የቆለቆል፣ የቅንጭብ፣ የበለስ፣ የጂባራ፣ የቁልቋል፣ የእንተርፋ ደማቸውን የሙጨጭላ ደም ከርቤ አልቴት ነጭ ሽንኩርት ጤና አዳም ጅንጅብል የተገኙትን ሰብስቦ መቀመምና የጉመን የምሳና የዋጊኖስ የጥቁር አዝሙድ የሰሊጥ ሁሉንም በአንድ ላይ ዘይት አውጥቶ በቅመሙ ለውሶ ሲያመው በአፍንጫው ያድርግ። እሩብ ማንኪያ በባዶ ሆድ ይውሰድ ከዘር ወደዘር አይተላለፍም ያመክነዋል ለሁሉም ይሆናል።

## 5ኛ/ የራስ ማዞር ፈውስ

ራስ ማዞር መጨነቅ የሆነ ድምፅ ሲሰሙ መጥላት የሚያመጣው የራስ ህመም መንስኤው ከደም ማነስና ከደም ብዛት ወይም ከደም መቅጠንና መወፈር ልኩን ባለመቆጣጠር የደም ግፊት ወይም የደም መታገድ ይፈጠራል። ምክንያቱም በአንዳንድ ምግብና መጠጥ መጠኑን በመተላለፍ የደም ስሮችን ወይም ቱቦዎችን የሚዘጉ እጢዎች ይፈጠራሉ። በዚህን ጊዜ ለአካል ብልቶች አላፊ የሆነውን ራስን እንዳይቆጣጠር እነዚህ እጢዎች ያስቸግሩታል ይበጠብጡታል። በህመሙ የተጠቃው ሰውም ማቅለሽለሽ ጉበት መታወክ ራስ መዞር መጨነቅ ሊተፋም መሞከር ተለያዩ ጠባዮች ይታዩበታል። ስለዚህ ልብን የሚያስጨንቀውና የሚያቅለሸልሸው ህመም ራስ ማዞር ወይም ራስ አዙር ተብሎ ይጠራል። አንዳንድ ጊዜም ወደጉን ስለሚዞር

ለዚህ ለራስ አዙር ወይም ራስ ማዞር ለተባለው ህመም መድኃኒቱን ማስታገሻውን ወይም መቀነሻውን መድኃኒት ከመውሰድ በፊት የሊጥ ማስነሻ እርሾ ያለው ወይም የበዛው ሆምጣጣ ነገር ስኳር፣ ጨው ለብዙ ጊዜ አለመጠቀም ውኃ በብዙው መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

1. የእንስላል፣ የሮዝመሪ፣ የሸርባ፣ የቡና ቅጠል የናና፣ የቆላ ጦስኝ የሎሚ የትርንጎ ቅጠላቸውን ሰብስቦ ቀምሞ እንደሻይ ጧት ማታ እያፈሉ መጠጣት ነው።
2. ከድከዴ አበባውን በብዙ ለቅሞ ደሙ ለበዛበት አቅጥኖ ደሙ ለአነሰው አወፍሮ እንደሻይ ከሎሚ ውኃ ጋር ማጠጣት ነው።
3. ቀይስር ካሮት ዘቢብ የሎሚ ውኃ የፓፓያ ቅጠል ወይም ፍሬውን የሸርባ ቅጠል ስረ ቴ፣ ስፒናች/የወፍ ጐመን/ ብርቱካን እነዚህንና አረንጓዴ ቅጠል ያላቸውን ፍራፍሬዎች አቀላቅሎ መቀመምና እንደሻይ ቅጠል እያፈሉ ጧት ማታ መጠጣት ነው።
4. ወርቅ በሜዳ፣ ነጭ ሽንኩርት፣ የጅብ ሽንኩርት፣ እፀመናሂ፣ ግመሮ፣ ግምአረግ፣ ታእርይገማ ሥራቸውን በአንድ ላይ ወቅጦ በነጭ ማር ለውሶ ጧት ጧት መዋጥ ወይም ሲያመው በአፍንጫው ይሳብ።



Scanned by CamScanner

## 6ኛ/ ራስ መቁሰል

የራስ መቁሰል መንስኤው በጥንቃቄ ያልተያዘ ወይም በአንድ ነገር የተለከፈ ቅባት በመቀባት ወይም በተመረዘ ምላጭ በመላጨትና ቆሻሻ በሆነ ነገር የሚነጣ የራስ ልክፍት ነው። ይህ ህመም በትንሹ ጀምሮ የሚስፋፋ ወደሌላም የሚተላለፍ የራስ ህመም የሆነ ቁስል ነው። እንደእከክ እየሆነ ግማሹ እጉር ሲኖረው ሌላው እጉር የሌለው ሆኖ ብናይና ቅርፍት የሆነ ነጭ ነገር ይወጣዋል ፎረፎርም የሚባለው ከራሰ ቁስል ጋር ተስማሚና ተመሳሳይ ነው።

ለዚህ ሁሉ በራስ ለሚወጣ ቁስል የአስተናግር የአደስ የጉርጠብ ቅጠላቸውን በብዙው ወቅጦ ከቅቤ ጋር ለውሶ በራስ ላይ ደፍድፎ በሻሽ ሸፍኖ ማሰር ነው። በየሶስት ቀኑ እየታጠቡ ደጋግሞ ማድረግ ነው ያጠፋዋል ይፈውሳል። ለአራት ጊዜ አድርጉ ካልጠፋ ከዚህ በታች የማቀርባቸውን የራስ ቁስል መድኃኒት ቅመም መጠቀም ነው።

1. ነጭ ሽንኩርትና ዋጊኖስ ቅጠሉን ፍሬውን ወቅጦ በማር አቡክቶ ራሱን ላጭቶ መደፍደፍና ማሰር ነው የአቆስለዋል ያነፈርቀዋል አለመፍራት ነው በማር ከተለወሰውም ግማሽ ማንካ መዋጥ ነው።

በሶስተኛው ቀን ራሱን አጥቦ የእስተናግር የጉርጠብ የሁለገብ ቅጠል ደቁሶ ከሰሊጥ ዘይት ጋር መቀባት ነው።

2. የልት የአደስ የወይናግፍት የሥረብዙ የሴት ቀስት የጅብ ሽንኩርት ሥራቸውን ቅጠላቸውን የቀንድ ስር አክስሎ በቅቤ ወይም በዘይት ለውሶ መቀባት ነው።

3. የቁራ አረግ የዋጊኖስ የልት ቅጠላቸውን ወቅጦ ከድኝ ጋር በቅቤ ለውሶ ከራሱ ላይ ደፍድፎ በሻሽ ሸፍኖ ማሰርና በሶስተኛው ቀን አጥቦ ዘይት መቀባት ነው።

4. የግራር ፍሬ ደቁሶ ከቀንድ ስር ጋር አክስሎ ወይም የግራሩን ፍሬ ደምድሞ በበላዩ የቀንዱን ስር አክስሎ በዘይት ለውሶ መቀባትና በሻሽ ሸፍኖ ማሰር ነው፡ ደጋግሞ ከአደረጉት ይጠፋል።



Scanned by CamScanner

## 7ኛ/ ራስ መክፈል ወይም ግመሽ ራሱን መታመም

ይህ የግማሽ ራስ መታመም ራስ መርዘን ተብሎ ከሚጠራው የራስ ህመም ልዩነት የለውም ልዩነቱ አንድ ቀን አንደኛውን የራስ ጐን በሌላ ቀን ሌላውን ክፍል ለይቶ ስለሚያም ነው እንጂ አንድ ናቸው።

መንስኤውም አንድ ነገር ሲሸት ወይም የሆመጠጠ ወይም አርተፊሻል ምግብና መጠጥ ከተጠቀሙ ከበሉና ከጠጡ ሊያዘወትር ይችላል። ለዚህ መድኃኒቱ ወይም ማስታገሻው፡-

1. የወርቅ በሜዳ ስር የምድር እንቧይ ፍሬ ከርቤ አልቴት ሁሉንም በቅቤ አንጥሮ ሲያመው በአፍንጫው ውስጥ ማድረግ ነው።
2. የገተምና የሺነት የምድር አለንጋ ሥራቸውን ከጅንጅብል ጋር ወቅጦ በሚያመው በኩል በአፍንጫው ይሳበው።



Scanned by CamScanner

## 8ኛ/ ራስ ስንቀን

ራስ ስንቀን ተብሎ የሚጠራው የራስ ህመም የራስ ግንባርን ቅንድብ የአይንን አካባቢ የሚያሰቃይ ህመም ነው።

የዚህ ህመም መንስኤው በምግብ ውስጥ የሚጨመሩ የአሲድ ቅመሞች ሆምጣጣ የሆኑ የሲጥ ማስነሻ ስኳር ጨው የአበባ ብናኞች ሺቶዎች የኬሚካል ዘይቶች እንዲሁም ከእንስሳትና ከአራዊት የሚበኑ ጠረኖች ሁሉ በአፍንጫ ውስጥ የገቡና እጢዎችን ይፈጥራሉ እነዚህ እጢዎች እያደጉ እንደገና የሆነ ብናይ ሺታ እየሳቡ የራስ ግንባርን ቅንድብን አካባቢ ያሰቃያሉ፡ እያቅለሸለሸ እራስን ያዞራል፡ ስለዚህ የራስ ስንቀን ተብሎ ህመሙ ይጠራል።

ለዚህ ህመም መድኃኒቱን ከመውሰድ በፊት በጥንቃቄ የሚበሉትን የሚጠጡትን ወይም የሚያስነሣውን ለይቶ ማወቅና መጠንቀቅ አለበት።

1. እፀመናሂ እንስላል ስሚዛ ጭቁኝ አጋም ግመሮ ጂባራ ሺነት ሸተሬ ግምሐረግ እንዘረዘይ ጤና አዳም ነጭ ሽንኩርት አልቴት አርገፍጋፎ ሰመግ ሞይደር አርማጉሣ ታርይገማ ዱርሺት እነዚህን ሁሉ ቀምሞ በፍየል ቅቤ አንጥሮ በአፍንጫው



Scanned by CamScanner

ይውሰድ ወይም በሎሚ ውኃ ለውሶ በአፍንጫው ያድርግ፡ ከሚያመው ላይም ይሰር።

2. የእፀዘዌ ስር በኑግ ዘይት ቀቅሎ ሲተኛ በአፍንጫው ያድርግ።

## 9ኛ/ የራስቅሉ ወይም ናላው ለተጐዳ ወይም የአንጐል ነቀርሣ ይዞት በአፍንጫው መጥፎ ጠረን ለሚሸተው፡-

1. የምድር እንቧይ ፍሬ የቀጠጥ ፍሬ ከርቤ አልቴት ጥቁር አዝሙድ ጭቁኝ እነዚህን ወቅጦ በፍየል ቅቤ ወይም በቅልጥሙ ቅባት አንጥሮ በአፍንጫው ላይ ተኝቶ ያስገባ፡ ድፍድፉን ከመሃል ራሱ ላይ አድርጐ በሻሽ ያሽገው ደጋግሞ ያድርግ።



Scanned by CamScanner

## 10ኛ/ የአየር ጠባይ በሚቀያየርበት ጊዜ ኢንፍሉዌንዛ/ፍሉ

ይህ ህመም በክረምት ወራት የሚሰራጭ ቢሆንም ከአንድ ሰው ወደሌላው ሰው በቀላሉ የሚተላለፍ ነው። ሲጀምርም ራስን ማዞር ማቅለሽለሽ የሰውነትን አካል ማድቀቅ ማድከም ማተኮስ ማዛል ይታይበታል። ጉሮሮውንም መዝጋት ጉልበት ማድከም ሳል በአፍንጫ ላይም ፈሳሽ ይፈጥራል።

ለዚህ መድኃኒቱ አስቀድሞ

1. ቁንዶ በርበሬ ወይም ሎሚ ያለው ጅንጅብል ነጭ ሽንኩርት እነዚህን የመሰሉ በቀን እንደሻይ ሶስት ጊዜ መጠጣት ነው።
2. በሕመሙ ከተያዙ የባህር ዛፍ ቅጠል ወይም የዳማ ከሴ ቅጠል ቀቅሎ መታጠንና መተኛት ነው ወይም የውሻ ኩስ ታጥኖ ተሸፋፍኖ መተኛትና ሲነቁ ለብ ባለ ውኃ ገላን መታጠብ ነው።
3. የጦስኝ የዳማ ከሴ የዝንጅብል የከርቤ ሻይ የብርቱካን የሎሚ ጭማቂ መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

## ለማንኛውም ነገር አስፈላጊውን መርጦ መጸለይ

1. ያሸምኪሳ ወያተምሺሳ ወያተምኪ አጅብ ከሸፈያኤል
   ለማንኛውም ነገር ሁሉ በንጽህና ሁነህ ድገም
2. ድሙሳ አጅብ ያደውዳኤል በረውቅያኤል
   እሄን አዘውትሮ የሚደግም ከድንጋጤና ከደዌ ይድናል ይህ ጸሎት በረውቅያኤል መልአክ የተጻፈ ነው።
3. ያሺለሁስያ የሽሙሺላ አጅብ መድአያኤል
   እሄን ጸሎት ከሁለት ጽሮ በጭን አስሮ ቢሄዱ አያደክምም በየቀኑ ጸልይ
4. ያሙዚስፍ ያኑረሽሳ አጅብ ያሚካኤል
   መከራ የደረሰበት ሰው ቢጸልየው ከመከራው ይወጣለ ይድናል።
5. ያከሩኻጀጠብ አጅብ ያማህያኤል
   ጸር ሥቃይ የደረሰበት ሰው ቢደግመው ጸዕሩ ይጠፋል ሥቃዩና ኃጢአቱ ይደመሰስለታል።
6. ያሐጅታታ ሻፍሻህዩሳ አጅብ ያመቅያኤል
   ይህን የሚደግም ከአደጋ ነገር የሰወራል።
7. ያጣውዓጤፍ አጅብ ያከርመያኤል
   ጽፎ ለሚይዘው የሚናገረው ተሰሚ ይሆናል።

8. ያመስጢዓኑ ሪ አጥሊቅ ሰማተረ አጅብ
ያራህያኤል
ይህን ጸሎት አዘውትሮ ቢደግሙት እግዚአብሔር
የፈለገውን ይሰጠዋል ጸሎቱ ስሙር ይሆናል።
9. ያስፍሐማ አጅብ ያስርፈጠያኤል ማጅራር
ይህን ጸሎት አዘውትሮ ለሚደግመው ጠላት
አያሸንፈውም ከመከራም ይሠወራል።
10. ይጠይሁ አስጅ አጅብ ያከርፍያኤል
አዘውትሮ በንጽህና ለሚደግመው በሀገር ከመጣ
መከራና መቅሰፍት ያመልጣል እግዚአብሔር
ይጠብቀዋል።
11. ያሰውመለከፍያኤል አጅብ ያሰልመያኤል ያለዩል
ይህን የሚደግም ምስጢር ይገለጽለታል ጽፎ
ቢያስቀምጡት ወይም ቢቀብሩት የራቀ ሰው
ይመለሳል።
12. ያባቂ ያአላሁ አዶናይ አስባኡት አልሻይ አጅብ
ያጠውጠያኤል
ይህን የሚጸልይ ከእሥር ቤት ይወጣል ነገሩንም
ሰዎች ይቀበሉታል የሰሙታል
13. ያማንለቀጅ ለቀጅ አጅብ ያመጢጣል
አዘውትሮ ለሚደግመው ጠላትም አያሸንፈው



Scanned by CamScanner

## ፈውስ

14. ያቅያስ መንቅላሰላሁ ያአልሻዳይ ያመንላይሶ
ከሚሰሊሂ ያበረ ያዋሂድ ያአሐድ ያስመድ ያአላሀ
ያሐዩ የቀይም ያዳኢም ያበዳል ያበይል አበድ
ምንገድ ሲሄዱ መከራ ቢደርስበት ይህን
ለሚደግመው ከሚፈራው ነገር ሁሉ ይድናል
ከአሰበው በሰላም ይደርሳል።

15. አጅብ ያቀርጠያኤል አጅብ ያአሸፈረሳኤል
አጅብ ያአስፈርያኤል አጅብ ያደርሐያኤል
አጅብ ያበድ ያኤል አጅብ ያቀስፈያኤል
አጅብ ያኸርያኤል አጅብ ያመድያኤል
አጅብ ያኢዝራኤል አጅብ ያቀድያኤል
አድብ ያመቅርያኤል አጅብ ያደርዳያኤል
ያጣሙሳ ያሳሊጠጢተሳ ያቀርድያኤል

ይህን ጸሎት ስሙን እያስገባ ለሚጸልየው
በሄደበት ሁሉ ሰው ይወደዋል ያከብረዋል ከሁሉ
ነገር ታዋቂ ተወዳጅ ይሆናል።

16. ያጣዕመስስ ያጠሙሰስ ያአሊ ወጠጢስ አጅብ
ያደፍያኤል ያደርመያኤል
ይህን ጸሎት ከስሙ ጋር የሚፈልገውን አብሮ
አስገብቶ ጽፎ ቢደግመው ያፈቅረዋል



Scanned by CamScanner

17. /ያሙሺጢሳ/ ያመውሸጢሳ አጅብ ያሐድቃኤል ያሐውስያኤል
ለዚህ አስማት በፍየለፈጅ ቅጠል ወይም በማዕስ ወይጠል ጽፎ ከአፍ ከንፍ ቢያስርና ቢደግም መላእክት ከፈለገበት አገር ያደርሱታል እንዲሁ ጋኔን ለያዘው ቢደግምበት ይለቀዋል።
18. ያጠይፋጅ ወጠይረሑጅ አጅብ ያደቅያኤሁ
ለዚህ ጸሎት አዘውትሮ ለሚደግመው ከመከራ ሁሉ ይሠውረዋል በህልሙ መጭውን ያሳየዋል።
19. ያቀትፌጅጅ ያአሒተጅ አጅብ ያስምሰማኤል
ይህን የሚደግም ባህር አያሰጥመውም አዝመራውን ከአንበጣ ከበረድ ይጠብቅለታል
20. ያመይ ጠንሐያ ያዳርሁታ አጅብ ያሐርያኤል
ይህን የሚደግም ስልጣን ከእርሱና ከልጅ ልጁ አይወጣም
21. ያመትሱስ ያጠርቂለ ያመርቁዳ ያርሁዳ አጅብ ያጠርጠርያኤል
ይህን ጸሎት ጽፎ ለየአንዳንዱ ፊደል በምስማር እየወጋ ቢጸልይ ከጥርስ ህመምና ከአጥንት ደዌ ይፈወሳል እንዲሁ በድንጋይ ጽፎ ከእርሻ መሐል



Scanned by CamScanner

ቢቀብሩት በረከት ይሆናል አንበጣና ሌሎችም ተባዮች የጠፋሉ።

22. ያሰጥስሐ ያጣህረኅ ያማዕታርቱስ አጅብ የአልሐያኤል አጅብ ያአጅ ለንጃያኤል ወየሂን ያመንለያስሙ ማህዋ ኢላህዋ ላኢላሃ ኢላህዎ ይህን የሚደግም ጠላት አያጠቃውም የአሰበውን ያገኛል

23. ያሽምኢሳ ያነውዕረሳ ይህን በመጀመሪያ ደግሞ ቀጥሉ ያለውን መጸለይ ነው መሬት መሬት እያየ - ሻሐቲል ውጁሀ ወአንቲል ውጁሀ ሲልሐየል ቀዩሚ ወቀድ ኻባ መንሐመለዙልመል — ያአላሀ ያመንፁፍኒል ሙሉከ ወየብቃሕዎ ያመን ላኢላሃ ኢላህዎ ያመን ህወሉ አወለወል አሂሩ ወዘሂሩ ወልባጢኑ
ይህን የሚደግም ከጠብ ይድናል

24. ያሻጢሳ ያላኩሲሳ አጅብ ያሐርቀያኤል ይህን ለሚደግም ጥበብና ትንቢት ይገለጽለታል የሰማውን አይረሳም ሰዎችም ቃሉን ይጠብቁለታል



Scanned by CamScanner

25. የአሀለዩም ያሂን ዋሂን - - - የሂን ዋሂን ሸሙድ ወሸሚላሀ መልሂ ሐምሉሂም አጅብ ያሳዕ ፈያኤል

ይህን ጸሉት ጽፎ ለሚይዘው ከአጋንንትና ከክፉ ሰዎች እግዚአብሔር ይጠብቀዋል።

26. ያሸሂሳ ያጃምሊህ ኸይሰያ ያለውሰረ ያሉያ አሀያ

ይህን በውኃ እየደገመ ለሚጠጣ ከፍርሃቱ ከጭንቀቱ ነጻ ይሆናል ይድናል

27. ያሐጠጥዩሳ ያዶርዩስ ዘልሚስ ሙሳ

እሄን ጽፎ በደረቱ ለሚይዘው የአየው ሰው ያፈቅረዋል በውኃ ደግሞ ቢጠጣው ህመሙ ይቀንስለታል

28. ያሐጅሐያ ያሸፍ ሳሀዩሳ

ይህን በብረት ላይ ጽፎ የእገሌን ሥራይ ሙዋርት ሻር ብሉ በእሳት ቢጨምሩት ይፈታል

29. ያፈርሻ ያሸረሻ ያሻርዩላ - - - ወጀአልና ሚንብይኒ አይዲሂም ሱደን ወሚን ኻልፈሂም ሱደን ፋአቅሸይናሁም ፊሁም ላሀዩብ ሲሩን ሺኮቲል ውልጁሁ ፫ ኸዙ አዕደነሁም ወአብሰራሁም ሐታላ የረውኒ



Scanned by CamScanner

ይህን አዘውትሮ የሚደግም ጠላቶቹ አያዩትም ወደፈቀደው ቢሄድም ጠላት አያገኘውም

30. ያሸምሐ ደይላህ መሊህ ደይለሐለህ የልሚሳ
ይህን ጸሎት አዘውትሮ የሚጸልይ ሰዎች ፈቃዱን ይፈጽሙለታል የጠየቀውን ይሰጡታል።

31. አልወሂሃ ወያሸማኽሊደን ወያመንጢሳ ከሃን ከልሙሳ አላ ሐውሲሳ
ይህን ጽፎ በቀለበት ደግሞ ቢሄዱ ሁሉ ይሆናል

32. ያሸከረሳ መውሙርዋ መርሰያ
ይህን ቃላት በመስታየት ላይ ጽፎ ሮሃንያ ረውሃንያን የዚህን ነገር አሳዩኝ ብሉ ቢተኛ በህልሙ የፈቀደውን ያሳዩታል።

33. ያሺመሂተለወረያ አይሂን ወይሂን እየደገምክ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል በብር ወይም በወርቅ ቀበለት አፅፈህ ብትይዝ አገር ሁሉ ይታዘዝልሃል ያሻኩረሳ አንድም በቆጽለ አንጉት ጽፈህ በንጽህና ሶስት ቀን የጠላትህን ስም እየጠራህ ብትደግምና በመጨረሻው ቀን ከእሳት ብትከተው በጠላትህ ላይ መከራ ይደርስበታል ከዚህ ጠልሰም ጋር በወይራ ቅጠል ፅፈህ በእሳት ብትከተው ጉዳይህ ይፈጸማል።



Scanned by CamScanner

ወደፈለከው አገር ስትሄድ በፍየል ጂማት ደግመህ ጽሁፉን በግራ ክንድህ እሰርና ሂድ ጠላት አያይህም በጥቁር ፍየል ልብ ደግመህ እስረህ ከኩል ጋር ተኩለህ ሂድ

1. አልዓም አልሐኪም
   አዘውትሮ ለሚደግም ጥበብ ይገለጽለታል።
2. አልቀረብ ዓልሙቢን
   ይህን ሺ ጊዜ ቢደግሙት የተደበቀውን ነገር ሁሉ ይገለጽለታል።
3. አልኸቢር
   ይህን ጸሎት አዘውትሮ ለሚደግም ረውኃንያ መጭውን ይገልጹለታል
4. አልሙቢን
   በቀን ሺህ ጊዜ ቢደግሙት የፈለጉት ሁሉ ይገኛል የአሰቡት ይፈጸማል
5. አልሐዲ አልከቢር ዓልሙቢን ዓላሙልቁዩብ
   በመንፈቀ ሌሊት መቶ ጊዜ ከደገሙ በኋላ የሚቀጥለውን ድገም - ኢህዲኒ ያሐዲ ወአሕቢርኒ ያከቢር ወበይንሊ ያሙቢን ወዓለምኒ ያንካ



Scanned by CamScanner

መልቅዩብ። ይህን ደግሞ ቢተኙ ሁሉ ነገር ይገለጻል ስሙን እያስገባ ይጻፍ ይድገም

| | | | |
|---|---|---|---|
| 6 | ፰ | 10 | 6 |
| ፲፪ | ፯ | ፯ | ፰፯ |
| ፯ | 6 | PI | ፰ |
| 1፫ | ፫ | ፱ | 17 |

ሀውለሁ ለኢላሃ ኢላህዎ አልዓሊሙ አልሙለቂዩብ አልሙተከሊም አልሐኪም አልሐፊዝ አረቂብ አልሐዲ

እሁድ ሌሊት 21 ደግሞ ሙተኛት በሰባተኛው ቀን ከዚህ ቀጥሉ ያለውን መድገም ነው።

ቀውሉሁ ሐቁ ወለሁል ሙሉኩ የውመዩንፈሁ ሬሱረ አሊሙል ቀይቢ ወሰሐደቲ ወሕወል አዚዙ አልሐኪም

ድምፁን ይሰማል ቃሉንም ያደምጣል መልኩን ግን አያየውም። ይህ ሁሉ እሚደገም በንጽህና ሁኖ ከአሰት ከመጥፎ ነገር እርቆ ነው በግዴለሽ ቢደግሙት ያስቀስፋል።



Scanned by CamScanner

1. ረብ ረህማን ረዑፍ ረዘቅ ረፍዕ ረቂብ ረሸድ
መሊኮ ልሙልከ አዙል ጀአሊ ወጢዕ ከሪም
ለሐብት በእፀ እስራኤል ስር ደግመህ /99/ ያዝ
2. ረሸድ ረብ ረህማን ረሂም ረው ረዘቅ ረፍዕ
ረቂብ የቁሾን ሐዋሾን ትዝሊ ʼልቦ ኩሊሀሊ
ቢሙ ሀበቱለኒ
ለፍቅር በሴት ቀስት ስር 99 ደግሰ ሀ አሳምጥ
3. ረቂብ ረሸድ ረብ ረህማን ረሂ ረዘቅ ረዑፍ
ያህይን አንተለዚ ሻኢን ተአኩሳ ( ኤልመን
ለሐብት በሙዋጠሺ /አበዛገጣ/ ( ፡ሺኮኩ ጉመን
99 ደገመህ ያዝ
4. ረፍህ ረቂብ ረሸድ ረብ ረህማ ረሂም ረዑፍ
ረዘቅ ወሀብሊ ኤልመን ያህ ወሂከሙተን
ወሊረዘቁ ያዘቁኩንሊ ሙስሐሳ
ለሐብት በእፀእስራኤል በቁራ አረግ ስር 99
ደግመህ ያዝ
5. ረዘቅ ረፍዕ ረቂብ ረሸድ ረቢ ረሂም ረዑፍ
አየአፍል አሳዚነ አሙኑ ለተኩኒ ከለዘዚነ አዘው



Scanned by CamScanner

ሙላ ፌፊሁ አላሁምመማ ቃለ ኮነ ኢን ዩኢላሂ መጀሐብ

በእፀ አንበሳ በፍየለ ፈጂ ስር ለገርማሞገስ 99 ደግመህ ያዝ

6. ረዑፍ ረዘቅ ረፍዕ ረሸድ ረቢ ረሂማን ረሂም ያኑረሚን ኩንሌ ሸኤን ወሁል ያላሁ አንተለዚና ፈላት ተዙል ማቲያኸኸውም

ለማንኛውም በውኃ ደግመህ ጠጣ ታጠብ ተጠመቅ

7. ረሂም ረዑፍ ረዚቅ ረፍዕ ረቂብ ረሸድ ረብ ረህማን አዘሊል አያዚዙ ዙሌአኒ ኢያላም በኢዜኪ ያጀብሩ ሙከፈን ሙጅብላ ኢልቦ ኮሞጊ በምድር እንቧይ ስር ዲኝ ከርቤ እያጤስክ ብትደግም ጠላትህ ይጠፉል

8. ረብ ረህማን ረሂም ረዘቅ ረፍዕ ረቂብ ረሸድ ረብ ያመኢዙ ቢኢዚከ ቅጽሪ መአቢዛን ሙዚሉን ረኩን ሊዞሊሚነ ሙሊሳ

ለፀር 99 ድገም



Scanned by CamScanner

# መፍትሔ ሐብት

## ቡሩክ ሹር

ስመ አብ ስመ ወልድ ስመ መንፈስ ቅዱስ ቡሩክ ሹር ሰውታን ቀንታን ቀስታን ይታን ዋይታን ረዋይታን ሮዳታን ዳሚሎ ዠዲ ዳታን ንታአ ረፈአ ሀአ ሰአ ነዓ አርእየኒ ንዋየ አምጽእ ንዋየ አስተጋብእ ንዋየ ሰጣቂ ንዋይ በርዳጊ ንዋይ ቀሳጢ ንዋይ ዘተመነይኩ ንዋየ ኢይትርፍ መንዲገከ አውሪደከ ከመ እሳት አንዲደከ ልበሰብአዓለም አጥፊአከ ወአእዛኒሆሙ አጽሚመከ ወአእይንቲሆሙ አጽሊመከ አምጽእ ንዋየ ወርቀ ወብሩረ ጥሪተ ወንብረተ ሊተ፡

ሻውዳ ሹዋዳ ሮሐውዳ ሮምዳ ሜልካሆ ሲልካሆ በሥልጣነ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ዠር አላዠር ፯ ዠሮ ፯ ተከለስም ተከለረድአል ስሐቦሙ ወአቅረቦሙ ሰብአዓለም ለውሂበንዋይ አቅገፎር አድቀገፎር ሰሐብ ወሰብስብ ንጠቀ ወመንድግ ንዋየ ወርቀ ወብሩረ ሊተ እመላ እወላ እቀላ ኢአኡን መጁን ወጂምጂም አብርር አስተጋብእ አክንፍ አክነፍንፍ አምጽእ ኀቤየ ወስልብ

ሬውስ

ልቦናቲሆሙ ለሰብእ ዓለም ከመ የኀቡኒ ንዋየ መጥሪተ ሊተ

አግርርናኤል ቀቒኢኤል ወርደማኤል መርደመላጢእ አቅስዮን በኃይለ ዝንቱ አስማቲከ መንድግ መንዲገከ ንዋየ ኀበኒ ንዋየ ሊተ ቀሪና ኩቁና ፍርቃ በዝንቱ አስማተአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ በስሙ ለእግዚእነ እየሱስ ክርስቶስ መንድግ መንዲገከ ኀበኒ ንዋየ ሊተ

ሜጠለሾ ፮ አሸራሆይ አሸራዳይ በከመ አትለውከ ለናጌብ ከማሁ አትሉ ንዋየ ሊተ

ላህ ወያላህ አትልል ፮ ልቦሙ ለኵሉሙ ሰብእ ዓለም ሊተ

አላሁማን አጀሚህ አሸር አሸማሁማን በዝንቱ አስማቲከ ፍታህ እደዊሆሙ ለሰብእ ዛቲ ዓለም ከመ የሀቡኒ ንዋየ ሊተ

በስሙ ሙራኤል ኤርዮን ሰዋል ሕልቅ መልቅ መሊሃ እምሩከ ገዘተቦሙ ሐሸልቀት ወአቅረብታ ወያማሳንቅ ወያዩብ ወሸሩን ኃይልከን ወረሀምት ሰመዋት ሸቶሬ ሩሪሀ በኃይለእሉ አስማቲከ ፍታህ ምእሰረ እደዊሆሙ ለሰብዓ ዛቲ ዓለም ከመየሀቡኒ ንዋየ ሊተ



Scanned by CamScanner

ያላሁምሙ ያሆማ ያዋህ ሩረሁህ ወዘመልያየ ምን ያውሉን ልቡይ ህጀር ላሙንሊስ የህን ኩንሊየ አኺያ ሸራኺያ አልሻዳይ ኤልሻዳይ ፀባኦት አዶናይ በኃይለ ዝንቱ አስማቲከ ሀበኒ ዘተመነይኩ ወዘሀሠስኩ ንዋየ ወፈጽም ፈቃደ ልብየ በኩሉ ጊዜ ወበኩሉ መዋእለ ሕይወትየ ሊተ

ዝቢር ከአበዛንጣ ስር አዲስ መስታወት ዘርግቶ ነጭ አርዶ ፺፱ ደግሞ ስሩን መቁረጥ ነው በመጀመሪያ የስረብዙ የቀረጥ የፍየለ ፈጅ ፍሬና ስር የችፍርግ አበባ አንድ በቀል አሩጥ የዝግባ የዶቅማ የዋርካ ተቀጽላ የወርቅ የብር ሙራጂ ሁሉንም በንጽህና ደቁሶ በህጥር ሺቶ ወይም በሜሮን ቅባት ለውሶ ሁሉንም በአንድ ላይ አዋህዶ እየደገሙ መቀባት ነው ስርክርኩን በቦርሳ መያዝ ነው።

ጸሉተ መንድግ ጀማን ለጀማን አለጁማን ፫ መጀጁማን ፫ አቅጁማን ፫ መንድግ መንድጋቸው መንጥቅ መንጥቃቸው አንጿጽያ መዘውያ አለሁማ መጀር ሰሐቦሙ ወአቅረቦሙ አሆ ይቤሉኒ ኩሎሙ ሰብአ ዓለም ሊተ

በ፫ ሉሚ ፺፱ ደግሞ አንዱን መጠጣት ሁለተኛውን መያዝ ሶስተኛውን ከቤት ውስጥ ማስቀመጥ



Scanned by CamScanner

## ፈውስ

ያወሀቡ ሐቢል ኢልማን ሂኪሚት የርዝቁ ወለርዝቁ ኩሊሙሱፋሉ ሙሱፋሉ የሀቡ የቅድምርም ሲሊሱ ሰሊሉ ሰሊሉማ ታውተንታን ረዋይታን ዘዲ ገዲ በኃይለ እሉ አስማቲከ መንድግ መንድጋቸው መንትፍ መንትፋቸው ለንዋየ ኩሉ ፍጥረት ሊተ ለሀእገሌ

በሺቶ ወይም በዘይት ፺፮ ደግመህ ተኛ

ጸሎተ መንድግ ያንጿጿያ ያሙሐመያ ያምላሁ አልኪ ፈቲሃ መሠራቂሁ አቅያቱ ወናህያቱ መላሊን ሊሽን ወአላሁ ረሂም ወቃል ብሂል አፉስዮት ተድባራት አራህርህ አረህርህ ልቦሙ ለሰብአ ዓለም ከመ የሀቡኒ ንዋየ ዘወርቅ ወዘብሩር ዘተመነይኩ በልብየ በዘኅጸርኩ በአእይንትየ ሊተ ለእገሌ

፺፱ በሜሮን ወይም ውኃ ባልነካው ቅቤ እየደገምክ ተቀባ



Scanned by CamScanner

በስመ እግዚአብሔር ምሕሳበ ንዋይ ዘውስጥ ዘውሳጤ
መቤት

አውናኤል ፫ አቅናኤል ፫ ኢያኤል ፫ ድምናኤል ፫ አክምናኤል ፫ አልፋኤል ፫ ሹሹድናኤል ፫ ከማሁአግናኤል ፫ አርጋኤል ፫ አርግናኤል ፫ አርዮጋርናኤል ፫ አግድራኤል ፫ በብርናኤል ፫ ብርስባሔል ፫ ብርሃናኤል ፫ ሚካኤል ገብርኤል ሱራፌል ኪሩቤል ሩፋኤል ፋኑኤል ዑራኤል ራጉኤል ራሙኤል ግሙኤል አፍኒንኤል ሣቁኤል በኃይለ እሉ አስማተ መላእክቲከ አብርህ ሐብትየ ወጥሪትየ ሰሐብ ወሱበስብ በእዲየ ወርቀ ወብሩረ ወንዋያተ ዓለም ሀበኒ ኃብተ ወብእለ ወጸግወኒ ጸጋ ወሞገስ በዛቲ ዓለም ለገብርከ እገሌ

ዝቢር በበትረ ሙሴ በቁልቋል በግመሮ በጉፋተቀጽላ ከሰባት ቀለማት ጋር ጨምረህ ጽፈህ ፵፱ ደግመህ ያዝ

ጸሎተ በእንተ መፍትሔ ሐብት ወመንድግ ያጭጭቁቁል ፫ ያጭላሃ ፫ ያጡኡሃ ፫ ያጠጹሃ ፫ ሠረገላኤልያስ ደያምሸት ፫ በይሙት ፫ ያሐል ፫ ጥብሃ ፫ ያሸልጥ ፫ ያፍቶሂ ፫ ያአጥብር ፫ አርጋ ሠጋር አልጋር እልፋስክድ ድያር ቢስሚላሂ አርሂ አርሂሚላ አርሐጂም ፫ አፍጂን ፫ አፍናኤል ፫ ደመናኤል ፫ በኃይለ ዝንቱ አስማቲከ አርእየኒ ገጽከ ወአስምአኒ ቃለከ መንድግ በንድጋቸው ፫ መንጥቅ መንጥቃቸው ፫ ሰብአ ዓለም የሐቡኒ ንዋዮሙ ወያፍቅሩኒ በኩሉ ግብር ሻግር መኛንቅር ጨሮጨጨርናኤል ብርስባሔል ሸርኤል ፯ አግዝዞሙ ወአደንግዞሙ ፫ ሆሆሆ ነዓ ነዓ ነዓ ይቤሉኒ ለውሂበ ንዋይ ዘወርቅ ወዘብሩር ፍቅረ ወሰላመ ሰብአዓለም ኩሉሙ ህዝብ ወአህዛብ ሊተ ለገብርከ እገሌ

ዝቢር እጣን ወይም ሰንደል እያጤሱ በቀን ፯ ጊዜ መድገም ቤቱን በሉሚ ውሃና በውሃ እየደገሙ መርጨት ፊትን መቀባት

## አስማተ መላእክቲሁ ለእግዚአብሔር

አጅብ ያቀርጠያኤል ያአሸፈረሳኤል

አ/ ያቀርጠያኤል ያአስፈረያኤል

- ያአክፈረኤል
- ያጸርሕያኤል ያደርሕያኤል
- ያበጅኤል ያበድያኤል
- ያጀብርኤል
- ያበድራኤል
- ያቅስፍኤል - ያቀስፈያኤል
- ያክልኤል - ያኽርያኤል
- ያመድራኤል - ያመድያኤል
- ያዱርደኤል
- ያመቅርያኤል
- ያጣፅሙሳኤል
- ያሊጠጢተሳ
- ያቀድያኤል - ያቀርድያኤል
- ረውቅያኤል
- ጅብሬኤል ጂብሪል ገብርኤል ሰራድያኤል
- ሰምሰማኤል ሰምሰማኤል
- ሚካኤል ያቢካኤል
- ሰርፍያኤል



Scanned by CamScanner

## ፈውስ

- አንያኤል
- ኢዝራኤል
- ራስፍያኤል
- ረስርፍያኤል ሰርፈርያኤል
- ዳርዳኤል
- ደርሀመያኤል
- ኸርርያኤል
- ቀስመያኤል
- ሻርአያኤል
- ቀምያኤል
- ፈርያኤል
- ሐርመክያኤል
- ክርስያል
- አስራያኤል
- ኢስራፊኤል
- ረውዘያያኤል
- ኢስማኤል
- ሐምዘኪኤል
- ሰርሐማኤል
- ካልክያኤል
- ረወብያኤል



Scanned by CamScanner

አጅብ ስምያኤል
አጅብ ጂብራኤል
አጅብ ላሀያኤል
አጅብ ሖርጣኤል
>> ያአኪሩቢኤል
>> ያኢሸራፊኤል
>> ያደወደኤል
>> መድአያኤል
>> ያማሀያኤል
>> ያመቅያኤል
>> ያከርመያኤል
>> ያራሀያኤል
>> ያሰርፈጠያኤል
>> ያከርፍያኤል
>> ያሰልመያኤል
>> ያጠውጠያኤል
>> ያአሸቀያኤል
>> ያመጢጣልኤል
>> ያዳፍያኤል
>> ያሐድቃያኤል
>> ያሐውያሳያኤል

አጅብ ያሖርቀያኤል
አጅብ ያሳዕፊያኤል

አጅብ አሰፋኤል - አልፋያኤል
አጅብ አጀጽሀያኤል
አጅብ ያብድያኤል
አጅብ ያቅሰያኤል
አጅብ ያኽልያኤል
አጅብ ያመድያኤል
አጅብ ያኤዝያኤል
አጅብ ያቀልድያኤል
አጅብ ያዶርያኤል
አጅብ ያመንቅያኤል
አጅብ ያኤል
አጅብ ያረውቅያኤል
አጅብ ያሸርቅያኤል
አጅብ ያጀፍሸሀያኤል
አጅብ ያዱዋኻዝያኤል-
ያጁካዝያኤል
አጅብ ያወኸርፈሃኤል
አጅብ ያደሺበባኤል



Scanned by CamScanner

» ያደቅያኤል

» ያሐርያኤል

አጅብ ያጠርጠርያኤል

አጅብ ያአልሐያኤል

አጅብ ያአጀለንጃኤል

አጅብ ያጎማኤል

አጅብ ያከሪፈሉያኤል

አጅብ ያጠርጦያኤል

አጅብ ያጠውብያኤል

አልዓም አልሐኪም

አልቀረብ አልሙቢን

አልከቢር አልሙቢን

አልሐዲ አልከቢር አልሙቢን

አልኢልዩም አልቀዩም

ኅቡአተ አስማቲሁ ለእግዚአብሔር

ኬዱናኤል

ዮድናኤል

ቁርስድናኤል

ብርሱዲናኤል

ዮኬድናኤል

ጉድናኤል



Scanned by CamScanner

## ሁሉን ቻይ የሆነው የፍጥረት ባለቤትና ጌታ እግዚአብሔር የሚመሰገንበት ቅዱስ ስሙ

| | |
|---|---|
| አልፋኤል | ማምያኤል |
| ያኤል ኢያኤል | ራምያኤል |
| ያህዌኤል | ላልያኤል |
| እየንኤል | ዳንያኤል ድምናኤል |
| ኸማንያኤል ኤልማስ | ዳሌጥናኤል |
| ኤልሻዳይ | ጣቃኤል |
| ኢልያኤል ኤልኢያኤል | ታቱኤል |
| ኤልኦያኤል | ሣህልኤል |
| አዱዋናያኤል | ጼቃኤል |
| ኤልአሄያኤል | ዛዝያኤል |
| ኢውታኤል | ጫትኩታኤል |
| ኡዋውኤል | ቻቻኤል |
| አዋኦሜጋኤል | ሻትኩያኤል |
| | ዣትያኤል |
| ዋዋኤል | ጇርጂናኤል |
| ዋውያኤል | ጋግኤል |
| ውናኤል | ጋቱያኤል |
| ያየያኤል | ቃቃቃኤል ቃአታኤል |



Scanned by CamScanner

| | |
|---|---|
| ያየኤል | ካክርኑኤል |
| ኛናኤል | ኻሃኤል |
| ናርናኤል | ያአኸያኤል |
| ፋታኤል | ያሸራሀያኤል |
| ሻባኤል ቤቃኤል | ያበራኸያኤል |
| በኤትኤል | ያኤልሻዳያኤል |
| ፓፓኤል | ያአዶናይያኤል |
| ጳጳያኤል | ሐራዋኤል |
| ቁርስድናኤል | ኤልማስያ |
| ብርሱዲናኤል | ኤልያስያ |
| ዮኬድናኤል | ኤልባህያ |
| ጉድናኤል | አማኑኤል |
| አዊንያኤል | ዮድናኤል |
| አዊልያኤል | አጋኤል |
| ብርስባሔል ብርስባህኤል | አዊኤል |
| ብርሃናኤል | ራውኤል |
| ክስብኤል | ጤርማኤል |
| አቅናኤል | ድምናኤል |
| አክምናኤል | ሄጠሙናኤል |
| ሹሹድናኤል | ጥስራቱኤል |
| ከማሁአግናኤል | ጠሉልኤል |



Scanned by CamScanner

| | |
|---|---|
| አርጋኤል | ርቱኤል |
| አርግናኤል | ጣኤል |
| አርዮጋርናኤል | ጡጣኤል |
| አግድራኤል | [illegible] |
| | [illegible]ኤል |
| ሕናኤል | አፍሬናኤል |
| ኻራንፌኤል | ሜድያኤል |
| ድምናህኤል ድማህኤል | ሄናላህኤል |
| አፈረኤል | ዳኬብኤል |
| ኢያቡያኤል | ሌፕኤል |
| እየሱስናኤል | ምናትኤል |
| ሰካኤል | ማርዮናልል |
| አስርናኤል | ኤልኦሄያኤል |
| አካኤል | አካኤል ኢትናኤል |
| ኑኤል | ሃሌሉያ ላሄሉሄ ኤልኦሄ |
| | ኤልሻዳይ አሐዱ እግዚአብሔር |

አንተ እግዚኦ አምላክነ ወሀብከነ ህቡአተ አስማቲከ ከመንድኃን እምኩሉ ሥቃይ ወመከራ ራፎን ፫፡ ራኮን ፫፡ ጺስ ፫፡ አፍሊስ ፫፡ መልዮስ ፫፡ እናኤል ፫፡ ጽራኤል ፫፡ ሕናኤል ፫፡ ናሮስ ፫፡ ካሮስ ፫፡ ፋሉስ ፫፡ ሊናስ ፫፡ ሊፋረናስ ፫፡ ኤሮስ ፫፡ ብርስጣሕልዮስ ፫፡



Scanned by CamScanner

## ለሰላምና ለምህረት ለመልካም ዜና የተዘጋጁና የሚላኩ የእግዚአብሔር ቅዱሳን መላእክት ስም

| | |
|---|---|
| ሚካኤል፡ ቢካኤል | አቅማሀኤል |
| ገብርኤል፡ ጀብርኤል ሰራድ | አቃብያኤል |
| ሱራፌል፡ ሹራፍኤል | ብርሱብሔር |
| ኪሩቤያኤል፡ ኪሩብኤል | ኢየሩማናኤል |
| ኡራኤል፡ ኡርኤል | አሜሩኢል |
| ሩፋኤል፡ ሩፍኢል | ኢዮርናኤል |
| አፍኒን፡ አፍኒናኤል | ኢየሩማኤል |
| ራጉኤል፡ ርጉናኤል | ጽጽራኤል |
| ሳቁኤል፡ ረውትያኤል | ሙራኤል |
| አኑኤል፡ ራሙኤል | ጂዳፎርኤል |
| ነሙያኤል፡ ሙራኤል | ብርሀያኤል |
| ሱፍፍያኤል፡ ሰፍፍያኤል | ጽጽርሚኤል |
| ሱርኤል፡ ሰርፊርያኤል | ቱላዳኤል |
| ሱራኤል፡ | አካኤል |
| ሱርያኤል | ሱታኤል ያጠውብያኤል |
| አናንያኤል፡ አንያኤል | ዶትናኤል አፕያኤል |
| ጕርማኤል | ሕዝዝካኤል |
| ድርማኤል | ሩሙኤል ሩማኑኤል |

| | |
|---|---|
| መሐካኤል ስምስማኤል | አልጂፎኤል |
| ከዲራኤል አርድያኤል | ዝልልማኤል |
| ኸድርያኤል | ጣውርኤል |
| አውሳክኤል | ኡድኤል |
| ሰረቃኤል | አድማናኤል አድማኤል |
| ዘሩባብኤል ዙጡኤል | ፋኑኤል |
| ክስብኤል | ሻፍኤል |
| ኢዝሩናኤል ኢዝራኤል | ሳውርናኤል |
| ዙጠያኤል | ጣውርናኤል |
| አድናኤል | ኢትኤል |
| ቤታናኤል | ማውሳልአል |
| ድማህኤል | መናኤል |
| ዴታኤል ድንያኤል | ሱታኤል |
| | ሙራኤል |



Scanned by CamScanner

# ለጥፋትና ለመቅሰፍት ለፍርድ የተዘጋጁ የፍዳ መላእክት ነገዶች

| | |
|---|---|
| ሱቃኤል ዙቃቃኤል | ቀማጥኤል |
| ስቃይ | አግፍላላኤል |
| ሣጥናኤል ሰይጣን ሾይጣን | ጸጸርርሜል |
| ፋጉኤል ግፍ | ሜምሮስኤል |
| ዝዝማኤል | ጥብልያል ጥብልያኮስ |
| ሱቡሐናኤል | ጋቱኤል |
| ኩማኤል ኩታኤል | ናፍታኤል |
| አውላካኤል | ጴጥሮንስኤል |
| ራሙኤል | ጋንኤል |
| ግጃኤል | ኢዚቃኤል |
| ጠምጃኤል | ሱርቃኤል |
| አዛዝኤል | አስኤል |
| አሚዛር | አርሞስ |
| አርማሮስ | በጥርኤል |
| በቅርኤል | ጉልጃንያኤል |
| ኩከብኤል | አኖንኤል |
| ጥሞኤል | ዘቂብ |
| አስራድኤል | ሳምሳቢኤል |



Scanned by CamScanner

| | |
|---|---|
| ሰማዝያስ | ስርትኤል |
| ራምኤል | ጠርኤል |
| ኡራኪኤል | አራዝኤል |
| አኪቢኤል | ጋድርኤል |
| ጣምኤል | አስብኤል |
| ጋራሙኤል | አንጦኤል |
| ዳንጋኤል | እየራያኤል |
| ካድያስ | ኩምኩማኤል |
| ሰዳካኤል | ሽርኤል |
| ሰላታኤል | ሙራያኤል |
| ቶርኤል | ቤኤል ዘኤልቡል |
| ሱሱናኤል | ብኤል ሆር |
| መጂጂናኤል | ብርያኤል ብርያል |
| አጣጥኤል | |



Scanned by CamScanner

# የነቀርሣ መንስኤውና ፈውሱ

በነቀርሣ ለተለከፉ ለማንኛውም ጾታ መጠቀም ወይም አለመጠቀም የሚገባቸውን እዘረዝራለሁ፦ ጥናት የወሰድኩትና የአወኩትን የምጽፍላችሁ መሪራስ አማን በላይ

1. ቅባት የበዛበት ምግብ አልኮል ቡና ጨው ስኳር የፍርኖ ዱቄት እርሾ የአላቸው ሆምጣጣ የሆኑ እንደዚሁ እንቁላል ጮማ ሥጋ እነዚህን የመሰሉትን ሁሉ አለመጠቀም አለመውሰድ ነው፡
2. የሚጠቅሙአቸው አስፈላጊ ምግብና መጠጦች ሽንብራ ዳጉሣ ገብስ ቀይ ጤፍ ማሽላ ካሮት ነጭ ሽንኩርት ጅንጅብል ከዘይት የተልባና የኑግ የሰሊጥ የሱፍ ከሥጋ ጪማ ያልሆነ የፍየል የቆቅ ይመረጣል የፍየል የቅልጥሙ ቅባት ቅቤው ወተቱ አዘውትሮ ቢወስዱት መልካም ነው።
3. በበሽታው ለተለከፉና ላልተለከፉ ከማንኛውም ኬሚካል ብዙ ጊዜ ታሽጉ ከኖረ ከቆርቆሮ ምግብ የቆዳ ቅባቶችና ሽቶ በፀሐይ ጨረር ላይ መጠቀም ለበሽታው መጋለጥና በውስጥ

የሚኖረው የነቀርሣ ደዌ እንደገና ያብብና ይነሣል። ለዚህ መጠንቀቁ የተሻለ ነው ነገር ግን ከሬት ልብ የተዘጋጀና የፍየል ቅቤ ቢቀቡት ለቆዳ ደዌ የመከላከሉ ኃይል ከሁሉ የተሻለ ነው

4. ከነቀርሣና ከምሽሮ ነጻ ሁኖ ለመኖር አረንጓዴ ቅጠል ያላቸውን የጥራጥሬ እሸት መጠቀሙ ወይም መድኃኒቱን ሲወስዱ እነዚህን የመሰሉትን መጠቀም ያስፈልጋል። እንዲሁ ለመጠጥ የእንጆሪ የእንኮይ የዋንዛ የኮርቪም የዶቅማ የሮማን የፍሬያቸውን ጭማቂ ቅርፍታቸውን ቅጠላቸውን ወቅጦ እያፈሉ ከአሚራ ጋር መጠጣት ነው።

## ለማንኛውም ለጡት ህመም ፈውስ

1. የነጭላ የአለብላቢት ቅጠል ደቁሰህ ከሚያማት ላይ እሰርላት እንደዚሁ ሺንጉግ የተባለው የእባጭ መድኃኒት ቅጠሉ ነጫ የመሰለ አጭር እሱን እሰርላት፡
እንስላል ቀቅለህ አጠጣት ጅማቱ ለታሰረም ይሆናል ይፍታታል፡



Scanned by CamScanner

2. የግመሮ የምስርች የአረግ ሬሣ የአሞራ ምሳ የችፍርግ የሰንሰል የሎሚሽት የአዛምር የሁለገብ የጭቁኝ የጥንጁት የእንጉቺት የአሽኮኮ ጉመን የምድር እንቧይ የቀጠጥና የአሚራ የጠሌንጅ የጉርጠብ ከነዚህ የተገኙትን ቅጠላቸውን ሥራቸውን እኩል በኩል ሰብስበህ ወቅጠህ በጋን ቀቅለህ አውዛቸውን አውጥተህ በሻሽ ጨምቀህ በጥቁር ስንዴ ወይም በቀይ ጤፍ ዱቄት ለውስህ እንደ ዳቦቆሎ አድርገህ ለህመምተኛ በባዶ ሆድ በማር ለአርባ ቀን አብላው ለማንኛውም ይሆናል።

3. ጡትዋን ለአቆሰላት ወይም እበጥ ለሆነባት በመጀመሪያ የጉርጠብ ቅጠል ወቅጠህ አድርቀህ ከቁስሉ ላይ ደምድመህ እሰርላት ወይም ጎርጂጂት ወይራ ምስርች ክትክታ አብታ የጅብ ምርኩዝ ኮሸሽላ ጨሬጮ አሉማ ቅሞ ጠንበለል ነጭ የጅብ ምርኩዝ ቀጋ ቀጠጥና ጨጉጉት ቱልት ሁለገብ ጠሌንጅ አሚራ እፀመናሂ አንደንድሺ ምሳና ስረብዙ ሰመግ ከነዚህ የተገኙትን የሥራቸውን ቅርፍትና ቀንበጣቸውን ሰብስበህ ወቅጠህ በማርና በቅቤ አንጥረህ አስቀምጠው ስታመመ ግማሽ



Scanned by CamScanner

ማንኪያ በባዶ ሆድ አብላ ከሚያመው ላይ ደፍድፈህ በሻሽ አሽገህ እሰርለት፡

4. በብብትና በጡት ላይ ለወጣ ነቀርሣ ወይም ምሽሮ የጥቁር እንጆሪ የዋንዛ ፍሬ ጨምቆ ጧትና ማታ ለብዙ ጊዜ አጠጣ ከሚያመው ላይ ቅርፍታቸውን በእሳት አክስለህ ለውሰህ ደምድምበት ወይም ጎርጂት ኧሰርላት

5. ቁስሉ እንዲደርቅ የጉርጠብ የክትክታ የፈላጺት የአቱች የቀጠጥና የአሺክት የድግጣ ቅጠላቸው ከከርቤ ጋር ወቅጠህ ከቁስሉ ላይ ደምድምበት

## ለተደበቀ ወይም ውስጥ ውስጡን ለሚያመውና በውጭ ለአበጠ ነቀርሣ ወይም ለቆሰለ ምሺሮ

### ፈውስ

1. ምስርች ቀይ ግመሮ ዋጊኖስ አጋም ጉርጠብ ቀጠጥና ሥራቸውን ፍሬያቸውን ቅጠላቸውን ቀቅለህ አውዛውን አጥለህ በጥቁር ጤፍ ዱቄት ለውሰህ እንደዳቦ ቆሎ አድርገህ የባቄላ ፍሬ ያክል ጧትና ማታ አብላ የሬት ልቡን አውጥተህ ተቀብቶ ፀሐይ ይሙቅ ለሃያ አንድ ቀን ይጠቀም

2. መቅመቆ የቁራ ውሽሽ በቶ አይደደም ወርቅበሜዳ እንዘረዘይ አደንድሺ ምሣና ሥራቸውን ወቅጠህ በፍየል ሽንት በአረግሬሣ ቅጠል ውኃ ለውስህ አድርቅና ወቅጠህ በሱፍ ውኃ አንድ ማንኪያ ስጠው ለ40 ቀን ይውሰድ፡ ቢያስቀምጠውና ቢያስታውከውም ይውሰድ አያስታጉል ነገር ግን ሌላ ደዌ በሆዱ ላለበትና ለልበ ደካማ ሰርጀሪ ለሆነ ሰው አትስጥ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

3. ሣንባ ነቀርሣ ለሆነበት

አፈጉማ ዝግጣ ብሳና ሮማን ቅርፍታቸውን ከዝንጅብል ጋር ወቅጠህ በማር አውጥ፡ መግል እየመሰለ ከሆዱ ይወጣል።

4. በዘር ለሚተላለፍና ሴቴ ተብሎ ለሚጠራው የውስጥ ነቀርሣ፡-

የምሣና የዋጊኖስ ፍሬ ወቅጠህ ቀቅለውና አጥለህ በጥቁር ስንዴ ወይም በቀይ ጤፍ ዱቄት ለውስህ እንደዳቦ ቆሎ አድርገህ በቀን በቀን አንዳአንድ ስጠው እንዲያስቀምጠው አንት አጠጣው።

5. የአዞ አረግ የዋጊኖስ ቅጠላቸውን እሩብ የወይራ የአሚራ ሙሉ ቅጠላቸውን መቅመቆ ግማሽ



Scanned by CamScanner

አድርገህ ሁሉንም በአንድ ላይ ወቅጠህ እሩብ ማንኪያ በማር ሻይ አጠጣ።

6. አንጀቱ ለታመመ ሣንባ ነቀርሣ በቶ ዋጊኖስ መቅመቆ ምስርች የቤት ቀስት ስረብዙ እንዘረዘይ የምድር በርበሬ የእረኛ ቆሎ ሮማን ዝንጅብል ነጭ ሽንኩርት ቁልቋል ሥራቸውን ቅርፍታቸውን በአንድ ላይ እኩል በኩል ወቅጠህ አቡካና በቀበ /ጦቢያ/ ቅጠል አሽገህ ለሰባት ቀን ቅበረው በሰባተኛው ቀን አውጥተህ ቀቅለውና ጨምቀህ በቀይ ጤፍ ወይም በጥቁር ገብስ ሰመሬታ ወይም በጥቁር ስንዴ ዱቄት ለውስህ ለሰማኒያ ቀን የባቄላ ያክል በማር አውጥ።

7. ቁስል ለሆነ ምቺሮ ነቀርሣ

የአሞጭ ስር የዋጊኖስ የአባሎ የድግንግና የድግጣ የአዞአረግ የቀጠጥና የሁለገብ የሰመግ የጉርጠብ ቅጠላቸውን በእሳት አምስህ ውቀጥና አስቀምጠው ከዚያ የበሽተኛውን ቁስል አጥበህ ዙሪያውን ያልተጉዳውን ቀዳ ማር ቀብተህ ከቁስሉ ላይ መድኃኒቱን ደምድመህ በበላዩ የጠሌንጂ ቅጠል ወቅጠህ ምረገው፡ በሶስት ቀኑ ፍታውና ደግመህ አድርግለት፡ በመጨረሻ ቁስሉ እንዲጠፋ የአሽክት



Scanned by CamScanner

የድግጣ የጉርጠብ ቅጠል በቅቤ ለውሰህ ቀባው ለምጡ ይጠፋል።

8. ጉሮሮውን ለዘጋው በእንደበቱ ለወጣበት የጠሴንጂ የአሺክት የአቱች ቅጠል ደቁሰህ በውኃ አፍልተህ ይጉመጥመጥና ይትፋው፡ ደጋግሞ ያድርግ ይከፈትለታል፡ አፉ ለቆሰለም እንደዚሁ ያድርግ፡ የቁስሉ ስሜት እንዲወጣ ለማድረግ የክትክታ የጥፍርንዶ የአዞ አረግ ቅጠላቸውን በአንድ ላይ ወቅጦ በቁስሉ ላይ መደምደም ነው ጉትቶ ያወጣለታል።

9. ለሚመግል ወይም ለሚነዘንዝ ምሽር የበለስ የነጭላ የአዞ አረግ ቅጠላቸውን ወቅጠህ በቁስሉ ላይ ነስንስና በሻሽ ሸፍነህ እሰረው።

10. ከገላው ላይ አልፎ አልፎ ለቆሰለ ቀለዋ ወይራ ብሳና ጨጮ ጉመን ኑግ ተልባ ዋጊኖስ ፍሬያቸውን በአንድ ላይ ወቅጦ ቅባኑግ ማስወጣት ነው። አሽክት አቱች ጉርጠብ እፀፋርስ ጠሴንጅ አስተናግር ቅጠላቸውን ወቅጠህ በቅባቱ እየለወስክ ቀባው ወይም ደምድምበት።

11. በቆዳው ላይ እልፍ እልፍ እያለ እንደ እጢ ለሚወጣበትና ለለገመ ነቀርሣ፦



Scanned by CamScanner

በብዙ ቅንቡር አውጥቶ ከእርያ ስብ ጋር አቅልጦ ቅባቱን ይቀባ ደጋግሞ፡ ለማንኛውም እጢ ከእንቧይ ቅጠል ላይ እጢ መስሎ የሚወጣውን ቆርጦ አበጡን ማሸት ነው ይጠፋል፡ ድንገት ለአበጠበት ኀርጂት ቅጠል እሰርለት ሽንጉግም ይባላል።

12. ለቆሰለ ምኺሮ

የፍየል የአሽኮኮ የሚዳቋዋ ፍግ የአባሉ ቅጠል መቅመቆ ተሆጭ የዶግ ስር በአንድ ላይ ወቅጦ በፍየል ኺንት ለውሶ በጠቢያ /ቀቦ/ ቅጠል እንደብቅል አምቆ ለሶስት ቀን ድንጋይ ጫንበት በሶስተኛው ቀን አውጥቶ አድርቆ መውቀጥና ዱቄቱን በቁስሉ ላይ ደምድሞ በንጹህ ሻሽ ማሰር በሶስተኛው ቀን ፈትቶ እንደገና ማድረግ ነው ይወጣለታል ወይም የአሞጭ ስር ከነብር ሥጋ ጋር ወቅጠህ ደምድመህ እሰርለት ጉትቶ ሲያወጣው ቁስሉ እንዲደርቅ የጠሌንጂና የጉርጣብ የሁለገብ ቅጠል ወቅጠህ እሰርለት ይደርቃል።

13. ጂማት በበዛበት አካባቢ ለሚወጣ ነቀርሣ



Scanned by CamScanner

እፀመናሂ እፀእስራኤል እፀዘዌ እፀሣቤቅ አሰረት እፀተከዜ አባሎ እፀፋርስ በለስ አንኮርሟ ዳብዛ ብርብራ ዋጊኖስ አዞ አረግ አሞጭ የጂብ ሽንኩርት ሥራቸውን ቅጠላቸውን በአንድ ላይ ወቅጦ ቢገኝ በፍየል ሽንት ወይም በላም ሽንት ለውሶ በቅቦ /ጦቢያ/ ቅጠል አሽጐ መቅበርና በበላዩ እሳት ማንደድ በሰባተኛው ቀን አውጥቶ ለማንኛውም ቁስል በሰመግ ወይም በጐርጠብ ቅጠል ውኃ እየለወሱ ማሰርና በእሳት ማሞቅ ነው፡ ለኪንታሮትም እንደዚሁ አድርግ።

14. ከአንድ ወደሌላው የአካል ብልቶች ለሚተላለፍ የውስጥ ነቀርሣ፡-

የበቶ የአንዳንድሺ ሥራቸውን የምሳና ግንድ ቅርፍት የምድር እንቧይ የእንዘረዘይ የቀጠጥና የእንዶድ ሥራቸውን ቅጠላቸውን በአንድ ላይ ወቅጠህ በቁልቋል ወተት ላይ እንዲደርቅ አድርግ ከደረቀ በኋላ ከጥቁር ስንዴ ገብስ ወይም በጥቁር ጤፍ ዱቄት ጋር ለውሰህ ባቄላ ያክል ለአርባ ቀን ይውሰድ ድንገት ቢደክመው የዶሮ ጉበት አብላው ተልባ አጠጣው፡

15. ሰውነቱ እየቆሰለ ለሚሰነጠቅ ገላና ለቆዳ ነቀርሣ፡-



Scanned by CamScanner

የጥጥ የዋጊኖስ የድግጣ የምሳና የጃባል ፍሬያቸውን ወቅጠህ ቅባኑግ አውጣ። የአምሳ እግር ቅንቡር ዲን ወቅጠህ ሁሉንም በቅባቱ ለውሰህ ቅባውና ፀሐይ ይመታና ይታጠብ፡ የግሜ አረግ /ግምአረግ/ ስር ታጥኖ ይተኛ እንደገና እሳት ተቀብቶ ይሙቅ።

16. ለማንኛውም ነቀርሣ

ወርቅ በሜዳ ምሳና ዶግ እፀመናሂ እንዘረዘይ አሚራ ጥፍርንዶ ቀጠጥና ሁለገብ የጅብ ምርኩዝ ድግጣ ምስርች ጥቁር ጨጉጉት ጠንበለል ሥራቸውን ቅጠላቸውን የተገኙትን ወቅጠህ ግማሽ ማንኪያ ያክል ከቀይ ጤፍ ቂጣ ጋር ማብላት ነው።

17. ከራሱ ለወጣበት ምሺሮ ወንዶቃጫ ምስርች ሥራቸውን ወቅጦ ከአስተናግር ቅጠልና ከወንዶ ቃጫ ጭማቂ ውኃ ጋር ለውሶ በፍየል ቅቤ አንጥሮ በአፍንጫው ማድረግና ከራሱ ላይ ደፈድፎ ማሰር ነው።

18. ቁስሉ እንደገና እንዳይመለስ ከነብር አፅም ጋር የቀይ ጠሌንጂ ስር ወቅጦ በፍየል ቅቤ ለውሶ በሻሽ ማሰር ነው፡



Scanned by CamScanner

19. ጆሮው ለሚመግልበት የበለስ የአስተናግር የሰመግ ቅጠላቸው የወንዴ ቃጫ ውኃውን በአንድ ላይ አጥርቶ በጆሮው ውስጥ ማድረግ ነው።

20. እንጉሉ ውስጥ ለተደበቀና አፍንጫው ለሚገማ እንጭብር አውጥ የጂባራ ፍሬ በፍየል ቅቤ አንጥሮ በአፍንጫው ማድረግ ነው።

21. ቁስሉ አልድን ላለና ለሚለበልበው፡-
የአዞ አረግ ቅጠል ወቅጦ የቁስሉን ዙሪያ ማር ቀብቶ መደምደምና በበላዩ የስንዴ ሊጥ መለጠፍና ማሰር ነው።

22. ለቁስል ማድረቂያ የቅንጭብ ተቀጽላ የጉርጠብ ቅጠል የሰጉን እንቁላል ሁሉን በአንድ ላይ ደቁሶ መደምደምና ማሰር ነው።

23. እንገቱን ለአቆሰለው ምሺሮ የሮማን ቅርፍት ነጭ አንፋር ዝንጂብል ወቅጦ በአንገቱ ላይ ደፍድፎ ማሰር ነው። በሶስተኛው ቀን አምሣግር የተባለውን ቅንቡርስ በአንድ ላይ ጨቅጭቆ አድርቆ ደምድሞ ማሰር ነው።

24. ከማንኛውም ገላ ላይ ለወጣ ነቀርሣ የድንጋይ ልብስ የሰጉን እንቁላል የጃርት እሾህ በአንድ ላይ

አክሰሉ የአሺክት የአንዳሁላ የአዞአረግ ቅጠል ወቅጦ መደምደምና ማሰር ነው፣ በምጨረሻ ቀብቶ በሻሽ ማሰር ነው።

## የኪንታሮት ፈውስ

ክንታሮት ወይም ኪንታሮት ተብሉ የሚጠሩ የአካል ተቃዋሚዎች አምስት አይነት ናቸው። ለአምስቱም የተለያየ የመነሺአ እበጥና ቁስል አላቸው፡-

1. በእጅና በእግር ጅማትም በበዛባቸው የሚወጣና ሥሩን በየገላ ቆዳው ላይ የሚወጣ ነው። እሄንም መጀመሪያ ላይ የወጣውን ሳይቆርጡ በጭራ ማሰርና ማጥበቅ ነው እንዳይደማ መጠንቀቅ ነው። በጭራ እንደታሰረ ከደረቀ ሌላው ሁሉ ይጠፋል ይደርቃል።

   እንደዚሁ በፈጦ እንጨት ወይም በቅጠሉና በነጭ ሽንኩርት መተኮስ ነው። የጥቁር አዞ አረግና የዋጊናስ ስራቸውን ቅጠላቸውን ወቅጦ እያሞቁ መተኮስ ነው።

2. የአኽያ ኪንታሮት ተብሉ በቋንጃና በቅርጥም የሚወጣና የሚያሰቃይ ነው።

መድኃኒቱ የአዞ አረግ የዋጊኖስ የእፀሲአል ቅጠላቸውን ወቅጦ አድርቆ ቁስሉን አጥቦ መደምደምና በሻሽ ማሰር ነው፡ በሶስተኛው ቀን ፈትቶ ማጠብና እንደገና ማድረግ ወይም የጉርጠብ ቅጠልና ከርቤ ደቁሶ በሻሽ ሸፍኖ ማሰር ነው።

ወይም የጥቁር አዞ አረግ ቅጠል የአኽያ ፋንድያ ደቁሶ የቅቦ የቁልቋል የቆለቆል ደማቸውን አቀላቅሎ ሁሉንም በአንድ ላይ ለውሶ በቁስሉ ላይ መደምደምና የስንዴ ሊጥ በበላዩ አድርጐ በሻሽ ማሰር ነው።

3. ወንዶው ኪንታሮት

በፊንጢጣ ዙሪያ የሚወጣ ነው ይህ ደዌ የሚፈጠረው ካለመታጠብና በንጹህ ነገር አለ መጸዳዳት ነው፡ ሌላው ደግሞ አሜባን ህመም የሚፈጥሩ ምግቦችን በመመገብ ወይም ብዙ ጊዜ በሞቀ መቀመጫ መቀመጥ ወይም ከባድ እቃ መሸከም ወይም የበሉት አለመስማማትና ከጽዳት ቤት ገብቶ ማማጥ የፊንጢጣን ዙሪያ ኪንታሮት ይፈጥራሉ፡ ከቀን ወደቀን ባማጡ ቁጥር እያደገ ይሄድና ወደሌላ ይቀየራል።



Scanned by CamScanner

ለዚህ ደዌ መድኃኒት ከመውሰድ በፊት ጥራጥሬ ገለባ ያላቸውን መመገብ ተልባ ቢገኝ የለንቋጣ ልጥ ተወቅጦ በባዶ ሆድ መውሰድ ነው። ለጊዜው ከህመሙ ለመታገስ የማር ወለላ በመኝታ ጊዜ ቀብቶ መተኛት ነው።

በመኝታ ጊዜ የሚደረጉ ነጭ ሽንኩርት ዝጉርጉር እንዳሁላ ጠብሶ ልጡን ጥሎ በፊንጢጣ ውስጥ ማድረግ ነው።

ሀ. መድኃኒቱ የጥቁር አዞ አረግ የቅቦ ቅጠል ወቅጦ በእሳት እያሞቁ መተኮስ ወይም በሻሽ አድርጎ ከፊንጢጣው ውስጥ አድርጉ መተኛት ጧት ሽንቱን እያጠራቀመ በሽንቱ ውኃ ማጠብ ነው፡ ከሁለት ግዜ በኋላ የጉርጠብ የሁለገብ ቅጠላቸውን ከርቤ በአንድ ላይ ወቅጦ በማር እየቀቡ በሻሽ መወተፍ ነው፡ በየጊዜው ንጽሕና ያስፈልጋል እሄን ከአደረገ ከደዌ ነጻ መሆን ይችላል።

ለ. ወይም የሴት ቀስት ስሩን ቅጠሉን ፍሬውን የጃርት የእሾህ ሁሉንም አክስሎ በቅንቦ ደም ለውሶ መቀባት ነው።

ሐ. ደባ ቀድ ሥሩን የጅብ ሽንኩርት ነጭ ሽንኩርት እንዳሁላ ጅንጅብል ሁሉን በአንድ ላይ ወቅጦና በሻሽ

Scanned by CamScanner

አስሮ በጋመ ሽክላ ላይ አድርጐ በበላዩ መቀመጥ ነው። እስከሚያልበው መቆየት ነው። እንደዚሁ የሁለገብ የእንደሁላ ቅጠል ወቅጦ እንደመቀመጫ ሽክላ አሰርቶ በውስጥ የፍህም እሳት አድርጐ መድኃኒቱ በበላዩ ደምድሞ መቀመጥ ነው።

መ. የሴት ቀስት የሞይደር የእንዳሁላ የአረግ ሬሣ የዳማከሴ የጐርጠብ ቅጠላቸውን ወቅጦ በማር እየለወሱ በፊንጢጣው ውስጥ ማድረግ ነው።

ረ. ሰገራ ለከለከለውና ለሚያስምጠው ወይም ሴት ልጅዋን ስትወልድ ከመጠን በላይ ስለምታምጥ የጀርባ መውጣትና መታመም ይመጣልና ወደ ኪንታሮት ሳይቀየር በሽንት ቧትና ማታ በቀዝቃዛ ውኃ በቀን ሦስት ጊዜ መታጠብና የጐርጠብና የሁለገብ ቅጠል ነቅጦ ደጋግሞ መደምደም ነው።

4. ሴቴና ወንዴ ተብሎ የሚጠራው ኪንታሮት መጀመሪያ ከአንጅቱ ውስጥ ሥሩን ይሰድና በመቀመጫው ማለት በፊንጢጣው በኩል እንደትርፍ ገላ ሁኖ ይወጣል። በመጸዳዳት ጊዜም ከሰውነቱ ጋር ስለሚፋተግ ይሰነጠቅና ደም ይወጣዋል አንዳንድ ጊዜም ንፍጥ የተቀላቀለ ቆሻሻ ይወጣል።



Scanned by CamScanner

ይህ ደዌ የአለበት የማሳከክና የመለብለብ የመጠዝጠዝ የውጋት ስሜቶች ይታዩበታል። ይህን ህመም ሊፈጠር የቻለው ናይሎን የመሰለ ሰውነትን የሚያሞቁ የውስጥ ልብሶችን ለሚለብሱ ወይም በአልጸዳ ነገር በሚያጸዱ በቀላሉ ለደዌው ይጋለጣሉ። ከሌላ የፈሰሰው ደምና ወይም ንፋጭ ቆሻሻ ወደሌላ ሰው ለመተላለፍ ካልተጠነቀቁ በቀላሉ ለበሽታው ይጋለጣሉ።

መድኃኒቱ

ሀ. የረኛ ቆሎ የበለስ ቅጠል ቀንበጥ የአዞ አረግ ቅጠል ቀንበጥ የምድር እንቧይ ፍሬ ደቁሶ በአይደርቄ ጉመን ውኃ ለውሶ ሲተኛ በፊንጢጣው ውስጥ ያድርግ።

ለ. የሰጉን እንቁላል የቆርነናት ቤት በእሳት ቆልቶ ከጭጫት እንቁላል ጋር በጥፍርንዶ በጦቢያ ደም ለውሶ መቀባት ነው።

ሐ. የአንዳሁላ የሴት ቀስት የእሰረት የአስተናግር የበለስ ቅጠላቸውን ወቅጦ በቅንጭብ ወይም በቅንቦ ደም ለውሶ በፊንጢጣው ላይ አድርጉ መተኛት ነው።



Scanned by CamScanner

መ. ሠገራ ለከለከለውና ለሚያስቃየው የእንደሁላና የድቡሽቡሽ ልጡን ልጠ ውስጡን ደቁሶ በእሳት እያሞቁ በመቀመጫው ውስጥ ማድረግ ነው።

ሠ. ደም ለሚፈሰውና ለቆሰለ የልትና የአቱች የጉርጠብ ቅጠል ወቅጦ በማር ለውሶ ውስጡን መቀባትና በንጹህ ሻሽ አድርጉ መወተፍ ነው።

ረ. የዋንዛና የእንኮይ ቅርፍት አክስሎ በአዞ አረግ ወይም በዋጊኖስ ቅጠል ውኃ ለውሶ በፊንጢጣው ውስጥ አስገብቶ ይተኛ በጣም ካመመው የዋጊኖስ ፍሬ መቅጦ በማር ለውሶ መዋጥ ነው ህመሙን ያስታግስለታል።

5. **እሴቴው ኪንታሮት**

ይህ ኪንታሮት እንደሌሎች በውጭ የሚታይ ነገር የለውም ነገር ግን ውስጥ ለውስጥ ስለሚኖር በቆሽትና በአንጀት ላይ አልፎ አልፎ ይወጣና የጀርባን ውስጥ እንደ እከክ ሆኖ ይወጣበታል። ወደጽዳት ሲሄዱም ቀይ ትኩስ ደም ይፈሰዋል።



Scanned by CamScanner

ቅባት የበዛው ምግብ ሲበሉ ይጮሃል ድርቀት ያበዛል ድካም ይሰማል አንጀትም ይስባል።

ይህ ኪንታሮት ከጀርባ ጀምሮ እስከ ላይ በአለው አንጀት እንደ እጢ ሆኖ እርስ በእርሱ ስለሚፋተግ ደም ይፈስዋልና ስለዚህ በዚህ ለተለከፉ ሰዎች አስቀድመው መውሰድ የአለባቸው የተልባ የነጭ ሽንኩርት ዘይት ጉመን ካሩት ቆስጣ ስፒናች የመሰሉትን መመገብ ነው። የማይወሰዱ ከእንስሳት የሚገኙ ወተት ቅቤ ጮማ ሥጋ የአሣማ የአሣ የበግ የፍየል ሥጋ ፈጽሞ አይወሰድም፡ አብሽ ባቄላ ዘንጋዳ ስንዴ የመሰሉት የእሉብት ምግብ አይወሰድም አይበላም።

ሀ. በሆድ ለተሠራዉ ኪንታሮት፦ የበትረ ሙሴና የዋጊኖስ ፍሬ ቅርፍት የበቶ ቅጠልና አበባ ሁሉን በአንድ ላይ ወቅጦ ጧትና ማታ እያፈሉ መጠጣት ነው።

ለ. የቆላ አሜራ ቅጠል የምድር እንቧይ የሁለገብ የእንደሁላ ቅጠላቸውን ወቅጦ በመቀመጫው ውስጥ ያድርግና ከትኩስ ነገር ላይ ይቀመጥ።

ሐ. የአሚራና የአደስ ስር እንደሻሂ እያፈሉ ጧትና ማታ መጠጣት ነው።

መ. ለኪንታሮት ለነቀርሣ የዋንዛ ቅርፍት የጥንጁት ስር የእንባጮ የጥፍርንዶ የቅንቦ ቅጠል በአንድ ላይ ወቅጦ በማር ለውሶ መቀባት ነው።

ሠ. የሬትና የምድር እንቧይ ፍሬ አቃጥሎ አልሞ ደጋግሞ በማር መቀባት ነው።

ረ. የቀንጣፋ ቀንበጥ የጉርጠብ ቅጠል ኮረሪማ በአንድ ላይ ደቁሶ ውስጡን በቀባት ነው።

ለኪንታሮት የሚሆኑ እፅዋቶችን ለይቶ ለማወቅና ለመመራመር ጥናትም ለመውሰድ የሚያግዙ ስለሆኑ የስም ዝርዝራቸውን መ/ራ አማን በላይ ለወጌሾችና ለባለመድኃኒቶች እጽፍላችሁ አለሁ።

ሀ. የሴት ቀስት፣ የእረኛ ቆሎ፣ ዳባቀድ፣ የደጋ የቆላ እንዳሁላ፣ ነብሮ እንዳሁላ፣ የጂብሽንኩርት፣ ምሳና፣ አሚራ፣ አሰረት፣ እንዘረዘይ፣ ጠሌንጂ፣ የእነዚህ ቅጠላቸው ሥራቸው ቅርፍታቸው፡

ለ. ጨጉጉት፣ አዞአረግ፣ አስተናግር፣ እፀታቤቅ፣ እንተርፋ፣ ዋጊኖስ፣ አባሎ፣ ቅንቦ



Scanned by CamScanner

ጦቢያ፥ በለስ፥ ሁለገብ፥ ጅንጅብል፥ ወርቅ በሜዳ፥ አሞጭ፥ ነጭ ሽንኩርት ሥራቸው፤

ሐ. የበትረ ሙሴ የዋንዛ የእንኮይ ቅርፍታቸው የቅንጭብ የቁልቋል የቆለቆል የቅንቦ የጦቢያ የበለስ የአንተርፋ አቢዳሞ ደማቸውን፡

መ. የሰጐን እንቁላል የቆርነናት ቤት የጃርት እሾህ የጭሜት እንቁላል ዲን ከርቤ አልቴት ስመአንፋር ክብረ ሰማይ ኩል ዘጭመረጭ ብጫ እንጉዳይ የድንጋይ እጣን የድንጋይ ተቀጽላ፡

ሠ. የምድር እንቧይ የገበር አንቧይ የዘርጭ እንቧይ የበትረሙሴ የዋጊኖስ የምድር ቅንጭብ ፍሬያቸው እነዚህና እነዚህን የመሰሉ ሁሉ ለኪንታሮት መድኃኒት ይሆናሉ። ነገር ግን በድፍረት ቢያደርጉ አደጋ ስለሚያደርስ ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚበልጥ አስቀድሞ ማጥናትና የመድኃኒት ቅመማ ልምድ ካላቸው ሰዎች ጋር መማከርና ማጥናት አለበት። እነዚህም ብዙ ግዜ በፊንጢጣው በኩል የሚደረጉ እንጂ በአፍ የሚወሰዱ አይደሉም። ነገር ግን መድኃኒቱ ሲደረግለት



Scanned by CamScanner

ለአንድ ሰው ጀርባውንና ማጅራቱን ስለሚሰማው ለማደንዘዝ የዋጊኖስ ፍሬ ብቻ በማር ለውሶ መዋጥ ነው። አደጋ ላይ ፈጽሞ አያደርስም ትንሽ የጉሮሮ መቁሰል አንዳንድ ጊዜ ለአንድ ቀን ያመጣልና አለመደንገጥ ነው።

## ለለምጥ ሥጋ ደዌ ፈውስ

1. የቀረጥ የኮሶ ቅጠል የፍየል ቀንድ አክስሎ ከውኃ አረንጓዴ ጋር በበለስ ወተት ለውሶ ከሜቅማ ጉሎ ዘይት ጋር አዘውትሮ መቀባት ነው።
2. የመካን እንዶድ የቀረጥ የሰንሰል የርምሳ የምሳና ሥራቸውን ቅጠላቸውን የሸንበቆ የቀበርቻ ሥራቸውን የወርካ ተቀጽላ የዘርጭ እንቧይ ፍሬ ሁሉን በአንድ ላይ ወቅጦ በላም ምልጓድ ቢገኝ በዘንዶ ሞራ ለውሶ መቀባት ነው።
3. የአዞ አረግ የዝግጣ የደድሆ የአንካ የዋርካ የበለስ ቅርፍታቸውን ቅጠላቸውን ጤናአዳም ነጭ ሽንኩርት የቁራ አረግ ፍሬ ዋግራ አልቴት ከርቤ ወቅጦ በጭልፊት ስብ ለውሶ መቀባትና ፀሐይ መሞቅ ነው።



Scanned by CamScanner

4. የዋርካ የሺነት የግራር የሆማ ቅርፍት ስር በአንድ ላይ ወቅጦ ከጣዝማ ማርና ከተምር ፍሬ ጋር ቀቅሎ መጠጣት ነው።

5. ዋግራ ጊንጥ በብዙ ሰብስቦ የጃርት እሾህ አክስሎ በጃርት ስብ ወይም በሐሞትዋ ለውሶ መቀባት ነው። አጥንቱንም በጉሎ ዘይት አክስሎ መቀባት የሥጋዋን መረቅ መጠጣት ነው።

6. የለምጥ ሥጋ ደዌ
እፀመናሂ አዞ አረግ ድግጣ ቅጠላቸውን ዋግራ አልቴት ሰናፍጭ ፈጦ ቁንዶ በርበሬ ነጭ ሽንኩርት የጅብሽንኩርት አልቴት ሁሉንም በአንድ ላይ ወቅጦ በሴት ጉሽ ሞራ ወይም በዘንዶ ስብ ለውሶ መቀባት ነው።

7. ለለምጥ ሥጋ ደዌ የሚሆኑ ቅባቶች የጭላት ስብ የዘንዶ ትፋቱና ስቡ የጉሽ ሞራውና ስቡ የጃርት ሞራና ስብ የፍየል ቅልጥም የጫቅማ ዘይት ነው። እንደዚሁ ከለምጥ መድኃኒት ጋር የሚጨመሩ የጥቁር ፍየልና ላም ቀንድ የጃርት እሾህ አክስሎ ከቅባቱ ጋር መጨመርና መቀባት ነው።



Scanned by CamScanner

8. ነጭ ለሆነበት ሥጋ ደዌ፦ የነጭ አሞራ የጭልፊት ስብ ኩስ ክንፍ የእባብ ልብስ የጃርት እሾህ የእፀ አብርሂ ቅርፍት የአንቃ ልብስ የድንጋይ ሽበት እሄን ሁሉ በአንድ ላይ ቀልቶና ደቁሶ በዘይቱ ለውሶ መቀባት ነው።

9. አሽክት በብዙ ሰብስቦ በጋን መቀቀልና ውኃው ትንሽ ሲቀር አጥሉ በባዶ ሆድ ማጠጣት፣ የጃርት እሾህ አክስሉ ከጊጥን ጋር ወቅጦ መቀባት ነው።

## ለቁስል ለሥጋ ደዌና ለነቀርሣና ለኪንታሮት የሚሆኑ እጽዋቶች ፈውስ

1. የአካልን ብልቶችን ለሚያምና ለሚያፈዝ ዓይንንም ለሚገለባብጥ ደዌ ሥጋና ኪንታሮት ፦ አርኮሣ ምሳና ደድሆ እንዘረዘይ አሚራ እፀዘዌ ጋንቢሉ ሺነት እፀመናሂ ሥራቸውን ቅርፍታቸውን፡ ዋጊኖስ አዞአረግ ቅምቦ ምስርች ብርብራ ምሬንዝ አቱች እፀሲኦል ግዜዋ የረኛ ቀሉ ምድር እንቡዋይ ቀረጥ ቀለዋ ጂባራ ፍሬያቸውን



Scanned by CamScanner

ቅጠላቸውን ሁሉንም እኩል በኩል ወቅጦ አድርቆ እንደገና አቡክቶ በቅንቦ /ጦቢያ/ ቅጠል አሽጉ ለሰባት ቀን መቅበር በሰባተኛው ቀን አውጥቶ መቀቀልና በንጹህ ሻሽ መጨምቀቅ ከዚያ ከጥቁር ጤፍ ዱቄት ጋር ለውሶ እንደ በቆሎ ማድረግና በቀን የባቄላ ፍሬ ያክል ለአርባ ቀን መዋጥ ነው። ለሌላም ደዌ ሁሉ ይሆናል።

2. እከክ መሰሉ ለሚወጣው ሥጋ ደዌ ቂጥጥ ወይም ኪንታሮት፡-

አፈጉማ እንዘረዘይ ምሳና ደጭመረጭ መቅመቆ የምድር እንቧይ እፀ መናሂ የምድር ቁልቋል የምድር ቅንጭብ አሰረት ወርቅ በሜዳ ቀጠጥና እንዳሁላ ሰመግ ኮክ ሮማን እንጆሪ ሺነት ሥራቸውን ቅርፍታቸው ቅጠላቸውን በአንድ ላይ ወቅጦ ማሸግና በሰባተኛው ቀን አድርቆ መቀቀልና አውዛውን ከጥቁር ስንዴ ወይም ጤፍ ዱቄት ጋር ለውሶ ማድረቅና እሩብ ማንካ በማር ማብላት በቅቤ አሽቶ ቆዳን መቀባትና ፀሐይ መሞቅ ነው።

3. ሰውነቱ ሁሉ በቁስል ለተሸፈነ ምሬዝ ብርብራ ቀበርቾ ቱልት አዞአረግ ዋጊናስ ግመሮ ደብዛ

ቀለዋ ፍሬአቸውን ሥራቸውን ዲን አልቴት
የድንጋይ እጣን ሁሉንም በአንድ ላይ ደቁሶ
ማቡካትና መደፍደፍ እንደገና አድርቆ
መውቀጥና በቅቤ ለውሶ መቀባት ከፀሐይ ላይ
ወይም እሳት እያነደዱ መሞቅ ነው። ይነፈርቃል
በሶስተኛው ቀን የጐርጠብ የእንባጮ የሁለገብ
የጠሴንጂ ቅጠል ደቁሶ ታጥቦ መቀባት ነው።

4. እንደአባጭ ሆኖ ለሚሰቃይ ደዌ የአዞአረግ የጦቢያ /ቅንቦ/ የበቶ የጥፌ የአንፋር የዋጊኖስ ቅጠላቸውን ወቅጦ ከእባጩ ላይ ማሰር ነው።
5. ደዌ ሥጋ ይዞት ሰውነቱ ለሚሰነጠቅ ዝግባ ቀለዋ ቃጭማ ብሳና ዋጊኖስ ዋንዛ ኮክ ብርብራ ድግጣ ወይራ የነዚህ ፍሬያቸውን አጠራቅሞ ወቅጦ ሱፍ ኑግ ሰሊጥ ተልባ ነጭ ሽንኩርት ሁሉንም በአንድ ላይ አስወቅጦ ዘይት ማውጣትና ቅባቱን ቆዳው ለተበላሸ ሁሉ መቀባት ነው።
6. እጅና እግሩ ለሚሰነጠቅ ደዌ ሥጋ የዋጊኖስ ፍሬ የአዞ አረግ ቅጠል የቀበርቾ ስር የሺነት ቅርፍት የቀለዋ ፍሬ ደቁሶ ከሰሊጥ ዘይት ጋር ቀብቶ እሳት መሞቅ ነው።



Scanned by CamScanner

7. እንደ እከክ ሆኖ ለሚወጣ ሥጋ ደዌ የእፀመናሂ የጠንበለል ቅጠላቸውን ወቅጦ በቅቤ ለውሶ መቀባት ነው።
8. የጊዜዋ የምድር እንቧይ ሥራቸውን የቀረጥ ፍሬ ሁሉን ቀቅሉ አውዛውን ማጠጣት ነው።
9. የግመሮ የደድሆ ሥራቸውን ቅርፍታቸውን ደቁሶ በቅቤ ለውሶ መቀባት ነው።
10. እንደ እከክ ሰውነቱን ለሚያሳክከው ፦ የዋጊኖስ የእፀመናሂ የጠንበለል ሥራቸውን ደቁሶ በቅቤ ለውሶ መቀባትና እሳት መሞቅ ነው። ለሰባት ቀን።
11. ለማንኛውም የቁስል ደዌ የምሬንዝ ሰር በቁልቋል ደም ለውሶ በፍየል ቅቤ ለውሶ መቀባት ነው።



Scanned by CamScanner

በመነካካትና በምች በሙቀት በመጠጥ ለሚቆራኙ የሥጋ ደዌዎች ለኪንታሮት ለነቀርሣ ለቂጥኝ ለአመንምን ለቁመኛና እነዚህን ለመሰሉ ሁሉ የሚከላከሉና የሚፈውሱ የእፅዋት ስም ዝርዝር፡-

1. ደደሆ ኮሶ ደብዛ ጂባራ ሺነት ምስርች ዋጊናስ አጋም ምሳና አደንድሺ አሰረት ሮማን አሚራ ጎተም የግንዳቸው ቅርፍት ቅጠላቸው ፍሬአቸው ሥራቸው፡

አሰርኩሺ ግሜሐረግ /ግምሐረግ/ እፀዘዌ የምድር አለንጋ እንዘረዘይ ወገርት መቅመቆ ወርቅበሜዳ የጅብ ሽንኩርት ነጭ ሽንኩርት ድቡሺቡሺ የቁራ ሐረግ የምድር እንቧይ ዘርጭ እንቧይ ሥረብዙ አረግሬሣ አዞአረግ በቶ ቀጠጥና ሥራቸው።

እንባሮ ምሬዝ ልት ቱልት ቅንቦ ጠሌንጂ ሁለገብ ጥቁር አዞ አረግ ጉርጠብ አረግ ሬሣ እፀ ሲኦል የምድር በርበሬ እፀገሞራ ቅጠላቸውን፡

እነዚህ የተገኙትን አጠራቅሞ ወቅጦ አቡኩቶ ለሰባት ቀን በጉፋና /በብብሻ/ በጦቢያ ቅጠል አሽጉ ለሰባት ቀን መቅበር በሰባተኛው ቀን አውጥቶ መቀቀልና ውኃውን ሲበርድ

ጨምቆ በጥቁር ጤፍ ዱቄት ወይም በጥቁር ለሜሬታ ገብስ ለውሶ እንደ ዳቦ ቆሎ አድርጉ ማስቀመጥና ለታመመ ሆነ ላልተያዘ በአመት እሩብ ማንካ ለሰባት ቀን በማር መውሰድ በህመም ላይ ለሚሰቃይ አርባ ቀን ይውሰድ፣ ከማንኛውም ልክፍት ይጠብቃል።

2. ለሚያመነምነው ለሣል ለወስፋት የሚሆኑ፡

ሥረብዙ የምድር አለንጋ ፍየለፈጂ ምስርች ቀበርቾ ደድሆ አሰሪት ዘርጭ እንቧይ የምድር እንቧይ አቱች ቀጠጥና የቆላ አምጃ መቅመቆ አዛምራ ገተም አሚራ ሞይደር የእሺሽኮኮ ጉመን ምሳና እፀተከዜ ሥራቸው ቅጠላቸውን በወተት አፍልቶ ጧት ማታ ማጠጣት ነው።

ለወስፋት በቀይ ጤፍ ቂጣ አብልቶ አንጓት ማጠጣት በሆድ ላለ ነቀርሣ በነጭ ማር ጧት ጧት እሩብ ማንካ መስጠት ነው።

ለአመንምን ከፌቆ ወይም ከጃርት ወይም ከጥንቸል ወይም ከእሽኮኮ ወይም ከበርሃ ፍየል ሥጋ ጋር ቀቅሎ መረቁን ማጠጣት ነው። ለብዙ ግዜ።



Scanned by CamScanner

3. ሰውነቱ እየደማ ምግብ ለሚያስጠላውና ለሚያከሣው፡

እንጆሪ አቱች ዋጊኖስ ግራዋ እሺኮኮ ጉመን አፀፋርስ እንባጮ ዳማከሴ ኮሶ ጠስኝ ግዜዋ ወይናግፍት እፀመናሂ ሙት አንሣ የምድር አለንጋ እንፋር ሥራቸውን ቅጠላቸውን።

የምድር እንቧይ የቀለዋ የፓፓያ ፍሬአቸውን የዋንዛ የገተም የጋንቢሎ ቅርፍታቸውን ነጭ ሽንኩርት ጥቁር አዝሙድ ከርቤ እልቴት ሁሉንም በአንድ ላይ ደቁሶ አርባ ቀን አኩክቶ ማሽግ በአርባ ቀን አውጥቶ ከአጥሚት ከሻይ ጋር እያደረጉ መስጠት ነው።

4. ሰውነቱ ለሚከሣና ያልታወቀ ደዌ በሰውነቱ ለተሰራጨ፡-

አደንድን ሙትአንሣ ደርደሮ አብታ ሰንበታ ሥረብዙ የሴት ቀስት የምድር አለንጋ ወገርት መቅመቆ ሥራቸውን፡

ነጭ ሽንኩርት ጅንጅብል ቁንደበርበሬ ሚጥሚጣ ሁሉንም በአንድ ላይ ወቅጦ በቀይ ጤፍ ገንፎ ግማሽ ማንካ ጨምሮ መብላት ነው። ወይም በማር እንደሻይ መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

5. ሆድ ለሚጮህበት ለተነፋ ያልታወቀ ደዌም ላለበት፦

ቀበርቾ ደንደሮ ኮባሌ ከርምድ ወርቅበሜዳ ሥራቸውን ምሳና አዛምር አዞአረግ ቅጠላቸውን ፈጦ ጅንጅብል የኮሶ ፍሬ ሁሉንም እኩል በኩል ወቅጦ ከአልቴትና ከዘጭመረጭ ጋር ማቡካትና ለሰባት ቀን ማቆየት በሰባተኛው ቀን አድርቆ ግማሽ ማንካ በቀይ ጤፍ ቂጣ በልቶ አንት በብዙው መጠጣት ነው። ወይም ከተልባ ጋር በባዶ ሆድ እያሰገሩ መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

## ለውነትን ለሚያንቀጠቅጥና ለሚጥል ለሚያዝል ለሴጌምን መድኃኒት ፈውስ

1. የጂባራ ወተት የውሻ የጂብ ሐሞት በሰውነቱ ውስጥ ማስገባት ወይም ሲጥለው በአፍንጫው ውስጥ ማድረግ ነው።
2. የግሜ አረግ /ግምሐረግ/ የቀይ ግመር የእፀመናሂ የጂባራ ሥራቸውን የአርማጉሣ የታርይጥማ ቅጠላቸውን ወቅጦ ሲጥለው በመራራ ቅል ዘፍዝፎ በአፍንጫው ማድረግ እስከ ሰባት ጊዜ እንዲሁ የእፀመናሂ የአሰረት የግምሐረግ የእንዘረዘይ የቀጠጥና የአንፋር የዋጊናስ የቁራ አረግ ሥራቸውን ወቅጦ ነጭ ሽንኩርት አልቴት አደባልቆ በየቀኑ በአፍንጫው ይሳብ ታጥናም ተሸፍኖ ይተኛ ለማንኛውም ተፃራሪ የመንፈስ ደዌን ያስለቅቃል ይፈውሳል።
3. ለማኛውም አጋንንት መጠበቂያ የዘረጭ እንቧይ የእንደሁላ የጭቁኝ የቀስታንቻ የጥፍርንዶ የዋጊናስ የአጋም የገመር የግሜ ሐረግ የጂባራ የልምጭ ሥራቸውን የጂባራ ደም የጽድ የግብ

ሙጫ አልቴት ከርቤ እንቆቆ ነጭ ሽንኩርት ጤና አዳም ሁሉንም በአንድ ላይ ወቅጦ ከጂብ ጉበት ጋር ቀላቅሎ ለሚያስጨንቀው ለሚያስደነግጠው ሁሉ በአፍንጫው ይሳብ።

4. ሰውነቱን አፍዞ ለሚጥለውና አእምሮውን ለሚያስረሣ ክፉ መንፈስ እፀፋርስ አስተናግር ቀይአብሽ እኩል በኩል ወቅጦ ደፍድፎ በጠላ ማቅመስ ሲሰክር የጂባራ ወተት የሙጫጭላ ወይም የዱር ድመት ሐሞት በአንድ ላይ በሰውነቱ ውስጥ ማስገባት ነው።

5. ለጉድፍ በሽታና እርኩስ መንፈስ ለሚጥለውና ለሚያሰቃየው የአዛምር የጭቁኝ የእንስላል የገበር እንቧይ የምስርች የልምጭ የጤናአዳም የመርቆ የግመሮ የአፈጉማ የወይናግፍት የቁራ አረግ ግምሐረግ የዶሮኩስ የግዜዋ የእፀመናሂ ሥራቸውን የተገኙትን ሰብስቦ ወቅጦ በፍየል ሥጋ መረቅ ማጠጣት በአዲስ ሸክላ ዘፍዝፎ ጧት ማታ ማጥመቅ ወይም ታጥኖ መተኛት በመጨረሻው ቀን የውሻ የሙጫጭላ ኩስ ደጋግሞ መታጠን ነው። ለወባ ለንድፍት ሁሉ ይሆናል።

6. የሰሌን የግዜዋ የግመሮ የአሚራ የመርቆ የጂብ ብትር የጂባራ የምሬንዝ የሺነት የዋሽንት የደብዛ የሞይደር የአረግ ሬሣ የግሜ ሐረግ የታርይገማ ሥራቸውን ቅጠላቸውን ወቅጦ ሲያመው በአፍንጫው ይሳብ ወይም በአረግ ሬሣና በግሜ አረግ ውሃ ለውሶ ሲያመው በአፍንጫው ማድረግ ነው።

7. የዶሮ ኩስ የምሳና የጂባራ የከርመድ የግመሮ የዋጊኖስ ፍሬያቸውን ወቅጦ በጂባራ ደምና በጂብ ሐሞት ለውሶ መቅበር ነው።

8. የቁራ አረግ የልምጭ የምሳና የከርመድ የዋጊኖስ የግመሮ የግዜዋ የጭቁኝ የግሜአረግ ሥራቸውን ፍሬያቸውን ወቅጦ አልቴት ነጭሽንኩርት የውሻና የጅብ ኩስ ጋር በመራራ ቅል ዘፍዝፎ ማጥመቅና በአፍንጫው ማድረግ ነው።

## ስለ አራዊትና ስለ እንስሳ ሥጋ መድኃኒትነት

**መውጫ**     ሥጋውና ደሙን ለሚያስጨንቅ መንፈስ

**ምጥማጥ**     ሥጋውና ደሙ ቆዳው ለሴጌዎን

**ሚዳቋ - ድርቃ**     ለፍጥነት

**ሜሮ** ከቅንቡርስ የተዘጋጀ ቅባት

ሆዱ ለተነፋ ሰውነቱ ለመነመነ በቅባቱ ቢያሹበት ይሻለዋል፡ ከቀይ ግራር ዛፍ ግንድ አበስብሶ ቢቀብሩት ብዙ ቅቡርስ ይሆናልና አጠራቅሞ ሲቆሉት ዘይቱ የወጣዋል።

**ሰጉን - ሲናርን**

1. አጥንቱን ቅልጥሙን ሰፍቶ ቢይዙትና የቅልጥሙን ጅማት ቢያስሩት ብርቱ ያደርጋል፡
2. አንገቱ ለአበጠበት ስቡን ቢቀቡት እንቁላሉንም ቢጠጡት ይበጃል።



Scanned by CamScanner

3. ለድካም የሥጋውን መረቅ ቢጠጡት ስቡንም ቢቀቡት ጠንካራ ቆዳ ይሆናል።

## ሶረት ቆቅ

1. ዓይኑ ለታመመ እንደጉም ለሸፈነው ሃሞትዋን ቢኳሉት ይገፈዋል።
2. ሐሞትዋን በአፍንጫው ቢወስዱት ብልህ ያደርጋል፡ አያስረሣም ሥጋዋንም አዘውትረው ቢበሉት ንቁና ቀልጣፋ ያደርጋል።

## ሸላ

ሥጋው ለደዌ ሥጋ ደሙና ሐሞቱ ለሚጥለው አጥንቱና ስቡ ለቁስለ ሥጋ ይሆናል።

## ሺኮኮ /ግሄ/

ለከሣ ሰው ሥጋዋን ቀቅሉ መረቁን መጠጣት፡ ለምሕሳብ ጉበቱዋን አፍንጫዋን ሰፍቶ መያዝ

## ቀበሮ - ሰርኔስ

ለአበደ ሰው ጉበቱን ማብላት ነው።

Scanned by CamScanner

## በቅሎ - በቅል

ጠጉር ለባብቀል ሰኮናውን አሣርሮ መቀባት ነው። ለነፍሰ ጡር ጠንቅ ሲሆንባት ሽንትዋን መስጠት ያወጣላታል።

### በግ - በግዕ

1. ዓይኑ ለነጣ ሐሞቱን መቀባት ነው·
2. ለመላጣ የበግ ላት ከሰሊጥ ዘይት [illegible] ብዙ ግዜ መቀባት ነው።

## አለቅት

ለእባጭ ለቁርጥማት ለተመረዘ ገላ ደሙን ከነመርዙ እንዲያወጣው ማሳብ።

## አሣማ - ሰራግልዮን - ሐንዘር

ለቁርጥማት ደሙን ለብልዝ ሞራውን መጠቀም ነው።

## አርጃኖ

1. ለዓይነጥላ በአርጃኖ ቆዳ እንደዋንጫ አድርጉ በባዶ ሆድ ውኃ መጠጣት ነው።
2. ለማድያት በጠጉሩን በቅቤ ለውሶ መቀባት ነው፡



Scanned by CamScanner

3. ከዓይኑ ላይ ለሞጥ ለጣለበት በጠጡን ከኩል ጋር ደቁሶ መቀባት ነው።

## አንበሳ

ልቡን ቢበሉት ወይም ቢቀቡት ደፋር ያደርጋል።

## አነር ድመት - ሑሴሜት

ሥጋውን ቢበሉት ወይም ቢይዙት ብልህ ያደርጋል ዓይኑንና ሐሞቱን ቢኳሉት ዓይን ያበራል።

የድመት እንግዲህ ልጅ ደቁሶ ከብር ጋር ቢይዙት ሐብታም ያደርጋል ለንግድም ይሆናል።

## አጋዘን - ቶራ

ለብልዝ ሞራውን ማሰር ነው።

## አኸያ - አድግ

ለዛር ውላጅ ወተቱን ከምስር ጋር ማብላት ነው።
ኤሉስ ወይም ግልገል አንሣ ነስር የሰማይ ቀበሮ - ጊጳ

1. ጡትዋ ለአበጠባትና ወተት ለማይወጣት የቅልጥሙን ስብ መቀባት ነው።



Scanned by CamScanner

2. ምላሱን ካወርቅ ውስጥ አድርጉ ቢይዙት የተናገሩት ሁሉ ሰውን ያስደንቃል።
3. ሕፃን ገና ሲወለድ የእግሩን ቅልጥም ቢያስሩለት ከንቱን አክስሉ በቅቤ ቢቀቡት ቀልጣፋ ንቁ ይሆናል ጠላት አያጠቃውም።
4. ልቡን በወይራ ፍህም ጠብሰው ቢበሉት ደፋር ጉበዝ ያደርጋል፡ የሚመጣውን ሁሉ ያውቃል እድሜም ያስረዝማል።
5. ቅልጥሙን በጅማቱ ሰፍቶ ቢይዙት አያደክምም ወይም እንቁላሉን ቢበሉት እሩዋጭ ፈጣን ይሆናል።
6. እንዳለ ሥጋውን ከግቢ ቢቀብሩት ሥራይ ይፈታል።

**እስስት - ከሚሌዎን ሥጋዋን አቃጥሉ በቅባት ለሚመነምን ልጅ መቀባት።**

**እርኩም - እርጽዮን**

ዓይኑ ለዉመዉመ ሐሞቱን መኳል ነው፡ ለአበደ ሰው ልቡን ማብላት ነው፡ ለእድሜ ሥጋውን ከእፀሕይወት ሥጋ ጋር ወይም ከአንድ መቶ ኮሽም ፍሬ ጋር ቀቅሉ

መረቁን መጠጣት ሥጋውን መብላት ነው። እረጅም እድሜ ይሰጣል።

የኤሉስና የእርኩም ሥጋ እፀማቱሳላ ወይም እንደማቱሳላ ከተባለው እፅ ስር ስርና ፍሬ ጋር ወቅጦ በሰመሬታ ገብስ ለነጭ ግልገል በግ ማብላት በሰባተኛው ቀን በጉን አርዶ ሥጋውን መብላት መረቁን መጠጣት ቆዳውን አጥንቱን ማቃጠል ነው።

## እባብ ዋጭ አሞራ ቁንጮ ያለው

ለሣንባ ለሣል ለሴላም ደዌ እንቁላሉን መጠጣት ነው።

## እርያ

ጆሮው ለአበጠና ለቆሰለ ስቡን አቅልጦ በጆሮው ማድረግ ነው፡ ለቁርጥማት ደሙን መጠጣት ሥጋውን መብላት ነው

## ንብ - ንህብ

እጁ እግሩ ለሰለለ የሰለለውን ለንቦች ማስነከስ እጩን ማብላት



Scanned by CamScanner

## ውሻ - ከልብ

የጥቁር ውሻ ሃሞት ጋኔን ለሚጥለው በአፍንጫው ማድረግ ነው።
የውሻ ኩስ ለምች ለንዳድ ለድንገተኛ ህመም ታጥኖ ተሸፍኖ መተኛት ነው።

ካካቲ ከሰባት ምስር ፍሬ ጋር በበቅሎ ጭራ ሰፍቶ ቢይዙ ሰው ሁሉ ያፈቅረዋል ለመስተፋቅር።

## ዝሆን

ግማሽ ሰውነቱን ለሚያመው ቆዳውን ቀቅሎ በትኩሱ ተሸፋፍኖበት ይተኛ እንዲያልበው፣ የጀርባ ህመም ለአለው ይታጠነው።

## ዝንጀሮ - ቀርድ

ለቆዳ ለምጥ ሥጋውን ቀቅሎ መረቁን ቢጠጡት አያስፋፋውም።
ብልቱን ወቅጦ በሰመሬታ ገብስ ቢጠጡት ቅንዝር ያደርጋል።



Scanned by CamScanner

ለልክፍት የዝንጀሮ ኩስ ከሰስት ቦታ አንስቶ በጥቁር አኽያ ወተት ለውሶ ከዳጉሣ ጋር ቂጣ ጋግሮ ማብላት ነው ለአበደ ለተዋለበት 3 ቀን ደጋግሞ ማብላት ነው።

## ጊንጥ - አቅራብ ኩጥጥሜ

ለለምጥ አሣርሮ በዘይት ለውሶ መቀባት ነው። ወይም ከጃርት እሾህ ጋር አክስሎ መቀባት ነው።

## ግመል

ዓይኑ ለሚያለቅስ ለሚያመው አልድን ሳለ ምሺሮ ሐሞቱን መቀባት ነው።

/ለሚሸና/ በህልሙ ለሚሸና ፀጉሩን ከእስስት ሥጋ ጋር ማሰር ነው።

ራሱን ለሚያዞረው የቅልጥሙን ቅባት መቀባት ወይም የቅልጥሙን አጥንት አክስሎ ከዘይት ጋር መቀባት ነው።

## ግሥላ ወይም ነብር - ክልዮን

ለዓይን ሐሞቱን መኳል ነው። ለቁስል ስቡን ማሰር ነው፡ ሥጋውን ቢበሉት መርዝ ሥራይ ከሆድ ውስጥ አያቆይም።

ለአጥንት ደዌ ሥጋውን ይሁን አጥንቱን ቀቅሎ መረቁን መጠጣት ነው። ለኪንታሮት ለነቀርሣ አፅሙን ደቁሶ ከጨለንጂ ስርና ቅጠል ጋር መቀባት ነው።

## የሜዳ አኽያ

ልቡን ለረሣ የእግሩን ጫማ ማሰር ነው፡ ለነቀርሣ ሥጋውን ማብላት ነው።

## የቆላ ፍየል - ዘራት እጣሴ

ዓይኑ ጠጉሩ ለሚበቅልበት ነቅሎ ሐሞቱን ደጋግሞ መቀባት ነው ለዓይን ህመም ይበጃል።

ወተቱ ቢጠጡት ለጉልበት ቅቤው ለነቀርሣ ይሆናል ለጆሮ ህመም ለአንጉል በአፍንጫው ማግባት

## የደጋ ፍየል - ዘራት

ነምጥ ደዌ ቀንዱን አሣርሮ በስቡ በቅልጥሙ ለውሶ መቀባት ነው።

ለሩጫ ጅራቱን ቀንዱን አክስሎ በቅቤ ለውሶ መሃል እግሩን እየቀባ ይሩጥ አይደክምም።

## የሰይጣን ዶሮ

ራሱ ለተመለጠ ቅልጥሙን ደጋግሞ መቅባት ነው። ሥጋዋን ለሌላ ዶሮ አብልቶ ዶሮዋን አርዶ ቢበሏት ልባም ብልህ ታደርጋለች። ሐሞትዋን ከሰውነት ቢቀብሩት ከጠላት ፊት ይሰውራል።
ሥጋዋን ለቡዳ ለዓይነ ጥላ ደጋግሞ መታጠን ነው።

## ዶሮ - ደርሆ

የአውራ ዶሮ ኳኩና ከቆለጡ ጋር ሰፍተው ቢይዙት ግርማ ሞገስ ይሆናል።
ለተመለጠ ቅልጥሙን መቀባት ነው።

## ድኩላ - ዋእላ ዋሊያ

ከሐሞቱ ውስጥ የሚገኝ ሉል ድንጋይ አለ እሱን ሰፍቶ ቢይዙ ከብዙ ነገር ይጠብቃል ለራእይ ለሐብት ለፍቅር ይሆናል።

ድመት - ሐሴሜት?



Scanned by CamScanner

## ቿርት - ዛርት

ለለቢሰ ሥጋ ለለምጥ ደዌ ከተምር ፍሬ ጋር ወቅጦ ሥጋውን ወቅጦ አድርቆ እንደሾርባ ጧትና ማታ መጠጣት ነው።
ለእጢ ለኪንታሮት እሾሁን እሣርሮ ከጐርጠብ ቅጠል ጋር በማር ለውሶ መቀባት ነው።
ለለምጥ ደዌ አጥንቱን እሾሁን አክስሎ ከጊንጥ ጋር በፍየል ቅቤ ሰውነቱን ቀብቶ ማሸትና ፀሐይ መሞቅ ነው።

## ጅብ /ዝሂብ/ ዝእብ

1. ለሙግት የጅብ ምላሱን ሰፍተው ቢይዙት አያስረታም ውሻም አያስነካም
2. ከከንፈሩ እስከ መንጋጋው ያለውን ቢይዙት ነገር አያስረሣም
3. ለዓይነጥላ ለቡዳ የፊት ግራ እግሩንና ቀጭን ተደራቢ አጥንቱን በእሳት እያሞቁ መተኮስ ነው።
4. ሐሞቱን ከድንቢጥ ደምና ከኩል ጋር ቢኳሉት የተሰወረን ያሳያል። ሐሞቱን ከሰውነት ውስጥ ቢቀብሩት ዓይነጥላ ገርጋሪ ይጠፋል።
5. ለገበያ የጅራቱን ጫፍ መያዝ ነው



Scanned by CamScanner

6. ለሕዝብ መስተፋቅር ሞራውን ቅንድቡን ወቅጦ ከቅባአቅዱስ ጋር አንጥሮ ቢቀቡት መልካም ነው።
7. ለመፍትሔ ሐብት መዳፉን ሰፍቶ መያዝ ነው።
8. ሐብቱ ለተሰናከለ ጥርሱን ጭራውን ቅንድቦቹን የኋላና የፊት የግራ እግሮቹን መዳፍ በአንድነት ወቅጦ መያዝ ነው።
9. ነገር እንዲገለጽ ለሙግት ግራና ቀኝ አይኑን የልምጭ ተቀጽላ ከኩል ጋር መኳል ነው። ነገር ይገለጸል
10. ለመጽንኤ አስኪት ብልቱን ደቁሶ ከብርዝ ጋር መጠጣት ጦምን ውሎ የሺንብራ ንፍሮ ውኃ እየጠጡ የአጃ ወይም የሰመሬታ ገብስ ቅንጬ መብላት ነው።
11. ቡዳ ለበላው ለቁመኛ ለማንኛውም ጉበቱንና ሐሞቱን ታጥኖ ተሸፋፍኖ መተኛት ነው።
12. ለገንዘብ በቦርሳ ለእህል በጉተራ እንዲበረክት የግራ መዳፉን መያዝ ነው።
13. ልብ የተመኘውን ለማግኘት ወይም ለመልካም እድል ከግራ መንጋጋው አንድ ጥርስ የብልቱን ራስ የጉጉት ምላስ በወርቅ ለብጦ መያዝ ነው።



Scanned by CamScanner

14. ለግርማ ሞገስ የጅብራስ አጥንት የእፀአንበሳ ስር ደቁሶ ከጅብ አንጉልና ከሰባት ቀለማት ጋር በግራ ጉን መቅበርና በበላዩ የአንበሳ አጉፂ አክስሎ መደምደም ነው።
15. ጋኔን ለሚጥለው የጅብ ደም ሰባት ዝንብ ከጽድ ሙጫ ጋር ወቅጦ በሰውነቱ መቅበር ነው።
16. ለምሕላበ ንዋይ የጅብ የሽኮኮ አፍንጫቸውን የጅብ ጭራ ከጠንበለል ተቀጽላ ጋር ወቅጦ በሽቶ ለውሶ መያዝ ነው።
17. ለሚጥለው የጅብ ጉበት የበግ ጉበት የአይጥ ሥጋ የጂባራ ደሙና ስሩን በአንድ ላይ ደቁሶ ሲያመው ማብላት ነው እንዲሁ በጅቡ ጉሮሮ አጥንት መተኮስ ነው።
18. ነገር እንዳይረሱ ክርንቻቸውን ለጀርባ ደዌ ደሙን ለአፍረተ ሥጋ ሐሞቱን መቅባት ነው።
19. ራሱ ለተመለጠ የጅብ ኩሱን ቀቅሎ በትኩሱ መቀባትና በሻሽ ማሰር ነው መደጋገም ነው ይበቅላል።
20. ለብልህነት ለዘኢያገድፍ አንጉሉን ከቀንጣፋ ተቀጽላ ጋር ደጋግሞ በነጭ ማር ማብላት ነው።



Scanned by CamScanner

21. ለምሕሳበ ንዋይ የጅብ አፍንጫ የጉጉት ጆሮ የክትክታ ተቀጽላ የሰጉን እንቁላል ሁሉንም በአንድ ላይ ደቁሶ ሰፍቶ መያዝ ነው።
22. ለመንድግ የጅራቱን ጫፍ የብልቱን ጫፍ ቆለጡን የጉጉት ምላስ ከጅቡ የግራ ጥርስ ጋር ሰፍቶ መያዝ ነው።
23. ለፍቅር ለመስተዋድድ የእንስቲቱን የጅብ ብልት እንብርት የግራ ጥርሱዋን በቆዳዋ ሰፍቶ መያዝ ነው ሲሰምር አክስሎ ለወንድ ከትከሻው ለሴት ከጭንዋ መቅበር ወይም መነቀስ ነው።
24. ለአእምሮ ለምስጢር ለዓይነጥላ አንጐሉን በምስር ዱቄት ለውሶ አድርቆ ሰልቆ በሸንብራ ሽሮ ወይም በአዋዜ በነጭ ሽንኩርት አዘጋጅቶ በጤፍ እንጀራ ደጋግሞ ማብላት ነው።
25. አንጀቱን አድርቆ ከባቄላ ሽሮ ጋር ወጥ አሰርቶ ሶስት ቀን ቢያበሉት ልክፍት የያዘው ይለቀዋል ጤነኛ ይሆናል።
26. ለዓይነ ጥላ ልቡን ደቁሶ የእፀእየሱስን ስር የእገሴን ዓይነጥላ ቁረጥ ብሎ ቆርጦ 3 ቀን በማር ማብላት ነው።



Scanned by CamScanner

## ጥቁር አሞራ ቁራ - ቋዕ

ለሽበት አፅሙን አክስሉ ከዋጊኖስ ፍሬ ጋር በቅቤ ለውሶ ራስን ተላጭቶ መቀባት ነው። ደጋግሞ እቁስሉ ሲድን ጥቁር ጠጉር ይበቅላል።

ለምሕሳበ ንዋይ የምሙጠሺ ተቀጽላና የአበዛንጣ ስር ብቁራ ደም ለውሶ ቢይዙት ምሕሳበ ንዋይ ይሆናል።

## ጥቁር ድመት

ዓይኑ ለፈዘዘ ሐሞቱን መኳል ነው።

ለሐብት የእንግዲሁን ልጅ ደቁሶ ከብር ጋር መያዝ ነው።

## ጭልፊት - አንቄ

ለፍጥነት ለሩጫ የእርግዋን ጥፍር ከራስዋ ጋር ሰፍተው ቢይዙት ፈጣን ያደርጋል።

## ፎጥ

የጥቁር ፎጥ ወይም ሙጭጭላ ሥጋ ደቁሶ ለዓይነ ጥላ ለገርጋሪ በባዶ ሆድ በማር ሶስት ቀን ማዋጥ ነው ጠጉሩን ሲተኙ መታጠን ነው ይለቀዋል።



Scanned by CamScanner

# የአትክልትና የእህል አገልግሎት ፈውስ

## ሀብሌ

ሀብሌ የድንች ዘር ዓይነት ለድክመት ለኩላሊት ከወር አንድ ቀን ቢበሉት ያገለግላል ሰውነት ይገነባል።

## ለውዝ

ለውዝ ለሆድ እርጥበት እርጥብ ትኩስ ነው። ከማር ጋር አዘውትረው ቢበሉት ዓይን ያጠራል።

## ሎሚ/በግእዝ ከርካዕ/

ሎሚ ለሣል ቅጠሉን ከወተት ጋር አፍልቶ መጠጣት ነው። የሎሚ ውኃ ከሚበሉት ከሚጠጡት ጋር ጨምሮ ቢጠቀሙበት ንጹህ ጤነኛ ያደርጋል።

የራስ ምታት ለሚያዘወትርበት አዘውትሮ የሎሚውን ውኃ ከቡና ወይም ከሻይ ወይም ከአሚራ ሻይ ጋር አፍልቶ መጠጣት ህመሙ እየተቀነሰ ይመጣልና መጠቀም ነው። ሎሚና ጥቁር አዝሙድ ተቃራኒ ነውና አለመጠቀም ነው።



Scanned by CamScanner

## ሊንደን

ለራስ መርዝ ቅጠሉን አበባውን ቅርፍቱን እንደሻይ እያፈሉ መጠጣት ነው።

## ሙዝ

1. ሙዝ ለደረት ህመም ከወተት ጋር ቢጠጡት ያስታገሣል አልሰር ጨጓራ ህመም ያለው ሰው አይብላ ያባብሰዋል።
2. ለችፌ አጥቦ ደጋግሞ መቀባት ነው።

## ሚጥሚጣ

ለሰውነት ንቃት ለብርድ ለነርብ ህመም ለቁርጥማት ባሆድ ውስጥ ያለን ጋዝ ለማስወገድ ጨጓራን የምግብ ተቀባይነት እንዲኖረው ያደርጋል።

## ምስር

ለሆድ ቀላል ነው ነገር ግን አዘውትረው ቢበሉት ዓይን ያደክማል ከነጭ ሽንኩርትና ከወተት ጋር አገንፍለው ቢጠጡት ወይም ቂጣውን በወተት እያማት



Scanned by CamScanner

ቢበሉት አፍረተ ሥጋ ይቀሰቅሳል ከሰንዴ ጋር ቂጣው ቢበሉት ፍትወት ያበዛል።

## ማሽላ

ማሽላ የማሽላ ዛፍ ኳንቻ ቡሌ ጋን ሰበር እየተባሉ የሚጠራ ዓይነት ቢኖረውም የተገኙትን እሸታቸውን ጠብሶ ወይም ንፍሮአቸውን የንፍሮውን ውኃ ቢጠጡት ስብራት ይጠግናል።
ለዉኃራ ለአፍረተ ሥጋ ጥሩ ነው እንዲሰራ ያደርገዋል።

## ስንዴ /ሥርናይ/

ለሆድ ያልቦካው ይከብዳል የቦካው ይቀላል፡ ከአብሽና ከወተት ጋር ቢበሉት ጥሩ ነው፡ የቆዳ ደዌ ወይም ነቀርሣ ያለበት ሰው እንዳያፋፋው ባይበላው ጥሩ ነው። ነገር ግን ለቁስል ቢደፈድፉት ያደርቃል ከአብሽ ጋር እበጥን ቢደመድሙት ይፈውሳል።

## ሰሊጥ - አፍላጢስ

ለሆድ እርጥብም ደረቅም ነው ከወተት ጋር ቀቅሉ ቢጠጡት የደረት ህመምን ከአብሽ ጋር የሳንባ ህመምን ያስወግዳል። ዉኃራንም ያጠራል።



Scanned by CamScanner

ቅባቱ ለጆሮ ደዌ ለድርቀት ይሆናልና መጠቀም ነው። ከአደስ ጋር ራስን ቢቀቡት ጠጉር ያሳምራል።

## ሰሪቲ - ርሔ

እንቅልፍ ለከለከለው ለሽንትማጥ ጥሩ ነው ከወተት ከሻይ ጋር ቢጠጡት ይበጃል የደረት ህመምንም ያስወግዳል።

## ሰናፍጭ

ለአእምሮ ንቃት ጥሩ ነው ለሆድ እርጥብም ትኩስም ነው ለጉሮሮ ለሳል ይበጃል። እጁን ለሚያሳክከው ከአብሽ ጋር መጠጣት ነው።

## ሱፍ

ሆድ ለማለስለስ ዘይቱ ጭልቃው ለልብ ደዌ ጥሩ ነው ከማር ጋር አፍልቶ ጧት በባዶ ሆድ ሲተኙ ደጋግሞ መጠጣት ነው፡ የልብ ህመምን ይቀንሳል እንዲሁ ከነጭ ሽንኩርት ጋር።

## ስፒናች

የደም ማነስን ያስወግዳል ነገር ግን የጉበትና የኩላሊት ህመም ላለው ሰው እንዳይወስደው ያባብሳል።

## ሽንብራ - ዚፋል - ጼርካ

ለሆድ ደረቅም ትኩስም ነው ደም ያጠራል ንፍሮውን የንፍሮውን ውኃ በባዶ ሆድ ቢጠጡት ለአፍረተሥጋ ጥሩ ነው ያጠነክራል።

የሽንብራ በቆልት ቢበሉት የሆድ ትልን ያስወግዳል።

## ሽንኩርት /ቀይ ሽንኩርት/

እርጥቡን ቢበሉት የደም ግፊት ይቀንሣል ለጉንፋን ይበጃል ቀቅለው ውኃውን ቢጠጡት ኩላሊትን ያጠራል ለጨጓራ ጥሩ ነው።

## ሽንብሩት የአይጥ ሽንብራ

ለጽናት ለጤንነት ፍሬውን መብላት ነው።



Scanned by CamScanner

## ሽንኮር አገዳ

ለሣል አገዳውን ቀቅሎ መጠጣት ነው።

## ሾርባ ቅጠል

የወር አበባን ለማስተካከል ሥሩን እየቀቀሉ እንደሻይ መጠጣት ነው።
የሆድ እቃ ሲስተሙን ያስተካክላል እንደልብ ያሸናል።
ለፊት ቆዳ ቅጠሉን ከምግብ ጋር አዘውትሮ መብላት ያሳምራል።

ቁንዶ በርበሬ ?

በሶብላ ?

## በኩረ ሉሚ

ለካልስትሮ ለጉበት ለነቀርሣ ለውፍረት ጭማቂውን መጠቀም

## በቆሎ

ለሆድ ቀላል ነው ጨጓራንም ያለዝባል ነገር ግን የጨጓራ ህመም ላለው ያባብሰዋል።



Scanned by CamScanner

## ባምያ

ለሆድ ቀላል ነው እርጥብም ነው ሆድን ያለዝባል ያለሰልሳል ለጨጓራ ህመም ይበጃል።

## ባቄላ

እልበቱ ስልጆው የንፍሮው ውኃ መልካም ነው አዘውትረው ቢበሉት ግን የአይን ዳፍንት ይሆናል ለእባጭ ለቁስል ያባብሳል የአለበት አይብላ።

ብርቱካን ?

## ተልባ - ከሙን

ዘይቱ ጭልቃው ለቆዳ ሆድንም ለማለስለስ ይሆናል። ለጨጓራ ፍሬውን በባዶ ሆድ አንድ እፍኝ በባዶ ሆድ በውኃ መውሰድ ነው፡ ወይም ፍሬውን ገንፊል አድርጎ አጥሎ ውኃውን ሲበርድ መጠጣትና ጠምን መዋል ነው።

ተልባ ብዙ መድኃኒቶቹን ይሽራል ማርከሻም ነው፡ ነገር ግን ሰው በፀሐይ ላይ ሁኖ አይጠጣው አይብላበት ተከፍቶ የዋለውንና የአደረውን የተልባ ጭልቃ አይውሰድ ምች ልክፍት ያሲዘዋል።



Scanned by CamScanner

## ቲማቲም

ለጉበት ለደም ማነስ ለሪህ /በሽታ/ ደዌ ፈጭተው ቢጠጡት ይበጃል።

## ነጭ ሽንኩርት - ቱሜ

ለውስጥ አንጀት ህመምን የቆዳ እከክ ህመምን በማር ለውሶ አስቀምጦ በባዶ ሆድ መውሰድ ነው ያስወግዳል። ለደም ብዛት ህመም ይበጃል።
ለደረቅ ሣል ከወተት ጋር እያፈሉ ጧት ማታ መጠጣት ነው ይፈውሳል።

## ነጭ አዝሙድ ?

## ነጭ ጥቅል ጎመን

ለአንጀትና ለጨጓራ ህመምተኛ ቀቅሎ ውኃውን ብዙ ቀን በባዶ ሆድ መጠጣት ነው፡ ነገር ግን ቅጠሉን ቢበሉት ህመምተኛ ወይም የተጎዳ ጨጓራ መፍጨት ስለማይችል ባይበሉት ይሻላል።



Scanned by CamScanner

ናና

ለራስ ህመም ከሎሚ ውኃ ጋር እያፈሉ አዘውትሮ ቢጠጡት ይበጃል።

አተር

ከሌላ እህል ጋር ቢበሉት ሰውነትን ያፋፋል ነገር ግን ብቻውን ቢበሉት ይነፋል ድርቀትም ያመጣል።

አብሽ

ለሆድ እርጥብም ትኩስም ነው ዱቄቱን ከቅቤ ጋር ቢጠጡት ጂማት ያፍታታል ለሸንት ማጥ ለኩላሊት ለሣንባ ለአንጀት ከማር ጋር በባዶ ሆድ መጠጣት ነው። ለደረቅ ሣል ቆልቶ መብላት ከወተት ጋር አፍልቶ መጠጣት ነው፡ ለሆድ ሲስተም ለስባት በባዶ ሆድ ጥሬውን በውኃ አዘውትሮ መውሰድ ነው የተፈጨው ዱቄት ትርፍ አንጀት ላለው ስለሚያሳድግበት አይውሰድ።

አደንጓሬ

ለሆድ ደረቅ ነው ከቅቤ ጋር ቢበሉት ለቆዳ ድርቀት ይበጃል ጥቁር ሐሞት ያበዛል።



Scanned by CamScanner

## አጃ

ለጨጓራ ህመም ሙቁን ቢጠጡት ያስታግሣል ለወገብ ለብልት ቂጣውን በወተት እያማጉ ገንፎውን በቅቤ ቢበሉት ያጠነክራል፡

## እሩዝ

ለሆድ ቀላል ነው በወተት አንፍሮ ውኃውን ቢጠጡት ተቅማጥ ያቆማል ለጤና ቡላው ወይም ጥቁር እሩዝ ይመረጣል።

## እንስላል - ሲላን

ዓይኑ ለፈዘዘ ለኩላሊት ፍሬውን ከእንጀራ ጋር መብላት ነው ወይም እንደሻይ አፍልቶ መጠጣት ነው። ለሣል ቀንበጡን ቀቅሎ ከቅቤ ጋር መጠጣት ነው፡ ወይም ከርቤ ጋር

ጡትዋ ለአበጠባት ቅጠሉን ቀቅሎ መጠጣት ሆዱን ለነፋው ሽንቱን ለከለከለው ከጦስኝ ጋር መጠጣት ነው።

ሽንቱን ለከለከለው ከቲማቲም ቅጠል ጋር አፍልቶ መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

## ካሮት

ለአይን ዳፍንት ለኩላሊት ለጉበት ለቆሰለ ገላ ሥሩ ፍሬው ቅጠሉ ለሴላም ደዌ ያገለግላል መጠቀም ነው።

## ወይን /ዘቢብ/

የሆድ ድርቀትን የሪህ በሽታን የአበጠ ጉበትን ትውኪያን ያስታግሳል።

## ዘንጋዳ ባሶኬ ቁጭብየ

ለተሰበረ ቁስሉ አልጠግን ላለ የንፍሮውን ውኃ በባዶ ሆድ ሲተኙም መጠጣት ነው ይጠግናል።

## ገብስ

ለሆድ ደረቅ ነው ከትኩስ ወተት ጋር ቢበሉት ጉልበት ያበረታል። በሶው ለተቅማጥ ሙቁ ለገመምተኛ መልካም ነው።



Scanned by CamScanner

### ግብጦ

ለሆድ ቀላል ደረቅ ነው ከቅቤ ከወተት ጋር ቢበሉት ደም ያጠራል ለደም ብዛት አረቄውን በቀን አንድ አንድ ማንካ መውሰድ ነው።

### ጓያ

ለምሕሳበ ንዋይ ከእፀበለድ ስር የጓያ ቂጣና ንፍሮ ቀብሮ ስሩን ፍሬውን ቅጠሉን ከሰባት ጓያ ፍሬ ጋር መያዝ ከሚቀመጡበት ማስቀመጥ ነው።

### የስኳር ድንች

የስኳር ድንች የሚባለው ስለጣፈጠ ነውና እርሱን የሚመስል የበርሃ ድንች የሚባለውን ቢበሉት ብልት ያወፍራል ያጠነክራል።

### ዳጉሣ

ለሆድ ደረቅ ነው ከወተት ጋር ቢበሉት ጉልበት ያጸናል ለወገብ ህመም ይበጃል።

## ድሁን በራስዋ የምታፈራ በቆሎ የመሰለ

ለጉለበት ለወገብ ገንፎውን ቂጣውን መብላት ነው



Scanned by CamScanner

## ድንች

የድንች ዘሩ ዓይነቱ ብዙ ነው እንዳንዶቹ ለሰውነት ጥሩ ናቸው ያወፍራሉ የአገው ድንች የተባለው ቢበሉት ሙሉ ጤነኛ ያደርጋል።

## ድንብላል ?

## ጅንጅብል /ዝንጅብል/

ለራስ ምታት አላምጦ በአፍንጫ መሳብ ነው። ለጉንፋን ከሎሚ ውኃ ጋር በቀን ሶስት ጊዜ እያፈሉ መጠጣት ነው።

## ጤፍ

የጤፍ ዓይነት ዘር ብዙም ቢሆን ጥቁር ወይም ቀይ ጤፍ ተብሎ የሚጠራው ገንፎው ለወገብ ቂጣው ለጉልበት ሙቁ ለህመምተኛ ይሆናል። ለነቀርሣም አጋልጦ አይሰጥም።

ለጤንነት ከአብሽ ጋር እንጀራውን እየጋገሩ ቢበሉት መልካም ነው።



Scanned by CamScanner

**ጥቁር አዝሙድ /ተቃራኒው ሎሚ/**

ዘይቱ ለምች ለስሚት ለሆድ ለቆዳ ሲስተም ይበጃል። እንዲሁ ለመፍትሔ ሥራይ ይሆናል በቀን ግማሽ ማንካ።

**ጥቁር ሺንብራ**

የጣፊያን ችግር ያስወግዳል ለምች አደርም ጥሩ ነው ለአእምሮ ያድሳል ለትምህርት ጥሩ ነው

**ፉጀል**

ለምች የጣፊያ ችግር ላለበት ይመገበው

**ፌጦ**

ለአስም ከአሚራ ፍሬ ጋር በባዶ ሆድ ጧት ጧት መጠጣት ነው። እድም ለሚያስቀምጠው ከእርጎ ጋር ይጠጣው።

**ፓፓዬ**

ለሆድ ቀላል ነው አዘውትሮ ቢበሉት ደምን ቆዳን ያጠራል ፊትን ቢቀቡት ቆሻሻን ይጠርጋል ፍሬውን

ወይም ቅጠሉን አምስ እንደሻይ ቢጠጡት ለጨጓራ ህመም ለሆድ ህመም ያስታግሣል።

## ፖም

ፍሬውን አዘውትረው ቢበሉት የኩላሊትን ችግር ያስወግዳል። የጉበትንና አንጀትን ያጥባል ለሪህ በሽታ ላለውም እረፍት ይሰጣል።

## መክስት - እፀአንግሥ

## ጸሎተ በእንተ እፀዋት

ድፍናኤል ፫ ለቶፎን አቅላጥፎን ገረፎን አግራፎን አቅናፊአን መልአከሰላም ጌቴሬ መልክዮን መላክዮን ኣሉ አስማት ክስት ኃይሉ ለእፅ ሊተ ለገብርከ ለአርእዮ ኃይሉሙ ለእፀዋት በገዳም ወበሐቅል እለ ሀለው ለሠናያን ወለእኩያን አቅላፎን ፫ ሔልሜሉን ሜልዮን አግልዮን አንተ ከሣቴ ዕፅ ክስት ልብየ ወአብርህ አእይንትየ ለነጽሮ ዕፀው ወለገቢረ ሆሣእና ክርስትናኤል ፯ አጥላሹም በጠሹም በኃይለ ዝንቱ አስማቲከ ክስት ለኲሉን ዕፀዋት ለመፍትሔ ሐብት ወሥርያት ክርስትናኤል ፯ ሙጥአኤል መጥናኤል ሰልዋንዮን አናንዮን ጸጸጸ በስምኤል ንመውአ

በድፍራኤል ንመውአ በብክዮስ ንመውአ ነዓ ነዓ አንተ ከሣቴ እፅ ጥጥያሮን ሰሐቦሙ ወአቅረቦሙ ለኩሎሙ እፀዋት ፍታህ ምስዋሮሙ ወሠአር ምሪሪሆሙ ወአርህቱ ለዘይሜውሮሙ አጋንንት እኩያን ወቀጥቅጥ ኃይሎሙ ለሠይጣናት ለዘይትቃረኖሙ ለእፀዋት መሀቅል መስተሀቅል መግዱር መሀድር መኢለዮን መቴ ክልዮን መክልዮን መካክልዮን አቅጽላፌድ ትክላፊድ ግምላትዮን ንሁ ንሁ እፀዋት እለሀለውክሙ በገዳም ወበኃቅል ክስቱ ኃይልክሙ ለገቢረ ኩሉ ሠናይ በእደ ካህን አገሌ ፵፬

በጠንበለል በቀንጣፉ ተቀጽላ ደግሞ በነጭ ማር መብላት ወይም ዘፍዝፎ ሰባት ቀን መጠመቅ እጅን በእፁ ማሸት ዓይንንም መኳል ነው።

እፅ ብሩክ ይእቲ እፀሕይወት ዘውስተ ገነት ወእፀ መድኃኒት በዲበ ምድር




# በግእዝና በአማርኛ ከሀ እስከ ፈ የእፀዋት ስም ዝርዝር ገቢር

## ከ ሀ እስከ ፈ

**ሃሉ ሁለገብ ሌላው ስሙ ተሰላት ለምች ቀባው**

1. ለኪንታሮት ቅጠሉን ወቅጠህ ከጉርጠብ ጋር በእሳት አሙቀህ ተሱሰው ይፈውሣል።
2. ለልብ ድካም ሥሩን ከአቱች ስር ከእንጭብር ስር ጋር ሀምል ገላ አንገቱን ለአመመው ቅጠሉን ከአሚራ ቅጠል ጋር ውስጡን መቀባት ነው።

**ሀመር ሁመር** - ፍሬውን ለትርፍ አንጀት ከስንገላ ቅጠል ጋር አጠጣ።

ሃምቦ ?

ሃረገ ወይን ?

ሐረግ ሬሣ /አ/ ተመልከት

ሀብሌ ?

## ሐበዛንጣ ወይም የሽኮኮ ጉመን

ቁራኛ ለያዘው ህፃን የሰመግ የምስርች ቅጠላቸውን ሥራቸውን ወቅጠህ በውሀ ዘፍዝፈህ ለሰባት ቀን አጠበው።

ሐበዛንጣ ማለት ቦዝ መስላ ትንሽዋ ናት እንጂ ትልቁንም አበዛንጣ የሚሉት አሉ ሁለቱም ለመፍትሔ ሐብት ይሆናሉ።

ሐበዝ አምጣ የሚባሉ እፀዋት አበዛንጣ የአየኸውን ለእኔ አምጣ ቀረጥ ቆርጠህ አምጣ ሚጠሽ ሚጠህ አምጣ ከሴ ከሰህ አምጣ ጉፋ ገፈህ አምጣ ዋሽንት ዋሽተህ አምጣ ኮሸሽላ ኮሻሽተህ አምጣ ፍየለፈጅ አፋጅተህ አምጣ ግራምጣ ግራ

አጋብተህ አምጣ እየተባሉ የሚቀረጡና ለመፍትሔ ሐብት ለገበያ የሚሆኑ ሁሉ ሐበዝ አምጣ የቆላ ሐበዛንጣ ኃበዝ አምጣ የቆላ በርገሌ፡ ሀበዠ ዘበርገሌ የደጋ ሐበዛንጣ ኀበዝአምጣ የደጋ በርገሌ ሀበዝ ዘበርገሌ ኀበዝ አምጣ ዝበያን ክፈት እየተባለ የሁሉንም ተቀጽላ በዶሮ ደም አንግሰው ይቆርጣሉ።

## ሑለገብ ሃሉ ወይም ተሰላት ይባላል

1. ለድንገተኛ ህመም ሥሩን ማላመጥ ቅጠሉን ወቅጦ በእሳት እያሞቁ ቁስልን መተኮስ ያደርቃል።

## ሑመር ወይም ሐመር ይባላል

1. ለሆድ ፍሬውን ዘፍዝፎ መጠጣት ጤነኛ ያደርጋል።

## ሑስጹ አሽክት ይባላል፡ አንሀስት

ለቁስል ቅጠሉን አድርቆ መደምደም ነው።



Scanned by CamScanner

## ሂና

በረድ ደረቅ ነው በሐሞት ለመጣ ደዌ ከጉበት ጋር ቢወስዱት ይበጃል። ሂናውን አሙቀው ብልትን ቢያሹበት ይበረታል ያሳድጋል።

ሂስጰ ?

ሂጰ ?

ሃያ /ኻያ/ የወንዝ ዛፍ ?

ሆማ ?

ሆሜ ጥቁር ዛፍ ?

ሆጭ ?

## ሆበኔ ሐበኔ በግእዝ እፀ ባሮክ ወይም እፀ ኤልያስ ትባላለች።

በትረ ሙሴ መስላ ከበትረሙሴ ዛፍ አጠገብ የምትበቅል ባለማእዘን የሆነች ናት።



Scanned by CamScanner

1. ፍሬዋን ለቅሞ አርባ ቀን በሱባኤ የበላ አያረጅም ቢያረጅም ይታደሳል።
2. ውኃ ለማፍለቅ በለበቅዋ ሰረገላ ኤልያስን ደግመህ ነቅአ ማይ የተባለውን ድንጋይ ምታው ይፈልቃል። ለደረቀ ምንጭም በበላዩ ቅበርበት አይነጥፍም አይደርቅም።
3. ቅጠሉን ከቀረጥና ከጉፋ ቅጠል ጋር ወቅጠህ ነስንስበት አይፈርስም።
4. የእንጨቱን ውስጡ አውጥተህ ከሰባት ቀለማት ከእፀሣቤቅ ቅጠል ከሎሚ ውኃ ጋር አድርገህ የተመኘኸውን እያስገባህ ጻፍበትና በእብነበረድ ውስጥ አስገብተህ በስውር ቦታ ቅበረው ትከብራለህ።
5. ለራእይ እንጨቱን እንደ መስቀል እንደ መቁጠሪያ አድርገህ ጸልይ ሁሉ ይሰምርልሃል።
6. እሄን አስማት ከቅጠሉ ጋር ጽፈህ ለሁሉ አጠጣ ይፈወሣል ለውጥ ያያል ከአረ ያሬድ ደም ጋር ጸፈው ብትሄድ አትደክምም
“ሰረገላ ኤልያስ አስማተ እግዚአብሔር ያሸመሰት ያሸስተጽምያሁ መጠጢታ ያመሊጠ ያጠልብህ ያጠውብሔር ነያንፒፐ ያእዣትዣ

ሸጌታ ያሸሊጥዕ ያጊሙት ያፍቶሕ ያሸሰረረ
ያርፍዕ ያምን ሁስብትጥያ ያሸልኩፉ ክምጡሺ
የሐዝ ሕንብያ ያታፍአይታ መጠሽ ያሸዕሸዕ
ያሟማዕ ሊኪ ያጥኢና ይአትዠ ያመጠሸ
ያፍአይታ ያፍፍጥያ ያሐዩ ያቀዩም ያሸልክፉ
ያጠዊጢ ያረስከብት ያህዱይይ ያአሸብርት
መቅደሰ ዘየም ሻልቁኩየ አፍዝብል ሕርኬና
ወተመናጽልም ለጽለል ራብኤል አቀት ትዱቅ"

# ለ - L

ለሀ ?

ላንቂሶ ?

## ለንቁጣ ሆዱ ለደረቀ ሰገራ ለከለከለው

የለንቁጣ ልጥ የላንቁስ ቅጠል ከእንስላል ጋር አጠጣ ወይም ለንቁጣውን ከተልባ ጋር በማር /አውጥ/ አብላ



Scanned by CamScanner

## ለውዝ

እርጥብ ነው ቅባት አለው አዘውትሮ ለሚበላው ንቀት ይሆናል አእምሮውን ያጠራዋል ከገብስ ጋር ቢበሉት ሀዘንን ያስቀራል ዓይንን ያጠራል ብልትንም ያጠነክራል ለራስ ምታትም ከሎሚ ጋር ቢጠጡት ያስታግሣል ደጋግመው ከወሰዱት ህመሙን ያስተዋል።

## ሊንደን (Linden)

ለራስ ህመም ቅጠሉን አበባውን ቅርፍቱን እንደሻይ መጠጣት ነው።

## ላንቂሶ

ላንቂሶ አንድ ነው ተቀጽላውን ከቀጠጥና ቅጠል ጋር ደቁሶ የታሰሩበትን ሰንሰለት ቢቀቡት ይፈታል።

ላሎ ?



Scanned by CamScanner

## ልት

1. ዓይኑ ለአበጠበት የእንቁላል ብጫውን ጥሎ ከልት ቅጠል ውኃ ጋር አድርጐ ማጠብና ማሰር ነው ወይም የልቱን ቅጠል ቀቅሎ በውኃው የገብስ ዱቄት ለውሶ ከማር ወይም ከእንቁላል ውኃ ጋር በአንድ ላይ ከአይኑ ደፍድፎ ማሰር ነው የእንቁላል ብጫው እንዳይጨመር።
2. ጠጉር ለማጥቆርና ለማሳመር የኑግ የአባሎ የልት የአደስ ቅጠላቸውን የቁራ አረግ ቅጠል ፍሬ ሁሉንም ወቅጠህ በኑግ ዘይት አዘውትረህ ቀባው።
3. ለአንጀት በሽታ ቅጠሉን ቀቅለህ አጠጣው።
4. አፍረተ ሥጋው ለሚመግልበት የልት ቅጠሉን እንደጐመን ቀቅሎ መብላት ወይም በኑግ ዘይት ጠብሶ መብላት ነው። ወይም በትኩስ ከአፍረተ ሥጋው ላይ ደፍድፎ ማሰር ነው።

ልምጭ ?

ሉል ?



Scanned by CamScanner

ሉሚ ለመፍትሔ ሁሉ የሚገባ እፅ ነው፡ ከርካፅ

ጸሎተ መፍትሔ ሐብት ወመፍትሔ ሥራይ

በሐበርጂን ፮ መርታደን ፮ በጂር ፮ አክሉግ ፮ በስፍዛዜዎር ፮ በኃይለ እሉ አስማቲከ ፍታሕ ወሰአሮ ሥራየ ወከስት ሐብትየ ሊተ

1. በሉሚ ተቀጽላ ደግመህ በማር አውጥ ወይም በሉሚ ውኃ ደግመህ አጠጣ
2. ለሣል ቅጠሉን ከነጭ ሽንኩርትና ከነጭ እጣን ጋር በወተት አፍልተህ ጧትና ማታ አጠጣ።
3. ለትኩሣት ለጉንፋን ለራስ ህመም ፍሬውን አበባውን ቅርፍቱን ቅጠሉን ወቅጠህ አድርቀህ አጠጣ ለሌላውም እንደዚሁ አጠጣ።
4. ለሆድ እከክ ለራስ መቆሸሽ የሉሚ ውሃ ከማርና ከነጭ ሽንኩርት ጋር ለውሰህ በባዶ ሆድ አብላ።
5. እራሱን ሁልጊዜ ለሚያመው የሉሚ ውኃ ከጥቁር አዝሙድ ዘይት ጋር አደባልቆ ከቡና ጋር አጠጣው ደጋግሞ ይውሰድ ይፈወሣል።

ሉሚሸት

1. ሉሚሸት ደም ለሚበዛበት ከጠንበለል ስር ጋር ሰፍተህ አሲዝ



Scanned by CamScanner

2. ለገበያ ከሰባት ቦታ ቅጠሉን ስሩን ነቅሎ ከሞይደር ጋር በነጭ ዶሮ ደም ለውሶ ከሚሸጥበት ቦታ መቅበር ነው በበላዩ ነጭ እጣን ማጤስ ነው።

መ - M

መሉክያ

ለወጥ እንደጉመን ቅጠሉን ቀቅለህ በመንታ እንጨት ስበቀው እርሱን ከገንፎ ጋር ለውሰው ቢበሉት ሆድ ያለሰልሳል ለሽንት ጥሩ ነው

መረቃ ?

ነጦስ ?

መርቆ ?



Scanned by CamScanner

## መናሂ - እፀመናሂ

1. ጆሮው ለመገለ አፍንጫው ለሚገማ ጉሮሮው ለተዘጋ የስሩን ቅርፍትና ከወርቅ በሜዳ ጋር በቅቤ አንጥሮ በአፍንጫው ማድረግ ነው።
2. ለብብት ቅርናት በቅባት ለውሶ መቀባት ነው።
3. ለልብ ደዌ ከአሚራ ጋር በመጠጫ አንደሲጃራ ይጠጣው።
4. ለቁርጥማት ለውጋት ለራስ ህመም ለሆድ ደዌ ከቅቤ ጋር አንጥሮ በባዶ ሆድ መጠጣት ነው።
5. ለማንኛውም ደዌ ሥራይ ከወርቅ በሜዳ ጋር ወቅጦ በቅቤ አንጥሮ በባዶ ሆድ መጠጣት ነው።
6. ለራስ ፍልጠት ከሺነት ቅርፍት ጋር ወቅጦ ሲያመው ዱቄቱን በአፍንጫው ይሳብ።
7. ለመካን እሴት ከወተት ጋር እያፈላች ደጋግማ ትጠጣ።
8. ለፎረፎር ከደረጭ መረጭ ጋር በቅቤ ለውሶ በፀሐይ ማቅለጥና የቀለጠውን ንጥር ቅቤ መቀባት ነው።
9. ለሥጋ ደዌ እከክ ለመሰለው የእፀመናሂና የጠንበለል ቅጠላቸውን በቅቤ ለውሶ መቀባት ነው።



Scanned by CamScanner

10. እንደ እከክ ሰውነቱን ለሚያሳክከው የጠንበለል የዋጊኖስ የእፀመናሂ ሥራቸውን ወቅጦ በቅቤ ለውሶ መቀባትና ፀሐይ መመታት ታጥቦ እንደገና ተቀብቶ እሳት መሞቅ አለበት፡፡

11. ጉሮሮው ለአበጠ ከወርቅ በሜዳ ጋር ደቁሶ በቅቤ ለውሶ መቀባት ነው፡፡

12. ለመፍትሔ ለሥራይ ለቁመኛ ለቡዳ ሥሩን ከግሜ አረግ /ግምአረግ/ ሥር ጋር ወቅጦ ዘፍዝፎ መታጠብ፡፡ ለሰባት ቀን ያህል መጠመቅ አለበት፡፡

## መሬንዝ ምሬንዝ

1. መሬዝ - ምሬዝ ፦ አጥንት ለሆነበት ተቀጽላውን ቅጠሉን ቅርፍቱን በአንድ ላይ ደቁሶ በነጭ ማር ሰባት ቀን ማብላት ነው፡፡ በሰባተኛው ቀን የዋጊኖስ ቅጠል ከወተት ጋር ቀቅሎ ሣያበዙ ለብ ሲል ማጠጣት ነው ይወጣል፡፡
2. ለቆዳ በሽታ ሥሩን ቅጠሉን ቀቅለህ በውኃው ሰውነቱን እየተቀባ ፀሐይ ይሙቅ በበነጋው የምድር እንቧይ የግዜዋ የቀረጥ ፍሬ በአንድ ላይ ቀቅለህ አጠጣው፡፡



Scanned by CamScanner

3. ለማንኛውም የቁስል ደዌ ሥሩን ከፍየል ቅቤ ጋር አንጥረህ ቅባው ይፈውሣል።

## መዝረንጁስ

ትኩስ ደረቅ ነው አፉ ለተጣመመ አፍንጫው ለተዘጋ ቁርጥማት ላመመው አሽተው ይፈውሣል በአፍንጫ ማሽተትና መሣብ ነው።

## መቅመቆ ለፅንስ

1. ከሰሊጥና ከኑግ ቅባት ዘይት ጋር ቀቅለህ በባዶ ሆድ አጠጣ ይወጣል።
2. ሰገራ ለከለከለውና ለሚያስምጠው ከወተት ጋር አፍልተህ አጠጣው።
3. ለእከክ በቅቤ ለውሰህ ቅባው እንደሻይም ይጠጣ።
4. ለሣል ከጦስኝና ከእንጭብር ጋር በቅቤ አንጥረህ ቅባው ይፈውሳል።

## ቀይ ሙርጀን ፦

ለልብ ደዌ ከዶሮ መረቅ ጋር አጠጣው ወይም ከሱፍ ውኃ ጋር ይጠጣ ደጋግሞ

ሙሬ ?

ሙዝ

ለችፌ አጥበህ ቀባው

ሚዳቋያ

ሙታንሣ

የሙታንሣ ቤተሰቦች አደንድን አደንዶ የሰይጣን ሙቀጫ ጂልዋት ዛብና

እነዚህን የመሰሉና የሚመሣሰሉ ብዙ ናቸው ሌሎችን በፊደል ቤታቸው ተመልከት

የሙታንሣ ስሩን በወተት ቀቅለህ ብትጠጣው ከራስ እስከ እግርህ ያለው ጅማት ይፍታታል አዘውትረህ በሰሙሬታ ገብስ ብትጠጣው ብልትህ ይበረታል ወይም በብርዝ ብትጠጣውና ከመረቅ ጋር ብትወስደው የሰውነትህ ድካም ይጠፋል የሶሪ ቆቅ ሐሞትና ጉበትዋን ወስደህ ሥጋዋን ከአደንድን ስር ጋር አሰርተህ መረቁን ብትጠጣ ንቁ የማትረሣ ትሆናለህ። ተሐድሶነት አለውና ለማንኛውም ብርታት ይሆናል።



Scanned by CamScanner

**ማቱሣላ**

ለእድሜ ለሰባት ወር ግልገል በግ አብልተህ በ3 ቀን አርዶ መብላት

**ማሽላ - ቃቤላ፡**

በረድ ደረቅ እርጥብም ነው ለሆድ ቀላል ነው ውስጡንም ያለሰልሣል።

**ሚጥሚጣ ፡-**

ለሰውነት ብርታት ማነቃቂያ ይሆናል። ስብን ካልስትሮን ስለሚያስወግድ ከተልባ ጋር መጠጣት ነው።

**ምሳና**

1. ለሣል ለወስፋት ለቂጥኝ ፍሬውን ሰልቀህ በወተት አፍልተህ ግማሽ ኩባያ አጠጣ፡ ማርከሻው ቡና ነው። ፍሬው ከአሥር እንዳይበልጥ ለደካማ ሰው ከአንድ እስከ አምስት እንዳይበልጥ
2. ለጭብጦ ለኪንታሮት ወገቡን ለሚይዘው ቀንበጡን ቅርፍቱን የበቶ ስር ጋር ወቅጦ ግማሽ



Scanned by CamScanner

ማንኪያ በቀይ ጤፍ ቂጣ አብልቶ አጓት መጠጣት ነው።

3. ለቂጥኝ ለወስፋት ለሣል ለቆዳ ደዌ ፍሬውን ደቁሶ ግማሽ ማንኪያ በወተት አፍልቶ መጠጣት ነው። በሶ ቡና ማርከሻ።
4. ለነስር ቅጠሉን በአፍንጫ ለሴት ደም በብልትዋ ማድረግ ነው ለማንኛውም ህመም ፍሬውን ከዋጊኖስ ፍሬ ጋር መውሰድ

## ምስር

ለሆድ ቀላል ደረቅ ነው አዘውትረው ቢበሉት ዓይን ያደክማል ከወተት ጋር ቀቅለው ቢበሉት አፍረተ ሥጋ ያበረታል።

## ምስርች

1. ዓይኑ ለሚቀላና ብጫ ለሚሆን ለወፍ ቅጠሉን ቀቅለህ አጠጣ
2. እጁን ለሚቆረጥመው የምስርች የሰመግ የአንደሁላ ሥራቸውን ደቁሰህ በቅቤ አንጥረህ ቀባ ወይም አጠጣ።



Scanned by CamScanner

3. ለመፍትሔ ሐብት ቅጠሉን ከፍየለፈጅና ከቀጠጥና ፍሬ ጋር በዶሮ እንቁላል ለውሰህ በጅብ አር ደምድመህ ያዝ።

## ምጫምጮ

የወርቅ በሜዳ ዘር ለወስፋት ለኮሶ ከወገርት ጋር በኑግ መብላት ነው።

## ምስንጭሮ

ለትምህርት የዋርካ ተቀጽላ የእንጆሪ የቀጠጥና የአቱች ሥራቸውን ቅጠላቸውን ጋር የምስንጭሮን ቅጠል ወቅጠህ በምስር ንፍሮ አብላ ወይም በነጭ ማር ለውሰህ አውጥ።

## ምንጭርር

ለሣል የአሚራ የመቅመቆ የቀጠጥና የሥረ ብዙ የምድር እንቧይ ሥራቸውን ከምንጭር ስር ጋር በቅቤ አንጥሮ ማጠጣት ነው ወይም ስሩን ከነጭ ሽንኩርትና ከጤና አዳም ጋር በወተት እያፈላህ ጧትና ማታ አጠጣ።



Scanned by CamScanner

አንድም ለኖረ ሣል ስሩን ከጦስኝና ከአቱች ከኮርሺም ከእንዘረዘይ ስር ጋር በነጭ ሽንኩርት ጤና አዳም ጋር ቀቅለህ ውኃውን ከጣዝማ ማር ጋር በትንሹ አጠጣ

ምድር እንቧይ "የ" የምድር እንቡዋይ ከሚል ተመ/

## ሞይደር በግእዝ እጽአይደር

1. ለመፍትሔ ሐብትና ለማንኛውም ነገር የሞይደር የወገርት የጉሽርጥ የአጋም ሥራቸውን ከሴቴ ብርጉድ ጋር ደጋግሞ መታጠን ነው፡፡
2. ለሴት ባል ላጣች ወይም ባልዋ ለጠላት ሥሩን ከሴት ዶሮ ሥጋ ጋር አሰርታ ትብላ፡ ወደባልዋ ስትሄድ ወይም ስትተኛ ከከርቤ ጋር ትታጠን ወይም ከጉዝ ጠቀስና ከሴቴ ብርጉድ ጋር ወቅጣ ማታ ማታ ትታጠነው ጉኛዋን የጠላት የናቃት ያፈቅራታል፡፡
3. ከሰባት ቦታ የሞይደር ስር ቆፍሮ ከአደስ ቅጠል ጋር ወቅጣ በቅቤ ለውሳ ትቀባና ማታ ትታጠን ወንድም ለጠላች ሴት እንደዚሁ ታድርግ



Scanned by CamScanner

ከመኝታዋ ላይ የተወቀጠውን የሞይደር ስር ነስንሣ ትተኛበት

4. ከወንድ ጋር አልስማማ ላለችም ከሎሚ ጋር ቀቅላ ትታጠን በውኃው ሰውነትዋን ትታጠብበት።

5. ለማንኛውም ነገር ሴቶች ወንዶች እንዲወዷቸው ከሰባት ከሰባት ቦታ የሞይደር የቆንጥር የቀንጣፋ የጉበዝ ጠቀስ የቀጠጥና የወገርት ከሴት ብርጉድ ጋር ይታጠኑት ከቅባት ጋርም ለውሰው ይቀቡት።

6. ለወንድ ስሩን ደቁሶ ቀቅሎ ይታጠን ወይም ብልቱን ቀብቶ በተቀቀለው ድፍድፍ ይሸው ወይም ከቅቤ ጋር ለውሶ ቀብቶ ይገናኝ። ለማንኛውም ከሜሮን ጋር ለውሶ ይቀባ ሰው ሁሉ ያፈቅረዋል። ሥሩን ማላመጥ ለብዙ ነገር ይሆናል።

7. ለትምህርት ለመክሰት ከጥቁር ገብስ ጋር ወይም ከዘቢብ ጋር ወቅጠህ በነጭ ማር እየለወስክ ሰባት ቀን ይብላና ትምህርቱን ያጥና ይገለጽለታል ብልህ ይሆናል።

8. ለጥበብ ስሩን ከቀንጣፋ ተቀጽላ ጋር በምስር ንፍሮ ቀቅለህ ለአርባ ቀን አብላው አጠጣውም።



Scanned by CamScanner

9. ለፍጥነት ስሩን ከጭላት ልብ ጋር ሰፍተህ አሲዝ ወይም ከድመትና ከጭላት ጥፍር ጋር አሲዝ፡
10. ለእግረ መልስ ወይም ለተጣሉ ባልና ሚስት ለማገናኘት የሁለቱን ወዝ ከሞይደር ስር ጋር በጥፍሬና አበባና ደም ለውሰህ ከጥፍሬናው ልጥ ጠምጥመህ ከሁለት ከፍለህ አንዱን መታጠን ሌላውን ከአልጋው አጠገብ መስቀል ነው።
11. ለማንኛውም ነገር ሞይደርን ዘፍዝፎ መታጠብ ወይም ሲተኛ መታጠን አይነጥላን ገርጋሪን ያስለቅቃል።
12. ሞይደር ሲቆረጥ የሚጸለየው ጸሎት፡- ጸሎተ መስተሣልም ወመስተዋድድ በፍቅር ወበሰላም ምሳለ ሕዝብ ወአህዛብ ወምስለ ብእሲ ወብእሲት ሹርፍዝ ፫ ፓርታሉና አጀጁ ቆመጀጁ አስተፋቅር ወአስተጸምር በዛቲ እፅ ቡሩክ ወዕፀ ፍቅር በአፈ ካህን እገሌ ለገብርከ /ለዓመትከ/ እ፡
13. ለጥበብ እንዲሰምር "ያሽጣኤል ፯ ያሸርጣኤል ፯ እጅ ከማሁ አስምሮ ጥበበ በእዴየ ለገ/እ." የሞይደርን ሥር ከቀይ ቀለም ጋር ጨምሮ ጽፎ በብርዝ ላይ ዘፍዝፎ 49 ደግሞ መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

14. ሥሩን ከበርሃ እንቁራሪት ጋር አክስሎ በጣዝማ ማር ለውሶ እጅን ወይም ብልትን ቀብቶ ማስነካት ነው።

## ምናሄ በግእዙ እፀ መናሂ

1. ጆሮው ለመገለ አፍንጫው ለሚገማ ጆሮው ለተዘጋ ከወርቅ በሜዳ ጋር ወቅጦ በሰሊጥ ዘይት ለውሶ መቀቀልና ማጥለል ከሚያመው ላይ ማድረግ ነው በቅቤም እንዲሁ አንጥሮ ማድረግ ነው።
2. ለብብት ቅርናት የእፀመናሂን ስር በቅቤ አንጥሮ መቀባት ወይም ብቻውን መቀባት ነው።
3. ለልብ ደዌ ከአሚራ ጋር በመጠጫ መሳብ ነው።
4. ለቁርጥማት ለውጋት ለራስ ህመም ለሆድ ደዌ ከቅቤ ጋር አንጥሮ መጠጣት ነው።
5. ለማንኛውም ደዌ ከወርቅ በሜዳ ጋር ወቅጦ በቅቤ አንጥሮ መጠጣት ነው።
6. ለራስ ፍልጠት ከሺነት ቅርፍት ጋር ሲያመው በአፍንጫው ይሳብ።
7. ለመካን ሴት ከወተት ጋር እያፈላህ አጠጣ



Scanned by CamScanner

ፈውስ

8. ለፎረፎር ከደጭ መረጭ ጋር በቅቤ ለውሶ መቀባት ነው።
9. ለሥጋ ደዌ እከክ ለመሰለው የእፀመናሂ የጠንበለል ቅጠላቸውን በቅቤ ለውሶ መቀባት ነው።
10. እንደ እከክ ሰውነቱን ለሚያሳክከው የጠንበለል የዋጊኖስ ስራቸውን ከእፀመናሂ ጋር ደቁሶ መቀባት ነው።
11. ጉሮሮው ለአበጠ ከወርቅ በሜዳ ጋር በቅቤ ለውሶ መቀባት ነው።

## ሚጠሺ

1. ለገበያ ቅጠሉን ከሞይደር ስር ጋር መታጠን ተቀጽላውን ከከሴ ከጉፋ ተቀጽላ ጋር ከአለት ላይ ወቅጦ በነጭ ቄብ ዶሮ ደም ለውሶ ከገንዘብ ጋር መያዝ ነው።



Scanned by CamScanner

# S - ሠሰ -

## ሠሀ

## ሰሴን - ፀመርት

ጆሮው ለደነቆረ ፍሬውን ከሰሊጥ ጋር ዘይት አውጥቶ በጆሮው ቢጨምሩበት ደጋግሞ ይከፈትለታል ይሰማል።

## ሰሊጥ - አፍላጢስ

1. ትኩስ ደረቅ እርጥበት አለው፡ ቆልቶ ቢበሉት ጩንራ ያለሰልሣል ከነጭ ሐሞት የመን እበጥ ይጠፋል።
2. ለሣል ለጉሮሮ በሽታ ከወተት ጋር ቅባቱን አፍልቶ መጠጣት ነው፡
3. ለጆሮ ህመም ዘይቱን በጆሮ ማድረግ ወይም ከአደስ ቅጠል ጋር ለውሶ በራስ ላይ ደፍድሮ ማሰር ጠጉርንም ያሳምራል።

## ሰላቢላ

የቆላ የደጋ አለው መልኩ ይነስ እንጂ ሴቴውን ቃጫ ይመስላል፡ ትንሹን የጅንጀሮ እመጫት የሚሉም አሉ።

## ፈውስ

1. ጉልበቱን ለሚያመው በቀይ ጤፍ ወይም በጥቁር ገብስ ቂጣ ጋግሮ በወተት እያማጉ ብዙ ቀን መብላት ነው ያጠነክራል ቢሄድ አይደክምም።
2. ለወገብ በሽታ እንደዚሁ በቀይ ጤፍ ወይም በሰመሬታ ገብስ ዱቄት ጋር ገንፎ አድርጎ መብላት ነው።
3. የሰላቢላን ስር አዘውትሮ ቢበሉት ፍትወት ይቀንሳል ለነፍሰ ጡር ሴት እንዳትበላው ያስወርዳል ትጠንቀቅ።
4. ለሐብት ለፍቅር የሰላቢላን ስር ስትቆርጥ ማርና ወተት አፍስህ ለዚህ ሁነኝ ብለህ ንቀልና ከማር ጋር አላምጥ በኪስህም ያዝ
5. ለሐብት ለንግድ ስሩን በሸኮኮ ራስ ውስጥ ከተህ የሸኮኮ ጉመን ቅጠል በአዲስ ሸክላ ራሱን ከተህ ወትፍና በቤትህ ውስጥ ቅበር
6. ለመካን ሴት ወይም ለሚያስወርዳት ከቀጠጥና አበባና ሺል ከተያዘች ከሴት ፍየል ማህፀን ጋር ደቁስህ በባዶ ሆድዋ ለሰባት ቀን በነጭ ማር አብላት ትወልዳለች
7. ለንብ መሣቢያ ንቡ እንዲበረታ ስሩን ከቁልቋል ተቀጽላ ጋር በቀፎው ሸጉጠው ወይም የቁልቋል



Scanned by CamScanner

ልብ የሰው አጽም የሰላቢላ ስር ንቡን አጠነው፣ የጃርት እሾህና የንብጥራ ቅጠል አብረህ ጨምረህ አጠነው ንቡ ይበረታል። ማር ያደርጋል።

8. ለከሣ ሰው ችምግ ብላ እንደሰላቢላ የምትበቅል የምድር ቁልቋል ጋር ከዶሮ ወይም ከሽኮኮ መረቅ ጋር አብላ።

9. ቁመኛ ለያዘው ሰው ስሩን የስረብዙ የሽኮኮ ጉመን የምድር ቅንጭብ ስር ጋር እንደሻይ አጠጣው ወይም በፍየል ሥጋ መረቅ ጋር አጠጣው።

## ስመ አንፋር

ለአኽያ ኪንታሮት ለነቀርሣ ለብሽሮ ከሥር ኩል ጋር በአንድላይ ደቁሰህ በቁስሉ ላይ ብጫ ሌላ ንጹህ ገላውን ሣታስነካ ደምድመህ የስንዴ ሊጥ በበላዩ አሽገህ በጥጥና በሻሽ ለሶስት ቀን እሰርለት፣ ሲፈነዳ የባቄላ ገለፈትና የዋንዛ ልጥ ደቁሰህ ደምድምበት ወይም ፌጦ ከሬት ልጋግ ጋር ለውሰህ ደምድምበት።



Scanned by CamScanner

## ለመቶ ሰዎች

ቆሽት ያበረታል የበሉትን ቶሎ ያጠፋል ገላው ለተለወጠና ለፋቀ አዘውትረው ቢወስዱት ይበጃል።

## ሰመግ፡-

ሰባት ፍሬ በደምዋ ጊዜ ብትበላ ትመክንአለች ለውጋት ለስብራት ለእባብ ለመርዝ ነገር ሁሉ የሰመግ ስር ቅጠል የአሬት የቀበርቾ ስር የበቀለ ቀንድ እጣን ከርቤ ሁሉንም አክስሎ በቅቤ ለውሶ ተቀብቶ እሳት ይሙቅ።

## ሰረቲ

1. ለነቀርሣ ስሩን እንጨቱን ከቅንጭ ተቀጽላ ጋር በአንድ ላይ ደቁሶ በቁልቋልና በቅንጭብ ደም ለውሶ ከቁስሉ ላይ ማሰር ነው በእየሶስት ቀን መቀየር ነው።
2. ለስኳር በሽታ ስሩን ቅጠሉን ደቁሰህ ከሚበላው ከሚጠጣው ጋር ጨምረህ ስጠው ወይም ከአርማጉሣ /አቀራራጭ/ ጋር ደቁሰህ በማር እየለወስክ አብላውና የተልባ ፍሬ በባዶ ሆዱ ይውሰድበት፡



Scanned by CamScanner

3. ለመፍትሔ ሐብት፦ ጸሎተ በእንተ መፍትሔ ሐብት ያረኡፍ ያረፈኡፍ አልመኢዙ አለሐሲሙ አልመናን በኃይለ እሉ አስማቲከ ወበእሉ ቃላቲከ ፈጽም ፈቃደ ልብየ ወክስት ሐብትየ በስመ እግዚእነ እየሱስ ክርስቶስ ሊተ ለገብርከ እ/

በሰረቲ ሰርከ መንፈቀ ሌሊት 49 ደግመህ በኪስህ ያዝ

4. እንቅልፍ ለከለከለው ለደረት ህማም ለሽንት በወተት በሻይ አፍልተህ አጠጣ ለሆድ እርጥብም ደረቅም ነው።

ሰርኪን - ተ?

## ሰርዶ - ተ

አርባ ቅልጥም ሰርዶ ከሌት ወፍ ሥጋ ጋር ደቁሶ በሽንት ውኃ ለውሶ ቀብቶ ቢገናኝ መስተፋቅር ይሆናል ወይም የተቀመመውን ከሽንቱ ወይም ከሽንትዋ ጋር ቀላቅሎ ቢያስቀምጡት ያፋቅራል በጭሬ ወፍም እንደዚሁ ይሆናል።

ሰሳ - ተ/



Scanned by CamScanner

## ሰንበታ

የጂልዋት ዘር ነው ቢበሉት ኩላሊት ያጠራል ስሩ እንደስኳር ድንች ሆኖ አረት እንደአደንጓሬ አረግ ነው በክረምት ይገኛል።

## ስንገላ ብርብራ የመሰለ

ለትርፍ አንጀት ቅጠሉን ከሁመር ፍሬ ጋር ዘፍዝፎ መጠጣት ነው።

ሰቃ - ተ/?

## ሰናፍጭ

1. ጆሮው የሆነ ድምጽ ለሚሰማ ከማርና ከቅቤ ጋር አንጥረህ በጆሮው አግባና ወትፈው
2. ደም ለሚያስቀምጠው ሰናፍጭና አብሽ የሬትና የሎሚ ውኃ በቀይ ጤፍ ገንፎ አድርጐ ከተልባ ጋር ማብላት ነው።
3. እጁን ለሚቆረጥመው ከቁንዶ በርበሬ ጋር ወቅጠህ በማር አብላው።



Scanned by CamScanner

4. ሰናፍጭ ትኩስ እርጥብ ነው ለሣል ይበጃል ጉሮሮ ያጠራል የዓይን ጠጉርና የቅንድብ ፀጉር ለረገፈ ይኪለው ለአእምሮ ንቃት ጥሩ ነው።

ሰውራ ?

## ሱማያ

ሶማ ሰፋ ሲሃ አንድ ዛፍ ነው ለዘንግ ለብትር ይሆናል።

## ሱፍ

ለልብ ደዌ የሱፍ ጭልቃ ለብዙ ግዜ መጠጣት ነው ወይም ከማር ጋር አፍልቶ ጧትና ማታ መጠጣት ነው።

ሢሣ - ተ?

## ስንዴ - ሥርናይ

ስንዴ እህል ድርቀትና እርጥበት አለው የቦካው ለሆድ ሲቀል ያልቦካው ይከብዳል። ከአብሽና ከወተት ጋር ቢበሉት ጥሩ ነው።



Scanned by CamScanner

ቁስል ደዌ ላለው አይሆንም ይበረታበታል፡ ተቅማጥ ላለው ቂጣውን በቅቤ ለውሶ ይብላ።

## ስረብዙ - ብዙኃሥርው

1. የስረብዙ የምስርች የፍየለ ፈጂ የአቱች የዶግ የምድር እንቧይ ሥራቸውን የድብርቅ ፍሬና ቅጠል ወቅጠህ በባዶ ሆድ በማር አብላ፡ ለሥራይ ለሣል ላልታወቀ ህመም ሁሉ ይሆናል፡ ይፈታል።
2. ለደም ብዛት በማር ለውሰህ ሰባት ቀን አብላ
3. ለሣል ከጦስኝና ከአቱች ከኮርሺም ቅጠል ጋር እንዘረዘይ ምስንጭር ነጭ ሽንኩርት ጋር በጣዝማ ማር አቡክተህ በቅቤ አንጥረህ አንድ ማንካ ስጥና አቀበት እንዲወጣ አድርግ ያስተፋዋል።
4. ለሆድ ደዌ የሥረብዙ የዘንኪላ ስር የድብርቅ ፍሬ በአንድ ላይ ደቁሶ በጣዝማ ማር የኖረ ቅቤ ጨምሮ ጧት ጧት ማብላት።

## ሰረቲ - አርቲ

ያሰብከውን ለማግኘት "ያረኡፍ ያረፈኡፍ አልመኢዙ አለሐሊሙ አልመናን በኃይለ እሉ አስማቲከ ፈጽም



Scanned by CamScanner

ፈቃደ ልብየ በስመ እግዚእነ እየሱስ ክርስቶስ ሲተ ለገ/እ/" በሰረቲ ስር 49 በመንፈቀ ሌሊት ደግመህ ያዝ

## ሣማ በግእዝ እፀ ሌላም

1. ለመጽንኤ ስሩን ወቅጠህ በማር ዘፍዝፈህ እንደ ብርዝ አድርገህ ጠጣ
2. ለመስተፋቅር ስሩን በጧት ሺ/ ውኃ ሰባት ጠብ እያደረጉ ዘፍዝፎ በስቴ አው በመብልእ ስጥ
3. ደም ለሚያስተፋው ቅጠሉን በባዶ ሆዱ እየጨመክ አጠጣ
4. ለወሊድ ስሩን ከተልባ ጭልቃ ጋር አጠጣ

## ሳልብያ

በዘንጋዳ ከማሽላ መሐል የሚበቅል አረም ነው

1. ለማንኛውም እብጠት ቅጠሉን ወቅጠህ በሻሽ እሰርለት
2. ዓይኑ ለቀላና ለታመመ ቅጠሉን በሻሽ ሸፍነህ እሰርለት
3. ዓይኑ ለፈዘዘ የስልብያ ቅጠል አልቴት የበርበሬ ፍሬ ሁሉን ደቁሰህ በፍየል ሐሞት ለውስህ ቀባው



Scanned by CamScanner

4. ጠጉር ለማብቀል የስልብያ የዋጊኖስ ቅጠል ወቅጠህ በኑግ ዘይት ደፍድፈህ በራሱ እስርለት ቢቆስልም አይደንግጥ ቁስሉ ሲደርቅ አዲስ ጠጉር ያበቅላል።

## ስሚዛ ወይም ሰልሰል - ሰንሰል

1. ለአስም ለወፍ በሽታ ቅጠሉን ከሽንቱ ጋር ጨቅጭቆ ግማሽ ማንኪያ ይውሰድ፡ በበነጋታው አንድ ሙሉ ማንኪያ ይጠጣ።
2. የስሚዛውን ስር ከትክቶ ከጠላ ጋር ዘፍዝፎ ሲጠራ ቢጠጡት ቁርጥማት ይጠፋል።

ስቃ፡ ተ/ ?

ስቡት፡ ተ/ ?

ስንን፡ ተ/ ?

ስንደዶ ?

## ሰረት

በሆዱ ውስጥ ሥራይ ላለበት ቅጠሉን የሮማን የምሳና ቅርፍት የእንቧይ ፍሬ አጥበህ ወቅጠህ በቀይ ጤፍ ቂጣ ግማሽ ማንካ ያህል ጨምረህ አስጋግረህ አብላ።



Scanned by CamScanner

# - ረ - R

ሩት ?

## ሩዝ - እሩዝ

ትኩስ ደረቅ ነው ለሆድ ይቀላል ከወተት ጋር ቀቅሎ ቢጠጡት ተቅማጥ ያቆማል።

**ሬት እሬት** በግእዝ እፀመሐሪ ወይም እፀማራ - እንስታር

የሬት ዓይነት ብዙም ቢሆን የታወቁት ሴቴው ለስላሣ እሾህ የሌለው ወንዴው እሚወጋ የአለው ናቸው። ከሴቴው ወንዴው ይመራል ነገር ግን የላዩን ቆዳውን አንስቶ የውስጡን ልቡን መጠቀም ነው።

1. የሬት /ልቡ/ ውስጡ ለተለያዩ ለአካል ደዌዎች ህመሞች ወይም ለቆዳ ድርቀቶች ለአይን መድከም ጧት ጧት ከአብሽ ጋር መጠጣት ወይም ከሰውነት ቅባት ጋር ቀላቅሎ መቀባት ነው።
2. ለሚሰነጣጠቅ ለሚደማ ለተጫረ ለቆሰለ ለጭርት ለቋቁቻ ለኩፍኝ ለጠባሳ ጠጉሩ ለሚረግፍበት



Scanned by CamScanner

ብሜ ልጋጉን አጠራቅመህ ከአደስና ከቅቤ ጋር አቡክተህ ቀባው። እንዲሁ የውስጡን ልቡን አብላው።

3. ለስኳር ለአንጀት ድርቀት ለልብ ህመም ለወገብ ህመም ለስብራት ለሐሞት ጠጠር ለኩላሊት ጠጠር ለሆድ ህመም ለጥርስ ለጆሮ ህመም ለቃር ለትውኪያ ለአእምሮ ጭንቀት ለራስ ህመም ለደም ብዛት ለምች አደር እነዚህን ለመሰሉ ሁሉ የውስጡን ልቡን አውጥተህ ከተቀቀለ ተልባ ውኃ ጋር በማር አዋህደህ ለብዙ ቀን አጠጣው ወይም ከአብሽ ጋር በማር አጠጣው ይፈወሣል።
4. ከጆሮ ውስጥ እንደትል ለሚላወስበት የሬት ልጋግ የኮክ ፍሬ የላም ሃሞት ከሰሊጥ ዘይት ጋር ለውሰህ አንጥረህ በሻሽ አድርግለት።
5. ለኪንታሮት የሬትና የምድር እንቧይ ፍሬ አቃጥለህ ከህመሙ ላይ ደምድመው።

## ራማን ራስ አበራ /አበራ/

አፈማህፀንዋ ለቀየረባት ሥሩን ቅጠሉን ወቅጦ በቀዝቃዛ ውኃ ዘፍዝፎ ደጋግማ ትታጠብበት።



Scanned by CamScanner

## ራስክምር

ለምች ቀቅለህ እጠነው ለወስፋት ሳይበዛ ቅጠሉን አጠጣው

ሬንጭ ፡ ተ/ ?

ሬንዝ ፡ ተ/ ?

## ርምጣ

ለለምጥ ደዌ ከዝግባ ቅጠል ጋር ወቅጠህ ቀባው

## ሮዝሜሪ

ለራስ ህመም ከሎሚ ጋር አፍልቶ መጠጣት ለሥጋ መጥበሻ የሚሆን ቅመም ነው።

## ሮማን

1. ደም ለሚያስተፋው ፍሬውን ሳይበስል ወቅጠህ አጠጣ። ለአስም እንዲሁ ስጠው።
2. የሮማን ቅርፍትና ጅንጅብል በአንድ ላይ ደቁስህ በሆድ ነቀርሣ ላለው ደጋግመህ ስጠው።



Scanned by CamScanner

3. አንገቱን ላመመው የሮማን ቅርፍት አብሽ ኑጭ ሽንኩርት ኑጭ እጣን ከእንኮይ ፍሬ ጋር ወቅጠህ እሰርለት።
4. ጥርሱ ለተነቃነቀ የሮማን አበባ ደቁሰህ ከድዱ ላይ ይደምድምበት ወይም አበባውንና የወይራ ቀንበጥ በአንድ ላይ ደቁሶ ይጠቀርበት።
5. ሆዱን እያመመ ደም ለሚያስቀምጠው የሮማን ቅርፍት የተምርና የቀረጥ ፍሬ ሂናና ጦስኝ በአንድ ላይ ቀምመህ በቅቤ አንጥረህ አጠጣ።
6. ተቅማጥ ላመመው ቅርፍቱንና ፍሬውን እያስፈላ እንደሻይ ይጠጣ።
7. ለሚያስተፋው ፍሬውን ወቅጦ በማር ወይም ከዘቢብ ጋር /መብላት ነው/ ስጠው።

## - ሻ - Sha

ሸ - እሼ፡ ኮሞል



Scanned by CamScanner

ለእውቀት ፍሬውን አዘውትሮ መብላት ነው። ደሙን ለትምህርት ከሚሆን መድኃኒት ጋር አብረህ ስጥ ወተት ወደደም ይቀይራል።

## ሸውሻዊት ባለሐረግዋ አዝዋሪት ናት

ለመፍዝዝ የመቃብር አፈር ነስንሰህ ቆርጠህ በአደንግዝ ሐሞት ለውሰህ በቆዳው ሰፍተህ መያዝ ነው። አዝዋሪት ከሚለው ተመልከት።

ሸተሬ ፡ ተ/

ሻል

ከስኮሰ የመለቸው ፡ ተ/

## ሸንኮርአገዳ በግእዝ ሰኮረነቢያት

ለሣል አገዳውን ቀቅሉ ማጠጣት ነው።

ሽንጉግ /ጨጉጉት የካህን ቂም/ የሞኝ ፍቅር

1. ለእባጭ ለቁርባ ቀጥቅጠህ ደፍድፈህ እሰር
2. ለራስ ፍልጠት ቅጠሉን ከወሊትና ከዳማ ከሴ ጋር ደቁሰህ ሲያመው በአፍንጫው ይሳብ።
3. ለመስተፋቅር ደቁሰህ በዘይት ለውሰህ እጅህን ቀብተህ ሰላም በል እንዲሁም ፊትህን በጣዝማ ማር ለውሰህ ቀብተህ ተገናኝ። ስሙን የሞኝ



Scanned by CamScanner

ፍቅር ወይም የካህን ቂም ይሉታል፡ የፍሬው መያዣ ከልብስ ላይ ወይም አልፈው ሲሄዱ ልብሱን ከነካው አይለቀውም።

## ሽንጉግ

ከጭንጫ ቦታ የሚበቅለው ቅጠሉ ነጫ የመሰለው አጭር ሺንጉግ የሚሉ አሉ። የውሻ ነጫም የሚሉ አሉ፡ ቅጠሉ ለቁርባ ለአባጭ ቀጥቅጠህ እሰርለት ይሰበስበዋል።

## ሺብ

ዓይኑ ደርሶ ለሚያለቅስ ቅጠሉን ከእንቁላል ጋር ቀላቅሉ መቀባትና በሻሽ አስሮ መተኛት ነው።

## ሺንብሩት

የአይጥ ሽንብራም ትባላለች ስሩዋን ቢያላምጡ ፍሬዋን ለቅመው ቢበሉ ብልት ታበረታለች ደም ታጠራለች፡ እንደሽንብራ በቅላ ትታያለች ከእህል ዘርአይነት ወይም እንደ እህል ዘር ቢዘሩዋት ጥሩ ምርት ይወጣታል። ሺንብሩት የሚሉት ዛፍ አለ።



Scanned by CamScanner

ቯንቯና ኻያ ቾንቯና በወንዝ ዳር የሚበቅል ዛፍ ቅጠሉ በክረምት የሚረግፍ።

## ሾቯ - ቯሻ በግእዝ እፀከርመድ

1. ለመስቀል ለመቁጠሪያ ብታስረው ከመናፍቅ ጠብ ይጠብቃል።
2. ለመፍትሔ ሐብትና ለሥራይ ቅጠሉን ቅርፍቱን ወቅጠህ በውኃ ዘፍዝፈህ አጥምቅበት።
3. ለሆድ ሥራይ ከአቱች ጋር እንደሻይ እያፈላህ አጠጣ።

## ቯነት

1. ለአስም የገተም የቯነት ቅርፍት ወቅጠህ በማር አቡክተህ በባዶ ሆድ እንደሻይ አጠጣ።
2. ለራስ ምታት ቅርፍቱን ከእፀመናሂ ጋር ወቅጠህ በቅቤ አንጥረህ በአፍንጫው ይውሰድ።
3. ለፅንስ በማር ቀቅለህ አጠጣ፡
4. ለፍቅር ቅርፍቱን በሽንት ውሃ ዘፍዝፈህ አቅምስ።



Scanned by CamScanner

## ሽንኩርት ፡ ቢጸልቁማ

ቀይ ሽንኩርት፡ ነጭ ሽንኩርት፡ የጅብ ሽንኩርት የሚባሉ ብዙ ናቸው።

1. ነጭ ሽንኩርት የውስጥ አንጀት ህመምን ያስወግዳል በማር ለውሶ በባዶ ሆድ ይዋጥ።
2. የውስጥ የውጭ የእከክ ደዌን በማር ለውሶ አስቀምጦ በባዶ ሆድ አንዳንድ ማንካ ቢወስዱ ይፈውሳል። ቢያጥወለውለውና ቢያቃጥልም መቻል ነው።
3. መንጋጋው ለሚያመው ጨቅጭቀህ ውኃውን በሚያመው በኩል ያድርግ ወይም ይደፍድፍበት።
4. ለሣል በወተት አፍልቶ ከሰባት ቀን በላይ ይጠጣ ይፈወሣል።
5. ትኩስም ደረቅም እርጥብም ነው። ሰውነቱ ለበረደ በየጊዜው ከወተት ጋር እያፈላ ወይም ከሽንብራ ጋር ቀቅሎ ይጠጣ ንፍሮውንም ይብላ ደሙን ያጠራለታል። የደም ግፊትን ያስተካክላል ለብዙ ህመሞች መከላከያና መፈወሻ ነው።



Scanned by CamScanner

## ቀይ ሽንኩርት

1. ለኩላሊት በሽታ በብዙው ቀቅለህ ውኃውን ጧትና ማታ አጠጣው።
   ከአመድማዶ ስር ጋር ቀቅለህ አውዛውን አጠጣው ኩላሊቱ ያስተካክላል፡ ቆሻሻ ወይም ጠጠር ከአለው ከአልቴት ጋር ቀቅለህ አጥርተህ ስጠው።
2. እርጥቡን ቢበሉት የደም ግፊት ይቀንሣል፡ ለጉንፋንም ይበጃል፡ ጨጓራን ያጠራል።

የጅብ ሽንኩርት፡ ተ/ ?

ሺመል የበርሃው ድፍን ቀርከሃ ?

## ሺንብራ ፡ ዚፋል ጴርካ

አዘውትረው ቢበሉት ደም ያጠራል። ከወተት ጋር አንፍረው ቢጠጡት ብልት ያበረታል፡
ለሆድ እርጥብም ደረቅ ነው ብቻውን አዘውትረው ቢበሉት ሆድ ያማል።



Scanned by CamScanner

ሽንብራ ትኩስም ነው በሆድ ያለን ትል /ጀርም ወይም ባክቴሪያ/ ያጠፋል። የንፍሮውን ውኃ ከአልቴት ጋር ቢጠጡት በኩላሊት ያለን ጠጠር ያወጣል።

ሻሜት ፡ ተ/ ?

ሻሚ ፡ ተ/ ?

ሻሽ ነጭዛፍ ፡ ተ/ ?

## ሾላ ፡ ጳላጢኖስ

ፍሬውን ከወተት ጋር ቀቅሎ ቢጠጡት የሆድ ድርቀት ይቀንሳል።

## ሾርባ ቅጠል

ዶም ሥሩን ቢጠጡት የወር አበባን ያስተካክላል።

ድ እቃን ሥራ ያቀላጥፋል፡ እንደልብ ያሸናል ቅጠሉን ከምግብ ጋር ጨምረው ቢበሉት የፊት ቆዳን ያሳምራል።



Scanned by CamScanner

# - ቀ - Q

ቀለዋ ፡ ተ/ ?

## ቀንጠፋ፡ ፒርልዩ

1. ለኪንታሮት ቀንበጡን ከኮረሪማ ጋር ወቅጠህ በቅቤ ለውሰህ ቀባው።
2. ለጽሕፈት ለእጀፐበብ

ስሙ ለአብ ሙራኤል ስሙ ለወልድ ምናቴር ስሙ ለመንፈስ ቅዱስ አብያቴር፡ ቢካኤል ጉርኪሳኤል አብርሀ ሀሊናየ ወአስተፌስሀ ልብየ ለተናብቦ ምስጢር ወአሩጽ እደዊየ ለጽሕፈት ወአርትእ ልሳንየ ለገቢረ ድርሰት ወለተርጉሞ ቃላት ሊተ ለገብርከ እ/

በቀንጠፋ ተቀጽላና አበባ 49 ደግሞ ከምስር ንፍሮ ላይ ነስንሶ መብላት ነው።

3. ዘኢያገድፍ

ቶር አላቶር ነዓ አላቶር 7 አብርሀ ልቡናየ ከመፀሐይ ለአንብቦ መጽሐፍት ወለአእምሮ ምስጢራት ሊተ ለገብሮከ



Scanned by CamScanner

የዶቅማ የቀንጣፋ ተቀጽላቸውን አበባቸውን ቀንበጣቸውን በጥቁር ሽንብራና በምስር ንፍሮ በወይራ እንጨት ቀቅለህ ውኃውን በሞብርሌ አድርገህ 49 ደግመህ በየቀኑ ከዘቢብ ጭማቂ ጋር ሰባት ቀን አጠጣ የጥቁር ሽንብራ ቆሎ ብላ።

4. የቀንጣፋውን ተቀጽላ በሶሪ ቆቅ ደም ቆርጠህ ጨቅጭቀህ ከቆቅዋ ሥጋ ጋር ወጥ አሰርተህ ብቻህን መረቁን ጠጣ ሥጋውን ከሽንብራ ቂጣ ጋር ብላ፡ የቆቋን ሐሞትና ጉበት ከትክል ድንጋይ ቁመህ ዋጠው የሰማኸውን አትረሣም አትዘነጋም ንቁ ሰው ትሆናለህ።
5. ብልህ ለመሆን የቀንጣፋ ተቀፅላና የሶረኔ ቆቅ ሐሞት በማር መብላት ነው።

## ቀረፋ

ለተቅማጥ ከቡና ጋር ቆልቶ በወፍራሙ አፍልቶ መጠጣት ነው።

## ቀረጥ ፡ እፀቀምጥጥ

1. ለቁስል ማድረቂያ የቀረጥ የጉርጠብ የክትክታ ቅጠል በአንድ ላይ ወቅጦ ከቁስል ላይ ቢነሰንሱት



Scanned by CamScanner

ይደርቃል፡ ለምጡ እንዲጠፋ የዝግጣ ቅጠል ጨምርበት።

2. ቀረጥ ቀርጠህ እምጣ ኀበዝ እምጣ ተብሉ ተቀጽላው ተቆርጦ ለገበያ ይሆናል። ከእንባጮ ተቀጽላ ጋር ቢይዙት ወይጭ አይወጣም።

## ቀርር የጅብ ሽንኩርት ?

## ቀበርቾ

1. ለሣል ለቁመኛ ለከሣ ሰው፡- የቀበርቾ የአሚራ የእንጭብር የሙት አንሣ የአለብላቢት ሥራቸውን የቆላ ጦስኝ የአሽኮኮ ጐመን ቅጠላቸውን ሁሉን በአንድ ላይ ደቁሰህ ጧትና ማታ በማር ለውሰህ አብላ፡

2. ለሣንባ ከእንስላል ጋር ወቅጦ በራሱ ሽንት ለውሶ ወይም በጥብጦ ይጠጣው።

3. ለቃር የቀበርቾ ሰባት ፍሬ ከውስጥ አውጥቶ እንዱን መቆርጠም አንድ መያዝ ነው።



Scanned by CamScanner

## ቀርሸ ሸቦ

ለውጋት ሽንቱ ለከለከለው መርዝ በሆዱ ላደረበት ስሩን ወቅጦህ አጠጣው። የሆድ ትሉም ይጠፋል። መድኀኒ አስኪትም ይሆናል።

## ቀብቀቦ

1. ለምሕሳበ ዛር ወሰብእ ስሩን ከወገርትና ከሞይደር ጋር ማጤስ ነው።

## ቀስታንቻ

የሴት ቀስት የወንድ ቀስት ተብለው የሚጠሩና የተለያየ ዓይነት አላቸው።

ቀኑር ፡ ተ ?

ቀይ ሽንኩርት ከሸ ተራ ላይ ተመልከት
ቀይ ግራር ከገ ተራ ላይ ተመልከት



Scanned by CamScanner

## ቀጋ ፡ አርበት

1. የቀጋ የአልበሰለውን ፍሬ በብዙው ለትም እንደ ሙዝ ማሸግ ሲበስል አድርቆ መውቀጥና ለአረቂ ለጠጅ ይሆናል። እንዲሁም ከተለያዩ ምግቦች ጋር ጨምሮ ማዘጋጀትና መብላት ነው። ለጤና መልካም ነው።

## ቀጥበልና

ቀጠጥና በግእዝ እፀ ደብተራ እፀ እስራኤል ቁጢጥና የአኽያ ጆሮ ተብሎ ይጠራል።

1. ለወፍ በሽታ ለትፋት ስሩን ከአቱች ስርና ቅጠል ጋር ስጠው ወይም እንደሻይ ደጋግሞ ይጠጣ።
2. ለልብ ውጋት ስሩን ከኑግ ጋር ወቅጠህ አብላ።
3. ለልብ ድካምና ደዌ ስሩን ከሱፍ ጋር ጭልቃ አድርገህ አጠጣ ወይም አፍልተህ ሲበርድ አጠጣው።
4. ለጨንራ ከተቀቀለ ተልባ ውኃ ጋር ስሩን ፍሬውን ጨምረህ አጥለህ አጠጣ።
5. ለኩላሊት በሽታ ዓይኑ ጥፍሩ ብጫ ለሆነ ሥሩን ወቅጦ እንደሻይ ከማር ጋር አፍልቶ መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

6. የወር ደም ለሚበዛባት ከጠለንጂ ሥር ጋር ወቅጦ ለሰባት ቀን በማር ማዋጥ ነው።
7. ለመጽንኤ አስኪት ከነጭ ሽንኩርት ጋር እያፈሉ መጠጣት ነው።
8. ለሣል ላልታወቀ ደዌ የምሳና የአሚራ የሥረብዙ የምድር እንቧይ የቀጠጥና ሥራቸውን በአንድ ላይ ወቅጦ ከነጭ ሽንኩርት ጋር በቅቤ አንጥሮ መጠጣት ነው።
9. ወገቡን ለሚያመው በብዙው ሥሩን ወቅጦ ውኃውን ጨምቆ ማጠጣትና በተረፈው በውኃ ቀቅሎ በወገቡ ማሰር ነው።
10. አልድን ላለ ቁስል ቅጠሉን ከጉርጠብ ቅጠል ጋር ወቅጠህ አድርቀህ ደምድመህ እሰረው።
11. ለከሳ ሰው ሥሩን በወተት አፍልተህ አጠጣ ወይም ከበሶ ጋር አብላ።
12. ለራስ ህመም አበባውን ከአደይ አበባ ጋር ወቅጦ በአፍንጫ መሳብ ነው።
13. ለመገብና ለጆርባ ደዌ የአቱችና የቀጠጥና ሥርና ቅጠል ጋር ወቅጦ በአንት ዘፍዝፎ መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

14. ጆሮው ለደነቆረ ፍሬውን ከሰሊጥ ጋር ዘይት አውጥቶ በጆሮ ማድረግና ጥጥ መወተፍ ነው።
15. እራሱ ለቆሰለ ለአንጉል ነቀርሣ በአፍንጫው ግማት ለሚሰማው ቅጠሉን አበባውን የጭቁኝ የእንስሳል ቅጠል በፍየል ቅቤ አንጥሮ በአፍንጫው ተንጋሎ ማድረግና ጥጥ መወተፍ ነው ደጋግሞ ማድረግ ነው፡ ለችፌ ከምድር እንቧይ ስር ጋር በማር መቀባት ነው።
16. ለንግድ ሥሩን ከሞይደር ስርና ከእጣን ጋር ማጤስ ነው።
17. ለምሳጭና ለመቀስ ማድከሚያ ቅጠሉን ጠጉርን መቀባት ነው።

## ቀዘው /የአሞራ አሞጭ/

1. ለመስተፋቅር ለመስተሣልም እገሌና እገሌን አፋቅር አዋድድ አንድ አድርግ በፍቅር አንድ ይሁኑ ብሎ በእሳት ትርኳሽ ወይም በሁለት ክብሪት በሁለት በኩል ሥሩን መተኮስና እጅን ቀብቶ በሰላምታ መንካት ነው።



Scanned by CamScanner

2. ለተጣሉና ሁልጊዜ ለማይስማሙ ለማስታረቅ ቅጠሉን አሽቶ ግንባራቸውን ቀብቶ ታረቁ ብሎ ማስተቃቀፍ ነው።

## ቀዘበ የድመት ዓይና የመሰለ ስሩ ነጭ የሆነ

1. ለመስተፋቅር በእሳት ለብ ለብ አድርጉ እጅን አሻሽቶ ሰላም ማለት ነው።
2. ለበረድ መመለሻ በእሳት ስሩን ተኩስ የበረድ ዝናም ሲመጣ በሥሩ አይኑን አባብሶ እፍ እፍ ማለት ነው። ሰማዩን በአይን አይጠቀሱ ሰውየው የአለበትን አገር አይነካውም።

## ቀጤማ /የሣር ጉዝጓዝ/

ለሥራይ ከምድር እንቧይና ከምርች ጋር ሥሩን ወቅጠህ በአንት አጠጣ።

## ቀጤማ ዛፍ

ፍሬውንና ሥረብዙ ጋር በሽከከ ሥጋ መረቅ ቢጠጡት ለከሣ ሰው ጥሩ ነው ያወፍራል።

## ቀጨጭማ ፡ ተ/



Scanned by CamScanner

ቀጤሰን ፡ ተ/

ቀጨሞ ፡ ተ/

ቁልቋል ፡ ቀለምጤዳ

1. ለኪንታሮት የእንባጮ ቀንበጥ ደቁሶ በደሙ ለውሶ በጥቁር ስንዴ ሊጥ ለውሶ መደምደም ነው።
2. ለጭብጦ ለኪንታሮት በሆድ ውስጥ ላለው የቁልቋሉን ደም ከእንዶድ ስርና ቀንበጥ ጋር አቀላቅሎ ወቅጦ በንጹህ ሻሽ አጥሎ ማድረቅ እሩብ ማንካ በማር ለውሶ መዋጥ ነው። ማርከሻው ወተት ወይም ተልባ ነው።
3. ለማንኛውም በጥቁር ሽንብራ ዱቄት ደሙን ለውሶ ማድረቅና መውቀጥ ነው እሩብ ማንኪያ የሚያክል በማር መዋጥ ነው።



Scanned by CamScanner

## ቁንጶ በርበሬ

ለትምህርት ለእውቀት ከእፀመናሂና ከእፀነቢያት ስር ጋር ፍሬውን ተቀጽላውን ወቅጦ በጣዝማ ማር ለውሶ ቢገኝ በትንኝ ማር ሰባት ቀን በባዶ ሆድ መብላት ነው።

ቁርቁራ ፡ ተ/

ቁስ በደጀ ቂንጦ ?

## ቅል በግእዝ ሐምሐም

1. ጆሮው ለሚመግልበት ቅጠሉን ወቅጦ በሻሽ ጨምቆ በጆሮው ማድረግ ነው።
2. ለትኩሳት የቅል ለጋ አብላው
3. ለጋ ቅል ከአታክልት ጋር ቢበሉት መልካም ነው።

ቅሞ ፡ ተ/

## ቅንጭብ ከወንዱው ይልቅ እሴቴው የተሻለ ነው

1. ለነቀርሣ የቅንጭብ ተቀጽላ ቅጠል የሰሪቲ ስር ቅጠል የቁልቋልና የቅንጭብ ደም መቅመቆ



Scanned by CamScanner

ሁሉንም በአንድ ላይ ወቅጠህ እሰርለት፣ በሶስተኛው ቀን እየፈታህ አጥበህ እንደገና እየደመደምክ በሻሽ እሰርለት ያወጣለታል።

2. ለነቀርሣ የቅንጭብ ደም በባዘቶ ጥጥ ላይ አድርጉ ለአሥራ አምስት ቀን ማሰር ነው።

ቅርቅሃ የበርሃው ድፍኒ ሽመል ይባላል ?

## ቅርንፉድ ቅርፉል

ለርሄ፦ ኮረሪማ ሽንብራ ቅርንፉድ በማርና በቅቤ አቡክቶ ሰባት ቀን በባዶ ሆድ ጥማሽ ማንካ መብላት ነው።

ቃሬጣ ፡ ተ/

## ቅቤ ጉትት

እፀፈላጹትን የመሰለች ነጭ ደም የሚወጣት ናት

ቅቦ በግእዝ እፀ ጦቢያ ወይም ጦቢያ

1. ለነቀርሣ ሥሩን ቅጠሉን የመሬዝ የአዞ አረግ ቅጠል ዋዢንቢጥ ድኝ ክብረሰማይ ስመ አንፋር ጨው ሰናፍጭ ጥቀርሻ ሁሉንም ደቁሶ በቅቦ /ቅንቦ/ ወተት ለውሶ መደምደምና ማሰር ነው። ንጹህ ገላውን እንዳይነካው ማር መቀባት ነው



Scanned by CamScanner

ከዚያ ደምድሞ የስንዴ ሊጥ በበላዩ አፍና ማሰርና በሶስተኛው ቀን መፍታት ነው።

ቃጫ - ቢስታ ጭረት

ሴቴና ወንዴ አለው

አፍንጫውና ጆሮው ለታመመ ወይም ለሚመግልበት በእሳት እያሞቁ በጆሮው መጭመቅ ነው እንዲሁ በአፍንጫው ማድረግ ነው።

## ቅርሽሽቦ ቅርሻባ

1. ሆዱ ለታመመ ለሚያቅለሸልሸው የቅርሽሽቦ የጅንጅብል ቅጠል በአንድ ላይ ደቁሰህ ከስንዴ ጋር አክስለህ አጠጣው።
2. ለከሣ ሰው የበርሃ ግሜ /ማምሐረግ/ የግመሮ የስረ ብዙ ስር በአንድ ላይ ወቅጦ በቀይ ጤፍ ገንፎ ደጋግሞ መብላት ነው። ለከብት በስንዴ ቂጣ ማብላት ነው።

ቆባ ፡ ተ/



Scanned by CamScanner

**ቆቀባ**

ለመፍትሔ ሐብት የቆቀባ የዋርካ የቀረጥ ተቀጽላ ከነጭ ዶሮ ሥጋ መረቅ ጋር መጠጣት ነው።

**ቆንጥር** ቀንጦ ፡ አዲር፡ ለመንድግ

**ቆጋ** ፡ ተ/

**ቆቅመኝ** ፡ ተ/

**ቆለቆል**

1. ሆዱን ለሚነፋውና ለሚጮህ ከእንጆርይ ቅጠል ጋር አንድ ጠብታ አዋህደህ በማር ለውሰህ አብላ።
2. ለጭብጦ የቆለቆሉን ደም በሽንብራ ዱቄት መለወስና በቅቤ አንጥሮ አንድ ማንካ መዋጥ ነው።

**ቆለቆልዳ** የቆለቆልና የቆለቆልዳ ዘራቸው ቁመታቸውና መልካቸው ብዙ ዓይነት ናቸውና በጣም



Scanned by CamScanner

መርዘኛና አደገኛ የሆኑ ስላሉ መጀመሪያ ማጥናት ያስፈልጋል። ደማቸውን አጠራቅሞ ቢሰብቁት ውኃ የመሰለ የሚጠል ካወጣ አደገኛነት የለውም የማይለየውና እሾሃም የሆነው መርዘኛ ነው፡ አደጋ ላይ ያደርሣል ይህ ለቆዳ ደዌና ለነቀርሣ ለኪንታሮት ከሚቀባና ከሚደመደም መድኃኒቶች ውስጥ ይጨመራል።
ሌላው ደግሞ በጣም አጭር የሆነ አለ ቢወጉት ውኃ የመሰለ ይወጣዋል እርሱ ለከሣ ሰው ወይም ለከሣ እንስሣ አመንምን ለያዘው ይሆናል።

## ቋንደሐረግ

ለሚተላ ቁስል ሥሩን ወይም ቀንበጡን የአገሌን ቁስል እንደዚህ ቁረጥ ብሎ ቆርጦ መጣል ነው ወይም በወገቡ ማሰር ነው።

## ቋራ /ገተም የመሰለ ትልቅ ዛፍ/

ለውጋት ፍሬውን ደቁሶ ከጨው ጋር ከሚያመው ላይ ማሰር ወይም በጥቶ ማግባት ነው።



Scanned by CamScanner

## የቁልቋል ዓይነት ቀለምጤዳ

1. ቁልቋል፡- አራት ማዕዘን ያለው ደሙ ለሥጋ ደዌ ለቁስል
2. ቆለቆል፡- እሾሃም ደሙን አጠራቅሞ ሲያማስሉት ዓይብ የመሰለ ይወጣዋል፡ አይቡን አውጥቶ አንቱን መጠቀም ለመጋኛ ለደዌ
3. ቆለቆልዳ፡- እሾሃም በጣም መርዘኛ የሆነ ደም አለው ያቆስላል ሰውነትን ስለሚጐዳ ማጥናት ያስፈልጋል።
4. በግእዙ እፀ ኑር በአማርኛ አኑር ይባላል ቆለቆልዳ መስሉ ድቡልቡል አጭር ወፍራም ነው እርሱን እንዳለ ወቅጦ ከቀይ ጤፍ ቂጣ ጋር ቢበሉት ለወፍራም ሰው ያከሣል ይቀንሣል ሙሉ ሰያ ያደርጋል።
5. በግእዝ እፀናሁ በአማርኛ የላምጡት ወይም የምድር ቁልቋል ቁመትዋ ግማሽ ክንድ አትሆንም ችምግ ብሎ የሚበቅል ነው እንዳለ ወቅጦ ከሰመሬታ ገብስ ጋር ለከብት ርቢ ማብላት ለከሣ ለቁመኛ ሰው ከሚበላው ከሚጠጣው ጋር መስጠት ነው።



Scanned by CamScanner

የቁልቋል ዘር ዓይነት ከመቶ በላይ ቢሆንም ደም ወተት ያለው ሁሉ ማለት ወተት የመሰለ ነጭ ነገር የሚወጣው መርዘኛ ስለሆነ ለቁስል ሲጠቀሙ ጥናት ያስፈልጋል ከጥቅሙ አደጋው ይብልጣልና።

ውኃ የመሰለ ወይም ዘይት የመሰለው ለውስጥ አካል ይገነባል ደምን ያስተካክላል።

# በ - B

በሓ ፡ ተቀጽላው

ባህር አንጓ /ተ

## በለስ /ደም የሚወጣው/

1. ለእጢ ለእባጭ የበለስ የእረኛ ቆሎ ቅጠል ቀንበጥ የምድር እንቧይ ፍሬ በአንድ ላይ ደቁሶ በነጭ ጉመን ቅጠል ሸፍና በእሳት እያሞቁ መተኮስ ነው።



Scanned by CamScanner

2. ገላው ሁሉ ለአበጠበት ቅጠሉን ዘፍዝፎ በውኃው ማጠብ ነው።
3. ጆሮው ለሚመግልበት ቅጠሉን ጨምቆ በትንሹ ከጆሮው ማግባት ነው።
4. ለአድሜ የበለስ የኮሽም የውስጡ ፍሬአቸውን አንድ አንድ ቢበሉ ወይም ሰፍቶ ቢይዙ አድሜ ያስረዝማል። 7 ቀን ወይም 49 መብላት ነው ተቀጽላውን ሰፍቶ ቢይዙም መፍትሔ ሐብት ይሆናል።

ጸሎቱ "ጸሎተ አድሜ አልጦ አልሳዊሩ የከረሙን የከረረሙን ያከረረሚን ፩ አብ ቅዱስ ፩ ወልድ ቅዱስ ፩ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ አኑህ አድሜየ ሊተ ለገ/እ/ አልሙ ዘሚል ፪፩ ጊዜ ጽ/"

## በለስ

1. የኢየሩሳሌም ቁልቋል የሚባለውና ፍሬው ሲበስል በባዶ ሆድ ቢበሉት ለልብ ድካም ይበጃል። ነገር ግን ያልበሰለውን ቢበሉት የሆድ ድርቀትና ሠገራ ለመውጣት ያስቸግራል።
2. የበለስ ለጋው የሆነውን ቅጠል በካርቶን አሽጉ ማስቀመጥና ለመብል በእሳት ለብለብ አድርጉ



Scanned by CamScanner

እንደካሮት ፈቅፍቆ ከሥጋ ጋር ከአታክልት ጋር በእሳት ለብ አድርጎ ቢበሉት ለወገብ ድካም አቅሙ ለአነሰ ይሆናል፡ ያበረታል ፍሬውንም እንዲበስል በቆባው ሰብስቦ እንደሙዝ በካርቶን ማሸግ ነው ጥሩ ሆኖ ይበስላል።

በሶብላ ፡ ሐንከሶ ለመአዛ ናርዶስ ?

## በቆሎ/ባህር ማሽላ/

ለሆድ ቀላል ነው ጨጓራን ያለዝባል ነገር ግን ጨጓራ ህመም ላለው አይብላ ያብሰዋል።

## መረቋ - ባዝኝን

ለማንኛውም ደዌ ቀቅሎ ከቅቤ ጋር መጠጣት

## በቶ፡

ለኪንታሮት ለጭብጦ ለአባ ላባ ሥሩን ወቅጦ በውኃ ዘፍዝፎ ማጥለልና ከሙቅ ተልባ ውኃ ጋር መጠጣት ነው። በጣም ሲደክም ትኩስ ወተት መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

## በኩረሉሚ

1. ቆሽትን ያበረታል ነጭ ሐሞትን ያጠፋል የደም ግፊትን አዘውትሮ ቢወስዱት ያሽላል።
2. ለካልስትሮ ለጉበት ለነቀርሣ ለሣንባ ነቀርሣ ለወፈረ ሰው ጭማቂውን አዘውትሮ ለአርባ ቀን መውሰድ ነው።

## በትረ ሙሴ

ለአህያ ኪንታሮት ለሥራይ ቅርፍቱን ከበግ ላት ጋር ቀቅለህ መረቁን አጠጣ ከሆድ ያለን ነገር ጠርጐ ያወጣል።

## ገጠቋ

ራሱ ለሚቆሸሽ ለጠጉር ፡- ሙጫውን ከእንኮይ ፍሬና ከልት ቅጠል ጋር ወቅጦ መቀባት ነው ወይም ከኑግ ዘይት ጋር ቀላቅሉ አዘውትሮ መቀባት ነው ጠጉርን ያሳምራል።

ቡርቃ ተ/



Scanned by CamScanner

ቡና

1. ለአስም ቅጠሉን ቀቅሎ ከማዝማማ ማር ጋር በባዶ ሆድ መጠጣት ነው፡ የቡና ቅጠሉ ሥሩ በእሳት አምሶ ቢጠጡት እንደሻይ ያነቃል ደም ያጠራል።
2. ለራስ ምታት ከአቦል ቡና ጋር የሎሚ ውኃ ጨምሮ ቢያም ቢጠጡት ያስወግዳል መድኃኒም ነው።

ባቡሌዳ ባባ የሾላ ዓይነት ጳላጢኖስ

ያልበሰውን ቆንባ ሰብስቦ እንደሙዝ ቢያሸጉት ይበስላል እርሱን አውጥቶ ቢያደርቁት ለጠጅ ለጠላ ለአረቄ ቢያዘጋጁት ለጤና ጥሩ ተስማሚ ይሆናል።

ባምያ

ለሆድ ህመም ለጨጓራ ከስጋ መረቅ ጋር መጠጣት ነው ሆድን ያለሰልሣል። ለሆድ ቀላል እርጥብም ነው።

ባባያ

1. አካሉ ለደቀቀ ከበሉ በኋላ ማብላት ነው።
2. ለጨጓራ ቅጠሉን እንደሻይ መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

3. ለደም ብዛት ለሆድ ቁርጠት ፍሬውን ወቅጦ በማር ለውሶ በባዶ ሆድ መውሰድ ነው።

## ባርስነት

ለተሰበረ ከስብራቱ ላይ ደፍድፎ እሳት ያስመታው።

### ባቄላ

1. ለሰውነት አልበቱ ስልጆው የንፍሮው ውኃ ጥሩ ነው። ለሆድ ይስማማል አዘውትሮ ቢበሉት የአይን ዳፍንት ይሆናል፡ ለእባጭ ለቁስል ስለሚያፋፋው አለመብላቱ የተሻለ ነው። ነገር ግን የባቄላ ገለፈቱ ወቅጦ ቢጠጡት ከቁስል ቢደመድሙት ይፈውሣል።
2. ለተሰበረ ለተጐዳ ሰው የባቄላና የዘንጋዳ ንፍሮ ውኃ ጧት ማታ ቢያጠጡት ይፈወሣል።

ባስኬ የዘንጋዳ ዓይነት ነው

ለእንጀራ ለጠላ ጥሩ ነው።

ቢሉ የምቢሉ ?

## ባህርዛፍ በግእዝ ቀሌምንጦስ

ለጉንፋን ለምች አደር ቅጠሉን ቀቅሎ መታጠንና ተሸፍኖ መተኛት ነው።

ብርቱካን ፡ ቅጠሉን ፍሬው ቀቅሎ መጠጣት

ብብሻ ጉፋ

1. ቆዳ እንዳይበላሽ ብል እንዳይበላው የብብሻ የቀረጥ የድግጣ የምሬዝ ቅጠል ቅርፍት ወቅጠህ አጅልበት ለበድን ለብራና መጽሐፍ እንዲሁ አድርግ
2. ለማንኛውም ህመም ቅርፍቱን ከአርማጉሣ /ጦት አስጥል/ ጋር ወቅጠህ በቀይ ጤፍ ቂጣ መብላትና አንት መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

# ተ - ተ - Tt

ተሆጭ ተ/

## ተልባ

1. ለጨንራ ለሆድ ህመም ለካልስትሮ ፍሬውን በውኃ ቀቅሉ ገና ሲገነፍል በረድ አድርጉ ጧትና ማታ መጠጣት ነው።
2. ለማንኛውም ህመም በባዶ ሆድ ፍሬውን አዘውትሮ ቢወስዱት ሙሉ ጤነኛ ሰው ይሆናል።

## ተምር

ምጥ ለፀናባት ፍሬውን በብርዝ ወይም በማር በጥብጠህ አጠጣ።

## ተሉላት

ለቁርጠት ለሆድ ደዌ ከሥረ ብዙ ጋር በማር መዋጥ ነው።



Scanned by CamScanner

## ተረን

ለልብ ትኩሣት ከከርቤ ጋር በቅቤ አንጥር በባዶ ሆድ መጠጣት ነው።

ተረረንሣ ፡ በለሳን፡ ሽቶ ለመቀመም የሚያገዝ

## ተቢናግሬ

ዓይኑ ለቀላና ለታመመ ቅጠሉን ከስልብያ ቅጠል ጋር ወቅጦ በሻሽ ማሰር ነው።

## ቱልት

1. ለቋቁቻ ቅጠሉን በእሳት እያሞቁ ቢተኩሱት ይጠፋል፡ ማድያትም ከቅባት ጋር ለውሶ ቢቀቡት ይፈውሳል።
2. ለቁርጥማት ፍሬውን ደቁሶ በማር መውሰድ ነው ጊንጥም ቢነክስም አያምም።
3. ለአይን ማዝ ሥሩን ከፍትግ ገብስና ከምስር ገለፈት ጋር ወቅጦ በቅቤ አንጥሮ መቀባት ነው።
4. ሆዱን ለነፋው ስሩን ከቀጠጥና ሥር ጋር ወቅጦ በማር ወይም በወተት ማጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

5. ለሽንት ማጥ ከፋኛ ያለን ጠጠር ለማውጣት ሥሩን በውኃ ቀቅሉ ከወተት ጋር ቀላቅሉ መጠጣት ወይም ከሰሙሬታ ጉበስ ጠላ ጋር መጠጣት ነው።
6. ቱልት ትኩስ ደረቅ ነው የበሉትን ከሆድ ያጠፋል ሴትንም ያስፈቅዳል።
7. ለሪህ በሽታ ከጢብጢባ ስር ጋር ወቅጦ በሉፍ ውኃ ከእንጀራ ጋር ፈትፍቶ መብላት ነው።

## ቲማቲም

ለደም ጥራት ጭማቂን በባዶ ሆድ መጠጣት ነው።

ቱማ ?

/ትርኪ ቱርኪ/ ትለም ?

## ትርንጉ

1. የአንገቱን ውስጥ ለሚያመው ፍሬውን ከአሚራ ቅጠል ጋር ደቁሶ በፍየል ሐሞት ለውሶ መቀባት ነው።
2. ለቆሽትና ለጉበት ደዌ ቢበሉት መልካም ነው።
3. እህል ለከለከለው ቅርፍቱን መብላት ነው።



Scanned by CamScanner

4. ቁርጥማት የጀርባ ህመም መርዝ ጭንቀት ላለበት ፍሬውን በባዶ ሆድ መብላት ነው።

## ትንባሆ - የሱስ የወልፍ ችግር የሚያወጣ

ቶለላት "ሀ" ላይ ተመልከት ሁለገብ ነው እፀ ካባ ይባላል።

## ቶማይ ታርይገማ ዱርሺት

ለመወሐድ "አዛዝኤል አልያቡሊት በዚህች እፅ ያልኩህን አድርግ እኔን ጠብቀኝ አታስነካኝ ጠላቶቼን ያዝ አትልቀቅ አንተ የእፅ ንጉሥ" ብለህ እየሰገድክ እየተማፀንክ ቁረጥ ከዚያ በኋላ የፈለከውን ተናገረህ አድርግ ለመስተጻልእ ከውሻ ከዶሮ ኩስ ጋር ለማበላሸት ከሦስት ሥጋ ጋር ለማስታመም ከጥቁር ጉበት ጋር ይሆናል ለመመለስ ስሩን ማጤስ ነው ሁሉን ይፈታል ለመልካም ለመጥፎ ነገር የሚሆን እፅ ነው ከስሙ መረዳት ይቻላል።

ታርይገማ በግእዝ እፀ ቶማይ ዱርሺት የዱር ግማት የሚሉትም አሉ አረግ እሬሳን ይመስላል። ቅጠሉ

ከተቆረጠ በኋላ በጣም ስለሚገማ ነው ቃር ይገማ የተባለው፡

1. ለምህግብ ንዋይ አምጽኡ ለእግዚአብሔር ደግመህ የተመኘኸውን ተናገረህ ሥሩን ነቅልና ግማሹን ቃጠን ግማሹን በወርቀ ዘቦ ገምጃ ሸፍነህ ያዝ።
2. ለመቀትል በስሙ ረግሞ መቁረጥና ከጥቁር ዶሮ ጉበት ነስንሶ ለጥቁር ውሻ ወይንም ለጥቁር አሞራ መስጠት ነው።
3. ለመፍዝዝ ከሰባት ቀለማት ጋር ለውሶ መያዝ ነው።
4. ለአንደርቢ በስሙ ቆርጦ ከእባብ ሥጋ ጋር ወቅጦ ለአሞራ ማብላት።
5. ለመስተሐምም በስሙ ቆርጦ ከሽንቱ ወይም ከወዙ ጋር ደቁሶ በጥቁር ፍየል ጉበላ ላይ ነስንሶ ለአሞራ ማብላት ወይም ከትኩስ መቃብር መቅበር ነው።
6. ከጠላት ለመሰወር ሌሊት ራቁትን ሁኖ ቆርጦ ከአጽመ ሰብዕ ጋር ወቅጦ በጥቁር ድመት ደም ለውሶ በግራ ኪስ መያዝ ነው።



Scanned by CamScanner

7. የሰማዩ ለዞረበት ቅጠሉን በአዲስ ቅል ዝፍዝፎ ዘዋራ ቦታ ይታጠብ። ለአእምሮ ስሩን ከኑጭ ማር ጋር ይብላ።
8. ለመንድግ የአሰቡትን ተናገሮ ቀርጦ ከሞይደር ከከርቤና ከእጣን ጋር ማጤስ ነው።
9. ዝበያ ለመዝጋት ከዶሮና ከውሻ ኩስ ጋር ደቁሶ ቤቱን መርጨት ወይም ከስስት ሥጋ ጋር መቅበር
10. አንደረብ ለመመለስ ሥሩን ማጤስ ቅጠሉን ዘፍዝፎ ቤቱን መርጨት ነው። የግሜአረግ መጨመር ነው።

## - ቸ - Che

ቼብሃ ጥሉሣ ተ/

ቼርቼር ተ/

ቼፍርግ ከርሚል?



Scanned by CamScanner

# ነ - Na

### ነጭሉ

1. ለምሕሳበ ንዋይ አጽመሰብእ ወርቅና ብር የእህል የቅመም ዓይነት ሁሉን ሰብስበህ ማርና ወተት ሰኞ ማታ ከነጭሉ ስር አሣድረህ ማክሰኞ ጧት "ዋው የተመኘሁትን ወርቁን ብሩን ሰውን አሲዘህ አምጣልኝ እሰይ እሰይ ሐብትና ንብረቴን በቤቴ አብዛ ባርክልኝ ጠላቴን ያዝልኝ" ብለሁ ነጭ ዶሮ አርደህ ስሩን ቁረጥና ሌላውን ከዚያው ቅበርና ሌላ ነጭሉ በበላዩ ተክለህ ወደ ቤትህ ሂድ ከቤት ስትገባ ደጓሰህ ግማሹን ሥር ያዝ ግማሹን ስር ከቤትህ ውስጥ አኑር፡
2. ለምሕሳበ ሰብእ ቀይ ብጫ ሰማያዊ ሐር ከጫፉ አስረህ ሰኞ ቀን የዳቦ የንፍሮ ዓይነት ከሥሩ አስቀምጠህ ሂድ

   ሐሙስ ጧት ነጭ ዶሮ አርደህ ምኞትህን እየተናገርህ ከጫፍ እስከ ሥሩ ደሙን ቀባው አርብ ሺቶ ከማር ጋር ከሥሩ አፍሶ ቅዳሜ



Scanned by CamScanner

ጥቁር ዶሮ ከኑግ ጋር አርደህ ጣል፡ አሁድ ቀይ ዶሮ ይዘህ ሂደህ ሁሉንም በየቀናቸው አርደህ የፈለከውን ተናግረህ ከሰባት ቦታ ቆፍረህ ቁረጥ የአረድከበትን ካራ ከሥሩ ሰው እንዳይወስደው እንዳይገባ አድርገህ ቅበረው ከዚያ ሰው አምጣ እያልክ በለበቁ ደጁን ምንገዱን ምታ የሚሸጠውን እቃም እንደዚሁ ምታው።

3. ለመንድግ

"ፎመዛ ፖመዛ ጳመዛ ህምዛ ሎመዛ ቤዛ ቅምዛ ቢስሚላሂ አሮሂማን አሮሂም ነሡሩላሂ ብከ ወነሡሩላሂ ያመጽአ ለከዛር ሙርጃን ከደጋ ደባልቄ ከቆላ ደባልቄ የተመኘሁትን ሁሉ በእጅ አስገባልኝ የመጣውንም አበርክትልኝ አንተሙርጃን የወርቅ ንጉሥ ለእኔ ለእገሌ"

ይህን ከሶስት ላይ ጽፈህ በጥቁር ድመት ወይም ውሻ ደም ለውሰህ በጥፍንዶ እንጩት አክስለህ ከሰሉን በአይት ሐሞት ለውሰህ ከሰውነትህ ቅበርና ከነጭሎ ስር ሂደህ ለዚህ ሁነኝ ብለህ ቁረጥና ያዝ በለበቁም የአስብከውን ተናግረህ ንካው።



Scanned by CamScanner

4. ለእድሜ "የከረመኔ 49 ኤልሻዳይ 49 ኤልአሄ 49" በቅባአቅዱስና በሜሮን ደግመህ ነጭሉውን ቅባና ቁረጥ ከስሩ በኪስህ ትንሽ ያዝ ከመኝታህ አጠገብ ሰቅለህ አስቀምጥ በየአመቱ አድርግ
5. ለመንስኤ አስኪት የነጭሉን ቅጠል እየወቀጥክ ብልትህን ቅባና ሥሩን ከሙት አንሣ ጋር በማር ደጋግመህ ብላ ፍሬውን በመጠጫ ይሳብ ፍሬውን በጠጅ ቀቅሉ መብላት ነው።
6. ለማንኛውም የሶስት እስስት እራሳቸውን የነጭሉ የፍየለ ፈጂ ፍሬአቸውን ቅጠላቸውን ሁሉንም በጉርጥ አፍ ውስጥ ከተህ ያዝ ለሁሉ ይሆናል።
7. ለሚጥለው የነጭሉ ቅጠል የጂብ ሐሞትና ኩላሊቱን አንጉሉን ሁሉንም ወቅጠህ ሲጥለው በአፍንጫ አድርግ ከራሱ ላይ ደምድመህ እሰርለት፡
8. ደም ለሚያስተፋው ቅጠሉን ከወይናግፍትና ከጭቁኝ ቅጠል ጋር ወቅጠህ በማር ለውሰህ አብላ አውጠው፡
9. ለመፍትሔ አስኪት ስሩን እያላመጠ ፍሬውን እንደትንባሆ በመጠጫ ይጠጣው ቅጠሉንም ይቀባው።



Scanned by CamScanner

10. ነጭሉ ሲቆረጥና ሲማስ አምልኮት ስግደት ይወዳልና ለዚህ ነገር ሁነኝ እየተባለ እየተማጸኑ መቆፈርና መቁረጥ ነው።

የነጭሉ ዛፍ ዓይነቱ ብዙ ነው እርሱን የሚመስሉ ቅጠላቸውም ግንዳቸውም መልካቸው ነጭ ስለሆኑ ነጭሉ ነጭ ብሉ ነጭ ብላ ነጪጭሉ፡ ነጪጭላ፡ ነጭሊት፡ ነጮ፡ ነጭዛፍ፡ ነጫቴ፡ እየተባሉ የሚጠሩ አሉ ሁሉንም ለማወቅ ከሚያውቁ መጠየቅና መረዳት ያስፈልጋል። ካልሆነ ወይም ለይቶ የሚያውቅ ለይቶ የሚያስረዳ ካልተገኘ በገቢሩ መሞከር ጥናት መውሰድ ነው።

ነጭ ዛፍ ተ/

ነጪጭሉ ተ/

ነጪጭላ ተ/

ነጭብሉ ተ/



Scanned by CamScanner

ነጭብሳ ነጭሳ ተ/

ለእንግዴ ልጅ ማስወረጃ ቅጠሉን ቀቅሎ መታጠን ነው ይወርዳል።

ነጭሊት ተ/

ነጩቴ ተ/

ነጭሳ ወይም አመዶ ሚ፡ኬ

ለአጡት እበጥ ጂማቱ ሲታሰረ ቅጠሉን ከአለብላቢት ቅጠል ጋር እሰርለት።

ነጭሺምጥ ተ/

ነጭ ዳባቀድ ተ/

ነጭ አዝሙድ ተ/

ቱማ፡ ነጭ ሽንኩርትን ከሸ ቤት ውስጥ ተመልከት ተጨማሪ ለካልስትሮ ለሆድ እከክ ባክተሪያ ለእከክ ለልብ ድካም ለምች ለደም ብዛት በማር ለውሶ ጧት መውሰድ ነው።



Scanned by CamScanner

ነጭጥቅል ጉመን

ለአንጀት ለዉኃራ ህመምተኛ ቀቅሎ ውኃውን ብቻ ብዙ ቀን ደጋግሞ መጠጣት

ኑግ፡ ኮጥሜ ?

ኑርልኝ፡ እንደድንች የመሰለ ተቀቅሎ የሚበላ

ናና

ለራስ ህመም እንደሻይ አዘውትሮ መጠጣት

ናትራን ?

ንብጥራ

ለቀፎ ከሰው አጽምና ከቁልቋል ልብ ጋር ማጠን ነው። ንቡ ይበረታል ወይም የኮሸሸላ የቁልቋል ተቀጽላ የጃርት እሾህ ጋር በንብጥራ ቅጠል ሸፍና ከቀፎ መሻተ ነው።



Scanned by CamScanner

# - አዐ - A a

**አልቴት** ፡ ለማንኛውም በውኃ በጥብጦ ሰውነትን መታሸት

አሉማ ተ/

**አልማ ትንሽ አረም**

ለወገራ ህመም እንደጉመን ቀቅሉ መብላት ነው።

**አብላሊት፡** አለብላቢት ወንዴና ሴቴ አለው እፀ ተማስ /አለብላቢት አይደለም/ ለመስተፋቅር ስሩን ከአሰርኩሽና ከችፍገ ጋር ደቁሶ በሽንት ውኃ ዘፍዝፎ መስጠት ነው።

**አሚራ**

ጠገእዝ እፀ አሜር/ የደጋና የቆላ ስላለው ለህመም የቆላው ለጠጅ የደጋው ይመረጣል።

1. ቅጠሉን ለሣል ለአስም ለቁርጥማት በቅቤ አንጥሮ ማጠጣት ነው።
2. የአንገቱን ውስጥ ለሚያመው የአሚራ ቅጠል የትርንጐ ፍሬ ደቁሰህ በፍየል ሐሞት ለውሰህ



Scanned by CamScanner

ቀባው የሐመል ገላ የአሚራ ቅጠል እንደዚሁ አድርግ፡

3. ጆሮውን ለሚያመው የአሚራ ቅጠል የአሞጭ ፍሬ ከርቤ በአንድ ላይ ደቁሶ በፍየል ቅቤ አንጥሮ በጆሮው ማድረግ ነው።
4. ጥርሱን ለሚያመው ለሚቆረጥመው የአሚራ ስር ቅርፍት ከሚያመው ላይ በጥጥ አድርጉ መያዝ ነው ወይም እንደስጃራ ማጤስ ነው።
5. በሆድ ውስጥ ላለ ኪንታሮት ከወርቅ በሜዳና [illegible] ጠንስሶ መቆየት ከሰባት ቀን በኋላ መጠጣት ነው።
6. ለምሽሮ ነቀርሣ ቅጠሉን ከጉርጠብ ቅጠል ጋር ወቅጦ አድርቆ በቁስሉ ላይ ነስንሶ ማሰር ነው።
7. ለኪንታሮት ቅጠሉን ከእንፋር ቅጠል ጋር ወቅጦ በአህያ ደም ለውሶ በጥቶ መቅበር ነው።
8. ለኪንታሮት ለሥራይ ለውርጄ ለቁርጥማት ቅጠሉን ወቅጦ በቅቤ አንጥሮ መጠጣት እንዲሁ ከጉርጠብና ከሁለገብ ቅጠል ጋር ወቅጦ በመቀመጫው ውስጥ ማድረግ ነው።
9. ለሣልና ለአስም የአሚራ ፍሬና ፌጦ አሞሌጨው በአንድ ላይ ደቁሶ በባዶ ሆድ በማር መዋጥ ነው።



Scanned by CamScanner

10. ለአስም ፍሬውን ቅጠሉን ከዋጊኖስ ፍሬና ቅጠል ጋር ለውሰህ በማር አውጠው ከትንሽ ሰአት በኋላ አብሽ አጠጣው።

አመዳም አሚዳሞ አይብደም አበያደም ለቁስል ለሻህኝ ለመሰሉ ሁሉ ይጨመራል።

አመራሮ /ከአዝመራ መሐል የሚበቅል አረም/

1. ለስኳር ህመም ቅጠሉን እንደጐመን ቀቅሎ መብላት ነው። ወይም ከአርማጉሣ ቅጠል ጋር ወቅጦ አድርቆ በማር ለውሶ መዋጥ ነው።

ጦድማዶ፡ መዶኬ

1. ለአኽያ ኪንታሮት ቅጠሉን ከዋዥንቢጥ ጋር ወቅጦ በቁስሉ ላይ ማሰር በሶስተኛው ቀን አጥቦ የአመድማዶ ቅጠልና የጐርጠብ ቅጠል ደፍድፎ ማሰር ነው። አጥንቱ ለተሰበረም ደፍድፎ ማሰር ነው።

2. ለኩላሊት ቅጠሉን ከቀይ ሽንኩርት ጋር አፍልቶ ጧትና ማታ ውኃውን መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

3. ለሻህኝ ለጭንቁር ቅጠሉን ከቁልቋልና ከጠንበለል ፍሬ ጋር ወቅጠህ በማር ለውሰህ መቀባት ነው።

አመራሬ ዛፍ ተ

አግፕር አልቄ ተ

## አምከኒት

ለሆድ ደዌ ሁሉ፡- የአምከኒት የአዛምራ የምሳና ቅጠላቸውን ወቅጦ አቡክቶ በቀይ ጤፍ ዱቄት ገንፎ ወይም ቂጣ አንድ ማንካ ያክል ጨምሮ መብላትና አንት መጠጣት ነው።

## አሙጃ አምጃ

ለጆሮ በሽታ የአምጃ ፍሬ ደቁሰህ በውኃ በጥብጠህ በሻሽ ጨምቀህ አግባ፡

## አሞጭ /የአሞጭ አይነቱ ብዙ ነው/

1. አፍንጫው ለሚመግል ወቅጦ በቅቤ አንጥሮ በአፍንጫው መጨመር ነው።



Scanned by CamScanner

2. ለነቀርሣ የአሞጭ የእንዷሁላ ሥራቸውን የዋጊናስ ቅጠል በአንድ ላይ ወቅጠህ ከቁስሉ ላይ አድርገና የስንዴ ሊጥ ደፍድፍበትና እስረው በየሰስተኛው ቀን እየፈታህ አጥበህ እንዲሁ አድርግ፡

3. ሣንባው ታሞ ሣል ለሆነበት ሥሩን በእሳት ጠብሶ በማር ለውሶ ሳያጣጥም ይዋጥ ወይም በስንዴ ሊጥ ውስጥ አድበልብሉ ጉሮሮውን እንዳያመውና ምላሱን እንዳይጉለጉለው አፉን ከፍቶ ይዋጠው ለመጽንኤ እስኪትም እንደዚሁ አድርግ።

አሰርኩሽ በበረሃ የሚገኘው እፀ ሕይወት ይባላል። ስሩ ድንች የመሰለ አለው በቆላ የሚገኘው ሴቴው ነው። በደጋ የአለው ወንዶው ይባላል።

አሰርኩሽ /ወንዴ ሴቴ አለው/ እፀማእሱር

1. ያበደ ውሻ ለለከፈው ስሩን በወተት አጠጣ። እባብ ለነደፈው በማር አብላ።
2. ውሻ እንዳትወልድ ለማምከን የአሰርኩሽና የወይናግፍት ስር በአንገትዋ ማሰር ነው።
3. ለመስተፋቅር የሴቴ አሰርኩሽን ስር በማዝማ ማር ብቀብቶ መገናኘት ነው። በውኃ ሽንት



Scanned by CamScanner

ለውሶ ከተልባ ጋር ጨምሮ ቢበሉ የነገሩትን የነገሩዋትን ለማገም አይናገሩ።

4. ለሐብት ለፍቅር ለንግድ የምትፈልገውን ነገር ተናግሮ ለዚህ ሁነኝ ብሉ እፀ እንግሥ ደግሞ መቁረጥ ነው።
5. ባልዋ ለጠላት ሴት ወይም ሚስቱ ለናቀችው ወንድ ስሩን ከአለብላቢት ስር ጋር ወቅጦ በሻሽ ሸፍኖ በጉያ ውስጥ ማዋልና ማሳደር፡ ከዚህ በኋት የውኃ ሽንት ለውሶ ጨምቆ በሚበላ በሚጠጣ ቢሰጡት ይስማማሉ ይታረቃሉ የሌላ ሰው ወሬ አይሰሙም፡ ለእንስሳም እንደዚሁ ማድረግ ነው።
6. ለሐብት ለከብት እርባታ ስሩን ወቅጠህ በወተት በጥብጦ መርጨት ነው ለንብ በማር በጥብጦ መርጨት ነው።
7. ለቁስል ቅጠሉን ከፈላጹት ቅጠል ጋር ወቅጦ መደምደም ነው። ለኪንታሮት ለነቀርሣ እንደዚሁ ማድረግ ነው።
8. ለመስተፋቅር ፍሬውን ከአስተናግር ከትንባሆ ከእፀ ሳቤቅ ፍሬ ጋር ወቅጦ በማር ወይም በጣዝማ ማር ለውሶ ቀብቶ መገናኘት ነው።

9. ለሴት ወንድ እንዲወዳት ስሩን ከሴት ውሻ ብልት ጋር በግራ ጭን መቅበር ነው።

## አርማጉሣ አቆራራጭ ጡት አስጥል /ሐርማጉስ/

1. ለማንኛውም የሆድ ህመምን ስኳርን ካልስትሮን ለማስታገስና ለመፈወስ ሥሩን ቅጠሉን ወቅጦ በቀይ ጤፍ ገንፎ ውስጥ አስገብቶ መብላት ነው። ወይም ከምሣና ቅርፍት ጋር በቀይ ጤፍ ቂጣ በልቶ አጓት በብዙው መጠጣት ነው።
2. ለመናፍስት ለቡዳ ለቁመኛ ማጠን ነው ወይም ለጋኔን ከሌሎች መድኃኒት መጨመር ነው።
3. የወደደውን እንዲጠላ ወይም የሱስ ችግር ሱሰኛ ለሆነ ሰው ከሚወደው ከሚጠጣው ከሚበላው ጋር ጨምሮ ቢሰጡት ይጠላዋል። ያንገፈግፈዋል ወይም ከአይጥ አረግ ፍሬ ጋር ወቅጠህ እንደዚሁ ስጥ ለውጋት ለቁርጥማት ከጕርጠብ ጋር መጠጣት ነው።
4. ለአስም ለደም ብዛት በቅቤ አንጥሮ መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

## አረማሞ

ከእህል መሃል የሚበቅል የእህልን ፍሬ የሚያበላሽ ከሰል የመሰለ የአለውን የመካን ዛፍ አበባ ማለት የመካን እንዶድ አበባን በአንድ ላይ አድርጉ የእህል ዘርን ቢያሹትና ቢዘሩት በሁለተኛው ጊዜው አያፈራም ይመከናል። እንደዚሁ ህመም ደዌ ለሚመላለስበት ከመድኃኒቱ ጋር ቢሰጡት ህመሙ ዳግመኛ አይመለስም ይመከናል።

## አረግ ሬማ በግእዝ እፀ ማቤት

1. ለሚረግ ቅጠሉን የሉሚሸት የዮዲት የጠስኝ አበባቸውን የእንጉችት ስር ሁሉንም በአንድ ላይ ወቅጠህ በነጭ ማር ሰባት ቀን መብላት ነው
2. ለቅኔ ለድርሰት ለግጥም

   "ናዝ ሳቢሉ በርሃ መጆቸች ክሱት ሊተ/ሉቱ/ ነገራተ ወልሣናተ አብርሀ ልብየ ለድርሰት ወለተርጉሞ ቃላተ ለገብርከ እ/"

   ከአረግሬማ ተቀጽላ ጋር የሞይደርና የእንስላል ስር ደቁስህ በሚጻፉ ሐሞት ወይም በአረቄ መዋጥና መጻሕፍት ሲያነቡ መሰንዘበት ነው



Scanned by CamScanner

3. ደም ለቀረባት ቅጠሉን ወቅጦ ከአዋዜ ጋር መብላት ወይም መጠጣት ነው።

አሩጥ ጥፍርግና ከወንዝ ዳር የሚበቅል ?

ጥፍንዶ ጥፍሬና ከጭሜና ከሜዳ የሚበቅል ነው።

1. ለምርዋጽ ከእንጭብር ስር ጋር በሰመሬታ ገብስ መብላት ነው።
2. ለምሕሳብ ንዋይ
   “ያሙዚሉን ኵሉጀባሪን ሊቃህራን ሱልጧንሂ ወአብድሂማን ያፈርሂማን ኵለሽኢን ወአኪርሁ ቢኢዚኢኒሂ ወማትለፈሐን ሐበኒ አንተ ምሕሳበ ንዋይ ነጣቂ ንዋይ ሊተ ለገ” ሕፃን ልጅ ጥቁር ዶሮ ይዞ እራቁቱን እፁን ሶስት ጊዜ ወደግራ አዙሮ ፊቱን ወደ ደቡብ ሰግዶ የአንድ በቀል አሩጥ ሥር መቆፈርና ዶሮዋን አርዶ መንቀል ወይም መቁረጥ ነው። ደሙን ቀባብቶ ሌላውን ከዚያው ቀብሮ ለበቁን ይዞ ወደቤት መሄድ ነው። ከገንዘብ ጋር ለሠላሣ ቀን መቅበርና በሠላሳኛው ቀን አውጥቶ በሰባት እስስት ደም ለበቁንም



Scanned by CamScanner

ገንዘቡንም አሥነክቶ መያዝ ነው። ሲፈልጉ ገንዘብ አምጣ ብሎ በለበቁ መንካት ነው።

3. ከጭንጫ ወይም ከወንዝ ዳር ነጭ ቅጠል ያላት ሁና የምትበቅለው ለመንድግ ለመስለብ ትሆናለች። አዛና በሚባለው ዋሽንት ጋር መጠቀም ነው።
4. ለምርዋጽ ሥሩን ከእንጭብርና ከሰላቢላ ስር ጋር በሰመሬታ ገብስ ቂጣ ወይም ዳቦ ቆሎ አድርጉ እየበሉ መሮጥ ነው ጉልበት ይበረታል።

አርቴ ፡ ርሔ ?

## አርና

ለወስፋት ለሆድ ደዌ ስሩን ከምስር ጋር ቀቅሉ ውኃውን መጠጣት ነው።

## አርገፍጋፎ

1. ለሚጥለው ከሚበላው ከሚጠጣው ጨምር መስጠት ዘፍዝፎ ማጠብ ገላውን ሲጥለው ከሥሩ ወቅጦ ከጅብ ሐሞት ከስስት ደም ጋር በአፍንጫው ማድረግ ነው፣ ይለቀዋል የአርገፍጋፎ መስቀል ቢያሰሩት ከብዙ ይጠብቃል።



Scanned by CamScanner

## አሰራት

ለእባጭ ለእጢ ቅጠሉን ከእንዳሁላ ጋር በእሳት ጠብሶ እባጩን መተኮስ ነው።

## አስተናግር

1. ከጆሮ ውስጥ እንደትል ለሚላወስበት የቅጠሉን ውኃ ከጆሮ ውስጥ መክተትና ጥጥ መወተፍ ነው።
2. ለጆሮ ህመም ፍሬውን ደቁሶ በሻሽ አድርጐ በውኃ እየነከሩ በጆሮው ማድረግ ነው።
3. ራስ ለሚፈልጥ ጆሮ ደግፍ የአስተናግርና የአውጥ ቅጠል ወቅጦ ማሰር ነው።
4. አስም ለሚያፍነው ቅጠሉን እንደሲጃራ ማጤስ ከአሚ ቅጠል ጋር እንደሻይ መጠጣት ነው።
5. የአስተናግር ፍሬ ወቅጦ ቀምሞ ለሰው ቢያቀምሱት ይለፈልፋል ያደረገውን ይናገራል።

አብ ?



Scanned by CamScanner

## አብላሊት

ቅጠሉ አለብላቢት መስሉ አጭር ነው። በወይና ደጋ ይገኛል እንደአለብላቢት አረግ አይሆንም ቅጠሉ እንደሳማ ያቃጥላል።

1. ለመንስኤ አስኪት የአብላሊት የችፍርግ የዘርጭ አንቧይ የሣማ ሥራቸውን ወቅጦ በብርዝ በዶሮ መረቅ በርግብ ሥጋ መረቅ መጠጣት ነው። ደጋግሞ ይነሣለታል።

አስቃጭር ተ/
አሸንድየ ተ/
አሺቃሞ ተ/

## አሽከት ፡ አንሀስት

1. ለጆሮ ደግፍ ቅጠሉን ደቁሰህ አስርለት
2. ለነቀርሣ ቅጠሉን ከአርያ ስጋ ጋር ቁስሉን ማሰር ነው።
3. ለማንኛውም ቁስል ቅጠሉን መጠቀም ነው።

አኛማ ብርቱካን የመሰለ ተ

ለአቅራራጭ ጡት አስጥል ተ/
አታቅማ ሴቴና ወንዱ አለው ተ/
አበኔ በትረመሴ የመሰለ ?

## አበሱዳ

1. ለሣል አበሱዳ አብሽ ዝንጅብል ከርቤ አጣን ነጭ ሽንኩርት ሁሉንም ወቅጠህ በወተት እያፈላህ ጠጣ
2. ለራስ ፍልጠት ከሉሚ ጋር አፍልቶ መጠጣት ነው። ትኩሱም ደረቅም ነው እንደዚሁ ሆዱን የነፋው ይጠጣ
3. ለኪንታሮት መደፍደፍ ነው። ሽንቱን ለከለከለው ከሉሚ ውኃ ጋር አጠጣው

## አሸርሻራ

ለጆሮ ደግፍ ቅጠሉን በጆሮ ጨምቀህ አድርግ
ለሣል ፍሬውን ቅጠሉን ደቁሶ በማር መዋጥ ነው።

## አባሎ /የደፋት ቅጠል/

ለማህጠንት ጥሩ ነው



Scanned by CamScanner

## አቢናግሬ

ልቡን ለታመመ ደረቱን ለዘጋው ወይም ለሚተፋ ቀቅሉ ከወው ጋር ይጠጣው ይብሰው። ለምጀር ለኪንታርት ቢያበረው ይፈውሳል።

## አብሽ

1. ሆዱን እያመመው ደም ለሚያስተምጠው አብሽ ዝንጅብል ነጭ ሽንኩርት በአንድ ላይ ወቅጦ በማርና በቅቤ አንጥር መጠጣት ነው።
2. አብሽ እርጥብና ትኩስ ነው ከቅቤ ጋር አንጥር ቢጠጡት ጂማትን ያፍታታል የውስጥ ገላን ያለመልማል ከሁሉም በቀልቱ የተሻለ ነው አብቅሉ መጠተም
3. ለግል ለሚገነባ በሽታ እንደቡና ቆልቶ በቅቤ መጠጣት ነው ወይም ከነጭ ሽንኩርት ጋር ወቅጦ በወተት አፍልቶ መጠጣት በማር ቢወስዱት ከውስጥ ያለን እበጥ ያጠፋል ነገር ግን ትርፍ አንጀት ላለበት ስለሚያሳድገው አብሽ አለመጠጣት ነው።
4. ራሱን ለታመመ ቀትሉ ወቅጦ በሰሊጥ ቅባት ለውሶ ራስን ደጋግሞ መቀባት ነው።



Scanned by CamScanner

5. እጅን ለሚያሳክከው ከሰናፍጭ ጋር አብሮ መጠጣት ነው።
6. ለሽንት ማጥ ለኩላሊት ለጣንባ ለአንጀት በባዶ ሆድ በማር አዘውትሮ መጠጣት ነው።
7. ለካልስትሮ ለደም ብዛትም ይሁን ማነስ የውስጥ ሲስተሙን ለማስተካከል ተልባና አብሽ ጥሬውን በባዶ ሆድ አንድ እፍኝ በውኃ መውሰድ ነው። እሄን ደጋግሞ ለወሰደ ጠሙን እየዋለ ውኃ ብቻ እስከ ግማሽ ቀን ለወሰደ ሙሉ ጤነኛ ይሆናል።

## አብሽ ቀይ ጥቁር ነጭ ቡላ ፍሬ ያለው እፀ ሲባርዮን

1. ሁሉም ያስከራሉ ያሳብዳሉ ከሁሉ ነጩ ኃይል አለው በድቡሽት በበረሃ በጅረት ላይ ይበቅላል ሰባቱን ፍሬ ገና ሲወለድ በአንቃር ለህፃን ማቅመስ በአርባው ቀን እንዲሁ መስጠት ለአእምሮ ጥሩ ነው።

አተር ?

## አቱች

1. አፉ ለቆሰለ ጉሮሮው ለታመመ ቅጠሉን በውኃ ቀቅሎ ውኃውን በአፉ ውስጥ አድርጉ ይጉመጥመጥ፡ ቅጠሉን በትኩሱ ከአንገቱ ላይ



Scanned by CamScanner

ደፍድፎ በሻሽ ማሰር ነው። ወይም የአቱች ቅጠልና የጥጥ ፍሬ ፍልቃ /አጥሚት/ ሙቅ ይጠጣበት።

2. ለጠነከረ የጉርሮ ደዌ የአቱች የሰለብያ የእንሰላል ቅጠላቸውን ከከርቤና ከእጣን ጋር በአንድ ላይ ደቁሶ ከአንገቱ ላይ ማሰር ወይም በአፉ ውስጥ እያቆየ መትፋት ነው።

3. ጆሮው አልሰማ ባለ የአቱችና የአንፋር ቅጠል በፍየል ቅቤ ለውሶ በፀሐይ ላይ ማድረግና የቀለጠውን አጥሉ በጆሮው ውስጥ ማድረግና ጥጥ መወተፍ ነው።

4. ጆሮው ለሚመግልበት የአቱች የእንባሮ የበለስ የአስተናግር ቀንበጣቸውን የወንዴ ቃሚ /ቢስቃ/ ጨቅጭ ሁሉንም በአንድ ላይ ደቁሶ ማድረቅ ለበሽተኛው በሻሽ አስሮ በውኃ እያረጠቡ ከጆሮው ማድረግ ነው።

5. የጥርስ ህመም ላለውና ለሚሸትበት የአቱች ቅጠል ከርቤና አልቴት ደቁሶ ከሚያመው ላይ ያድርግ።

6. ምላሱን ለታመመ ቅጠሉን ቀቅሉ ውኃውን በትኩሱ በአፉ ውስጥ አድርጉ መጉመጥመጥና

መትፋት ነው። ጆሮውን ለአመመው እንደዚሁ ቀቅሉ በጆሮው ማድረግና ጥጥ መወተፍ ነው።

7. እጁ ለሚንቀጠቀጥ ከእፀ ፈላፁት ጋር ቅጠላቸውን ወቅጦ በጣዝማ ማር ብዙ ቀን ማብላት ነው።

8. ለሣንባ ህመም የበሉት አልስማማ ካለ ቅጠሉን ቀቅሉ መጠጣት ነው።

9. ልብ ሲያጥወለውል ለትፋት ስሩን ማላመጥ ነው።

10. ለልብ ደዌ ስሩን ቅጠሉን ከሱፍ ጭልቃ ጋር በባዶ ሆድ ሲተኙ መጠጣት ነው።

11. ለልብ ድካም ሥሩን ከእንጭብር ከሁለገብ ስር ጋር ደቁሶ በማር ወይም በቅቤ አንጥሮ መጠጣት ነው።

12. ለተቅማጥ ለአንሜባ ከጅንጅብል ጋር ቅጠሉን ሥሩን ቀቅሉ መጠጣት ነው።

13. የበሉት ካልተስማማ ከሆድ ውስጥ ለሚቆይበት ቅጠሉን ከእንጆሪ ቅጠል ጋር ወቅጦ በሉሚ ውኃ በጥብጦ ከሚበሉት ጋር እየጨመሩ መብላት ነው።



Scanned by CamScanner

14. ለማንኛውም ለአፍ ሽታ ለሚቆስልበት ቅጠሉን ከከርቤና ከአልቴት ጋር ወቅጦ በድድ ውስጥ ማድረግ ነው።
15. ለሳንባ በሽታ የአቱች ቅጠል በሦስት ብርጭቆ ብርዝ ቀቅሎ አንድ ብርጭቆ ሲቀር አብርዶ አጥሎ መጠጣት ነው።

## አትኳር

ጆሮው ለደነቆረ የተቀጽላውን ቅጠል ከሰሊጉ ፍሬ ጋር ወቅጦ በሰሊጥ ዘይት አንጥሮ በጆሮው ማድረግ ነው።

አትንኩኝ፦ ሲነኩት የሚሰበሰብ

አትንኩት፦ ሲነኩት የሚሞጭጭና መርዘኛ

ባትነኩት፦ ወይም አስነኩት ሲነኩት የሚቀጠቀጥ ቅጠሉን የሚገለብጥ እንጨቶች አሉ። እነዚህ ሁሉ በአምልኮት የሚመኙትን ተናግረው ቢቆርጧቸው ለአሰቡት ነገር ይሆናል።

አኑር ?



Scanned by CamScanner

### እንተርፋ ወይም አይበደሙ አሚዳሞ

1. ለቂጥኝ ቅጠሉን ሥሩን ወቅጦ አንድ ማንካ በአጓት አጠጣ ማርከሻው ተልባ ነው።
2. ለሻህኝ ለእጢ ወተቱን ከአዞ አረግ ቅጠል ጋር አደባልቀህ ቀባው።

## እንዳሁላ

የእንዳሁላ አይነት ከአሥር በላይ ስለሚሆን እኙ የመሰለ ውኃ ስለሚወጣውና ቅጠሉ ሰፋ ብሎ ዝጉርጉር ስለሆነው እንዳሁላ ጥቅም አብነት እጽፋለሁ።

1. ለነቀርሣና ለአባሰንጋ ስሩን ቀንበጡን ደቁሶ በማር ለውሶ መዋጥና ግማሹን ከሚያመው ላይ ማሰር ነው።
2. ለችፌ ሥሩን ወቅጦ በቅቤ ለውሶ ቁስሉን ቀብቶ እሳት መሞቅ ነው።
3. ለእጢ ለእባጭ ሥሩን ወቅጦ አድርቆ እበጡን በጥቶ መደምደምና በቅጠሉ መተኮስ ማሰር ነው። የተበጣው እንዲድንና እንዳይተካ የሰመጎ ወይም የጉርጠብ ቅጠል ወይም የጃርት እሾህ አክስሎ መደምደም ነው።



Scanned by CamScanner

4. ለኪንታሮት ለእጢ ሥሩን የቤት ቀስት ስርና ቅጠል የቆርኪናት ቤትና የጃርት እሾህ አክስለህ የጭሜት እንቁላል ጨምረህ ሁሉንም በአንድ ላይ ወቅጠህ ደምድምበት።
5. ለራስ ህመም ቅጠሉን ከሬት ልጋግ ጋር ለውሶ እንጥሮ በአፍንጫው ማድረግ ነው።
6. ለጥርስ ህመም ሥሩን ማላመጥ ወይም ደቁሶ ከሚያመው ላይ መደምደም ነው።

## እንፉር

1. ለቁርጥማት ለማንኛውም በሽታ ቅርፍቱን እያፈሉ መጠጣት ነው።
2. እሩ ለሚገማ ቅጠሉን ቀቅሎ በማር መጠጣት ነው።
3. ፅንስ እንዳይወርድ ስሩን ቅርፍቱን ቅጠሉን መጠጣት
4. እሩ ለሚገማ ለቂጥኝ ቅርፍቱን ከከርቤ ጋር መውሰድ ነው

## እንቋ እንቃ

ለምች ቅጠሉን ወቅጦ በቅቤ ለውሶ መቀባት ነው።



Scanned by CamScanner

አንከርሟ ተ/

አንጓ ተ/

አንጣጢት ተ/

አንጣርይ ተ/

አክርማ እርጋሄ ተ/

አኮርሟ ተ

## አክማ ክማ

ለማህጠንት መልካም ነው

ለታመመ ለሚያስለው ቅጠሉን በማር በጥብጦ ማጠጣት ነው። እብድ ውሻ ለነከሰውም ይጠጣ

## አውጥ

1. ለጆሮ ደግፍ ቅጠሉን ከጨው ጋር ወቅጦ ማሰር ነው።
2. ለድድና ለትናጋ የአውጥ የእንጆሪ የአቱች ቅጠል የበለስ የሮማን የኲብ ቅርፍት ወቅጦ በአንድ ላይ ለውሶ መስጠት ነው።
3. ሴት እንዳትወልድ የአውጥ 7 ፍሬ የሰመግ 7 ፍሬ በማር ትዋጥ



Scanned by CamScanner

ከሐረር ቀሐረር ሸሐረር ሸሐረድ በኃይለ ዝንቱ አስማቲከ ከመይቅልፐ ወይትመሐው ዜው ከማሁ ይቅልፐ ወይሜሐው ማህፀና ለ/ 49 ድገም

**አደስ ፡ ብርስኖት**

1. ትኩሳት እየሆነ ለታመመ ቅጠሉን እንደሻይ አፍልቶ መጠጣት ነው።
2. አንጆቱ ወይም /ጆርባው/ አሬቡ የመቀመጫው ውስጡ ለሚመጣበት የአደስ ስር ደቁሶ በማር ማብላት ነው ወይም ሥሩን ማላመጥ ነው በወገቡ ይሰረው የፈውሰዋል።
3. ጠጉር ለማሳመርና ለማስረዘም ቅጠሉን ከሰለብያ ከልት ቅጠል ጋር ደቁሶ በቅቤ ወይም በሰሊጥ ቅባት ለውሶ መቀባትና በሻሽ ማሰር ነው።
4. ድማቱ ለታሰረ ሥሩን ከሰጉን እንቁላል ጋር ማብላት ነው ከዚያ ደጋግሞ የተልባ ሙቅ ውኃ መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

## አደንድን ሐረግ

የአደንድን ስሩ እንደሙት አንሣ ወይም እንደሰይጣን ሙቀጫ ወፍራም ይሆንና ሐረጉ ከዛፍ ወደዛፍ የሚሻገር ነው። የቅል ዋምራ የመሰለ ያንጠለጥላል።

1. የአደንድኑን ፍሬ ዋምራ የመሰለውን በእሳት እያሞቁ አፍረተ ሥጋን ቢያሞቁት ብዙ ቀን ያወፍረዋል ያስረዝመዋል።
2. ስሩን በብዙ ወቅጦ በነጭ ማር ለውሶ ለብዙ ቀን ቢያበሉት አፍረተ ሥጋው የደከመበት ይነሣለታል ጂማቱም ይፍታታል።

## አደንጓሬ

በረድ ደረቅ ነው ጥቁር ሐሞት ያበዛል ከቅቤ ጋር ቢበሉት ገላ ያሳምራል ለእከታ የንፍሮውን ውኃ መጠጣት ነው።

አደንዳሺ ?

አደይ

ቅጠሉን ወቅጦ አድርቆ ለማንኛውም ደዌ በቅቤ አንጥሮ በባዶ ሆድ መስጠት ነው ይፈውሳል ደዌን ይነቅላል።



Scanned by CamScanner

የአደይ አበባ በብዙ ለቅሞ በቅቤ ለውሶ በፀሐይ ማቅለጥ ነው ለማንኛውም ደዌ ቢአጠጡት ይፈወሳል።

አጀ ተ/

አዙሪት ተ/

አዛና ተ/

## አዛምር

1. ለነቀርሣ ለቂጥኝ የአዛምር የአንፋር የዘርጭ እንቧይ ሥራቸውን ወቅጦ ማሰርና በየሶስት ቀን እየፈቱ መድገምና ሲወጣ የቅንጭ ተቀጽላ ደቁሶ መደምደም ነው።
2. ለወስፋት ቅጠሉን ቀቅሉ በገንፎ ማብላትና አጓት ማጠጣት ነው።
3. ለደም ብዛት ቅጠሉን ስሩን ወቅጦ ማጠጣት ነው።
4. ለቂጥኝ ከጅንጅብል ጋር ቅርፍቱን በማር መዋጥ ነው።

አዝዋሪት እፀጽሉም እፀአዋዲ ?



Scanned by CamScanner

## አዝዋሪት አዙር አዙሪት አሸሺ

/ሸዋሺውይት ነፋስ/ ሸውሻውይት አደናገር ጆብር የሚባል ስም አሉት ሲነኩዋቸው አእምሮ የሚያስረሱና የሚያፈዙ እፅዋቶች ብዙ አይነቶች ናቸው። ነገር ግን ከነዚህ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ በሰጣት የተፈጥሮ ባህሪይ ጥበብ የምታገለግለውን እፅ እፅፋለሁ። ከእነርሱም አንዷ ባለሐረግ ስትሆን ሁለተኛዋ ግን ድቃቃ ቅጠል ያላት ሁና ከሥርዋ ድንች የመሰለ እንደእንዝርት ክብ ሁና አዝዋሪት የአለው ነው።

መጀመሪያ በእፀእስክንድር /ወንዶው ምስርች/ ለበቅእኔ ቀደምኩሽ ሳትቀድሚኝ ብለህ ንካት ከዚያ በፈለከው ነገር ለዚህ ሁኘኝ ብለህ ነጭ ቂብ ዶሮ አርደህ ቁረጥ ከቆረጥክበት ቦታ ዶሮውን ቀብረህ ሥሩን ይዘህ ሂድ።

1. ለመፍዝዝ በጥቁር ዶሮ ቆርጠህ ስሩዋን ያዝ
2. ለገንዘብ ከሣጥን ውስጥ ማስቀመጥ
3. ለገበያ ከገቢያ መሃል ቀብር ገበያው ሲሞቅ አውጥቶ ከሚሸጡበት ማስቀመጥ
4. ለመሰውር ከጥቁር ድመት አንግሰህ ቆርጠህ በግራ ጉንህ ያዝ
5. ለእጣ አርብ ቀን ነቅለህ ከእጣን ጋር አጥነህ ያዝ



Scanned by CamScanner

6. ለመስተባርር እገሌን የእገሌን ልጅ ከዚህ አገር ነቅለህ አብረው ብለህ ነቅለህ በጥቁር ድንጋይ ወቅጠህ በጥቁር ዶሮ ጉበት ነስንሰህ ለጥቁር አሞራ ስጥ

7. ለመንድግ ለምህማዘ ንዋይ የገበሎና የእስስት እራስ ጊንጥ እንዳለች የእፀልባዊት የእሺኮክ ጐመን የአዝዋሪት /አዙሪት/ ስር በጥቁር ዶሮ ደም ለውሶ አድርቆ በጥቁር ፍየል ቆዳ ቦርሣ አሰፍቶ በውስጡ አድርጐ መያዝ።

8. ለግርማ ሞገስ "ሜኤል አላልኤል" 99 ጊዜ ደግመህ ለዚህ ነገር ሁነኝ ብለህ ቁረጥና ከቀጠጥና ከእፀአንበሳ ስር ጋር ደቁሰህ ግማሹን በነጭ ማር ብላ፡ ግማሹን በነጭ ዶሮ ደም ለውሰህ ያዝ።

9. ለተመኘው ሻኤል 3 ሸማልዳ 3 አሻማሺል ዘፈ በስርዋ ደግሞ ቀጥቅጦ በውኃ ዘፍዝፎ ፊትን ታጥቦ መሄድ ነው።

10. ገንዘብ ለማግኘት "አጂማን 99፡ አጁማን 49 አላጁማን 51" ጊዜ በዐደል ቀበሮ ብራና ጽፎ በማጥን ከሥርዋ ጋር ማስቀመጥ ነው።



Scanned by CamScanner

11. ለመፍትሔ ሐብት ለሲሳይ የገዴ እንቁላል ወይም ልብና ጥፍሩዋን ሥርዋን በጥጥፍሬና ጥጥ ሸፍነህ በበላዩ በወርቀ ዘቦ ገምጃ ጠምጥመህ ያዝ።
12. ለመስተፋቅር የጉርጉሮ ተቀጽላ የከልብ አፈማህፀን ከሥርዋ ጋር ደቁሶ ለሴት ከጭንዋ ለወንድ ከክንዱ መቅበር ነው።
13. ለምሕሣበ ንዋይ የጭላት ወይም የጭልፊት ልብ የእፀ ልባዊና የአዝዋሪት ሥር የወርቅ የብር ሙራጂ ጋር ከኪስ ወይም ከሣጥን ውስጥ ማስቀመጥ ነው።

አዝዋሪት ከዚህ በላይ ለተጻፉትና ያልተጻፉ ሰባአ ገቢሮችን ለመስራት መጀመሪያ ከሥርዋ ጠባቂ መልአክ ጋር መለማመድና መዋረስ ማለት መወሐድ የአስፈልጋል እሄም ማለት የተለያዩ ጢሶች እጣን ከርቤ ሉባንጃ እያጤሱ የኑግ የቆሎ ዓይነት የመጠጥ አይነት አቅርቦ ማርና ወተት ከሥርዋ አፍስሶ አንቺ እፅ በተጠጉሽ በሚጠብቁሽ በፈጠረሽ አምላክ ይሁንብሽ ፈቃዴን ፈጽሚልኝ እየተባለ ወይም የእፅ መላክ የእፅ ንጉሥ ምስህ ግብርህ እኄውልህ ለእኔም በዚህ እንጨት ስም ጉዳዬን ፈጽምልኝ አድርግልኝ እየተባለ ደጋግሞ መቁረጥና ለተባለው ነገር መሞከር ነው በአንድ ግዜ



Scanned by CamScanner

በአንድ ቀን ገበሬ እሆናለሁ ወይም በአንድ ቀን የመምህርን የዶክተርን ሞያ አውቄ አደርጋለሁ ማለት እስከአልተቻለ ድረስ ለእፅም በአንድ ቀን ለምን አልሰራም ብሎ ተስፋ መቁረጥ የለም። መስማመድ ወይም ለፈለጉት ነገር ለዚህ ሁነኝ ብሎ መቁረጥ ነው ለከፋም ለደግም ይሆናል።

14. ለምሕሳበ ንዋይ የጠላህ ሰው እንዳያይህ ሥሩን ከሬት ተቀጽላ ጋር በጥቁር ውርንጭላ አህያ በግራ ጆሮ ደም ለውሶ በግራ ኪስ መያዝ ነው።
15. ለእቃቤ ህግ ሥሩን በእሣ ሐሞት ለውሰህ ቀብተህ አውስብ

## እጋም (Chery) ቼሪ

1. ለቁስል ስሩን ከጕርጠብና ከዘርጭ እንቧይ ቅጠል ጋር ወቅጦ መደምደም ነው።
2. የአጋም ፍሬ የአልበሰለውን በብዙ ለቅሞ እንደ ሙዝ አሽጉ ሲበስል አድርቆ ለጠላ ለአረቄ ለተለያዩ ምግቦች ይሆናል።

## አዞ አረግ /ጥቁር አዞአረግ/

አዞአረግ ሴቴና ወንዴ ተብሉ የሚጠራ ሲሆን ሴቴው ቅጠሉ በጣም የለመለመና ለስላሳ የሆነ ወንዴው ቅጠሉ ከርደድ ያለ ነው። ከሴቴው የወንዴው ቅጠል ኃይል አለው ጥቁር አዞ አረግ አለ።

1. ለሻህኝ ለቁስል ለላሽ በሎሚ ውኃ ቁስሉን አጥቦ የቁስሉን ዙሪያ የማር ወለላ ቀብቶ በቁስሉ ላይ የአዞ አረጉን ቅጠል ወቅጦ የደረቀውን መደምደም ነው። በበላዩ የስንዴ ሊጥ ደፍድፎ በሻሽ ለሶስት ቀን ማሰር በሶስተኛው ቀን መፍታት ነው ሁሉ ከአልወጣ መድገም ወይም የጉርጠብ ቅጠል መደምደም ነው።
2. ለሻህኝ ለቁንጭር ለአኸያ ኪንታሮት ለጉርሚጥ የቆላ ቁስል ለናፍጭና እንከርዳድ ወቅጦ በአዞ አረግ ቅጠል ውኃ ለውሶ መደምደምና ማሰር ነው።
3. አልመገል ላለ እበጥ ወይም ለሚነዘንዝ ቁስል ቅጠሉን ከእንስላል ቅጠልና ከከርቤ ጋር ደምድሞ ማሰር ነው።
4. ለኪንታሮት ቅጠሉን ከሰባት ላይ ሸምጦ አድርቆና ወቅጦ በትንጭብ ደም ለውሶ ከቁስሉ ላይ



Scanned by CamScanner

መደምደም ወይም በመቀመጫው በማር ለውስ ማድረግ ነው። ወይም ከአጋምና ከቀጠጥና ስር ጋር ወቅጦ በቁልቋል ደም አቡክቶ ማሰር ነው። ሌላውን ገላ እንዳይነካው አስቀድሞ ማር መቀባት ነው።

5. ለልብ ደዌ በንዳድ ለተነሣ ደረቅ ሣል ቅጠሉን ወቅጦ ከበግ ሣንባ ውስጥ አስገብቶ መንፋትና መጥበስ ነው ሣንባውን በትኩሱ መብላትና መዋል ነው። እንዲሁም በቅቤ አንጥሮ ከነጭ ሽንኩርት በወተት እያፈሉ መጠጣት ነው።
6. ለላሽ ቅጠሉን ከትንባሆ ቅጠል ጋር ወቅጦ መቀባት ነው።
7. ለውጋት የጥቁሩን አዞ አረግ ሥር ከሚያመው ላይ መቅበር

ነጋም

1. ዓይኑ ለቀላ ቀንበጡን አሽቶ መቀባት ነው።
2. ለቁስል ሥሩን ወቅጦ ነስንሶ ማሰር ነው።



Scanned by CamScanner

## አጥግብ

በረሀብ ዘመን የሚበላ የስኳር ድንች የመሰለ ከስር ወፍራም ሆኖ የአደንጓሬ አረግ ቅጠል የመሰለ ነው። ለኩላሊት ቢበሉት ያጥባል ሽንት ሽንት ይላል

አጣጥ ?

## አፈጉማ

ለሣንባ ነቀርሣ፡- የአፈጉማ የድግጣ የምሳና የሮማን ቅርፍታቸውን ሥራቸውን ከጅንጅብል ጋር ወቅጦ በማር ለውሶ በባዶ ሆድ መብላት ነው።

እንሰት /ጉናጉና/ ?

## እናዝ ፡ ናዝ

1. ለተቅማጥ ከውተት ጋር ቀቅሎ መጠጣት ነው።

እሴቶ ተልባ መስላ ከጤፍ ጋር የምትበቅል ?



Scanned by CamScanner

## እንስላል ፡ ሲላን

1. ሽንቱን ለከለከለው ከቲማቲም ቅጠል ጋር ቀቅሎ ውኃውን መጠጣት ቅቅሉን በትኩሱ ከብልቱ ላይ አድርጎ ማሰር ነው።
2. ዓይኑ ለፈዘዘና ለኩላሊት በሽታ የእንስላል ፍሬ ከእንጀራ ጋር አስጋግሮ መብላት ነው ቅጠሉን ቀቅሎ እንደሻይ መጠጣት ነው።
3. ለሣል ቀንበጡን በቅቤ አንጥሮ ማጠጣት ነው።
4. ጡትዋ ላበጠባት እንደዚሁ ቀቅሎ ማጠጣት ነው።
5. ሆዱ ለነፋውና ሽንቱ ለከለከለው ብልቱን ለሚያመው ከጦስኝ ጋር ቀቅሎ መጠጣት ነው።

## እንቧይ

የእንቧይ ዘር ዓይነት ብዙ ነው ከነዚህም የምድር እንቧይ ዘርጭ እንቧይ ገበር እንቧይ እየተባሉ ስማቸው ይጠራል አሁን ስለ አንዱ እንቧይ ብቻ እድፋለሁ ለርሱም የቆላ እንቧይ ስለሚባለው ብቻ

1. እጢ ለማጥፋት ከቅጠሉ ላይ እጢ መስሉ የወጣን ቅጠል ቀርጦ በእሱ እጢውን ደጋግሞ ማሸት ወይም መተኮስ ነው ወይም ደቁሶ በበላዩ ደምድሞ ማሰር ነው።



Scanned by CamScanner

## እንቡስ እንብስ ?

### እንኮይ - ኮል

1. ለኪንታሮት ቅርፍቱን ከዋንዛ ልጥ ጋር አከስሉ በቁስሉ ላይ ደምድሞ ማሰር ነው።
2. ለሣንባ ቅርፍቱን ወቅጦ በማር አንጥሮ በባዶ ሆድ መውሰድ ነው።
3. ለሸንተ ማጥ ሜዳ ለከለከለው ቅጠሉን ወቅጦ ጨምቆ መጠጣት ነው።
4. ጠጉር ለማሳደግ ለቆዳ ድርቀት ፍሬውን ወቅጦ ከሰለብያ ቅጠል ጋር መቀባት ነው።

### ..ነባጮ ፡ ሲርብ

እሴቴም ወንዴም አለው ቅጠሉ ድቃቃ ወንዴው ሲሆን እሴቴው ቅጠሉ ሰፋ ያለ ነው።

1. ዓይኑ ለቀላና ለታመመ ቅጠሉን ወቅጦ በሻሽ አጥሉ ከዓይን ላይ ማድረግ ነው።
2. ለአኽያ ኪንታሮት ቅጠሉን ወቅጦ በጥፍርንዶ ደም ለውሶ በማር መቀባት ነው።



Scanned by CamScanner

3. ገንዘብ ከእጁ አልቆምም ላለ ተቀጽላውን በትከል ድንጋይ ደቁሶ ከግም አረግ /ግሚአረግ/ ስር ጋር ዘፍዝፎ ማጠብ ከተቀጽላው እንዲደርቅ ማድረግ ነው።
4. ሐሞት ለሚተፋ ለጋውን ከጨው ጋር ወቅጦ ማጠጣት ነው።

## እንጉዳይ

የእንጉዳይ ዓይነት ከአሥር በላይ ነው ሁናም በአርባጫ መሬትና የእንጨት ፍግ ስለሚበቅለው እጽፋለሁ፡ ከእንጉዳይ ዘር መርዘኞች ተባይን የሚገድሉ የሚያስከሩ ሲናሩ አንዳአንዶች ደግሞ ለምግብ ለወጥ ለሾርባ ሙቅ የሚሆኑ አሉ።

መርዘኛው እንጉዳይ መልኩ ይቀላና ደንበሩ እንደ አረንጓዴ ብጫ ይሆናል። ትል የወጋው የሚመስልና ነጫጭ ነገሮች በበላዩ ይታያሉ ወይም እከክ ቁስል መስለው ይታያሉ። እነዚህ የአለበትን እንጉዳይ የበላ ወዲያውኑ ይሞታል ወይም አእምሮውን አጥቶ ለብዙ ግዜ ይቆያል። ተልባ ወይም ወተት መስጠት ነው።

ለምግብ የሚሆነው እንጉዳይ ለስላሣና ንጹህ መልክ ይዞ ይታያል።



Scanned by CamScanner

እንጉርጉ ?

እንቆቆ ?

## እራስ ክምር

ትንሽዋ የፈረስ ዘንግ የመሰለች ፡ ለምች ለራስ ምታት መታጠን ነው።

## እንብጭሊት

ለትምህርት ከሰባት ቦታ ስሩዋን ወቅጠህ በነጭ ማር አውጥ

## እንዘረዘይ አሴቴው

የእንዘረዘይ ዘር ዓይነት ሶስት ሲሆኑ ከሦስቱ አንዱን ለተለያየ ነገር የሚሆነውን እጽፋለሁ። ከገደል አፋፍ የሚበቅለው በአለቱ ተጠግቶ ዘንግ የመሰለ ስር አለው የእርሱም ከአርባ በላይ የሚሆን የተደራረበ ክብ ነገር አሉት።

1. ለኪንታሮት ለነቀርሣ ለቆዳ ደዌ ከሰባት አመት በላይ ማለት ከሰባት ክርክር በላይ የአለውን የእንዘረዘይ ስር ደቁሶ ከርቤና ዲኝ አልቴት ጨምር በጥፍርንዶ ወይም በቀቦ /ጦቢያ/ ወይም



Scanned by CamScanner

በትንጭብ ደም ለውሶ ከቁሱፍ ላይ መደምደምና ማሰር ነው።

2. ለኪንታርት ስሩን ቅጠሉን ወቅጦ በማር ለውሶ መቀባትና በየጊዜው በሽንት ውኃው ይታጠብ።

3. ለምኺር ለነቀርሣ ለኪንታርት የእንዝረዘይ የምሳና የዶግ ሥራቸውን በአንት ዘፍዝፎ ማጠጣት ነው። ያስታውካል አለማብዛት ነው ማርከሻው የዶሮ ጉበት ወይም ተልባ አቦል ቡና መጠጣት ነው።

4. ለቁርጥማት የእንዝረዘይ የአሚራ የቀበርቾ የመቅመቆ [illegible] መልክ አዘጋጅቶ መጠጣት ነው።

5. ለማጅራት ገትር የኖረውን ስር ማላመጥና እትፍ እያሉ አንገትን ማሸት ነው።

6. መቀመጫው ለወጣበት ስሩን ወቅጦ በቅቤ መቀባት ነው።

7. የእንዝረዘይ ስሩ አዲሱ ነጭ መልክ በማር ቢወስዱት ከውስጥ ያለን ደዌ ያወጣል በጣም ያስታውካል ብጫና አረንጓዴ የሆነው ለላይ ቁስል እንጂ ለሆድ አይሆንም አደጋ ያደርሣል።

ቀይ ደምና ነጭ አረንጓዴ የመሰለው ለሚረሣ ለትምህርት ይሆናል። ሥራይም ነቅሎ ይጥላል።



Scanned by CamScanner

ሕይወትን ያድናል ደምን ያስተካክላል ነገር ግን በውስጡ የሚገድልና የሚያድን ስላለው ጥናት መውሰድ ያስፈልጋል።

## እንዘረዘይ ወንዶው

ከሴቴው እንዘረዘይ የሚለይበት በጭንጫ ቦታ በሜዳ ስለሚገኝና በየአመቱ አንድ ስር ብቻ እየሆነ የአለፈው አመት ስሩ ስለሚነግል ነው። ስለዚህ ለቁስል ደዌ ብቻ መስጠት እንጂ ጥናት ሳያደርጉ ቢወስዱት የውስጥ ሲስተምን ያናጋዋል። የልብ ድካም የጨጓራ ህመም ያጋጥመዋል መጠንቀቁ የተሻለ ነው።

## እንጉቺት

1. ለቁርባ ስሩን ማላመጥ ነው።

## እንዶድ

መካን እንዶድና እሴቴ እንዶድ አለ

1. ለቁርባ የመካን እንዶድ ስር ወይም ቀንበጥ ጉማሽ ማንካ መጠጣት ነው።
2. ለእከክ የእንዶድና የጌሾ ፍሬ ወቅጦ በትቤ መቀባትና ፀሐይ ወይም እሳት መሞቅ ነው።



Scanned by CamScanner

3. ለአባ ሰንጋ የመከን እንዶድ ቀንበጥ ደቁሶ እንደ ማንካ መስጠት ነው ከደከመ ተልባ ማጠጣት ነው።

## እንጆርይ

1. አፉ ለቆሰለ ሆዱ ለታመመ ቅጠሉን ማላመጥና መዋጥ ነው።
2. ለሆድ እመም ለትኩሳት ቅጠሉን ከዳማከሴና ከአረግ ሬሣ ቅጠል ጋር ወቅጦ አፍልቶ እንደሻይ መጠጣት ነው።
3. ሆዱ ለተነፋና የበላው ለሚቆይበት ቅጠሉን ከሚበላው ከሚጠጣው ጨምሮ መስጠት ነው።
4. ጆርባው ላመመው ቅጠሉን ከጦስኝና ከአቱች ቅጠል ጋር በቅቤ አንጥሮ ማብላት ወይም ማጠጣት ነው። ወይም ከሚያመው ላይ መደፍደፍ ነው።

## እጣን /እፀሰንድሮስ/

1. ሣል ለያዘው ከወተትና ከነጭ ሽንኩርት ጋር አፍልቶ ቢጠጡት ይፈውሣል።



Scanned by CamScanner

እፀአንግሥ

አዝጨ አዝቅአን አለራሀ መክኑን ከንትራዝም ቤተለዝ አንተ ውእቱ እፅ ቡሩክ እፀሕይወት ወእፀ መድኃኒት ሀየንተ እፀሕይወት ዘውስተ ገነት ከማሁ እፀሕይወት ወእፀመድኃኒት እፀ መፍዝዝ ወእፀግርማ ሞገስ እፀመፍትሔ ሐብት ወመፍትሔ ሥራይ እፀ መስተፋቅር ወምሕሳበ ንዋይ በዛቲ እፅ እ----- እንግሣ ወቀድሣ ለዛቲ እፅ ከመትፈጽም ፈቃደ ልብየ በአፈ እገሌ ------

እንጭብር

1. ለምርዋፅ ሥሩን ከአሩጥ ስር ጋር ወቅጦ በሠመሬታ ገብስ ዳቦ ቆሉ አድርጉ እየበሉ መሮጥ መሄድ ነው።
2. ለሣል እየቀቀሉ ጧትና ማታ መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

## ፈውስ



## እፅብሩክ ይእቲ እፀሕይወት ዘውስተ ገነት
## ወዕፀመድኃኒት በዲበ ምድር
## በግእዝና በአማርኛ የእጽዋት ስም ዝርዝር ገቢር

| በግእዝ | በአማርኛ | ገቢር |
|---|---|---|
| ሀ-ሐ-ኀ ፩-፫-፭ | | |
| እፀሣሌሱያ | መንቶች | ለፍቅር |
| እፀሀሉ | ከድንጋይ ላይ የሚበቅል | ለመአቅብ |
| እፀሐመር | ሶስት ማእዘን ያለው | |
| እፀ ሐዋርያ | ቆንጥር | ለፍጥነት |
| እፀሣሊላ፡ ሄላ | ሚዳቋያ | |
| እፀሀረገሕይወት | የበርሃው አሰርኩሽ | ለፍቅር ለማእሰር |
| እፀሐዊ ማህያ | ሹንሹና ሐያ | |
| እፀሕልው | ማቱማሳ/እንደማቱሳ/ | |
| እፀሀሊና አጸሂሶጵ | ጉፍጪጭ /የሳሙና እንጩት/ | |
| እፀሕርማኤል፡ ከርሚል | ችፍርግ | ለፍቅር |
| እፀሕይወት | ጂልዋት | ለተሐድሶ |
| እፀሕሪና | አርና | ሆድን ለማጽዳት |

| | | |
|---|---|---|
| እፀሆል | ሁለገብ | ለድንገተኛ |
| እፀሆህት | በዋሻ ውስጥ የሚገኝ ሃረግ | ለሐብት |
| እፀሆሣእና | የዘንባባ ዘር ስሌን | ለመጽንኤ |
| እፀሆርሣ | ድርቪት ታርይገማ | ለብዙ ነገር |
| እፀሆማ | ጥቁርዛፍ | ለጽናት |
| ሆምሔም፡ ሐምሐም | ቅል | |

ለ ፪

| | | |
|---|---|---|
| እፀለባዊ /ገፀሱብእ/ | የሰው አካልምስል ሴቴናወንዴ | ለፍቃድ |
| እፀለባዊት | በሽናሻ እምነት ደንዝ | ለብዙ ነገር |
| እፀፀሐይ/ ለት | ልት | ለማለስለስ |
| እፀ ልባዊ | ነጭ ብሉ ወርቅና ብር የመሰለ | ለመቀያየር |
| እፀልብ | የልብቅርፅ ያለባትየሴት ልብ/ | ለመስተፋቅር |
| እፀልቡና | ተልባ የመሰለች | ለመፍትሔ |
| እፀልባ | ቅጠልዋና አበባዋ የልብቅርፅ ያላት | ለፍቅር |
| እፀልቡ | የወይን ቅጠል የመሰለ የአለው ልቡን | ለነሣው |
| እፀልቡሰብእ | እንደ እንሰት ደም የሚፈሣት | |
| እፀልቦት | ትንሽዋ ሟጠሽ | ለዝቢያ |
| እፀ ልጉት | አዝዋሪት | ለብዙ ነገር |
| እፀልህም እፀላህም | የጥጃ ጨንገር | ለመፍትሔ |
| እፀሉልያ | ቅጠሉ ብርና ወርቅ የመሰለ | ለሐብት |
| እፀሉል | ሉል | ለሥራይ |
| እፀሉልና | ኀሉዛፍ | ለሆድ ደዌ |
| እፀሉምዝ | ሙዝ | ለደረት ለችፌ |



Scanned by CamScanner

| | | |
|---|---|---|
| እፀሉዛን | የሽቶ ተክል | |
| ፬ እፀመስውር | ከፈላ ጋር የሚገኝ ድታት እፅ | ለመስውር |
| እፀመስቀል | ከበባዋ ቅጠልዋ መስቀለኛ | ለአእምሮ |
| እፀመሶብ | አበባዋ መሶበወርቅ የመሰለች | ለሀብት |
| እፀመሐሪ መሪር | ሬት | ለሁሉ ለቁዳ |
| እፀ መቅር | መቅር የጣንዣፍ | |
| እፀ መና | እንጉቾት የመሰለ | ለተሐድሶ |
| እፀ መናሂ | መናሂ | ለመፍትሔ |
| እፀ ሙሴ | በትረ ሙሴ | ለሐብት |
| እፀ መዶኬ | አመድማዶ | |
| እፀማርያም | ማርየ ፍሬው ባፋጭ | ለቀለም |
| እፀመንድግ | ሚጠሺ | ለገብያ |
| እፀመክሱት | ጢብጢቦ | ለመክሰት |
| እፀ መንደንግፅ | የሰውገፅ ሥሩ የመሰለ | |
| እፀ መአዛ | አበባው ባለመአዛ | ለመአዛ |
| እፀ መአዝ | ስሩ ከብ_ | ለትምህርት |
| እፀ መንስኤ | ሙትአንሣ | ለተሐድሶ |
| እፀ መፍርሀ | ፍየለፈጂ | ለመፍትሔ ሰቃቤ |
| እፀ ማእዜ | ማቱሣላ እንደማቱሣላ | ለእድሜ |
| እፀ ምስያጥ | ቀበርቾ | ለማህጠንት |
| እፀምናሂና | ሂና | ለቀለም |
| ሠ፫ እፀሰለሞን ሰጢን | ጠነጉ የግራር ዓይነት | ለሚሮን |
| እፀሴሐብ | የላምጡት | ለጉልበት መጽንኤ |

እፀሰብዕ፡ ሰኪኖን ለወንዶው የወንድ ለሴቴው የሴት ብልት ያለው/ለፈለጉት የሚሆን/

| | | |
|---|---|---|
| እፀሰላቢላ | የጅንጀሮ እመጫት | ለወገብ መድኃኔ |
| እፀሰረገላ | ከዛፍ ወደዛፍ የሚሻገር ሃረግ | ለመድኃኔ ለሁሉ |
| እፀ ሰገም | ገብስ | |
| እፀሱብእብ | ከምችች ያለ የችፍርግ አይነት | ለስብስብ |
| እፀሰማይ፣ ሰንተው | እንደዋርካ ከዛፍ ላይ የሚበቅል ለራእይ | ለመአዛ |
| እፀሰቅል | የተመሳቀለ ስርና ድንች | ለዝናብ |
| እፀሰናይ ፡ ሰንበልት | ጥሩ መአዛ ያለው ዛፍ | ለመፍትሔ |
| እፀሲኦል | በረገረግ የምትበቅል | ለቁስል |
| እፀሲና | ዛና ዋሽንቶ ዋሽንት ለውኃ | ጥም ለመንድግ |
| እፀሲባርዮስ | ቀዩ አብሽ | ለመክስት ለማስከር |
| እፀሰንድርስ | የእጣን ዛፍ | ለመአዛ |
| እፀሲናር | እንክርዳድ | ለስካር ለቁስል |
| እፀሲናሬ ሰናር | እንግዶ እህል | ለምግብ |
| እፀ ሲላን | እንስላል | |
| እፀሳቤቅ | የአረገሬሣ | ለምች ለመፍትሔ |
| እፀሳዶቅ | ባንባ ወይም ባቡሴዳ | ለወይንጠጅ |
| እፀ ሲርብ | እንባጮ | |
| እፀሥጋ | የድንች ስር መሰሉ የቀላ | ለደም ጥራት |
| እፀ ሰገው | ፍሬው ሰውነት የሚያድስ | ለተሐድሶ |
| እፀሰርው | የአደንድን ዘር ሙታአንሣ | ለመድኃኔ |
| እፀሰብሐት | ዳቦ የመሰለ ክብስር ያለው | ለሐብት |
| እፀሶላ | የሾላ ዛፍ አይነት | ለወይን |
| እፀሶባ | ችብሃ ጥሉሣ | ለተሐድሶ |



Scanned by CamScanner

| | | |
|---|---|---|
| እፀ ሶማ | ሱማያ ስሩ ሰሃ | |
| ሬ-ጀ እፀረሃ | እሴቴው ሬት | ለልብ ለቆዳ |
| እፀረሴ | ከሥሩ ወፍ እንቁላል የምትጥልበት | ለመከን |
| እፀረጥይ | ቀንጣፋ የመሰለ | ለአእምሮ |
| እፀ ረደሰናርደስ | ቀረፋ | ለመፍትሄ ለትመም |
| እፀሩፋኤል | ቅጠሉ ሲነኩት የሚጣበጥ | ለብዙ ነገር |
| እፀ ሩት | አርቴ | ለመአዛ |
| እፀረታ | እሴቴሬት | ለብዙ ነገር |
| እፀሪሃ | ሰርቲ | ለመቀመም |
| እፀረማጄ | ግራምጣ | |
| እፀሬምናን | ደግ | ለመፍትሔ |
| እፀሬኅን | የባብጋል የመሰለ | ለመፍትሔ |
| እፀሬጄል | ጄልምልምዛፍ | ለእንክስ ርቢ |
| እፀርትሐት | መታገሚን የመሰለ | ለመንስኤ |
| እፀ ርቱእ | ዛፍ የመሰለ ዛፍ | ለመጸንኤ |
| እፀ ርግብ ፡ እሰካርን | አረግ የሆነ | የሽቶ ዛፍ |
| እፀ ሮማን | ሮማን | ለቁስል ለፍትር |
| እፀ ሮሚል | አዝዋሪት አረግ | ለመፍዝዝ |
| እፀ ርያል | አሩጥ መሰላ አረግ | ለምርጥዐ |
| እፀ ርዝ | ርዝመሪ | ለቅመም |
| እፀ ርዘይ | እንዘረዘይ | ለቁስል ደዌ |
| ቀ-፭ እፀ ቀላይ | ወንዝ አድምቅ | ለሐብት |
| እፀቀለሚንጦስ | ባህርዛፍ | ለምች ለጉንፋን |
| እፀቀታሌ | በራሪውን ሁሉ በቅጠልዋ አሽጋ የምትገድል | |
| እፀቀናና | የዳማከሴ ዘር | ለሽታ ለሱባኤ |



Scanned by CamScanner

| | | |
|---|---|---|
| እፀቃሬጣ | ቃሬጣ የግራር ዓይነት | ለከሣ ፍሬው |
| እፀቀቀር | ቀርቀሐ | |
| እፀ ቋውንቄ | ዋንዛ | |
| እፀቀመር | የጣን ዛፍ | ለመአዛ |
| እፀቀኑትቀንሞስ | ቀናንሞስ ከዛፍ ላይ የሚጠመጠም ሐረግ | ለፍትር |
| እፀ ቆጋ | ቆጋ | |
| እፀ ቆበር | እሳት የማይበላው ዛፍ | ለእካት ከላ |
| እፀቆለቆል | ቆለቆልዳ | ለከፉ ቁስል |
| እፀቆጽለገሄ | የሽኮኮ ጉመን አበዛንጣ | ለመፍትሔ ሐብት |
| በ፱ እፀበትረወርቅ | ቅንቦ | ለቁስል ደዌ |
| እፀ በለስ | በለስ | ለቁስል ደዌ |
| እፀ በትረ ዝሂብ | የጅብ ምርኩዝ | |
| እፀበኩር | ሰንበታይ | ለኩላሊት |
| እፀበትረቅዱሳን | በትረሙሴ መስላ የተቀለመች | ለተሐድሶ |
| እፀበሊድ | ጭቁኝ የመሰለ | ለዓይነስብእ |
| እፀበሃ | የቼብሃ ዘር ዓይነት ከድንጋይ | ለተሐድሶ |
| እፀቡሄ | አሽንድየ | ለመጽንኤ |
| እፀቡና | ቡና | ቅጠሉ ለደምጥራት |
| እፀባሀር | ከበሃር ላይ ተንሳፎ የሚበቅል | ቅጠለ ሰፊ |
| እፀባርከ | ከበትረሙሴ ተጠግታ የምትበቅል | ለቀሰም |
| እፀብርሃን | አንቃ መስሉ ፍልጡ የሚያበራ | |
| እፀብርሂት | ቅጠልዋ የሚያበራ ትንሽ አረም | |
| እፀ ብዙህ | ስረብዙ | ለመፍትሄ |
| እፀ ቤርዜል | | ለዘኢያገድፍ |
| እፀ ብሩት | ቅጠሉ ሌሊት የሚበራ ዛፍ | ለሆድ ደዌ |



Scanned by CamScanner

| | | |
|---|---|---|
| አፀበለድ | ጭቁኝ | ለአንጉል ኑቀርጫ |
| ተ· ፲ አፀ ተከዜ | ፎልምልም ዛፍ | ለእኸሳ ርቢ |
| አፀ ተድላ | | ለሐብት |
| አፀ ተሐድሶ | የጂልዋት ዓይነት | ለተሐድሶ |
| አፀ ቱት | አልቴት | ለምች ለመፍትሔ |
| አፀ ቴማን/አፀበለድ/ | ጭቁኝ | ለመፍትሔ |
| አፀ ቴሰቢ | ዘርጭ እንቧይ | ለዘኢያዉርድ |
| አፀ ቴክ | የሚያደነዝዝ | ለእንቅልፍ |
| አፀ ታይካ | ትል የመሰለ የሚጥል ትልገሐረግ | ለመጽንኤ |
| አፀ ታቦር | አሸንድየ | ለመፍትሔ ሥራይ |
| አፀ ቶማይ | ታርይጥግ | ለመፍትሔ ለማእሰሪ |
| አፀ ቶማይስ | አለብላቢት | ለፍትወት ለፍቅር |
| አፀ ቶዶ | የምድር ቅንጭብ የመሰለ | ለመእዛ |

| | | |
|---|---|---|
| ኑ - ፴ አፀ ነበልባል | ነበልባል | ለእሳተከላ |
| አፀነቢያት | ኍበዝ ጠቀስ | ለፍቅር ለትምህርት |
| አፀ ነዶ | | |
| አፀ ነዌ | ጠጠርማ ዛፍ | ለምትሐት |
| አፀ ኑብያ | ከምድረ በዳ የሚገኝ ድንች የሆነ ስሩ | ለጥም |
| አፀ ኑዝ | | |
| አፀ ኑማር | ንብ የሚወደው | ለቀፎ |
| አፀ ኑሜር | ንብ ጥራ | ለቀፎ |
| አፀኑር | አኑር የምድር ቁልቋል የመሰለ | ለመቅጠን |
| አፀኑመት | የደጋ ዉቄ የሚገኝ | የሚያንቀላፋ |
| አፀ ኑዋ ተ/ | | |



Scanned by CamScanner

| | | |
|---|---|---|
| እፀኤሃ | ናና | |
| እፀ ናርዶስ | የሽቶ ተክል | ለቅመም |
| እፀናስር | በቶ | |
| እፀንስር | የቁራ አረግ | ለውስጥ ደዌ |
| እፀንህብ | ገተም | |
| እፀናሆም | ጉርጠብ | ለተላላፊ ቁስል ለቁስል ማድረቂያ |
| እፀ ናሁ | የላም ጡት የምድር ቋልቋ | ለእርባታ |
| እፀ ናርዶስ | | |
| እፀ ኖብ | አንብስ | |
| እፀ ኖህ | ጥቁር ዛፍ ነፊር | ጠንካራ |
| እንጨት | | |
| እፀ ኖዳ | | |

አ - ፺ እፀ አሀው አስካሮን ተደራርቦ የሚበቅል ዛፍ

| | | |
|---|---|---|
| እፀ አምላክ እፀ አየሱስ | የአይጥ አረግ | |
| እፀ አሀመር | የፈረስ ዘንግ | |
| እፀ አልዋህ | አሉሣ | |
| እፀ አሜር | አሚራ | ለብዙ ነገር |
| እፀ አርበቅ | ቀጋ | |
| እፀ አሜከላ | አሜከላ | |
| እፀ አሮን | አርና | ለሆድ ለወስፋት |
| እፀ አብርሂ | አንቃ መስሉ ፍልፉ የሚያበራ | |
| እፀ አብርሂት | ቅጠሉ ሲደርግ ብርሃን ያለው | |
| እፀ አብርሃ/አብርሂት/ | ዉሬ | |
| እፀ አብዛ | የተከማቸ | ለሐብት ለእርባታ |
| እፀ አሰል | ገተም የማርዣፍ | ለተላላፊ በሽታ |



Scanned by CamScanner

| | | |
|---|---|---|
| እፀ አክል ፡ አዳር | ቆንጥር | ለመንድግ |
| እፀ አስግ እፀ ኤላም | ጎግ | ለጥንክርና |
| እፀ አርን | የሰው ነገር ነጭ አበባው | ለትምህርት |
| እፀ አንጉት | አንጉችት | ለአእምሮ |
| እፀ አዝቡሳ | የአዝቡሳ ጋግ | ለግርማ ሞገስ |
| እፀ አክሊል | የእህል ዓይነት | |
| እፀ እስክንድር | ምስርች የመሰለ | እፀ አንግሥ |
| እፀ አእምሮ | ዶቅማ | ለአእምሮ |
| እፀ አእጋር | ግራምጣ | ለጉብያ |
| እፀ አውልዕ | ወይራ | |
| እፀ አዳድ | እንቆቆ | |
| እፀ አድህና | የማይነቃ የማይነቅዝ ጥቁር ዛፍ | ለመፍትሔ |
| እፀ አፍላጢት | ሰሊጥ | |
| እፀ ኢትዮ | የሰንደል ዛፍ | |
| እፀ ኢትዮጵያ | ጦቢያ ትንባ ብትረወርት/ | ለቁስል |
| እፀ እሱር እፀኤሳ | ወንዶው አሰርኩሽ | ለቁስል |
| እፀ ኤልያስ | ባለመአዛ | ለንብ ለቀፎ |
| እፀ እስራኤል | ቀጠጥና | ለኩሉ ነገር |
| እስርት | እሴቴው አሰርኩሽ | ለንግድ ለመስተፋቅር |
| አርና | የማን ዛፍ ዞር | ለመአዛ |
| እፀ አባብ | የኮሶ ዛፍ | |
| እፀ አርጋና | ምሬንዝ | ለቁስል |
| እፀ አድ | የነድ ዛፍ | ለመአዛ |
| እፀ አይደር | ሞይደር | ለመፍትሔ |
| እፀአንዶ | ቋንዶ ሃረግ | |

እፀ ሰድያ　　የሚያዞር አረግ　　ለመፍዝዝ

እፀ አበን እፀ አብን　　ድንጋይ ሰበር

እፀ አጉስታር　　አሬት　　ለቆዳ ለእንጀት

ከ ፱ እፀከ ሙዳ　　ትጠሉ እንደብር ነዉ የሆን

እፀ ከሚና　　ካሩት　　ለዳፍንት ለኩላሊት ለጉበት

እፀከማ　　አከማ　　ለቀለም ለማህጠንት

እፀከረም　　ኮረሪማ　　ለመፍትሔ

እፀከርመድ　　ከርመድ

እፀከርሙዳ　　ነጭ ዛፍ የነጭሉ ዓይነት　　ለመከሰት

እፀ ከርቤ　　የከርቤ ዛፍ　　ለቁስል

እፀ ከርካስ　　የሎሚ ዛፍ　　ለመፍትሔ

እፀ ከንቱ　　በቀን በትላ በቀ የምትጠፋ

እፀ ከድር　　የከርመድ ዛፍ ዓይነት　　ለጽላት

እፀ ኩበካብ　　ሰርገኛ የማበለ ዛፍ　　ለመፍትሔ

እፀ ኩሉ　　ቁንዶ በርበሬ　　ለመፍትሔ

እፀ ከሚን　　ፈጦ

እፀ ኪርልያ　　አትንኩኝ ሲነኳት የምትሰበሰብ

እፀ ከይንት　　የብረት ዐር ብረቱን የሚስብር

እፀ ኩይናት　　እንደብረት የሚመህ ጠንካራ　　ለእታቤ ርዕስ

እፀ ከሱት　　የከሴ ድቃቃዋ ዓይነት　　ለመከሰት

እፀ ኩብር　　ብርቱካን

እፀ ኮል　　እንኮይ

እፀ ኮሞል　　አጄ

እፀ ኮሞል መርቆ የመስለችና ቀለቆል የምታከል ለትምህርት

እፀ ኩንቶ　　ልምጭ　　ለመፍትሔ



Scanned by CamScanner

| | | |
|---|---|---|
| እፀ ኮከብ | ጉሉ ኮከባ | ለመጡብት |
| እፀ ኮንከባ | ጉሉ ሜትማ | ለቅባት |
| እፀ ኮሚላ | ካምሚላ | |
| እፀ ኮክህ | ኮክ | |
| እፀ ኩጥሜ | የቅባት እንጨት | |
| ወ - ፳ እፀ ወይል | ወይሉ ውኃ | ለጽላት |
| እፀ ወል አጸወርቅ | ግብረ ቃይና | ፍሬው ለመጠጥ |
| እፀ ወም | ዝግባ | |
| እፀ ወርቅ | የወርቅ በሜዳ ዓይነቶች | ለሥራይ ለቁስል |
| እፀ ዋህድ | ድግጣ ዝግጣ | ለለምጥ ለቁስል |
| እፀ ዋዊ | ምሳና ብሳና | ለሆድ ደዌ |
| እፀ ዌና | ጠሌንጅ | ለቁስል |
| እፀ ዋግ | ዋግማ | |
| እፀ ዋፍና | የወፍ እንቁር | |
| እፀ ዋገራ | ዋገራ | |
| ዘ - ፳፩ እፀ ዘምራ | አዛምራ | ለሆድ ደዌ |
| እፀ ዝግባ | ዝግባ | ለመፍትሄ |
| እፀ ዘዌ | የአባቴ ዋፈር | ለመርዝ |
| እፀ ዘይት | የወይራ ዓይነት | ለዘይት |
| እፀ ዘይቤ | በሶብላ | ለመጣፍጥ |
| እፀ ዚፋል | ፊንብራ | ተ |
| እፀ ዚአየ | የአይጥ ጆሮ | |
| እፀ ዝማ | የሳማ ዘር | ለመጽንኤ |

| | | |
|---|---|---|
| እፀ ዜና | የእስናግር ዓይነት | ለቁስል |
| እፀ ዛውራ | በአመት መልኩ አራት ጊዜ የሚቀየር | ለክብር |
| እፀ ዣና | ዣና ዋሸንቶ ዋሸንት ለውጋጥም | ለመገድግ |
| እፀ ዝንባቤ | አበባው የበዛ ዣፍ | ለመእዛ |
| እፀ ዜዋዋ | እሴቴው እፀዘዬ | ለመርዝ |
| እፀ ዞብል | ችፍርግ የመሰለው ጠጡብ | ለመጽንኤ |
| እፀ ዞዝ | ጢብጢባ | ለመንክኤ |
| እፀ ዞ | ድንጋይ መስሉ ዱባ የሚያክል | ለመንክሴ አስኪት |

| | | |
|---|---|---|
| የ - ፺ እፀ የም | ባፋዌ ስኳር ድንች የመሰለ | |
| እጸ የሐዩ | ቁልቴ ሕይወቴ | ለመፍትሔ ሥራይ |

እፀ የሐዩ ወእፅ ይቀትል የሚገድል የሚያድን የተያያዙ ፍሬዎችና ስሮች የአሉት አረግ

| | | |
|---|---|---|
| እፀ የሐዩ ወይቀትል | ኩሜሳ የምትበትል ሬሳ የመሰለች | |
| እፀ ይብቤ | አበባዋ ስብስብ ዘር.ጋ የሚል | ለሐብት |
| እፀ ዩሃ | ኺያ | |
| እፀ ያም | የዝር እንቧይ ፍሬ የመሰለ ባፋዌ ፍሬ | |
| እፀ ይቤ | የእብሽ ዘር ዓይነት | የሚያስለፈልፍ |
| እፀ ዩሃው እፀ ይኸው | አዣምራ | ለሥራይ |
| እፀ ዮዲት | ትንሽ አረም | ለትንቢት |
| እፀ ዮጵ | ቅጠልዋ እንደወርቅ የመሰለ | ለሐብት |
| እፀ ዮጳዝዮን | ውስጡዋ ብጫወርቅ የመሰለ | |
| እፀ ዮሐንስ | አደይ አበባ | |



Scanned by CamScanner

| | | |
|---|---|---|
| ደ - ፲ እፀ ደሆ | ደድሆ | |
| እፀ ዳሀና | የደድሆ መልክ ያለው መልከም ፍሬ | ለበረከት |
| እፀ ዳማ | በየወሩ ደም የሚፈሣት ከሥርዋ | |
| እፀ ደማዊት | የደሜ ከትጠልዋና ከግንድዋ ቀይ ደም የማይለያት | |
| እፀ ዳማ | ዳማከሴ | ለመፍትሔ ለዎች |
| እፀ ዳንኤል | ስሩዋንግሜ የመሰለ | ለጥበብ |
| እፀ ደመና | ንድፍ ጥጥ የመሰለ | ለምህግብ |
| እፀ ደብተራ እፀ እስራኤል | ቀጠጥና | |
| እጸ ዳማት | ዲማ ዛፍ ወገቡ ከዋርካ የሚበልጥ | |
| እፀ ዳቢት | [illegible] የመሰለች | ለመንከስ |
| እፀ ድህነት | [illegible] | ለሆድ ለማለስለስ |
| እፀ ዲድ | ዲዲቴ | |
| ገ - ፳፬ እፀ ገሃድ | ነጭ ብሉ | ለራእይ ለመክሰት |
| እፀ ገምራ | የምድር በርበሬ የመሰለች | ለለምጥ ደዌ |
| እፀ ገነት | ሉሚጀት | ለመአዛ |
| እፀ ገምድድ | አምጭ | ለቁስል |
| እፀ ገፍጋ | ቅጠለ የሚጣበቅ | ለተባይ |
| እፀ ጉና | ጂባራ | ለመፍትሔ |
| እፀጉናጉኒት | ቀጮ እንሰት | |
| እፀ ጉዶ | | |
| እፀ ጊሃራ | ውኃ የሚያጠራ | ለማገባ ለጉበት |
| እፀ ጊሜራ | እስቴው ግመር | ለጸላኤ |
| እፀ ጊሜ | ገም ሐረግ | ለመፍትሔ |
| እፀ ጋው | ጀጀባ | ለመጽንኤ |



Scanned by CamScanner

| | | |
|---|---|---|
| አፀ ጋምር | እራስከምር | ለምች አደር |
| አጸ ጋጋ | ቁጊናስ የመሰለ ዝሩም አባሉ | |
| አፀ ጊልጊላ | የፈረስ ዘንግ የመሰለ | ለራስ ህመም |
| አፀ ጌና | ቁጊናስ የደጋ አባሉ | ለኩሉ ነገር |
| አፀ ግሄ | የአሲኮኮ ጉመን | ለምስያጥ |
| አፀ ግእዝ | ግዜዋ ጊዜዋ | ለድንገተኛ |
| አፀ ጉመር | አደንድን | ለመጽንኤ |
| አፀ ጉርጉር | ጎርጉር | |
| አፀ ጉሣ | የተያያዘ ሀረግ | ለማእሰር |
| አፀ ጉደስ /ጉቹ/ | ጭምቅ | ወገብ የሚሰብር መርዝ |
| አፀ ጉሜእ | ደንገል | |
| አፀ ጉድያ | ዋዝዋ | የኩብትን ሆድ የሚነፋ |
| አፀ ጉንጋ | ቆጋ | |
| አፀ ጉድ | እንጉዳይ | |
| አፀ ጉፋ | ብብሻ | ለገበያ ለተሐድሶ |
| አፀ ደብላ ደቤላ | አደናግር | |

| | | |
|---|---|---|
| ጠ- ፫፪ አፀ ጠንታይ | ጂፈራው | ለስኳር ለደም |
| አፀ ጠጠብ | ጠጠብ ጠጠባ | ለመጽንስ ለፍቅር |
| አፀ ጣጤ | ተልባ | ለሆድ ለጨንራ |
| አፀ ጥብብ | እሴቴ ቀንጠፋ | ለጥበብ ለእውቀት |
| አፀ ጡጡ | ጥጥ | ፍሬው ለልብ |
| አፀ ጥሙ አፀጠሊ | የፍየል ጨው | |
| አፀ ጥኡም | ፓፓያ | ለአንጀት |
| አፀ ጥዑዕ | የረኛ ቆሉ | ለቁስል |



Scanned by CamScanner

| | | |
|---|---|---|
| እፀ ጦማር | ልጡ ወረቀት የመሰለ ዛፍ | |
| እፀ ጦስን | የቆላ ጦስኝ | ለፍሉንዛ |
| ጸ - ፱፻ እፀ ጸራልዮ | ወንዶው ቀንጠፋ | |
| እፀ ጸጉሜ | አደይ አበባ | ለቁስል |
| እፀ ጸጦስ | መረቆ | ለጸላኢ |
| ፀ - ፩፻ እፀ ፀሐይ | ልት | ለሆድ |
| እጸ ጸሊም | ጥቁር ዛፍ | |
| እፀ ጸእዳ | ነጭሉ | ለመክሰት |
| እፀ ጸእድ | | አመድማደ |
| እፀ ጸእዳ | | ነጨጭሉ |
| እፀ ጽኡድ | ነጭ ዛፍ | ለመፍትሔ |
| እፀ ጸዲድ | ምስንጭር | ለትምህርት |
| እጽልመት | ጥቁር አረግ | ለመሰውር |
| እፀ ጽሉምየበደማን አረግ/ | አዙሪት አረግ | ለመፍዝዝ |
| እፀ ጽሂግ ነጭሪዝ መስሉ ከዛፍ ላይ የሚበቅል | | ለምትሐት |
| እፀ ጽድ | የጽድ ዛፍ | |
| ፈ - ፰፻ እፀ ፈሃም | ፍልጡ የሚያበራ ዛፍ | |
| እፀ ፈርፈር | የሆነ ነገር ሲነካት የምትንቀጠቀጥ | |
| እፀ ፈረስ | የበትሉ ዉንገር | |
| እፀ ፈታሂ | | |
| እፀ ፋርስ | | እንብጮ |
| እፀ ፈረስ | | አሽሽ |
| እፀ ፍርስ | | የፈረስ ዘንግ |
| እፀ ፍትሀ | | የበትሉ ጋማ |
| | | ምስርች |

# ከእግር እስከጫፍ የሚያፈራ

አፀፍሬ
አፀ ፍሩት
አፀ ፍቅር
አፀ ፍቱን
አፀ ፍሬት
አፀ ፍትሔ
አፀ ፍሱል
አፀ ፍና

የሞኝ ፍቅር ጨጉጉት የካህን ቲም ለፍቅር
ዳማከቤ ለድንገተኛ ለጣላት

ዘርጭ እንጂይ ዘኢያወርድ
እንቃ የመሰለ
የጅንጀር እጣት ለገበያ



Scanned by CamScanner

# ገ. ከ. K

## ከል

ቢረድ ቀላል ነው አዘውትሮ ቢበሉት ውፍረት ይቀንሣል።

## ከሴ

የከሴ ዓይነቱ ሰባት ነው ስማቸውም ዳማ ከሴ የአኸያ ከሴ ከስከሴ ካከሴ የዱር ዝቃቅቤ

## ከርመድ

ነጭ ዛፍ ነው እርሱን የሚመስል ነጭ ዛፍ አለ ቅርፍቱን ወቅጠህ ሠገራ ለከለከለው ሆዱን ለታመመ ከበግ ላት ጋር አንጥረህ አጠጣው ወይም እንደሻይ እያፈላ ይጠጣ።

## ከርከዴ ተ/

## ከርቤ

1. ለጨጓራ መታወክ ለመጋኛ ግማሽ ማንኪያ በጥብጠህ በየሁለት ቀን በባዶ ሆድ መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

2. ከርቤ ከአልቴት ጋር ለማህፀንና ለኩላሊት ህመም በባዶ ሆድ መጠጣት ነው።
3. ለሣል ከእንቁላል ጋር መጠጣት ነው።
4. አሶ ለሚሸት ከርቤ አልቴት የጽድ ፍሬ ሁሉንም ደቁሶ በሻሽ አድርጉ ይያዝ በጕብጦ በባዶ ሆዱ ጠጕቶ ውሃ ሲጠጣ ይዋል።
5. አፍንጫው ለሚቆስልና ለሚሸትበት ከርቤ ከሰሊጥ ጋር በቅቤ አንጥሮ በአፍንጫው ይሳብ።
6. ለልብ ትኩሳት ተረገና ከርቤን ከንጥር ቅቤ ጋር አንጥሮ መጠጣት ነው።

ከሩቴ ካሩት የመሰለ ፡ ለደም ለዓይን

## ከድከዴ

የከድከዴ አበባ በወፍራም ከጠጡት ደም ያደርቃል ከቀጠነም ደም ያበዛል መካከለኛ አድርጉ እንደሻይ መጠጣት ነው። ደም ለበዛባት ሴት አወፍራ ትጠጣው።

ለተሰበረ የከድከዴን ቅጠል ወቅጦ የተሰበረውን ማጀል ነው።



Scanned by CamScanner

ኩርንችት ችፍርግ የመሰለ የውድማ መጥረጊያ ወይም ኮርንችት ንብ ማር እንዲይዝ ቀፎውን ማጠን ነው።

## ካሩት

ለዓይን ዳፍንት ለኩላሊት ለእባጭ ለጉብት ለተቃጠለና ለቆሰለ ቆዳ ሥሩን ቅጠሉን ፍሬውን መጠቀም ነው።

## ካሞሚላ

ለጨጓራ ከከርቤ ጋር አፍልቶ መጠጣት ነው።

ካከቻ ተ

ከርከራ ተ/

## ከብረሰማይ

ጠጉር እንዳይበቅል በሎሚ ውኃ ለውሶ መፈግፈግ ነው ወይም ጠጉርን ነቅሎ መደምደም ነው። ለምትሐት ለቁስል ይሆናል።



Scanned by CamScanner

## ከማ

ለማህጠንት የውኃውን እቃ እጠነው ከመጠጥም ጨምር

## ክትክታ

1. ለቁስል ለምኺሮ የክትክታና የጥፍርንዶ ቅጠላቸውን ወቅጦ በቁስሉ ላይ መደምደም ነው።
2. ለሣል ቅጠሉን ሥሩን መታጠን ነው።
3. ከብትም ይሁን ሰው ለተሰበረ ቅጠሉን ወቅጦ ደፍድፎ ማሰር ነው፡ ይጠገናል።
4. ለመጥፎ ሣል ቅጠሉን ከድንጋይ ልብስ ጋር እንደሲጃራ ማጤስ ነው።

## ኮሸሺላ ፡ በራቄኔም

ለንብ ተቀጽላውን ከቀፎ ውስጥ መሻጥ ወይም ከሰው አጽም ከጃርት እሾህ ከንብ ጥራ ጋር ማጠን ነው።

## ካሶ ዛፍ

1. ጣቱን ለሚቆረጥመው ፍሬውን በቅቤ ለውሶ መዋጥ ነው።



Scanned by CamScanner

2. ሆዱን ለሚያመው ሰውነቱ ለሚነጣ የኮሶ የምሳና የእንቆቆ ፍሬያቸውን የአቱች የእንጆሪ የጡንጅት የአዛምር ቅጠላቸውን ወቅጦ አቡክቶ ማድረቅና ለሚያመው በቀይ ጤፍ ቂጣ በልቶ አጓት አብዝቶ እያረፋ መጠጣት ነው። ሁሉን ያጸዳዋል ይፈውሳል።

ኮሞ ተ/

ኮረሪማ ተ/

## ኮሽም

1. ለእድሜ ለዘጠና ዘጠኝ /99/ ቀን አዘውትሮ ፍሬውን ከበለስ ፍሬ ጋር በማር መዋጥ ነው።
2. ለአባጭ ለቡግንጅ ቅጠሉን አልሞ መደምደም ነው።

## ከባሌ

ከእግር እስከራሱ ሁለመናውን ለአመመው ጅንጅብል ኮረሪማ ጤና አዳም ነጭ ሽንኩርት ቁንዶ በርበሬ ሚጥሚጣ ነጭ አዝሙድ ሁሉንም ወቅጦ በነጭ ማር በባዶ ሆድ መብላት ነው።

ኮክናት ተ/

**ኮሙን**

ወይም ከሙን የእንስሳል ፍሬ ለሆድ ኪንታሮት ለጭብጦ ሽንቱን ለሚከለክለው ከምሳና ስር ቅርፍት ጋር ወቅጦ እንደሻይ በማር መጠጣት ነው።

**ኮክ**

ለራስ ምታት የፍሬውን ውስጡን የርግብ ኩስ ሰናፍጭ ጤና አዳም በአንድ ላይ ደቁሶ በፍየል ቅቤ አንጥሮ በአፍንጫው ማድረግ ነው ወይም ከሚያመው ላይ በትኩሱ ደፍድፎ ማሰር ነው።

## - ወ - W

**ወሊት**

ለራስ ፍልጠት የወሊት የዳማከሴ የጨጉጉት ቅጠሳቸውን ወቅጦ በአፍንጫ መሳብ ነው።



Scanned by CamScanner

## ወርቅ በሜዳ

ወርቅ በሜዳ የሚባሉት አንደኛው ስሩ እንደ ጅንጅብል ሁለተኛው እንደ አገው ድንች ሞለል ያለ ሦስተኛው ድቡልቡል ያለ ትንሽ ነው ከነዚህ ከሶስቱ ጅንጅብል የመሰለው ይበልጣል።

1. ራሱን ለሚያዞረው የደም ችግር ላለበት ቀይ ሽንኩርት ነጭ ሽንኩርት የጅብ ሽንኩርት ወርቅ በሜዳ ሁሉንም ወቅጦ በነጭ ማር ለውሶ በባዶ ሆድ 1 ማንኪያ ያህል ይዋጥ ሲደክመው ትኩስ ሻይ ወይም ቡና ይጠጣ።
2. ጉርሮው ለአበጠ ከእፀ መናሂ ስር ጋር ወቅጦ በቅቤ ለውሶ ውስጡ መቀባት ነው።
3. ለነቀርሣ ለውር ለእከክ ለሣል እንዘረዘይ ነጭ ሽንኩርት ወርቅ በሜዳ በአንድ ላይ ወቅጦ በአጓት አፍልቶ መጠጣት ነው ልኩ አንድ ማንኪያ ይሁን ማርከሻው የዶሮ ጉበት ወይም አቦል ቡና ነው።
4. ለወገብ ህመም የአሚራ የዶግ የመቅመቆ የደድሆ ሥራቸውን ከወርቅ በሜዳ ጋር ወቅጦ በቅቤ አንጥር በቀይ ጤፍ ቂጣ መብላት ነው ወይም ከገንፎው ጋር መብላት ነው።



Scanned by CamScanner

5. ጋኔን ለሚጥለው ራሱን ለሚያዞረው እንደ ሲጃራ ጢሱን ይሳብ
6. ልቡን እያመመ ለሚነፋው ለሚያሰቃየው ከአቱች ቅጠል ጋር ደቁሶ በአንት ዘፍዝፎ አሳድሮ መጠጣት ነው። ሲደክም ማርከሻው አርጐ ነው።
7. ራሱን ለሚያመው በፍየል ቅቤ አንጥሮ በአፍንጫው ማድረግ ነው። ተቀርፍፎ ወይም ትሉ ይወጣል።
8. በሆድ አጥንት ወይም ሥራይ ላለበት ከዋጊኖስ ቅጠል ጋር በውተት ቀቅሉ መጠጣት ነው።
9. ወርቅ በሜዳ ለሆድ ሥራይ ለሌላም ደዌ ሁሉ ስለሚሆን በነጭ ማር ለውሰው ቢበሉት ያስቀምጣል የሆድን ነገር ችግር ያስወግዳል አሰጣጡ ለአንድ ሰው ሩብ ማንኪያ ይሁን።

ወንዴ ቁልቋል ፡ ቀለምጤዳ ?

ወንዴቃጫ

ለመጽንኤ አስኪት ከምስር ንፍሮ ጋር ቀቅሉ ውኃውን መጠጣት ንፍሮውን መብላት



Scanned by CamScanner

## ወንዴሬት

ለድርቀት ለቆዳ ለቁስል ደጋግሞ መቀባት ወይም ለማንኛውም ሆድ ድርቀት የሬቱን ልብ በባዶ ሆድ አዘውትሮ መዋጥ ነው። ወይም አድርቆ ከአብሽ ጋር በጥብጦ መጠጣት ነው።

ወይሉውጋ /እንደጥቁር እንጨት ለጽላት የሚሆን/

## ወይራ

1. ዓይኑ ለሚያለቅስና ጨምጫማ ለሆነበት የወይራ የእንባጮ ቀንበጣቸውን ወቅጦ ጨምቆ ማጥለል የጠለለውን ከኩል ጋር መኳል ነው።
2. ለምግብ ፍሬውን በብዙው ለቅሞ ጥሬውን እንደሙዝ ማሸግ ሲበስል አድርቆ ዘይት ማውጣት ይቻላል። ሌላው ደግሞ ከብዙ ጨው ጋር እንደገብጦ በውኃ ውስጥ አድርጉ ማስንበትና አውጥቶ በሌላ ውኃ ለቅልቆ ከምግብ ጋር መብላት መልካም ጤነኛ ያደርጋል።



Scanned by CamScanner

## ወይን /ዘቢብ/

የሰማይ ለዞረው ወገቡን ለታመመ ሕፃን ቅጠሉን ወቅጦ በውኃ በጥብጦ ማጠጣትና የቪኮከ ጉመን የእንስሳል የወይን ቅጠላቸውን በአንድላይ ዘፍዝፎ ሰውነቱን ለሰባት ቀን ማጠብ ነው።

## ወይናግፍት

አብድ ውሻ ለለከፈው ስሩን አሲዝ

## ወዳጄ የጉምዝንግሥት

የጉምዞች ሴቶች ተንዘርክከው ይሰገዱለታል።

## ወገርት

1. ለዘኢያወርድ ሥሩን ማላመጥና በጉንጭ መያዝ ነው።
2. ሆዱን ላመመው ቀቅሎ በማር መጠጣት ነው።
3. ለሆድ ደዌ ወቅጦ ከማር ጋር አቅልጦ መጠጣት ነው ያስቀምጣል
4. ለህልመ ዮሴፍ ይቤሉ እግዚአ ለእዚየን ፵፱ ወገርቱን ታጥና የወይራ ቀንበጥ በአፍ ይዞ ቢተኙ መልካም ህልም ያሳያል።

ወፍ አርግፍ ተ/

ወፍ እንቁር ሱጭ ጦቁር ቡላ ዋንዜ መልክ አለው/ አጥንት ለተሰበረበትና ለውጋት ቅጠሉን ወቅጦ ከሚያመው ላይ ደፍድፎ ማሰር ነው።

## ዋርካ

ለመፍትሔ ሐብት ተቀጽላውን ወቅጦ በባዶ ሆድ በማር መዋጥ ወይም ከቅባት ጋር ለውሶ መቀባት ነው።

## ዋሽንት ዋሽንቶ ዛና

1. ለምሕሳበንዋይ ለገብያ ተቀጽላው ለበቁ ይሆናል። ለውኃ ጥም መፋቂያ ማድረግ ነው።
2. ለጆርባ ደዌ ደም ለሚፈስው ቅርፍቱን ደቁሶ መጠጣት ነው ወይም እንደሻይ መጠቀም ነው በማር መብላት ለሁሉ መልካም ነው።



Scanned by CamScanner

## ዋግራ

1. ራሱን ልቡን ለሚያመው ዋግራ ድብርት አልቴት ከጥቁር ስንዴ ጋር ፈጭቶ ለበግ ማብላትና በሰባተኛው ቀን በጉን አርዶ ሥጋውን መብላት መረቁን መጠጣት ነው።

## ዋይከ

ዋይከ መልኩ እንደባምያ ሁና የገረዘዘ ነው፡ እንደታርያ የመሰለውን ፍሬውን ወቅጦ ከምግብ ጋር ቢበሉት ሆድ ያለሰልሳል ለድርቀት መልካም ነው።

## ዋንዛ ቁውንቄ

1. ለኪንታርት ለነቀርሣ የዋንዛ ቅርፍት የጡንጂት የሥሩ ቅርፍት ደቁሶ በቅቤ ወይም በማር ለውሶ መቀባት ነው።
2. እንደዚሁ ለቆላ ቁስል ለኪንታርት ቅርፍቱን ከአሚራ ስር ጋር ወቅጦ በቅቤ አንጥር መጠጣትና ደምድሞ ማሰር ነው፡ አክስሉም ቢቀቡት ያደርቃል።



Scanned by CamScanner

ዋጊኖስ እፀጌና ወይም የደጋ አባሎ

እርሱን የሚመስል ገራም አባሎ የሚባልም አለ። የይፋት ቅጠል የተባለ ለማህጠንት የሚሆን አባሎ በቆላ አገርና በወይና ደጋ ይገኛል። ዋጊኖስ ግን በወይናደጋና በደጋ ስለሚገኝ የደጋ አባሎ የሚሉም አሉ።

1. ጋኔን ለሚጥለው ፍሬውን ስሩን የጂባራ የግመሮ የግሜሐረግ /ግምሐረግ/ የቁራ ሀረግ ሥራቸውን ወቅጦ በአዲስ ቅል ዘፍዝፎ ሲጥለው በአፍንጫው ማድረግ ነው። ለተላላፊ በሽታ ለወረርሺኝም በጓዳ በር አስገብቶ ቤቱን በመርጨት ሰውን ሁሉ ማጠብ ከሥሩ በኪሣቸው መያዝ ነው። ለሚተኛ ወይፈንም በአፍንጫው ማድረግ ነው።
2. ለተስሕቦ በሽታ ለተላላፊ ለገድፍት ፍሬውን ከነጭ ሽንኩርትና ከጤና አዳም አልቴት ከዶሮ ኩስ ከምሳና ከግሜ አረግ ጋር ወቅጦ በቅል ሶስት ቀን ዘዋራ ቦታ ዘፍዝፎ በሶስተኛው ቀን በጓዳ በር አስገብቶ የታመሙትን ሌሎችንም ማጠብ ቤቱን መርጨት ነው። ሰውነት ደጋግሞ መቀባት ነው።
3. ከማንኛውም ተላላፊ በሽታ ለመጠበቅ ፍሬውን ከጂባራ ፍሬ ጋር ወቅጦ በአዲስ ሸክላ አድርጉ



Scanned by CamScanner

ከቤት ደጃፍ መቅበር በማር ከአመት አንድ ጊዜ መብላት ነው ቤተሰብ እየታመሙ ከአስቸገሩ በማር ማብላት ነው።

4. ለሻህን ቅጠሉን ከአዞ አረግ ቅጠል ጋር ወቅጦ የቁስሉን ዙሪያ ማር ቀብቶ መደምደምና በበላዩ የስንዴ ሊጥ አድርጉ በሻሽና በጥጥ ሸፍና ለ፫ ቀን ማሰር ነው እንደዚሁ ፈትቶ ማድረግ ነው።

5. በውስጥ ገላው እጢ ለሆነበትና ለተደበቀ ነቀርሣ ፍሬውን ለአርባ ቀን በማር መዋጥ ነው።

6. መርዝ ለሆነበትና አልደርቅ ላለ ቁስል ፍሬውን ቅርፍቱን ቅጠሉን ወቅጦ በበላዩ ደፍድፎ ማሰር ነው፡ አነፍርቆ መጨረሻ ይደርቃል ወይም ከአሞጭ ስር ጋር ወቅጦ ማድረግ ጉትቶ ያወጣዋል፡ ሲወጣ የጉርጠብ ቅጠል የድግጣ ቅጠል ማድረግ ነው ለምጡ እንዲጠፋ

7. ለቆዳ ደዌ ለቺፌ ለእውር እከክ ፍሬውን ቅጠሉን ከዲን ጋር ወቅጦ በቅቤ ለውሶ መቀባትና ፀሐይ መመታት ወይም እሳት መሞቅና መታጠብ ነው።

8. ለነቀርሣ ለኪንታሮት ቅጠሉን ከአሞጭ ስር ጋር ደቁሶ በቅንጭብ ወይም በቁልቋል በበለስ በጦቢያ



Scanned by CamScanner

በተገኙት ለውሶ መደምደም ነው ቁስሉን ደጋግሞ በራሱ ሽንት ውኃ ይታጠብ ሲያመው ፍሬውን ደቁሶ በማር ይዋጥ።

9. በሆድዋ አጥንት ለሆነባት ቅጠሉን ከውተት ጋር አፍልታ ትጠጣ ወጥቶ ይወድቃል።

10. ጀርባው ለወጣ ፍሬውን ከነጭ ሽንኩርት ጋር ወቅጦ መቀባት ነው።

11. ለተቅማጥና ለተላላፊ በሽታ ሦስት ፍሬዎች ወቅጦ በማር መዋጥ ነው።

12. እብድ ውሻ ለለከፈውና ሥራይ ላለበት ፍሬውን ወቅጦ በማር ይዋጥ ያስተፋዋል።

13. ጠጉር ለማብዛት የዋጊናስ የአባሉ የስልብያ የልት የአደስ የራስክምር ቅጠላቸውን በአንድ ላይ ወቅጦ በኑግ ዘይት ደጋግሞ መቀባት ነው። ቢቆስልም ስለሚድን አለማቋረጥ በየቀኑ እየተቀቡ በሻሽ መሸፈን ነው።

14. ለአስም ፍሬውን ወቅጦ በማር መዋጥ ነው፡ ያስተፋዋል ገጦ እስከሚያወጣው አለማቋረጥ ጉርርም ስለሚያቆስል አለመፍራት ነው። የዋጊናስ ፍሬ ከውተት ወይም ከሎሚ ውኃ ጋር እንዳይጠጣ።

ዋርሙ ተ/

ውልክፋ ተ/

ውንጣውጦ ተ/

ውኸርኘ

1. ለእንጥል ቅጠሉን አሽቶ በአፍንጫ ማድረግ ነው።
2. ለእባብ ስሩን ወቅጦ በውኃ ማጠጣት ነው።
3. ለመጋኛ ቀንበጡን ከሰባት ቦታ ቆርጦ በውኃ መጠጣት ነው።
4. ለደም የእገሊትን ደም እንደዚህ ቁረጥ ብሎ ቆርጦ በወገብዋ

ዎፍጨጭ

1. ለልብስ ማጠቢያ ይሆናል ለሣሙና ቢያዘጋጁት መልካም ነው።
2. ለከሣ ሰው ቀቅሉ በትንሽ በትንሹ መስጠት ወይም ደቁሶ ከመረቅ ጋር ማጠጣት ከዱር አራዊት ጃርት በጣም ትወደው አለች።



Scanned by CamScanner

# - ዘ - ጊ

ዘሃአረግ ተ/

ዘምባባ ፡ ፀመርት የመሰለ ?

ዘነዘና ተ/

**ዘንጋዳ ፡ ቃቤላ**
የዘንጋዳ ዘፍ ዓይነት ብዙ ናቸው፡ ከነዚህ ለእንጀራም ሆነ ሰውነት የሚጠግኑ ባሶኬ ጋንሰበር አመደሺ ቁጭብየ ድኩን የእነዚህ የንፍሮአቸው ውኃ ለተሰበረ ለቆሰለ ሰው ስለሚጠግን በቀን በቀን መጠጣት ነው። የአሚራ ስርም ቢጨምሩበት የተሻለ ነው።

**ዘርጭ እንቧይ**

1. ለሣል ለሣንባ ለስኳር ለዘርጭ እንቧይ የገበር እንባይ /የደጋ እንቧይ/ ፍሬአቸውን አውጥቶ በውኃ አጥቦ ማድረቅና መውቀጥ በፍየል ቅቤ አንጥር መጠጣት ወይም በወተት አፍልቶ መጠጣት ነው።
2. ለማድያት ፍሬውን ከምሳና ፍሬ ጋር ደቁሶ በእንቁላል አስኳል ለውሶ መቀባት ነው።



Scanned by CamScanner

3. ለውጋት ለቁርጥማት ከጠሌንጂ ስር ጋር ወቅጦ መጠጣት ነው፡

4. ለቁስል ቅጠሉን ከአጋም ስር ጋር ወቅጦ መደምደም ነው።

5. ለቁርጥማት ከቱልት ስር ጋር ወቅጦ በተልባ ማጠጣት ነው።

6. ለቂጥኝ ከግመሮ ስር ጋር አረቄ አውጥቶ መጠጣት ነው።

ዘጭ መረጭ ቀይና ጥቁር ሁለት መልክ ያለው ነው። ከመሬት ውስጥ እንደ እንጉዳይ የሚወጣ ነው። ለኪንታሮት ወቅጦ መደምደምና በየጊዜው በሽንት ውኃ ማጠብ ነው።

ዛንኪላ

ለሆድ ደዌ በማር ወይም በበሶ ማብላት ነው። ለልብ ደዌ የዛንኪላ የድብርቅ ፍሬ የሥረብዙ ሥራቸውን ደቁስህ በኖረ ቅቤና በጣዝማ ማር ለውስህ ጠዋት ጠዋት መብላት።

## ዝንጅብል

1. ምላሱ ለተጉለጉለ ቁንዶ በርበሬና ጨው አብሮ ደቁሶ በሻሽ አስሮ ምላሱን መፈገፈግ ነው። በኋላ ከአቱች ቅጠል ጋር ቀቅሉ ይጉመጥመጥና ይትፋው ይድናል።
2. ለራስ ምታት ከቀበርቾ ጋር ወቅጦ በቅቤ አንጥሮ ከራስ ላይ መደፍደፍና ማሰር ነው።

## ዝግባ ፡ ዘግባ

1. ለእንቅርት የዝግባ የዘርጭ እንቧይ ፍሬአቸውን ከአልቴት ጋር ወቅጦ ከእበጡ ላይ ደፍድፎ በሻሽ ማሰር በየሶስት ቀኑ መቀየር ነው ይጉድላል።
2. ለማንኛውም እንገት ህመም የዝግባ የዘርጭ እንቡዋይ የእንኮይ የድግጣ ፍሬአቸውን ቅጠላቸውን የእንባጮ የገበር እንቧይ የእደሁላ ቅጠላቸውን የጨረቃ አር የሚባል ከኮሸሽላ ከሌላም እንጨት ላይ ተንጠልጥሉ ተጣብቆ የሚገኝ የትል ቤት አልቴት እንዚህን ሁሉ በአንድ ላይ ደቁሶ ለታመመ ከእንገቱ ላይ ደፍድፎ ማሰር ነው።



Scanned by CamScanner

3. ለሣል ለሣንባ ለስኳር በሽታ የዝግባ ሙጫ ቀንበጥ የቁልቋል የዶግ ቀንበጥ የእንጭብር የወርቅ በሜዳ ስር ከርቤ በአንድ ላይ ወቅጦ በጣዝማ ማር ለውሶ ግማሽ ማንኪያ መብላት ነው ወይም ከአቦል ቡና ጋር መጠጣት ነው።

## ዝብና ዛብና

ለቅጫም ለተባይ ስሩን ወቅጦ ዱቄቱን በቅባት መቀባትና መታጠብ ነው።
የዝብና ወይም የዛብና ስሩ እንደትልቅ ቅል ሁና በጣም ነጭ ነው ለተባይ ማጥፊያ ቢያዘጋጁት መልካም ውጤት አለው ሌላም ምስጢር በውስጡ አለ።

ዝምትጊት ተ/

# - የ - Y

## የላምጡት

የላምጡት መስሉ የተንጠለጠለ ፍያ ያለው ?

## የሉማሺሽት

1. ደም ለሚመላለስቤት ሴት ከጠንበለል ስር ጋር ሰፍቶ መያዝ
2. የሉማሺሽት ቅጠልዋ አበባዋ ለሽቶ ለመአዛ ይሆናል።

## የሰው ነገር በግእዝ እጸአሮን ትባላለች

1. ኢል ኢላዊ ቢአዊ ኢኤል ኤላዊ ቢኢዊ ከመድኤል ጀማኤል ምዋኤል ልዋኤል ሩዋኤል በከመ ሡወርኮሙ ለሄኖክ ወለኤልያስ በሕይወተ ሥጋ ወነፍስ ከማሆሙ ሡውረኒ እመከራ ሥጋ ወነፍስ በዛቲ እፀ አሮን በሀገረ እ— ሊተ ለገ/እ/ ማ፲ ድገም አርብና እሮብ ቀን ደግመህ ቁረጥና ከእስስት ደም ጋር ቀላቅለህ በብጫ ወረቀት ጽፈህ በግራ ኪስህ ያዝ ለማንኛውም ይሆንልሃል።



Scanned by CamScanner

2. ለሐብት "ኢፓኤል ሹዋኤል" በእስስት ደም ከቅጠሉ ላይ ጽፎ አቃጥሎ በትከሻ መጠቆር ነው።

3. ለፈለጉት ነገር ለዚህ ነገር ሁነኝ ብሎ በጥርስ ነቅሎ እያላመጡ ጉዳይን ማድረግ ነው።

4. ለምዋርት "ኢፓኤል አካኤል አጀኤል" ብሎ የሰው ነገርን የአሩጥን የእንጭብርን ስር ነቅሎ በስመሬታ ገብስ ዱቄት ጋር ቂጣ አስጋግሮ መብላት ነው።

5. ለፍጥነት "ኢል ኢላዊ ቢኢዊ ከመደኤል ከመደኤል ጃማኤል ሙዋኤል ሱዋኤል ሹዋኤል ሉዋኤል ሩዋኤል በኃይለ እሉ አስማተሠረገላ ኤልያስ በከመ ሠወርከሙ ለሄኖክ ወለኤልያስ ወለእዝራ ከማሆሙ ሰውረኒ እምዓይነ ኩሉ ጸር በይእቲ እፀአሮን" ለገ/እ/

ዝቢሩ አስማቱን ጽፈህ ከእስስት ሥጋ ጋር አክስለህ ተነቀስ ወይም በእስስት ደም በቢጫ ወረቀት ጽፈህ ሺህ ግዜ ደግማህ ማያዝ ነው።

6. ሐብቱ ለተሠወረበት "ኢጥኤል ሙዋኤል" 99 ጊዜ ጽፎ ከሉሚ አበባ ጋር ወቅጦ በማር ሰባት ቀን ማብላት ነው።



Scanned by CamScanner

7. “አኤል አፓኤል አካኤል አጃኤል” ብሎ በእጅ ይዞ ደግሞ መቁረጥና ከጅብ አይን ጋር መቅጦ በጅቡ ሐሞት ለውሶ መኳልና አስማቱን መድገም ነው የተደበቀው ሁሉ ይገለፃል።
8. ለእድሜ “ኤስ በስ ኤለበላሆን ፮ ወለቴሶን ፮ አስሄር ሚጣ ወልጣ ሚጣ ወወልጣ ለዛቲ ነፍስየ ውስተሀይወተ ሊተ ለገ/እ/” ሥሩን ከእንጭብር ጋር ወቅጦ በቀይ ቀለም ጽፎ አቃጥሎ መጠቆር ነው።

   ለሐብት የሚሆነው ነጭ አበባ ያለው ሲሆን ለአቃቤ ርእስ ለመሰውር ቀይ አበባው ነው።

## የሰይጣን ሙቀጫ

ከመሬት ላይ የበቀለው ወፈር ይልና እደቀጠነ ወደላይ ይወጣል ፦ ለመጽንኤ

## የሰይጣን ጉልቻ

ዱባ ያክል ሁና ድቡልቡል ነው ከገደል አፋፍ ላይ የበቀለውን ሥሩን ተከታትሎ ድንች የመሰለ ይገኝበታል እሱን ቢያላምጡት ዘኢያወርድ ይሆናል ብልትን ያወፍራል።

## የሰይጣን መርፌ

ቀንበጡን የካህን ቂም ቀንበጥ በአንድ ላይ ደቁሶ በቅባት ለውሶ ለመስተፋቅር ሰውነቱን ቀብቶ መገናኘት ወይም ሰላምታ ማለት።

የሰው እናት ?

## የሴት ልብ በግእዝ እጸልብ

ከመሬት የተለጠፈችና ቅጠልዋና አበባዋ የልብ ቅርፅ አላት። ለመስተፋቅር ሥሩዋን ደቁሶ በአምሳያ ላም ቅቤ ለውሶ መቀባትና መንካት ነው።

## የሴት ምላስ እሾሃም ነው

ለዘኢያወርድ እንዳይቸኩል ሥሩን በጉንጭ መያዝ መንከስ ነው።

የሴት ምሳ /ተ

## የሴት ቀስት

1. ለእጢ ለእባጭ ለኪንታሮት ሥሩን ቅጠሉን ወቅጦ በጦቢያ /ቅቦ/ ደም ለውሶ ወይም አክስሉ መደምደምና ማሰር ነው።

የሴት ሬት "ፒ" ላይ ሬት ከሚል ተመልከት

የረኛ ቆሉ ተ/

የረኛ ምሳ ተ/

## የምድር እንቡዋይ

1. ለጥርስ ሕመም ሥሩን ከበርበሬና ከከርቤ ጋር ቀቅሎ ውኃውን እየተጉመጠመጡ ይትፉው
2. ለኪንታሮት ፍሬውን ከሬት ፍሬ ጋር ወቅጦ እያሞቁ መደምደም ነው።
3. ሆዱን ለነፋው ለሥራይ በአጓት ሥሩን ቀቅሎ ማጠጣት ነው።
4. ናላው ለተጉዳ ፍሬውን ከከርቤና ከአልቴት ጋር ደቁሶ በቅቤ አንጥሮ በአፍንጫው ማድረግ ነው።
5. ለችፌ ከቀጠጥና ስር ጋር በማር ለውሶ መቀባት ነው።

## የምድር አሰንጋ

ብልቱ ለሞተበት ከሰባት ቦታ ቆፍሮ ሥሩን አምጥቶ አጥቦ በወተት እየቀቀሉ መጠጣት ነው ያበረታለታል ወይም ከእርግብ ሜጩት መረቅ ጋር ይጠጣ።

የምድር ቂጥኝ ተ/

## የምድር ጩንገር የበቅሉ ጩንገር

የምድር ቁልቋል የላምጡትም የሚሉ አሉ ከምድር ወደላይ ስንዝር የምታክልና ብዙ ሁና በጭንጫ መሬት የምትበቅል ናት።

1. ለከብት ርቢ ለወተት በሰመሬታ ገብስ ድፍድፍ ለከብት ማብላት ነው።
2. ለከሣ ሰው እንዳለ ወቅጠህ በገልገል ፍየል ሥጋ መረቅ ማጠጣት ነው።

የምድር ቅንጭብ ተ/

የምድር በርበሬ ተ/

የምድር ኮሶ ተ/

የምድር ቁገ ተ/



Scanned by CamScanner

የምድረበዳ ሽንኩርት ተ/

የማርያም ዋንጫ ተ/

## የቆላ እንቡዋይ

ለእጢ ከቅጠሉ ላይ የወጣውን እጢ ቆርጦ በሰው ገላ ላይ የወጣውን እጢ ማሸት።

## የቆላ ጦስኝ

1. ሣንባው ታሞ ሣል ለሆነበት ቅጠሉን ወቅጦ ከፌት ውኃና ከማር ጋር ይዋጥ።
2. እባብ ለነደፈው ቅጠሉን በውኃ በጥብጦ ማጠጣት ነው ከነከሰው ላይም መደምደም ነው።

የቆላ አባሉ አባሉ ከሚል መመልከት

የደጋ አባሉ ዋጊኖስ ከሚል ላይ መመልከት ነው

## የደጋ እንቧይ ገበር እንቧይ ቅጠሉ ነጭ ነው።

1. ለሣል ለሳንባ ፍሬውን አውጥቶ አጥቦ አድርቆ ከቅቤ ጋር ማጠጣት ነው።

የደጋ እስቅጭ ?



Scanned by CamScanner

የደጋ አሺታም ተ/

## የቁራ አረግ የአሞራ ምሳ

1. ለቂጥኝ ቅጠሉን ከዋጊኖስ ቅጠል ጋር ደቁሶ በቅቤ መቀባት በትንሹ መጠጣት ነው።

## የቁራውሺሺ የዶሮ ቅል

ለቡሃራስ የዶር ቅል የልት ቅጠል ከበግ ላት ጋር አቅልጦ መቀባት ነው።

## የባብጦር

የባብ ጦር የተባለው እፅ ባለበት እባብ ዘንዶ አይኖሩም ከቤት ቢያጤሱት እባብ አይቀርብም።

## የበርሃ ግሜ ግምሐረግ

1. እግሩ ለመነመነ ቀርሸሽቦ ገመሮ አሚራ ሥረብዙ ሁሉንም ወቅጦ በእርግብ ሥጋ ማብላት ነው።

2. ለማንኛውም ሥሩን ወቅጦ መታጠን ወይም ዘፍዝፎ መታጠብ መጠጣት ነው። ለቁመኛ ለጋኔን ለንዳድ ከውሻ ኩስ ጋር ታጥና መተኛት።

የበጋ ስንን ተ/

## የንብ አሰል

1. ሆዱን ለነፋው ሽንቱን ለከለከለው ከእንስላል ቅጠል ጋር በወተት አፍልቶ ማጠጣት ነው ወይም እንደሻይ በማር ማጠጣት ነው።
2. የሳንባ ደም ለሚወጣው የምስርች ቅርፍት ድንብላል ጋር ቆልቶ በጠጅ ማጠጣት ነው።

## የአሞራ አሞጭ ቀዘበ ቀዘው

ለፍቅር ሥሩን በእሳት ተኩሰህ የተመኘኸው ተናገረህ ሰውነትህን እጅህን ቀባ

የደሜ በምትባለው እጽ የረቀቀ የጥበብ ምስጢር አለና ለማወቅና ለመመራመር ማስተዋልና መትጋት ያስፈልጋል።

## የደሜ በግእዙ እጸደማዊት

በእጸደማዊት ቀንበጥ ላይ እኻ ሙጫ የመሰለ ሲኖራት ግንድዋና ስርዋ ደም የፈሰሰባት ትመስላለች።

የደሜ ወይም የእጸደማዊት ለሰው ልጅ አካል አገልግሎት የደሙን ሲስተም መመጠንና ማስተካከል ነው።

1. ሳፍራዊ ደም፡- ነጭ ሐሞትን የሚፈጥርና የሚያበዛ
2. በልቀማዊ ደም፡- ቀይ ሐሞትን የሚያጣራና የሚያሰራ



Scanned by CamScanner

3. ሳውዳዊ ደም፡- ብጫ ሐሞትን የሚያመጣና የሚመርዝ
4. ሐሞታዊ ደም፡- ጥቁር ሐሞትን የሚያባዛና የሚያወፍር

እነዚህ አራት የደም ዓይነቶችና ፈሳሾች ከእሳት ከውኃ ከመሬት ከነፋስ ከአገኙት የተፈጥሮ ባህሪያቸው እየተበረዙና እየተወሐዱ ሥጋን ለመገንባትና ለማፍረስ የሥጋን ብልቶችም እንዲያይሉና እንዲደክሙ ያደርጋሉ።

ለዚህ ነው በአካል ውስጥ የአለው የደም ሲስተም ዘዴ የደም ማነስን ወይም መብዛትን የደም መቅጠን ወይም መወፈርን ያሳይና በአካል ላይ ብርታትንና ጉዳትን ያመጣል። ምክንያቱም በሐሞት አማካኝነት ብጫ ደም ነጭ ደም ጥቁር ደም በመሆን በእኩልነት አካልን ያዳብራሉ ይገነባሉ ነገር ግን ከነዚህ አንዱ ከበዛና ሌላው ካነሰ ኃይሉ ብርታቱ ከአካል ይወገድና ጉዳት ያደርሳል። ስለዚህ የእፀደማዊትን ሥርና ቅጠል እንደሻይ መጠጣት ነው። ከሌላው መጽሐፈ ተመልከት

የአይጥ ሸንብራ ሸንብሩት ?



Scanned by CamScanner

የአይጥ አረግ እፀ እየሱስ የሚሉም አሉ
እፀ እየሱስ ግን ከሥሩ ክብ ድንች ያለው ነው
በሱስ ለተለከፈ የአይጥ አረግ ፍሬ ከሚወደው ጋር መስጠት ነው ወይም ከአርማጉሣ ቅጠል ጋር ወቅጦ ለሲጃራ ከሲጃራ ጋር ወይም እንዲተው ከተፈለገው ጋር ጨምሮ መስጠት ነው።

የጥቁር አዞ አረግ /ጥቁር አዞአረግ/
ለውጋት ሥሩን አሣርሮ ከሚወጋው ላይ በጥቶ ማስገባት። ለቁንጭር ቅጠሉን ወቅጦ አድርቆ ቁስሉን ከአጠገቡ በኋላ ዙሪያውን ማር መቀባትና ከቁስሉ ላይ ዱቄቱን ደምድሞ በስንዴ ሊጥ አፍኖ በሻሽ ማሰር በ3 ቀን መፍታትና እስከሚድን ማድረግ ነው።

የጥጃጨንገር
ለትምህርት አበባውን ከእፀነቢያት ስር ጋር በነጭ ማር ለውሰህ አብላ።

የአሽያ ጆሮ ቀጠጥና ከሚለው ተመልከት



Scanned by CamScanner

**የአኽያ ዝቃ ቅቤ**

ለራስ ምታት ቅጠሉን ከፈረስ ዘንግ ቅጠል ጋር ወቅጦ በአፍንጫው መሳብ ነው።

**የአኽያ ኮሸሽላ**

ለዘኢያወርድ ስሩን አላምጦ መተኛት ነው።

**የጅብ ልብ**

ለቁራኛ ስሩን ከአይጥ አረግ ሥር ጋር በማር ማቀጥ ነው።

**የጅብ ሽንኩርት**

ለአባጭ ለእጢ ጨፍልቆ አድርቆ በቅቤ ለውሶ መቀባት ነው ወይም ከእንዳሁላ ስር ጋር ወቅጦ በእሳት እያሞቁ መተኮስ ነው።

**የውሻ ምላስ ተ/**

**የውሻ ድንች**

1. እባብ ለነደፈው ስሩን ከነደፈው ላይ እሰር ወይም ከአሞጭ ስር ጋር ማሰር ነው።



Scanned by CamScanner

2. የአበደ ውሻ ለለከፈው ሥሩን ወቅጦ ማጠጣት ነው።

## የድንጋይ ሙጫ

ለሣል መግል ለሆነበት የድንጋይ ሙጫ ከርቤ እልቴት ሰናፍጭ ኑግ ዝንጅብል ነጭ ሽንኩርት በአንድ ላይ ወቅጦ ከቅቤ ቡና ጋር መጠጣት ነው።

የበሬ ቆለጥ ?

## የዶሮ ኩስ

ለተላላፊ ለልክፍት ለጋኔን ሥሩን ከግሜ አረግ ጋር ወቅጦ ዘፍዝፎ መታጠን ወይም መታጠብ ነው።



Scanned by CamScanner

# - ደ - D

ደለሹት የቤት ልብ የጂብ ኮቴ ?

ደስቶ ደብዛ ተ

## ደድሆ

1. ለጀርባ ደዌ ፍሬውን ከእንጆሪ ቅጠል ጋር ወቅጦ በመቀመጫው ማድረግ ወይም እያፈሉ እንደሻይ መጠጣት ነው።
2. ለሥራይ ቅርፍቱን ከሥጋ መረቅ ጋር መጠጣት ነው።
3. ለቆዳ በሽታ ከገመሮ ስር ጋር አውዛ አውጥቶ መጠጣት ነው።

## ደጭመረጭ

1. ለአበጥ ከቁጫጭ እንቁላል ጋር መቀባት ነው ይበተናል።
2. ለማድያት ከእርድ ጋር ወቅጦ በሎሚ ውኃ ለውሶ መቀባት ነው።



Scanned by CamScanner

## ዱባ

ለራስ ምታት ፍሬውን ወቅጦ ከራስ ደፍድፎ ማሰር ነው። የዱባ ፍሬ አዘውትሮ ቢበሉት አእምሮ ያጠራል ሙሉ ጤነኛ ያደርጋል።

## ዳጉሜ

በረድ ደረቅ ነው ለሆድ ይከብዳል ያደርቃል ከወተት ጋር ቢበሉት መልካም ነው ጉልበት ይሆናል ያጠነክራል።

## ዳማከሴ /ዳማከሴ ስትቆርጥ ሬላታእስ በል/

1. ለዓይን መድኃኒት ቅጠሉን ከወይናግፍትና ከእንባጮ ቅጠል ጋር ወቅጦ ውኃውን ጨምቆ ከሥር ኩል ጋር መኳል ነው ያጠራል።
2. ለጆሮ ቁንቁን ከምድር እንቧይና ከአረግ ሬሣ ቅጠል ጋር ወቅጦ በጆሮ ጨምቆ ውኃውን ጠብ ማድረግና ጥጥ መወተፍ ነው።
3. ለዘኢያወርድ ሥሩን ማላመጥ ነው ለጠላት ሰፍቶ መያዝ

## ዳብዛ

1. ለከፉ ደዌ ለአብያ ወይፈን ከገተም ቅርፍት ጋር ወቅጦ በጠላ ማጠጣት ወይም ሲወድቅ በአፍንጫው ማድረግ ነው።
2. ለፈራ ለሣል የዳብዛና የግመሮ የሥራቸውን ቅርፍት በወተት ማጠጣት ነው።

## ዳባቀድ

ለእጢ በመቀመጫው ለወጣ ሥሩን በእሳት እያሞቁ እጢውን መተኮስና ማሸት ነው።

## ድንብላል

1. ለእበጥ ከነጭ ሽንኩርት ጋር ወቅጦ በባዶ ሆድ በማር መዋጥ ነው።
2. ለኩላሊት በማር ሰባት ቀን በባዶ ሆድ መውሰድ ነው። ማህፀንዋ ለታመመች ከጥቁር መጣፍጥ ጋር ማብላት ነው። በህልም ለሚሸናም ስጠው፡

## ድንገቴ

ለቁርባ ለምች ለመጋኛ ሥሩን ማላመጥ ነው።



Scanned by CamScanner

ድንጋይ ሰበር ተ/

ድጉንጉና ወይም ዱዱና አንቋዛፍ የመሰለ
ለሆድ ደዌ በአንት ሥሩን ዘፍዝፎ መጠጣት ነው።
ያስቀምጣል።

ድብርቅ

1. ለሆድ ደዌ ፍሬውን በቅቤ ቅጠሉን በማር ማጠጣት ነው።
2. ለኪንታሮት በሆድ ውስጥ ላለ ከዋግራና ከአልቴት ጋር ወቅጦ በማር ማብላት ነው።

ድግጣ - ዝግጣ

1. ለወባ ለተላላፊ በሽታ ፍሬውን ከቀይ ግመሮ ቅርፍት ነጭ ሽንኩርት አልቴት ከርቤ በአንድ ላይ ደቁሶ መያዝ ነው።
2. ለችፌ ለእከክ እሳት ለበላው ቅጠሉን ከጉርጠብ ቅጠል ጋር ወቅጦ በቅቤ መቀባት ነው።
3. ድዱ ለሚደማ ፍሬውን መደምደም ነው



Scanned by CamScanner

4. ለተቅማጥ ሰባት ፍሬ መዋጥ ነው ወይም ቅጠሉን አሽቶ መጠጣት ነው።

## ዶቅማ

1. የዶቅማ ተቀድላው ከቀንጣፋ ተቀጽላ ጋር በነጭ ማር መጽሔተ አእምሮን ደግመው ቢበሉት ብልህ አዋቂ ይሆናል የሰማውን አይረሣም።
2. ለሆድ ህመም ለሥራይ የዶቅማ ፍሬና ቅርፍት ከእጀርይ ቅጠል ጋር ወቅጦ በማር ማብላት ነው።

## ዶግ - በግእዝ እፀራምኖን

ለመጽንኤ እስኪት ከሚመለከቱት እፀዋት ጋር አብሮ ደቁሶ መስጠት ነው።

## ዲዲቴ

እንግዴ ልጅ ለቀረባት ስሩን ታላምጥ



Scanned by CamScanner

# - ጀ ጀ ጀ - J

## ጀጀባ

1. ለመጽንኤ አስኪት ሥሩን ማላመጥ ወይም ከሳማ ስር ጋር ወቅጦ በማር በባዶ ሆድ ማብላትና ብርዝ ማጠጣት፡፡

ጀሮአስፊት ተ/

## ጂባራ

1. ለራስ ህመም ሥሩን ፍሬውን ከጭቁኝና ከጦስኝ ቅጠል ጋር ቢገኝ በፍየል ቅቤ በተገኘው አንጥረው በአፍንጫው ይሳብ፡፡
2. ለማንኛውም ደዌ ፍሬውን ከነጭ ሽንኩርት ጋር ደቁሶ በማር ለውሶ በባዶ ሆድ ለብዙ ቀን ማብላት ነው፡፡
3. ለደረት ህመም ፍሬውን ቀቅሉ እንደሻይ በማር መጠጣት ነው፡፡
4. ለቂጥኝ የጂባራ ደም ከቁልቋል ደም ጋር እኩል በእኩል ቀላቅሉ ከግራዋ ቀንበጥ ጋር በቀይ ጤፍ ቂጣ መብላትና አጓት በብዙው መጠጣት ነው፡፡



Scanned by CamScanner

5. ለጋኔን ለሥጋ ደዌ ፍሬውን ከዋጊኖስ ፍሬ ጋር ወቅጦ በማር ለብዙ ቀን መብላት ነው ወይም ቅርፍታቸውን ቅጠላቸውን ከአልቴት ጋር ደቁሶ ግማሽ ማንኪያ በማር ማቅመስና ዘፍዝፎ ሰውነቱን መታጠብ።
6. ለጋኔን ጂባራ እፀእየሱስ እፀፋርስ እፀመናሂ ሥራቸውን ፍሬያቸውን ወቅጦ በማር ደጋግሞ ማቅመስ ነው።
7. ለትምህርት የጂባራ የምስርች የቀጠጥና ፍሬያቸውን በነጭ ማር ለውሶ ሰባት ቀን ማዋጥ ነው።

## ጅንጅብል

ለጉንፋን በቀን ሶስት ጊዜ እያፈሉ መጠጣት ነው። ራስን ሲያም አላምጦ በአፍንጫ መሳብ ነው።

## ጂልዋት

አረግ መስሎ ውስጡ ጋን ያክል ስር አለው ቆርጠው ግማሹን ቢተውት ደፍኖ ሞልቶት ያድራል። ለተሐድሶ ለአድሜ ቢበሉት ይሆናል የሚገኘው በመልከጼዴቅ ገዳም በመራኝ እንዲሁ በከፋ ሁጭና ከሚሉት ጋር ይመሳሰላል።

# ዘ - ገ - G

## ገራም ጥንጁት

1. ለሆድ ቁርጠት ቀንበጡን ከሰባት ቦታ ቆርጦ በውኃ መጠጣት
2. ለውርጃ ሥሩን በወገብዋ ትሰር አያስወርዳትም

## ገራምሰገድ

ለቁርጥማት ሥሩን ከጋቢሉና ከደድሆ ስር ጋር ቀቅሉ በማር መጠጣት ነው፡

## ገበር እንቧይ

1. ለተሰበረና ለተጉዳ ቅጠሉን ቀጥቅጦ በሽንት ለውሶ ከተጉዳው ላይ ማሰር ነው።
2. ልቡን እያመመ ለአመነመነው ለሚተፋ የምድር እንቧይ ስሩን ከገበር እንቧይ ጋር ወቅጦ በአንት ዘፍዝፎ አሳድሮ መጠጣት ነው።
3. ለደም ተቅማጥ ሥሩን ከቀይ እርጥብ ሥጋ ጋር ለውሶ መብላት ነው።



Scanned by CamScanner

## ገብስ

በረድ ደረቅ ነው ሆድ ይነፋል በሶው ለተቅማጥ ቂጣው ከወተት ጋር ለጉልበት ይሆናል።

## ገተም ፡ ሰገም

1. ለቂጥኝ ቅርፍቱን ማላመጥ ወይም እንደጌሾ ከጥቁር ገብስ ጋር ጠላ አስደርጐ መጠጣት ነው።
2. ለቂጥኝ ለወርደ የሥሩን ቅርፍት አበባውን ዘርጭ እንቧይ የምድር አለንጋ ሁሉንም በአንድ ላይ ደቁሶ በብርዝ ዘፍዝፎ መጠጣት ነው።
3. ለማንኛውም ለተላላፊና ለውስጥ ደዌ የገተም የአሚራ የምሳና የደብዛ ቅርፍታቸውን ሥራቸውን ቀቅሎ ማውጣትና አውዛውን ጧት ጧት መጠጣት ነው።
4. ለአስም የገተም የሺነት ቅርፍት የአሚራ ቅጠል ከማር ጋር ጠንስሶ ማጠጣት ነው።

ገደል አድምቅ ተ/

ጉርምጫ ?



Scanned by CamScanner

ጉናጉና ጉናጉኒት እንስት የቆረጨ ዛፍ ?
ጉሉ /ጉሉ/ የወፍ ጉሉ ?
ዘይት የሚወጣው

## ጉሉ ኮከባ

ለአቃቤ ርእስ ስሩን ተቀጽላውን በነጭ ዶሮ ደም ቀርጦ መያዝ ነው።

## ጉሺርጥ /እንሶስላ ሴቶች እጅ እግራቸውን የሚሞቁት/

1. ለሣል ሥሩን ከነጭ ሽንኩርት ጋር አፍልቶ መጠጣት ነው።
2. ለመጽንኤ እስኬት በማር ለውሶ መዋጥ ነው።

ጋባ ተ/

## ጋንቢሉ ጎቤል

ለመጽንኤ አስኪት ቅርፍቱን ከብርዝ ጋር ደጋግሞ መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

4. ለቆዳ በሽታ ከደድሆ ስር ጋር ቀቅሎ መጠጣት ነው።
5. ለቡዳ ሥሩን ከግሜ አረግ ጋር መታጠን

ግብረቃይና /እፀወርቅ/ ?

## ግንዶሽ

ለለምጽ ሥሩን ከፍየል ቀንድ ጋር አክስሎ ከወይን ቅጠልና ከጉሎ ፍሬ ጋር ለውሶ መቀባት ነው።

ግራምጣ ፡ ራግሄ ተ/

## ግራዋ

1. ለመጋኛ ቅጠሉን ከቂጣ ጋር መብላት ነው።
2. ለልብ ህመም ቅጠሉን ከሰሊጥ ወይም ከሱፍ ጋር ቀቅሎ ውኃውን መጠጣት ነው።
3. ለመፍትሔ እስኪት ተቀጽላውን ደቁሶ በውኃ ማጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

## ግራር ፡ ሰጢን

1. ለውጋት ተቀጽላውን ሙጫውን በቅቤ ለውሶ ማሸት ነው ወይም ከኑግ ጋር በጥብጦ ማጠጣት ነው።
2. ብልቱ ላበጠበት ለሚመግል ቁስል ፍሬውን ደቁሶ በማር ለውሶ ማሰር ነው ወይም ቀቅሎ ማጠጣት ነው።

## የግራር ዘር ዓይነቶች ፡ ሰጢን

ቡላግራር ቀይግራር ባዝራግራር አቅባ ቆጋ ግራምዳ ቃሬጣ ቆንጥር ጨባ ነጭግራር የሚባሉ ሁሉ ተመሣሣይ አበቃቀል ሲኖራቸው በጽናት ሁሉም ይለያያሉ። ከነዚህ ውስጥ አንዱ ሲበሰብስ ቅንቡርስ ስለሚሆን ቅንቡርሱን ሰብስቦ በምጣድ ቢጠብሱት ቅባት ይወጣዋል። ቅባቱም ሜሮን ተብሎ በነገሥታቱና በጳጳሳቱ ዘንድ ክቡር ዘይት ነው። ለሚመነምን ህጻን ሰውነቱን ቢያሹበት ይፈውሣል መስተፋቅርም ነው።

## ግዜዋ

1. ሆዱ ለአበጠበት ሥሩን ከጥጥ ፍሬ ወቅጦ ቀቅሉ ጨምቆ ሙቁን መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

2. ለንብ ከሥረብዙ ጋር ማጠን ነው
3. ለሥራይ ለቡዳ ሥሩን ከሥረብዙ ጋር በባቄላ ንፍሮ ውኃ ማጠጣት ነው

**ግብጦ**

ትኩስ ደረቅ ቀሊል ነው ከቅቤ ጋር ቢበሉት ጤና ይሰጣል የተቀቀለወን የንፍሮ ውኃ ቢጠጡት የደም ብዛት ይቀንሳል ያጠራል።

ግጫ ተ/

ጉመን አይደርቄ ጉመን ?

የጉመን ዘር ዓይነት ብዙ ነው ?

**ጉበዝ ጠቀስ**

ባልዋ የጠላት ወይም ባል ላጣች ሴት ከሞይደር ጋር ጉያዋን ታጥና ትተኛ

**/ጉፋ/ ጉፋ ብብሻ**

በድን እንዳይበላሽ ቅጠሉን ቅርፍፊቱን ፍሬውን ከአከማና ከቀረጥ ቅርፍት ጋር ወቅጦ በአፍንጫው በሆድ እቃው መከተትና በድኑን ደፍድፎ መገነዝ ነው።

የጉፋና የዋሽንት ተቀጽላቸው ለመንድግ ለገቢያ ይሆናል በዶሮ ደም ቆርጦ መያዝ ነው፡

## ጉርጠብ እፀናሆም

1. ለቁስል አድርቅ ቅጠሉን በብዙው ወቅጦ ለቁስለኛው መደምደም ማሰር ነው፡
2. ለልብ ድንጋጤም ቅጠሉን ከቀረፋና ከገውዝ ከለውዝም ጋር በማር ለውሶ ማብላት ወይም እንደሻይ መጠጣት ነው።
3. ለውጋት ለቁርጥማት ከአርማጉሳ ጋር መጠጣት ነው

## ጎርጂጆት ሺንጉግ አጭር ቅጠሉ ናጫ የመሰለ

ለአባጭ ለቁርባ ቅጠሉን ማሰር ነው

## ጉርጂጂት ችፍርግ የመሰለ የውድማ መጥረጊያ

## ጉርጉር

ለመንስኤ እስኪት በሉሚ ውኃ ለውሶ መብላት ነው



Scanned by CamScanner

ጉሺርጥ

ጸሎት በእንተ ገብረኩሉ በጨት ስምከ በበጊጥያ ስምከ በቤት ስምከ በቀፋ በሴራ ስምከ በበርጤሜዎስ ስምከ ለወልደ በርጤሜዎስ ዘከስትከ ሎቱ ህቡአት ኩሉ ከማሁ ክስት በዛቲ እፅ ወፈጽም ፈቃደ ልብ ኩሉ ህቡአተ ለገብርከ እገሌ ፵፱ ድገም

1. ለአምጽአ ብሲት በቅጠሉ ቀለም ጽፈህ በስምዋ ከስሩ ጋር ከደጃፍ መስቀል ነው
2. ለመፍዝዝ ከሰባት ቀለም ጋር ቀላቅሎ ጽፎ መያዝ ነው
3. ለገንዘብ ለመስተፋቅር በደምህ በደሙ አስነክቶ ማሰር ነው
4. ለማንኛውም በሽታ ከግዜዋ ጋር ወቅጦ ቤትን መርጨት ነው

ጉሎ ኮከባ /ተቀጽላው ለመጠብቅ/



Scanned by CamScanner

# T - ጠ - (TH) T

## ጠሴንጂ

1. ለውጋት ሥሩን ከቱልትና ከሰመግ ሥር ጋር ወቅጦ በቅቤ ለውሶ ከሚያመው ላይ ቀብቶ እሳት መሞቅና መታሸት ነው
2. ለወፍ ሽንቱንም ለከለከለው ወቅጦ መጠጣት ነው።
3. ለደም ብዛት የቀዩን ጠለንጂ ስር ወይም ቀንበጡን አሺቶ በአፍንጫው ማሽተት ነው
4. ለኪንታሮት ለቁስል ቀንበጡን ሥሩን ወቅጦ ደፍድፎ ማሰር ነው

## ጠንበለል

## ጠጠብ ጠጠባ

የበረሃው ጠጠብ ሥሩን ቢያላምጡት ብልት ያጠነክራል መስተፋቅርም ይሆናል ችፍርግ መስሉ እሾህ የለውም።



Scanned by CamScanner

## ጠንገጉ ጠገጉ

ለኪንታሮት ለጡት ነቀርሣ ለሆድ ደዌ ቅጠሉን ወቅጦ በማር መውሰድ ነው በቅጠሉም አሙቆ ማሰር ነው።

## ጠጅሣር ?

## ጠሮሐረግ

ጡት አስጥል አርማጉሣ /አ/ ላይ ተመልከት
ለአስም ቅጠሉን በቅቤ አንጥሮ መጠጣት ነው።

## ጤናአዳም

1. ዓይኑ ለቀላና ለታመመ ቀቅሎ ሲበስል በውኃው ይታጠብ
2. ለሣል ከእንስላል ጋር በወተት አፍልቶ ማጠጣት ነው።
3. ለተመረዘ በቶሎው ቢያጠጡት መርዝነቱን ይሽረዋል



Scanned by CamScanner

## ጥንጁት

1. ለሣል አበባውን አጠራቅሞ እንደሲጃራ ማጠጣት ነው በበላዩ አንት ይጠማበት ዞፍ የመሰለ ይወጣዋል።
2. ለደረቅ ቁርጠት ቅጠሉን ማላመጥ ነው

## ጥቁር አዝሙድ

1. አፍንጫው ሽታ ለከለከለው በሰው ወተት በጥበጦ በአፍንጫው ደጋግሞ ያድርግ
2. ለቁርጥማት ቧትና ማታ በቅቤ አንጥሮ ማጠጣት ነው።
3. ለማንኛውም ህመም አልአርጂክ ምግቡም ይሁን መጠጡ ለሚሆንበት ሰው ዘይቱን ከሻይ ወይም ከቡና ጋር መጠጣት ነው። ለመጋኛ ብቻውን አንድ ማንኪያ ያክል መጠጣት ነው። እንዲሁም ከተለያዩ መድኃኒቶች ጋር ተስማሚና ፈዋሽ ቅባት ነው።

## ጥድ ፡ ሰጥረጺሉን

1. ጆሮው የሆነ ድምፅ ለሚሰማ ፍሬውን በቅቤ አንጥሮ በጆሮው ማግባት ነው



Scanned by CamScanner

2. አፉ ለሚሸትበት ፍሬውን ከአልቴትና ከከርቤ ጋር ወቅጦ ለብዙ ግዜ እንደትንባሆ በአፉ ያድርግ

## ጥጥ

1. ጉሮሮው ለታመመ ፍሬውን ደቁሶ በማር መቀባት ነው
2. ለጤንነት ሆድን ለማለስለስ የጥጥ ፍሬ ጭማቂ እያሞቁ መጠጣት ነው።

## ጥፍርንዶ

1. ለኪንታሮት ቅጠሉን ወይም እንጨቱን በእሳት እያሞቁ መተኮስ ነው
2. ለእጢ ለእባጭ /ወተቱን/ ደሙን ከስመአንፋር ጋር ለውሶ በጥትቶ መቅበር ነው።

## ጥፍሬና ነጣ ያለው

ለሽንት ማጥ ሥሩን ማላመጥ ወይም ቀቅሉ መጠጣት



Scanned by CamScanner

**ጥፍርግና አሩጥ**

በወንዝ ዳር የሚበቅል ለአምጽኦ ብዚት ለምሕሳበ ንዋይ በራሱ ዝቢር አድርግ ከሌላ ተመልከት

**ጥፌ**

ለአበጠ ቁስል ቅጠሉን ማሰር ነው

**ጥቁር አውጥ**

ሰውነቱ እየተከሰ አካሉ ለሚያብጥ በሱፍ ውኃ ከእንጀራ ጋር መብላት ነው ለማንኛውም ሰውነቱን መቀባት ነው።

**ጢቢጢባ /ደጫት/**

ለሪህ ከቱልት ስር ጋር ደቁሶ በማር ማብላት

**ጦስኝ /ለደጋና የቆላ አለው/**

1. ከጆሮ ውስጥ እንደትል ለሚላወስበት ቅጠሉን ወቅጦ በጆሮ ማድረግ ነው።
2. ለሚያስተፋው የጦስኝና የአቱች ቅጠል ዝንጅብልና ቁንዶ በርበሬ በአንድ ላይ አፍልቶ በማር መጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

3. ለሚረሣ ጦስኝ እፀዮዲት እፀሣቤት የጥጃ ጨንገር የሱሚሸት አበባቸውን በጣዝማ ማር ሥራቸውን በነጭ ማር ደጋግሞ መብላት ነው።
4. ሆዱን እየነፋ ለሚጮህበት የጦስኝና የእንስላል ቅጠል ቀቅሎ መጠጣት ነው።
5. ለሣልና ለጉበት ቅጠሉን እንደሻይ ሳባት ቀን ይጠጣበት
6. ማህፀንዋን ለሚያማትና ደም ለቀረባት ቤት ቀቅላ አፈማህፀንዋን ትታጠንበት
7. ጦስኝ ትኩስም ደረቅም ነው ቢጠጡት ቁርጥማት የሆድን ትል ያጠፋል ነገር ግን የሣንባ ህመም ላለው ሰው እንዳይጠጣው ያባብሰዋል።
8. ሆዱን ለሚነፋውና ለሚጮህበት ከሰንሰል ጋር ቅጠሉን ቀቅሎ መጠጣት ነው።

## ጦቢያ ቅንቦ

ለቆላ ቁስል ለማንኛውም ቁስል ደሙን ከቁስሉ ላይ ጠብ ማድረግና ማሰር ነው ለምጥ ሁና እንዳይቀር የድጥጣና የጉርጠብ ቅጠል ደቁሶ መደምደም ነው።



Scanned by CamScanner

## - ጨ - Ch

ጨባ ጠንካራ እንጨት

ጨጨባ ተ/

ጨጭሆ ተ/

ጨጮ እጸአብርሂ ለራእይ

ጭርጭር ጭራጭር ?

ጭቁኝ

1. ለኃይለኛ ራስ ምታት ጭቁኝ ወገርት እፀመናሂ በፍየል ቅቤ እንጥሮ ቅቤውን በአፍንጫው ሌላውን ከራሱ ላይ ይደፍድፍ
2. አፍንጫው ለሚገማ ጭቁኝ ጤና አዳም ከርቤ ስሊጥ ቁንዶ በርበሬ አውጥ ሁሉንም በአንድ ላይ ደቁሶ በፍየል ቅቤ እንጥሮ በአፍንጫው ያድርግ
3. ለሆድ ህመም ከነጭ ሽንኩርትና ከቁንዶ በርበሬ ጋር በማር ለውሶ ሰባት ቀን ይብላ።



Scanned by CamScanner

ጭምቅ

አራዊት ለመግደል ከሚበላው አድርጉ ቢሰጡት ወገቡ ተሸመድምዶ ይገኛል መርዘኛ እፅ ነው።

ጭልታ ?

ከጤፍ ጋር የሚበቅል

ጫብሌ ?

ጫት

ለአስም ቅጠሉን ከቡና ቅጠል ጋር ቀቅሎ በጣዝማ ማር መጠጣት ነው።

ጫቅማ

ለቁርጥማት ቅጠሉን ከልት ቅጠል ጋር ወቅጦ ከስንዴ ንፍሮ ጋር መብላት ወይም አብሮ ቀቅሎ ውኃውን መጠጣት ·

ጫንቋ ተ/



Scanned by CamScanner

ጨጐጐት የሞኝ ፍቅር የካህን ቂም ሺንጉግ

1. ለቂጥኝ ሥሩን ከእፀዘዌና ከእንኮይ ጋር ደቁሶ በቀይ ጤፍ ቂጣ መብላት ነው
2. ለራስ ምታት ቅጠሉን ከወሊትና ከዳማከሴ ጋር ወቅጦ ሲያመው በአፍንጫው ይሳብ
3. ለመስተፋቅር ከሰባት ቦታ ቅጠሉን ቆርጦ ወቅጦ አድርቆ በሜሮን በአምሳያ ላም ቅቤ ለውሶ ቀብቶ ስላም የበል ወይም በጣዝማ ማር ተለውሶ ቀብቶ ይውሰብ

ጭረት /ቢስቃ ቃጫ/

ለመፍትሔ እስኪት ለጆሮ ህመም



Scanned by CamScanner

## - ጸፀ - S

**ድጌረጻ**

ጆሮው ለአበጠና ለቆሰለ በውኃ ቅጠሉን አበባውን አፍልቶ በጆሮው አጥሎ ማድረግ ነው።

**ጽድ**

1. ለጉሮሮ ህመም ፍሬውን ከጤና አዳምና ከእንስላል ጋር ከዘቢብ ጋር ወቅጦ በፍየል ቅቤ መቀባት ነው።
2. ጥርሱ ለሚደማበት ለሚሰበርበት የጽድ የጽጌረዳ የድግጣ ፍሬያቸውን ወቅጦ ይደፍድፍበት
3. ለጥርስ ህመም የጽድ ሙጫ የጽጌረዳ ፍሬ የቋልቋል ደም የሺነት የጂባራ ሥራቸውን ወቅጦ ይደፍድፍበት
4. ቆሽቱ ለደከመ ለተቅማጥ ለትፋት ሙጫ ሙጫውን መቆርጠም ነው።



Scanned by CamScanner

# - ፈ - F

## ፈላጺት

ፈላጺት የሚባሉት አንድዋ ፈረፈር ቦታ የምትበቅል ነጭ ደም ከሥርዋ ያላት ሁለተኛይቱ ነጣ ብላ ቆም የምትል ለምሕስብ ለወተት ለቅቤ ለምሕሳብ ንዋይ የምትሆን ናት። ሦስተኛይቱ አረግ ሁና ወደላይ የምትወጣ ለመስተፋቅር የምትሆነው ናት ከሶስቱ ሁሉንም ውሂደት አድርጉ በገቢር መስራት ነው።

1. ለሐብት ለበረከት በገቢርዋ ቆርጦ በሸኮኮ ራስ ውስጥ አድርጉ ከቤት ውስጥ መቅበር ወይም ማስቀመጥ ነው፡
2. ለምቀኛ ከብት እር ጋር ለሰላቢ ከጅብ ኩስ ጋር ከቤት ውስጥ መቅበር ነው።
3. ወረርሽኝ ተስቦ በሽታ ወይም ሥራይ ደንቃራ ለሆነበት ሦሩን ከግሜሐረግ ከዋጊኖስ ከነጭ ሽንኩርት ጋር ዘፍዝፎ ማጥመቅ ቤቱንም መርጨት ነው ማጤስም ነው።
4. ምጥ ለተያዘች በስምዋ ቆርጦ በወገብዋ ማሰር ነው ወይም ከአኽያ ፋንድያ ጋር በጥብጦ አጥሉ ማጠጣት ነው።



Scanned by CamScanner

## ፈውስ

5. ቡዳ ለያዘው ጋኔን ለለከፈው ከግመርና ከጂባራ ከግሜሐረግ ጋር ደቁሶ በአፍንጫው ማድረግ ነው። ከአልቴት ጋር በአንገት ማሰር ነው፡
6. ለተመኙ ነገር ለዚህ ነገር ሁነኝ ብሉ በስሙ ቆርጦ ከሞይደር ከእጣን ጋር ማጤስ በደም አንግሶ ማስቀመጥ ነው።
7. ለመቀትል ለመስተሐምም የጠላትን ስም ረግሞ መቁረጥና ከወዙ ጋር ከንጉንቸር ጋር በቶፉ ውስጥ ከቶ መቅበር ነው፡
8. ለነቀርሳ ለኪንታርት ለትርፍ ምላስ ለሥጋ ደዌ ለቁስል ሁሉ ሥሩን ቅጠሉን በአንድ ላይ ወቅጦ ደምድሞ ማሰር ነው
9. ለጡት እበጥ ለቡግንጅ ለሌላም ሥሩን ቅጠሉን ወቅጦ በምጣድ ላይ ቅቤ አድርጉ እያሞቁ እበጡን መተኮስ ነው
10. ለወፍ በሽታ ለስርቅታ ለውጋት ለቁርጥማት ለመጋኛ ለሆድ ቁርጠት ለሾተላይ ለሌላም ደዌ በጥቁር ገብስ ጠላ ማጠጣት ነው
11. ለመስሪያ ቤት ለደጅ ጥናት ለማስታረቅ "ያወርብ ብሔር" 22 ጊዜ ደግሞ ሥሩን ነቅሎ እያላመጡ መሄድ ነው።

12. ለመስተሐምም "ፍትር" 100 ጊዜ "ጉዋትር" መቶ ጊዜ የእገሊትን ልጅ እገሌን አኮማትር አታውል አታሣድር ብሎ ሮብ ቀን ሥሩን መጠምዘዝና እንዳይፈታ ድንጋይ ጭኖ አፈር አልብሶ ዙሮ ሣያዩ መሄድና ከቤት መተኛት ነው።
13. ለተመኙትን ለማግኘት ሙሉ ጨረቃ ሌሊት ራቁትን ሁኖ መቆፈርና "የደጋ ሙርጀን የቆላ ሙርጀን እሄን ነገር አምጣልኝ አሳቤን ምኞቴን ፈጽምልኝ አክብረኝ አስከብረኝ" ብሎ መንቀልና ሥሩን ማላመጥ ለገብያ ለመስተፋቅር ይሆናል፡
14. ደም ለሚበዛበት ቅጠሉን ከቱልት ቅጠል ጋር ወቅጠህ ከኑግ ጋር ማብላት ወይም ማጠጣት
15. ለገበያ ከደንደሮ ስር ጋር ወቅጦ ማጤስ ነው ከእጣንም መጨመር ነው፡
16. ለመስተሐምም "ወረያሙን" 99 ደግሞ ስሙን ጠርቶ ማጠምዘዝና ጥቁር ድንጋይ መጫን ነው፡
17. ለመፍትሄ ሐብት "ሹቲ አላሹቲ ቁሹቲ ቤሮዓ ሙቲከ ያሙቲከ ኡኑሩኤል አፋፋሩኤል" ብሎ ፶፱ መድገምና ሥሩዋን መቁረጥና በትንሽ ጣት ልክ ከሶስት ቆርጦ ሁለቱን ማላመጥና አንዱን

በትንሽ ጣት ደም አስነክቶ በክንድ ማሰር ሌላውን ከተቆፈረበት ቀብሮ መሄድ ነው

18. ሃሃያኤል ሆሆያኤል እያሉ ፵፱ መድገም ሲደግሙ እፁዋን እየዞሩ ነው በአዲስ ካራ ለዚህ ነገር ሁነኝ ብሎ መቁረጥ

19. "ኪራያቁ ያኪራም ፍሎሪያም" ከመንቀል በፊት ፵፱ ደግሞ የጠላቴን ነገር አርክስ የእኔን ነገር አንግሥ ብሎ ነቅሎ ስሩን ይዞ ቀሪውን መቅበርና መሄድ ነው

20. ለግርማ ሞገስ እስስት ድንቢጥ ወፍ የጥቁር ዶሮ ቆለጥ የውሻ ምላስ ስር ከሥርዋ ጋር ሰፍቶ መያዝ ነው፡

21. ለመንስኤ እስኪት የውሻ ምላስ ስር ሥርዋን በቀይ ዶሮ ሥጋ ጋር አሰርቶ መብላት ነው፡

22. "አካእ ክስብኤል ቤቃ ሴቃ ቀንተው ሰንተው ቀርነለው በእሉ አስማቲከ ተማህፀንኩ ፈጽም ፈቃደ ልብየ ለገ/እ/ ብሎ ለሐብት ማር ወተት ቂጣ ቆሎ ንፍሮ ከሥርዋ አድርጉ እሄው ምስሽ ማለት ነው

ለመስተሐምም ለሌላ መጥፎ ነገር የውሻ የድመት የጅብ የዶሮ ኩስ አመድ ከሰል



Scanned by CamScanner

የመቃብር አፈር ከስርዋ ነስንሶ ነው የሚደገምና የሚቀረፃ እሄ መለማመጃ መወሐኛ ነው ጠልሰሙ በእጅ መዳፍ ተጽፎ እጁዋን ሳይቆርጡ አስቀድሞ ፶፬ መድገምና አሳብን መናገር ነው፡ ጠልሰሙ ይህ ነው

23. ለመስተፋቅር ኮይ ከለላይ ዘያፈልሆ ለማይ ወዘያርሆዎ ለሰማይ ኮይ ከለላይ ዘያረውጾ ለፀሐይ ኮይ ከለላይ ዘያፈልሆ ለማይ ከማሁ አፍልሀ ወአቅልጽ ልቡናሃ ለዓመትከ እ/ በፍቅረ ገብርከ እ/ ብሎ ደግሞ መፋቂያ አድርጉ እጁን መጨበጥ ነው

24. ለመፍዝዝ ከፈረስ አጽም ጋር ወቅጦ መያዝ

25. ለመስተፋቅር "ጨልታ መአዛ ለመአዛ በቃለ መአዛ ያጂጂ መጀጂ ልበ ደስታ ገጸብሩህ እምረሁቀ እስከ ቅሩብ ትቅነፐ ትቅነፐነፐ ለፍቅር እገሊት ለእ/ ብሎ ፶፮ ደግሞ መቁረጥና አላምጦ በእጅ እትፍ ብሎ ሰላምታ ማለት መንካት ነው

26. የፈላጼት ስር የአሩጥ የጥፍርንዶ ቀንበጥ ከሰባት ቦታ ላይ ቆርጦ የኤሊ ጉድን አጥንት ጋር ወቅጦ ውኃ ባልነካው ቅቤ ለውሶ "ኹድ ማኹድ" ፺፩ ጊዜ ደግሞ እጅን ቀብቶ መንካት ነው።

**ፌረስ ዘንግ**

ለራስ ምታት ቅጠሉን አሽቶ በአፍንጫ መሳብ ነው

**ፉላ**

ለውጋት ለሥብራት ቅጠሉን ቀቅሎ በማር መጠጣት ነው

**ፌላ ?**

**ፌውፋ ?**

**ፌጦ**

1. ለአስም ፍሬውን ከአሚራ ጋር ብዙ ቀን ዘፍዝፎ ከጨው ጋር በባዶ ሆድ መውሰድ ነው።
2. ደም ለሚያስቀምጠው ከእርጎ ጋር በጥብጦ መጠጣት ነው፡
3. ለኪንታሮት በእንጨቱ መተኮስ ነው
4. ለራስ ምታት ከነጭ ሽንኩርት ጋር ወቅጦ በአፍንጫ መሳብ ነው።



Scanned by CamScanner

ፍሕሶ

አርግዛ ደም ለሚታያት ለሾተላይ በማር ለውሶ ሰባት ቀን ትብላ

ፍርግፕ ብዩ ?

ፍየለፈጂ

ለቪንትማጥ ለጭብጦ ከሰባት ቦታ ቀንበጡን ቆርጦ በብርዝ መጠጣትና ከፀሐይ ላይ ተቀምጦ አንት መጠጣት ነው፡

ሐብተ አእምሮን ለሊቃውንት ቅዱሳን
ሐብተ ጥበብን ለአሐዱ ማህበረ ንጹሐን
የሰጠንና የገለጸልን እንዲሁ አስጀምሮ ስለአስፈጸመና እንድናስተውልና እንድንመረምረው ለአደረገ ለልዑል እግዚአብሔር የኢትዮጵያ አምላክ ክብርና ምስጋና ይገባዋል። አሜን!



Scanned by CamScanner

# ዜና እረፍት

# መሪራስ አማን በላይ

**የመሪራስ ትውልድ፡-** በሰሜን ጎንደር ክፍለ ሐገር በለሣ ቃላይ መድኃኒዓለም ከቄስ በላይ ድሉ/አባ በላይ ድሉ/ እና ከወ/ሮ ባዩሽ ቦጋለ /እማሆይ ባዩሽ ቦጋለ/ የካቲት 12 ቀን 1942 ዓ.ም ተወለዱ፡፡

- ከተወለዱበት አካባቢ በ1955 ዓ.ም እስከ 1957 ዓ.ም በጎንደር፣ በጎጃም፣ በአለፋ እና በጣቁሳ እንዲሁም በጎንደ ተክለሃይማኖት ገዳም ተዘዋውረዋል፡፡ በዚያም ከዲቁና እስከ ቅኔ አስነጋሪነት ደርሰዋል፡፡

## ጎጃም

1. በጎንደ ተክለሃይማኖት ገዳም የቅዳሴንና ዜማን ስርዓት አጥንተው ከአቡነ ጴጥሮስ በ55 ዓ.ም የዲቁና ማዕረግ ተቀብለዋል፡፡
2. ከደብረ ማርቆስ ከሚገኙት የቅኔ መምህር መርጌታ መንክር ግርማ ቅኔን ተምረዋል፡፡ ከእሳቸው ጋር ሆነው ወደ ሙተክል ደብረ ኤልያስ እና ዲማ ጊዮርጊስ ከአባ ማርቆስ ጋር ቆይተዋል፡፡
3. ወደ አዲስ አበባ መጥተው በቀጨኔ መድኃኒዓለም ከመሪጌታ መንግስቱ ተምረዋል፡፡
4. እንደገና ወደ ጎጃም ተመልሰው ጉቢያ ከመሪጌታ ግጨው መንክር ሀይሉ ጋር ቆይተዋል፡፡
5. ከእነዚህ መምህራን ቅኔን ለማወቅ በመማርና በማስነገር ቆይተዋል፡፡ በኋላም ወደ መሪጌታም ጉባኤ ሄደው ብዙ የተለያዩ የመጽሐፍት ሚስጥር እስከነ ትርጓሜአቸው ተምረዋል፡፡

መሪራስ የሚለውን የስማቸውን ትርጉም ያገኙት ከመሪጌታ ጉባዔ በነበሩበት ወቅት ነው፡፡

Scanned by CamScanner

ለበለጠ መረጃ ‹‹ሸገር አርካይቭ Shege Ancive

ትዝታ ዘአራዳ በተፈሪ አለሙ ገብተው ይጎብኙ።

**ስለ መጽሐፍቶቻቸው፣**

* የጥንቷን የኢትዮጵያ ታሪክ የብራና መጻሕፍት ያገኙት በሱዳን ጀበልኑባ አካባቢ ነው።

**ስለ መጽሐፍቶቻቸውና ይዘታቸው**

- የመሪራስ አማን በላይ መጽሐፍቶችን፡- በአጠቃላይ የጥንት ኢትዮጵያ አፃፃፍ ስልትና ሥርዓት የተጠበቀ ሲሆን ይዙቱ

ሀ/ መንፈሳዊ/ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የተያያዘ ነው ወይም መንፈሳዊ ሥርዓትን የሚያሳይ ነው።

ለ/ ታሪክና የቋንቋ ክፍል ጹሑፎች

፩. ባሕልንና ወግን ሥርዓትን የጠበቀና የሚያሳይ ነው።

ሐ/ የምርመር ጥናትና ጹሑፎች ደግሞ

፩. የስነ ከዋክብትና ሥነ ፈሊክ ምርመር

፪. ዕፀ ደብዳቤ የእፅዋት ጥናትና ሕክምና

፫. የድንጋይ ጥበብ የመሳሰሉትን ያካትታሉ።

መ/ የምክርና የተግሳጽ ስራዎች

**መሪራስ ወደ ፳፭ የሚደርሱ መጻሕፍት ጽፈዋል**

**ከእነዚህም፡-**

የልቤ ወዳጅ፣ ገፅ ፻፺፬-፻፺፫ ይገኛል።

በገበያ ላይ የዋሉ መጽሐፍቶቻቸው ፲፯ አካባቢ የሚሆኑት ታትመው ወጥተው በየመጻሕፍት ማከፋፈያና መሸጫ ቦታዎች ይገኛሉ።

**ሀ/ መንፈሳዊ ይዘት ያላቸው ሥራቸው**

፩. ምዕራፈ ሕያዋን ቃለ ሕይወት ዘወንጌል የአራቱ ወንጌላዊያን

Scanned by CamScanner

የምሳሌው ምስጢርን በሐተታና በትንተና የሚያስረዳ፣

፪. መጽሐፈ ብሩክ ብሩህ ዣንሸዋ

፫. መጽሐፈ ክቡር

፬. መርሐጽድቅ ወአሚን ወመርሐ ግብር

፭. ብርሃነ ሕወይት ዘበአማን

፮. ሰይፈ ሃይማኖት ተዋህዶ

፯. ሕይወት እንደገና በሦስት አለሞች ምስጢር

፰. መክሰተ ምስጢር ሕይወታዊ ርዕዮት

፱. መጽሐፈ ኤልያስ፣ ነብየ እግዚአብሔር

፲. ጸሎተ አሚን ዘበአማን ወጸሎተ ተዋሕዶ

**ለ/ የቋንቋና የታሪክ ይዘት ያላቸው ሥራዎች**

፩. የሱባ ቋንቋ በአማርኛና በእንግሊዘኛ

፪. የጥንቷ ኢትዮጵያ ትንሣኤ ታሪክ

፫. መጽሐፈ ሱባኤ ዘበአማን ካልዕ

፬. መጽሐፈ አብርሂት

፭. የልቤ ወዳጅ፣ የሰው ዘር ልጅ

**ሐ/ ለምርምርና ለጥናት የሚረዱና ጥልቅ ሚስጠር ያዘሉ መጻሕፍቶች**

፩. መጽሐፈ ሠረገላ ታቦር ዘኢዮር

፪. መጽሐፈ እንቆአእባን

፫. መጽሐፈ ፈውስ

፬. መጽሐፈ አድኅኖት

፭. ከኖህ እስከ አሁን በኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር

**መ/ምክርና ተግሳፅ አዘል ጹሑፎች**

፩. የእውነትን ሕይወት ወደዱ የሐሰትን ጥፋትን አስወገዱ

Scanned by CamScanner

፪. አፍሪ ካሁን
፫. ጥበብ ከእውቀት ትምህርት ከልጅነት
፬. ምክር ከእኔ ስማ አንተ ወገኔ

- «ሱዳን ጀበል ኑባ» ካገኙዋቸው መጻሕፍት
  ፩. መጽሐፍት ያሻር ሥነ-ጥጥረት መጽሐፈ ፀሐይ
  ፪. መጽሐፈ የሰባ ቋንቋ
  ፫. መጽሐፈ ሱባዔ ከአዳም እስከ ቀዳማዊ ሚኒሊክ
  ፬. መጽሐፈ አክሱማይ ሲራክ ከቀዳማዊ ሚኒሊክ እስከ ዮዲት
  ፭. መጽሐፈ ታሪክ ነገስት ዘኢትዮጵያ በዘግዱር ዘአንዳቤት ከዮዲት እስከ ዳግማዊ አፄ እያሱ
  ፮. ከአፄ እያሱ እስከ አፄ ኃ/ሥላሴ ከመሪጌታ ጉባኤ ጎጃም ሊበን ውስጥ ከተገኘ መጽሐፍ የተገኘ ነው፡፡
- ዜና ማርሐር የተለያዩ አስደናቂ ታሪኮች
- የእስያኤል የሰብዓ-ሰገል የኢትዮጵያ ስምና ትርጉም የሕንፃ አሰራር/ አክሱም፣ ላሊበላ፣ የዓለማት ምስጢር ጠዘተ .........

## <u>የ</u>ሱባ ቋንቋ

- ሱባ፡- ማለት ሰብዕ/ሰው/ሰብአዊ የአማረ አበባ ማለት፣ ለሁሉም ቋንቋ ነባር አላቸው
- <u>ነባር</u> የምንለው የሚጠሩበት ስም የአባቶቻችን የአገር የወንዝ፣ ስም በቋንቋው እንዲሰየምና ስሙ ከቋንቋ በፊት ስለነበረ ነባር ይባላል፡፡

፲ አናባቢ አስማተ መለኮት
፴፫ ተናባቢ ፊደሎች አሉት

አዘጋጅ እና አሳታሚ መለረአከ መዊዕ ቀሲስ ፀጋዬ ሽፈራው
0918252540/0909 270604/0974533780

Scanned by CamScanner



## መራራስ አማን በላይ

ዋጋው 150 ብር በኢትዮጵያ
ከኢትዮጵያ ውጪ 85 ዶላር

ቅዱስ ጊዮርጊስ ማተሚያ ቤት
☎ 058 222 1184 ባህር ዳር

Scanned by CamScanner